www.zeyeneta.com

ትርጓሜ መኃልየ ፤ቱ ወሯቱ ነቢያት
አንድምታ
ወምቅናየ ነቢያት ሐተታ::

ከቀድሞ ሊቃውንት አባቶች ጀምሮ ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣው
ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)

አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል::

፲፱፻፺፯ ዓ.ም
አዲስ አበባ

www.zeyeneta.com

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ መሉውንም ሆነ በከፊል ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያበል

ረዳት አዘጋጆች
ተማሪ ያርጋ ዓለም ወለኑ
እና
ተማሪ ዘውድነሽ አዳነ

ምሰጋና

፩ ከገጸ ንባብ እስክ ትርጉም መርምረው አቃንተው ለንትመት እንዲበቃ ጊዜያቸዉን መሥዋዕት አድርገው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለረዱኝ በሳንደር የአራቱ ንባኤያት መምህርና የትርንሜ መጻሕፍት ምስክር ለሆኑት እንዲሁም የመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ለታላቁ ሊቅ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ።
በተጨማሪም ለትርንሜ መጻሕፍት ተማሪሥቻቸው ለመምህር ፍቅረ ማርያም ጌትነት እና ለመምህር ኃይለ እግዚእ አሰፋ።
፪ በምሥራቅ ጎጃም ርእሰ አድባራት መርጡለ ማርያም ለቅኔ መምህሩ ለመሪጌታ ዲበ ኮሱ ዳምጤ
፫. ለቤተ መዛግብትና ለቤተ መጻሕፍት ድርጅት በኢትዮጵያ ጥናትና ጥናታዊ ሥነ-ጽሑፍ የጥንታውያን ጽሑፎች ክፍል ባለሙያዎች።

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ

፩ በሳንደር ደበረ ኃይል ወደብረ ጥበብ የአቋቋም ምስክር ለነበሩት ለታላቁ ሊቅ መጋዜ አዕላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤል።
፪ ለታላቁ ሊቅ ለመምህር ዲበ ኮሱ አምባዬ የፈለገ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፍኖተ ሰላም:
፫ ለመምህር ጎሩይ ንብረ ሥላሴ የመጽሐፍ መምህር ጥጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዲሁም ለትርንሜ መጻሕፍት መምህራን ይሁንልኝ።

www.zeyeneta.com



ምስለ ፍቁር ወልዳ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.zeyeneta.com



ከ ፲፱፻፲፱ - ፲፱፻፶፯ ዓ.ም
የቤተ ክርስቲያን ዓይን የሆኑት የአቋቋም ምስክር
ታላቁ ሊቅ መጋቤ አዕላፍ ሄኖክ ወልደሚካኤል እኒህ
ነበሩ



አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል

www.zeyeneta.com

ማውጫ

ገጽ

1. የ፲፪ቱ ነቢያት ማኅልይ የአርእስት ታሪክ.....1-14
2. ጸሎተ ሙሴ 14-21
3. ጸሎተ ሙሴ ዘዳግም 21-31
4. ጸሎተ ሙሴ ዘሣልስ 31-42
5. ጸሎተ ሐና እመ፡ ሳሙኤል ነቢይ 42-52
6. ጸሎተ ሕዝቅያስ 52-57
7. ጸሎተ ምናሴ 57-61
8. ጸሎተ ዮናስ.....61-65
9. ጸሎተ ዳንኤል 65-77
10. ጸሎተ ይቱ ደቂቅ 77-83
11. ጸሎተ ዕንባቆም 83-95
12. ጸሎተ ኢሳይያስ 95-103
13. ጸሎተ እግዝአትነ፡ ማርያም 103-117
14. ጸሎተ ዘካርያስ ካህን 117-127
15. ጸሎተ ስምዖን ነቢይ.....127-129

የአንድምታ ትርጉም ጥቅሶችና መገኛቸው

ከገጽ 129-133

ማውጫ

የክፍል ሁለት፡ የነቢያት ቃል ሐተታ

ገጽ

1. ስለ መኅልይ ትርጉም 135-136
2. ስለ ነቢይ ትርጉም 136
3. ስለ ጸሎት 137
4. ስለ ሙሴ የልደት ዘመንና የግብጽ ተልዕኮ 137-139
5. ስለ እስራኤል ከግብጽ አወጣጥ 139
6. ስለ ባሕረ ኤርትራ 139
7. ከአብርሃም እስከ እስራኤል ነፃ መውጣት ድረስ ያሉት የሦስቱ ፈርዖኖች ልዩ ስም 140
8. ስለ ሰማይ 140-141
9. ስለ ምድር 141
10. የእራቱ መንዞች ስምና መነሻ መድረሻ 141-143
11. ስለ እሳትና ባሕርይው 143
12. ስለ ሲኦል 144
13. ስለ አሪት አጻጻፍ 144
14. ስለ ሙሴ አገልግሎትና ዕረፍት 145
15. ስለነቢይት ሐና የልደት ዘመን 145
16. ስለ ስእለት 146
17. ስለ ሕዝቅያስ የትውልድ ዘመን 146-147

www.zeyeneta.com

18. ስለ ንጉሡ ምናሴ የትውልድ ዘመንና ንስሓ 147
19. ስለ ውቅያኖስ 148
20. ስለ ብሔሞት 148
21. ስለ ንስሓ ትርጉም 148
22. ስለ ነቢዩ ዮናስ የትውልድ ዘመን 148
23. ስለ ወንበሪ.....148
24. ስለ መልሕቅ 149
25. ስለ ነነዌ.....149
26. ስለ ነቢዩ ዳንኤል እና የትንቢቱ ፍጻሜ 149-150
27. ስለ ኢየሩሳሌም ጥንታዊ ስም 150-151
28. ስለ እናንያ አዛርያ ሚሳኤል ዘላለማዊ ምስጋና እና ስሞቻቸው 151-156
29. ስለ ዕንባቆም የትውልድ ዘመንና ዕረፍት ..156-157
30. ስለ ቴማን ትርጉም 157
31. ስለ ፋራን 157
32. ስለ መብረቅ 157-158
33. ስለ ኢሳይያስ የትውልድ ዘመንና ትንቢቱ..158-159
34. ስለ ድንግል ማርያም ዘመንና ምስጋናዋ.....159
35. ስለ ካህኑ ዘካርያስ የልደት ዘመንና የልጁ ዮሐንስ ልደት 159-160
36. ስለ ዘካርያስ እረፍትና የደሙ ጨኸት 160-161
37. ስለ ካህኑ ስምዖን የትውልድ ዘመንና ዕረፍቱ...162

መቅድም

የመጽሐፉ ስም መክሥተ ነቢያት ወምስክናየ ነቢያት በሚል ስያሜ ተሰይሟል።

መክሥት

፩. መክሥት፡- ማለት የሚገለጽ ገላጭ ማለት ሲሆን ነቢያትንና ሥራዎቻቸውን /ትንቢቶቻቸውን/ የሚገልጽ ማለት ነው። በተጨማሪም ነቢያትና ሥራዎቻቸው /ትንቢቶቻቸው / የሚገለጹበትና የሚታወቁበት ማለት ነው።

፪. ምስክናይ፡- ማለት በትርጉም መግዣ ማስገዣ ማለት ሲሆን በምሥጢር ነቢያት የሚቆንቡት የሚዳሰሱበት ታሪካቸውም የሚገለጽበት ማለት ነው።
ስለዚህ ምስክናየ ነቢያት ተባለ። ወ፡ በመክሥትና በምስክናይ መካከል የገባ አጫፋሪና አገናኝ ቃል ነው።
ከዚህ በመቀጠል ከየአንድ አንዱ ነቢይ የነገሰ ቃል ጥቅስን እናቀርባለን።
ዘለቅደመ ነጊረ በአፈ ነቢያቲሁ ወበመጻሕፍቲሁ።
በነቢያቱ አፍና በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋን የተናገረ ነው። ሮሜ ፩፡፪
ዳግመኛም አቅዲሙ ነገረ በአሪት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት እንዲል ቅዱስ ያሬድ ። በእነዚህ በሦቱ ጥቅሶች ፲፩ ቱ ሁሉ ይቃኙሉ /ይገለጻሉ/።

፫. በሲቶ ነቢያት ሙሴ፡- ወይቤ እብጻሕ ፡ዘ፡ ራእየ ወቢየ አፎ ኢትውሂ ዛ ዕፀት። ሙሴም ይህች እንጨት እንዴት እትቃጠልም? ይህን ደግ ራእይ ከዚህ ደርሼ ልይ አለ። ዘጸ ፫፡፫ ዘዳ ፴፫፡፲፮

www.zeyeneta.com

ይህ ማለት በምሥጢር መሴ በአምላለ ዕዕ ያያት ድንግል ማርያም እንደሆነች በመጀመሪያ አስቀድሞ ተናግሯል።

ፎ. **በነቢይት ሐና**፡- ወተፈሣሕኩ በእድኅንትከ።
ስጊዜው ልመናዋን ስለሰማት፡ በትድግናህ /በማዳንህ/ ደስ አለኝ አሰች እንጂ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን እንደሚያድን ተገልጸላት ትንቢትን ስትናገር ነው። ፩ኛ ሳሙ ፪፡፩

ቮ. **በደሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ**፡- ወአንግእካ ለነፍስየ።
ነፍሴን ከሞት አዳንኸት የሚለው ስጊዜው ለእርሱ ቢሆንም ፍጻሜው ግን የሰለተ ዓርብንና የሰለተ ትንሣኤን ትንቢት ያመለክታል።

ፀ. **በንጉሡ ምናሴ**፡- እስመ አኮ ሰጻድቅ ዘዝበርኮ ለንስሓ አላ ተመየጥ ንስሓ ዚእየ ሰንሃእ። ንስሓን የሠራሃው ለጻድቅ ሰው አይደለም የእኔን የኀጥኦኑን ንስሓ ወደማየት ተመለስ /ይቅር በል/ እንጂ። ፪ኛ ዜና መዋ በንእዙ ፴፫፡፲ የሚለው ቃል ከሐዲሱ ቃል ጋር የሚስማማ በመሆኑ።
ለዚህ ማስረጃ ኢመጻእኩ ኦጸውኦ ጻድቃነ አላ ለንስሓ ኃጥኦነ። ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ እልመጣሁም። ማቴ ፱፡፲፫

ጰ. **በነቢዩ ዮናስ**፡- ዮናስ የራሱ የክርስቶስ ምሳሌ ስመሆኑ ፫ ቀን በክርሠ ዐንበሪ ማደርና ከባሕር መውጣት የክርስቶስ ፫ ቀን በክርሠ መቃብር አድሮ መነሣት በቂ ማስረጃ ነው። ዮናስ ፪፡፪ ማቴ፲፪፡፴፱-፵፪

ፍ **በነቢዩ ዳንኤል**፡- ወትትሐነጽ ኢየሩሳሌም እስከ ክርስቶስ ንጉሥ።
ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ሆና ትሠራለች። ስማያዊ አምላክም በሐዲስ ክርስቶስ እንዲባል ገልጿል። ዳን ፱፡፳፭ ማቴ ፩፡፲፮

ጌ. **በቮቱ ደቂቅ**፡- ስፈጣሪያቸው በጸለዩት ጸሎት ውስጥ ፴፫ ቃላትን መናገራቸው ክርስቶስ በዚች ምድር ላይ ለ፴፫ ዓመት ያህል እንደሚመላለስ ተገልጾላቸው ትንቢትን በመናገራቸው።

ጎ. **በነቢዩ ዕንባቆም**፡- በማዕከለ ፪ዓ እንሰሳ ርኢኩከ፡ ከመ ከመ ያቀርብ ኅሙቲሁ አእምረከ፡ ወከመ ከመ ይብጽኅ ገቢሁ እሰ.በወከ። በሁለቱ እንስሳዎች /አድግና ሳሕም/ መካከል አየሁህ ዘመኑ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሳለሁ። ጊዜውም እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሳለሁ ብሎ የክርስቶስን ልደቱን ስትሰቱን ትንሣኤውን በመተንበዩ። ዕንባ ፫፡፪።

ሀ. **በነቢዩ ኢሳይያስ**፡- ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ።
እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ብሎ ደረት ትንቢትን ስሰተናገረ። ኢሳ ፯፡፲፬

ፈ. **በቅድስት ድንግል ማርያም**፡- ናሁ አምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ።
እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል በማለት ድንቅ ሥራንም ሠርቶልኛልና ስሙ ቅዱስ ነው ስትል፡ የጻነሰችሁም የኀሰም ፈጣሪ መሆኑን ይህንንም ክብር የሰጣት እርሱ መሆኑን ገልጻ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል አለች። ትንቢቱም የተፈጸመላት አማናዊት ድንግል እርሷ ናትና። ሉቃ ፩፡፵፰ ዘፍ ፫፡፩

ፐ **በካህኑና በነቢዩ ዘካርያስ**፡- አንሥእ ለነ ቀርነ መድኃኒተነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ። ከባለሟሉ ከዳዊት ወገን የድኅነታችን ቀርን ክርስቶስን ያስነሳልን ብሎ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለሙን ማዳኑን ተናግሯል።
በሣህሉ ወበምሕረቱ ለአምላክነ፡ ለዘሐወጸነ እምእርያም። ከስማየ ስማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በፍጹም ይቅርታውና በቸርነቱ

www.zeyeneta.com

ለኅበኝን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ብሎ ተናግሮአልና። ሉቃ ፩፥፷፰-፸፱

፲፪. በነቢዩና በካህኑ ስምዖን፡- የነቢዩ ኢሳይያስን ትንቢት። ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ የሚለውን አማናዊ ትንቢት በሚጽፍበት ጊዜ ትንቢቱ ተፈጽሞ ጌታችን ተወልዶ በሣ ቀኑ ቤተመቅደስ ገብቶ እንደሚታቀፈው በመንፈስ ቅዱስ የተነገረው ምስጢር ተፈጽሞለት እስመ ርኢያ አዕይንትየ አድኅኖተከ፡ ዘአስተዳለከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ። ከሁሉ አስቀድሞ ያዘጋጀኸው ትድግናህን ወይም ማዳንህን ዓይኖቼ አይተዋልና ብሎ ያየውን ነገር መስክሮ በዕለተ ዐርብም እንደሚሰቀልና ዓለምን እንደሚያድን የተናገረው ትንቢት የነቢያትን ትንቢት ሁሉ አጠቃሎ ስለሚገልጽና ለትንቢቶቻቸው መፈጸሚያና መደምደሚያ የሚሆነውን ትንቢት በመተንበዩ።

እኛም በዚሁ ከመሰሉ አስከ ስምዖን በለሉት በ፲፫ቱ ነቢያት ውስጥ ያለውን የመክሥተ ቃሉት መግለጫን እናጠቃልሳለን።

ከዚህ በመቀጠል መጀመሪያ ወደተነሣንበት ስንመለስ ይህን መጽሐፍ ከዋናው እንድምታ ትርጉም ጎን ለጎን እንዲዘጋጅ ያደረግንበት ምክንያት ትንቢት ከትንቢት። ምስጋና ከምስጋና፡ ታሪክ ከታሪክ፡ ትርጉም ከትርጉም ምሥጢር ከምሥጢር ጋራ ነውና።

፩ ለዚህም አንድ አንድ ማስረጃዎችን እናቀርባለን።
ከመዝሙረ ዳዊት፡ መዝሙረ ክርስቶስ

፪ ከትንቢተ ኢሳይያስ ዕርገተ ኢሳይያስ /ብሉይ አዋልድ/

፫ ከትንቢተ ኤርምያስ፡ ስቆቃው

፬ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት፡ ሄርማ

፭ ከቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት /ውዳሴ ማርያም/ መልክአ ውዳሴ፡ እንደተውጣጣ ሁሉ በዚህ መጽሐፍም ውስጥ እንደዚሁ የነቢያትን ኃይለ ቃልና ታሪክ እንቃኛለን።

ማብራሪያ

፩ኛ. ከዘወትር ምስጋና /ስብሐተ ነግህ/ የተለመደው ምስጋና ከተደረሰ /ከተፈጸመ/ በኋላ ምቅናይ ተብሎ የመጀመሪያው መደበኛ ድርሰትን መስሎ በውስጡ ስርዋጽ እየጠቀሰ ይሄዳል። ስርዋጽ ማለት ማቅኛ ማስረጃ ማስታወቂያ በነገር መካከል የሚገባ ነው። ይህም ምቅናይ ይባላል።

፪ኛ. በዐቢይ ጾም እንደዚሁ በምቅናይ ውስጥ ስርዋጽ ይገኛል።

፫ኛ. በዘመነ ጽጌ፡

፬ኛ. በዕለተ ሰንበት፡

፭ኛ. በዘመነ ስብከት።

ስለዚህ ይህም ምቅናየ ነቢያት ተብሎ ከዋናው እንድምታ ትርጉም ቀጥሎ ኃይለ ቃሉን እየተረጐመና ታሪኩን እስከ ዘመኑ እየቃኘ በግልጽ የሚያስረዳ በመሆኑ መክሥተ ነቢያት ወምቅናየ ነቢያት በሚል ስም ተሰይሞ ቀርቧል።

ከዚህ በመቀጠል በምዕራፍ ሳይሆን በእንቀጽ በእንቀጽ ተከፋፍሎ /ተዘጋጅቶ/ የቀረበ መሆኑንም ስለእንባብያን እናሳስባለን።

www.zeyeneta.com

የመግቢያ ማሳሰቢያ

አንቀጽ ማለት በር መውጫ መግቢያ ማለት ሲሆን ሌሎች ትርጉሞችም አሉት በተክታታይ ዝርዝሩን እናቀርባለን፡፡

፩ ቤትና ባለቤት፡- የመውጫና የመግቢያ በር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ለቤቱም መልክና ውበት የሚሰጠው ስበሩ መውጫና መግቢያ ሲኖረው ነው፡፡ ባለቤቱም በቤቱ ውስጥ እንገዳን የሚቀበልና የሚያስተናግድ መውጫና መግቢያውን አልፎ ነው፡፡ እንግዳውም ግቢውን አልፎ ወደ በርና ወደ ቤት ገብቶ ይስተናገዳል፡፡ ይህም የመጽሐፍ ክፍል የአንዱን ነቢይ ወይም የአንዱን ኃይለ ቃል ትርጉም ከተረጉመ በኋላ ወደዋናው ቋሚ ታሪክ ምሥጢርና ሐተታ ገብቶ ከመነሻው እስከ መድረሻው ያለውን ታሪክና ምሥጢር ያስረዳል፡፡

፪ አንቀጽ፡- ማለት የመጽሐፍ ክፍለ ምዕራፍ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አንቀጽና ምዕራፍ የተለያዩ አለመሆናቸውን ከዚህ ትርጉም መረዳት እንችላለን፡፡

፫. አንቀጽ፡- ማለት የዘማች ቃል ማሠሪያ ማለት ነው፡፡ ይህም ክፍል የተፈሳጊውን ኃይለ ቃል በርዝሮ በመፈለሻ በበቂ ማለረጃ ለታሪኩ መነሻና መድረሻ፡ ማሠሪያና መደምደሚያ ሰጥቶ ዝርዝሩን ይጨርሳል፡፡

፬. አንቀጽ ፡- ማለት የዜማ ስረይ ማለት ነው፡፡ ለሌላ ዜማ ምልክት የሚሆን አብነት ማለት ሲሆን የዜማው ጠባይ ብዙ ዓይነትና ብዙ መንገድ /ድርብ/ ሲኖረውና ከአንድ በላይ የሚሆንበት ሲገኝ አንቀጽ ይባላል፡፡
የመጽሐፉም አዘገጃጀትና መንገድ ተደራራቢ ትርጉም ምሥጢርና ታሪክ ያለው ስለሆነ፡፡

፭. አንቀጽ፡- ሃሌታ ተብሎ በኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ድርሰት የተወሰነ ለያሜ አለ፡፡ ሃሌ /ሃሌታ/ ማለት ደግሞ አዲስ ምስጋና፡ መዝሙር፡ ቅኔ፡ ሻናይ አገልግሎት ማለት ነው፡፡ አይኑ ሻናይ ወአይኑ አኮቴት፡፡ ምን መገዛት ነው ምን ምስጋና ነው እንዳለ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በመጽሐፈ ቅዳሴ፡፡

በዚህም ሳይ መዝሙር በሃሌ
ነገር በምሳሌ
ጠጅ በብርሌ እንዲሉ፡፡ ስለዚህ ሃሌታና አልልታ /መንፈሳዊውን/ አንድ እንደሆነ ሁሉ የአንድምታ ትርጉሙን ተከትሉ የተዘጋጀው ይህ የመጽሐፍ ክፍል ለአንድምታው የትርጉም ልጅ ነው፡፡ ልጅ ከአባትና ከእናቱ እንደሚገኝ ሁሉ ይህም ክፍል መከሥተ ነቢያት ወምቅናየ ነቢያት የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ በመጀመሪያው መቅድም ላይና በዚህ የመግቢያ ማሳሰቢያ ክፍል ያተረዘናቸውን ማለረጃዎችንና ማስገንዘቢያዎችን በዚህ አጠናቀን ወደ ዋናው የነቢያት መጎልይ አንድምታ ትርጉም ገብተን እንመለከታለን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን፡፡

www.zeyeneta.com

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

መጻልየ ነቢያት ወጸሎቱ ሰሙሌ። ሙሴ ማለት ምልክአም ማለት ነው። ምልክአምም ማለት መልእክ እግዚአብሔር ማለት ነው። ኋላ ግን ተርሙት ወለተ ፈርዖን ከውሃ ስላገኘችው ዕጓለ ማይ ተብሏል። እማይ ዘአውጸእክም እማይ ዘረከብክም ስትል።

ታሪክ

ሴሩህ የሚባል ሰው ነበረ። ብኑ/ብህኑ/ የሚባል ልጅ ነበረው።

ወእንዘ በቆው ተመስጠ ሕፃኑ። ወእንዘ ቆውም ይላል። ገና በሕፃንነቱ ሳለ ሞተበት። ገዘን ጻናበት ገዘን ሲጸናበት አያተው ዘመዶቹ እንጨት ጠርበው ዘይት ቀብተው ልብሱን አልብሰው ልጅህ ብኑ ይኸውልህ አሉት። ልጄ ብኑ ነህ? አለው። ሲያከናውኑት /ሲያጥቡት ሲገንዙት/ ሰይጣን ከውስጡ አድሮ አ አለው። አምላክ ቢሆን ነው እንጂ አምላክ ካልሆነ ይናገራል? ብሎው ሲያመልኩት ኖሩ።

ሴሩህ ናኮርን ናኮር ታራን ታራ አብርሃምን አራንን ናኮርን ይወልዳል። ይህ አብርሃም አባቱ ታራ ጣያት እየጠረበ እየሰጠው እሱ እየሸጠ ይመለሳል። ከዕለታት አንድ ቀን ረክሰበት /የሚገዛው አጥቶ/ ሲመለስ ከዋዕየ ፀሐይ የተነሣ ደክሞት ከዛፍ ጥላ ሥር አርፎ ሳለ አምላክ አይደለህምን? ራቦኝ አብላኝ አለው። ዝም አለው። ባይሆንም የደከመው ሰው ሲያጫውቱት ይጸናልና አጫውተኝ አለው። የማይመልለለት ሆነ እንኪያ ደንጊያ ተሸክሜ እሄዳለሁ? ብሎ ያን ቀጥቅጦ ጥሎ ጊዜው ቀትር ነበርና አቅንቶ ቢያይ ፀሐይ መልታ ሰፍታ ስታበራ አይቶ አምላክስ ይቺ ናት አለ። ቀጥሎ ሲያስብ ደፈር ጠፈር ሲከለክላት አየ ይቺ ስትገባ ማን ይገዛል ብሎ አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ ፀሐይን የፈጠርክ አምላክ ተገለጽልኝ አለ።

ያን ጊዜ ጌታ አብርሃም አብርሃም ነዐ ጻእ እምብሔርክ ወተፈለጥ እምአዝማዲክ ብሎ ቈይቱን ሥጎ-ፍጥረት ነገረው። ሄዶ አባቱ ሰማዩን ምድሩን ባሕሩን የብሉን የፈጠረ አምላክ አለሳ?

ወዲያውስ ምንት ውእቱ ዘንረክብ እምኀቤሁ ተድላ ወረድኤተ።

ከጣያቱ የምናገኘው ጥቅም ምንድር ነው አለው። ልጄ ፈጣሪስ እንዳያደለ አውቃለሁ እንደሀገሩ ይሸገሩ ብዬ ነው እንጂ። ነገር ግን የዚህ አገር ለምች ልቡናቸው በፋቅረ ጣያት ተመስጣል፡ ይገድሉሃል ገዘም በል አለው። አሺ ያስ መስሎ ሄዶ ቤተ ጣያቱን አቃጠለው።

ወሠረረ አራን ይላል። ጣያቱን ሲያመጣ ገባ አሳት ተሻምቶ አስቀርቶታል። ሰማዕተ ጣያት ሆኗል። ያን ጊዜ አባቱን የወንድሙ ልጅ ሎጥን ይዞ ካራን ወጣ። ከዚያ ፸፭ ዓመት ኖረ። አባቱ ሞተ አባቱን ቀብሮ ከነዓን ወጣ። ብሔረ ከነዓንን ከዚህ አስከዚህ አወርስሃለሁ ብሎ በዓይነ ሥጋ አሳየው በአግሪ ሥጋ አሰረገጠው። ብሔረ እስራኤልስ ሰፊ ናት ብሎ ቅርብ ቅርቡን በዓይነ ሥጋ አሳየው በእግረ ሥጋ አስረገጠው። ሩቅ ሩቁን በዓይነ ኅሊና አሳየው በእግረ ኅሊና አስረገጠው። ከዚያ ሲኖር ለወንድሙ ልጅ ለሎጥ የአባትህን ክብት ውስደ ብሎ ከፍሎ ሰጠው። ከብታቸው በዛ ኖሎተ አብርሃምና ሃሎተ ሎጥ /የአብርሃምና የሎጥ እረኞች/ በሣር በውሃ ምክንያት ይጣሉ ጀመር።

ለምንት ንጸባሪ እንዘ አኀው ንሕነ ተፈለጥ የማነ አው ፀጋመ። ቸኝ ግራ ብለህ ተሰደ አለው።

ወርእየ አሕታሳቲሃ ለዮርዳኖስ ይላል። አሻገር ቢያይ ይቺ ለዶም አምላኪዛ ለገነት ይጣታል። እጅግ ልምልምት ነበረች ሄዶ ከዚያች ተቀመጠ። ፭ቱ ነገሥተ ሰዶም ለ፱ቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ፲፫ ዓመት ሲገብሩ ኖሩ። በ፲፫ተኛው ዓመት በሰማይ የለ ዱር በሰዶም የለ ግብር ብለው ግብር አቀለጡ /ከለከሉ/። መጥተው ገጠሟቸው ፭ቱ ነገሥተ ሰዶም ድል ሆኑ ሎጥ ተማረከ ኧረ የወንድምህ ልጅ ሎጥ ተማረከ ብለው ለአብርሃም ነገሩት። ቤተሰቡን ቢያወጣጣ /ቢያስቆጥር/ ፫፻፲፰ ጭፍራ አገኘ። ኤስኬል መምራ የሚባሉ አርበኞች ነበሩ። እነዚያን እርዱኝ ብሎ በቆላተ ሴዋ።

እንተ ይእቲ ባሕረ ጼው ይላታል። ግዳይ /ምርኮ/ ሲያስጥል አደጋ ጥሎ ወንድሙን መልሷል። ይህ ምሳሌ ነው፡

www.zeyeneta.com

አብርሃም የወልደ እግዚአብሔር፡ ሎጥ የሃይማኖት፡ ይሄደኛ የይሄደኛ ሲቃውንት ምሳሌ፡ ከጅቱ ነገሥተ ሰዶም ቅቱ ሞተው አንዱ ቀርቶ ነበር። ቀረብ ብሎ ገንዘብ አልልህም አገር ያለ ሰው እንዳይሰማ ታውቃለህ ሰውን ስጠኝ አለው።

አሌዕል አደውየ ውስተ ሰማይ ከመ ኢይነሥእ እምንዋይከ ኢ ፈትሰ ወኢ ቶታነ አማዕን ከመ ኢትብል አነ አብዐልክም ለአብርሃም አለው።

ባሕቱ ይንሥኡ መክፈልቶሙ ኤስኬል ወመምሬ አለው።

አዘዘብን እንዳይሉ ጌታ ገንዘብ በመጥላቱ ደስ አለው።

አብርሃም ብዙኅ ዐስብክ በንቤየ አለው። ምንት ያብቍዐኒ አኮኑ ኢያቡር ወልደ ዘመድየ ዘይወርስኒ አለው። አኮ ኢያቡር ዘይወርስከ ንዋየከ አላ ወልድከ ዘይወጽእ እምሐቌከ ውእቱ ይወርስከ ንዋየከ አለው። ሴሊት ከተራራ አውጥቶ ጉልሙ ከዋክብተ ሰማይ አለው።

አንሰ ኢይክል ጉልቆቶሙ አለው። ከማሁ ኢያትኂለቍ ዘርዕከ /ኢይትኂለቍ ደቂቅከ/ አለው። ልጅህ የልጅ ልጅህ እንዲህ አይቆጠርም/ አይቆጠሩም/ ብሎታል። በከዋክብት የተመሰሉ አስራኤል ልጆቹ፡ በአሸዋ የተመሰሉ አሕዛብ ልጆቹ ናቸው። አንድም በከዋክብት የተመሰሉ በሥጋም በሃይማኖትም የሚወልዳቸው፡ በአሸዋ የተመሰሉ በሥጋ ብቻ የሚወልዳቸው። አንድም በከዋክብት የተመሰሉ ጻድቃን ልጆቹ፡ በአሸዋ የተመሰሉ ኃጥአን ልጆቹ ናቸው። ይህስ የሚወርሱበት ምን ጊዜ ነው አለው።

አምጽአ ላህመ ዘቮቱ ዓመቱ፡ ወአጣሌ ዘቮቱ ዓመቱ፡ ወበግዐ ዘቮቱ ዓመቱ፡ ርግበ ወማዕነቀ አለው። ይህን ስውተህ አንብር ዘተመትረ በአንጻረ ቢጹ። ከሁሰት ከሁሰት ክፍለህ በአንጻር በአንጻሩ አኑረው። ሰአዕዋፍሰ ኢትምትሮን አዕዋፍን ግን ገዘግዘህ ተዋቸው አትቁረጣቸው አለው። እንዳለው አደረገ። ወመጽአ ድንጋጼ ስአብራም ይላል። እንደ እንቅልፍ ወደብ አደረገው በሥጋው ላይ አሳት ነፋስ ጨለማ ሲመላለስ አዕዋፍ እንበላሰን ብሎው ሲመጡ በዘንግ ሲከለክላቸው ያያል። ይህም ምላሌ ነው። አሳት ነፋስ ጨለማ የመከራቸው፡ ሥጋ የአስራኤል፡ አዕዋፍ የአሕዛብ፡ ዘንግ የኪዳነ አብርሃም። አዕዋፍ እንበላሰን ሲሉ በዘንግ

ሲከለክላቸው ማየቱ አሕዛብ አስራኤልን እናጠፋሰን ሲሉ በኪዳነ አብርሃም ተጠብቀው የመኖራቸው ምሳሌ። ከሄ ክፈለው ማለቱ ፪፻፲፭ ዘመን በከነዓን ፪፻፲፭ ዘመን በግብፅ የመኖራቸው። በአንጻር አኑረው ማለቱ መከራው በጽርዕ በሚዶን በፋርስ በባቢሎን ተበትነው እንደተቀበሉት አያደለም። በአንድ በግብጽ ሁነው ተቀብለው ታልፍ። ከዚያውም ዘንድ በምድረ ጌሴም። ዘቮቱ፡ ዓመቱ ማለቱ በቮኛው ትውልድ በያዕቆብ ግብጽ የመውረዳቸው። አብርሃም ደሰሐቅ ያዕቆብን በሳም መስላቸው። ላም ከሁለት ትበረታለች በመጀመሪያው ፈርዖን በርትተው የመገዛታቸው /የመኖራቸው/ በፍየል መስላቸው ፍየል ከሳም ትደክማለች ከበግ ትበረታለች በሁለተኛው ፈርዖን እጅግም ሳይበረቱ እጅግም ሳይደክሙ የመኖራቸው በበግ መስላቸው። በግ ከሁለት ትደክማለች በሦስተኛው ፈርዖን ፈጽመው የመድከማቸው። ርግብ የሙሴ ስለ የዋህነቱ። ማዕነቅ የአሮን። አንድም ርግብ የአሮን ርግብ ከተማ እንዳትለቅ አሮንም በዘመዱቹ መካከል ይኖራልና። ዋኖስ መሥዋዕት እንድትሆን አሮንም መሥዋዕት ያቀርባልና። የአሮን ማዕነቅ የሙሴ ኑሮዋ በረሃ ነው። ተስዶ ምድረ ምድያም የመሄዱ መገዝገዛቸው በአስራኤል መከራ የማዘናቸው አለመቆረጣቸው ሙሴን አሮንን ፈጽሞ መከራ እንደ አስራኤል አላገኛቸውም። ላህም የጌታ፡ ጠሊ የሐዋርያት። በግዕ የአርያኦት። አንድም ስለማዕረጋቸው፡ ጠሊ የአርያኦት። በግዕ የሐዋርያት። ርግብ የእመቤታችን። ማዕነቅ የዮሐንስ። ወልደ ነጐድጓድ። መገዝገዛቸው በጌታ ሞት የማዘናቸው አለመቆረጣቸው እመቤታችን ዮሐንስ በስማዕትነት አልሞቱም። አንድም ዘቮቱ ዓመቱ፡ ማለቱ ሦስት ላም ሦስት ፍየል ሦስት በግ ሲል ነው ብሎ አንድ ወገን የመሥዋዕትነቱ ምሳሌ። ይህን ከሁለት ሲከፍሉት ፲፪ ይሆናል። ርግብና ዋኖስ ባሉበት /ሲጨመሩ/ ፲፭ ይሆናል። ተስፋውን ሰአብርሃም በነገረው በሁለት ሺህ ዘመን ጌታ ከሴተ አብርሃም ስው የመሆኑ፡ ሥጋ የመልበሱ ምሳሌ። በሦስተኛው ፈርዖን በጣም ጨርሰው የደከሙበት እንደምን ነው ቢሉ መምክሮን መማክሮን የሚባሉ የከነዓን ነገሥታት ነበሩ። እየወረዱ

www.zeyeneta.com

ግብጻውያንን ይወጓቸው ነበር። ዛሬስ ባሮቻችን እስራኤል ይርዱን ብለው አስለፏቸው ግብጻውያን እንደልማዳቸው ድል ሆኑ። እስራኤል ባሉበት ድል እድርገው ይዘፍኑ ያጨበጭቡ ጀመር። የአሕዛብ ምን ድንበር አለው ደርበህ በለው ብለው ወግተዋቸዋል አምቻችን አፈኛ ቢመለስ ወደእኛ ወይ እኛ ወይ እኛ ባመጣነው እዳ ሆን አሣረኛ ያለው እንጂ በእኛ ይደርሳል እንግዲህማ መውጫ መግቢያውን አውቀውታል ከጠላቶቻችን ጋራ ሆነው ወግተውን ሲሼዱ አይደለምን? ንው ንጠበብ ቦሙ ኖራ አናስወግጣቸው ጡብ /ጡበና/ እናሰረግጣቸው ብለው ራምሴ ጋምሴ በሚባል ቦታ አንፈቶን /ፊቶም/ የሚባል ግንብ አሠርተዋቸዋል። እንዲህ ማድረጋቸው ሲደክሙ ሲውሉ አይገናኙም ካልተገናኙ አይባዙም ብለው ነበር። እነሱ ግን በጥበበ እግዚአብሔር እየበዙ ሔዱ። ፍሀ ሲፓራ የሚባሉ ዐቀብተ መወልዳት ሾሙ። እናዋልዳለን አያላችሁ እየቀረባችሁ ወንድ ወንድ ሲወለድ ገርዎ ውሰተ ባሕረ ተክዚ አያነቃችሁ ከባሕር ጣሉት አሏቸው።

ታሪክ በዚያ ወራት ጌታ ሙሴን ሲያድነው ሲወድ በፊቱ ብርሃን ተሰሎበት ተወለደ። ወተሰብሐ ጎብረ ገጹ ለሙሴ እንዲል ወተራኅርኦ እልክቱ መወልዳት ይላል። ይህንስ የፈጠረው ፈጣሪ ይግደለው ብለው ራርተው ትተውት ወተሐፅነ ፫ተ አውራኃ ውሰተ ቤተ አቡሁ ይላል። በ፫ ወሩ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ሊያሰቅስ ሲለነጥስ ይታወቃል ንጉሥ የለማ እንደሆነ ለእናንተም ለእኛም መልካም አይደለም ለዚህ ነገር ብልሀት ፈልጉለት አሏቸው። አባቱ እንብረም ሣጥን ጠርቦ አፍሮዲጡ በሚባል የውሃ አረፋ ለብጦ ወስዶ ከጅብጅባ ስር ጣለው። ሌለ.ት ሌሊት እናቱ ዮካብድ እየወረደች ስታጠባው ታድራለች። ቀን ቀን ማርያም እኅቱ ስትጠብቀው ትውላለች። እንጨት የምትሰብር ውሃ የምትቀዳ እየመሰለች። ከምን ትጠብቀዋለች ቢሉ አንዳሰበር የሚባል አሞራ አለ። እሱ ሽቅብ ሣጥኑን ይዞ ወጥቶ ከድንጋይ ላይ ይጥለዋል አጥንቱ ይከለከላል ደሙ ይፈስላል ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ ይሄዳል: ከዚያ ትጠብቀው ነበር።

በ፯ተኛው ቀን ወወረደት ተርሙት ወለተ ፈርዖን ትትሐጸብ በማይ ይላል። ከባሕር ለምን ሔደች ቢሉ ኮብሽ የሚባል ደዌ ይዟት ነበርና ለመታጠብ: አንድም መንግሥት በጉርጉራ ላለ የነገሥታት የአፄ መለክ ስገድ ልጆች ይዋኙ እንደነበር ለመዋኘት። አንድም ባሕር ታመልክ ነበርና ለማሚረት: አንደም ዓሣ ዐንበሪ አዞ ጉማሬ ታመልክ ነበርና ለማሚረት ሔዳ። አንድም ደንገጥሮችዋ እየተመላለሱ ሲጫወቱ አይታ: አንድም ነጋዲ ወዳጅ ነበራት ለመገናኘት። በማናቸውም ምክንያት ከወረደች ዘንድ እሻግራ ዓይታ የነጋድያን እቃ /ወርቅ/ ማዕበል ሞገድ አስቀርቶባቸው /ያመጣው/ ይሆናል እምጡት ብላ አሰመጥታ ከፍታ ብታይ መልክ መልካም እንደ ፀሐይ የሚያበራ ልጅ አገኘች። ከዚህ በኋላ ዕብራውያን ፈርተው ጥሰውታል ልጅ ይሆነኛል አሳድገዋለሁ ሞግዚት ፈልጉልኝ አለች ማርያም እኅቱ ቀረብ ብላ ካልሽስ ትናንትና ልጂ የሞተባት ዕብራዊት ሴት አለች ብላ እናቱን መሰደችለት እናቱ ሞግዚት አኅቱ የሞግዚት ደንገጥር ሆነው አሳድገውታል። አባቱ እንበረምም የሞግዚት ባል ሆኖ ቀረበ። እናቱ ዜና አበውን አባቱ ተሰፋ አበውን እየነገሩት አደገ። ፳ ዓመት ሆነው: አንድም በ፵ ዓመቱ ቀስት ነፍጥ መጠረቅ መታጠቅ መፍታትን ይማር ተብሎ ከአያቱ ከፈርዖን ቤት ገባ። ፵ ዓመት ተቀመጠ። ፵ ዘመን ሆነው በ፵ ዘመኑ እስኪ በምድረ ጌሌም ያሉ ዘመዶቼን ጠይቄ ልምጣ ብሎ ሄደ። ሲኼድ ዕብራዊና ግብጻዊ ተጣልተው አገኘ ጠቡ /የጠቡ ምክንያት/ ፩ኛ. ዕብራዊ በበጠበጠው እንዶድ ግብጻዊ ልጠብ ብሎ: ፪ኛ. በዕብራዊ ፈንታ ግብጻዊ ሳጠጣ ብሎ ፫ኛ. ዕብራዊ ያወጣውን ዓሣ ግብጻዊ ልውሰድ ብሎ። ምነው አንተ እንዲህ አድርገህ ትገደረዋለህን /ትበድለዋለህን? አለው አንተ በገዛ ባሪያዬ ገላውን እንደ ቆርበት /ቆርበቱን እንደ ጀንዲ/ ሥጋውን እንደ እንዶድ ደሙን እንደውሃ አጥንቱን እንደ አለት አድርጌ ባጥብበት ታድነዋለህ? ብሎታል። ወነጸረ ሙሴ ለፌ ወለፌ ይላል። ቀኝ ግራ ብሎ አይቶ ይህ መምለኬ ጣያት መምለኬ እግዚአብሔርን ይገደረዋልን ብሎ ክቡደ መዝራዕት ነውና እንድ ጊዜ በጡጫ ቢለው አረፈ። ወደፈኖ ውሰተ ኖኅ ይላል። አሸዋ ጭሮ አልብሶት ሄዷል። ይህም ምሳሌ

www.zeyeneta.com

ነው። ሙሴ የጌታ፡ ዕብራዊ የአዳም፡ ግብጻዊ የዲያብሎስ፡ ኖኅ የሦስቱ አርእስተ ኃጣውኢ። <u>አንድም</u> ኖኅ የመስቀል ሥዑ በአንዱ ድል እንደነሳው። ጌታም በሦስቱ አርእስተ ኃጣውኢ ቢመጣበት በሦስቱ አርእስተ ምግባራት ድል ነስቶታል። ከዚያ ጠይቆ ሊመለስ ዕብራዊና ዕብራዊ ተጣልተው አገኘ <u>ጠቡ እንደዚሁ ነው</u>። ወፈቀደ ይዕርቆሙ ይላል። ሊያስታርቃቸው ወዶ ለምንት ትጸብው እንዘ አንተ አንትሙ አላቸው። ይልቁንም በደለኛውን አይቶ አንተ ወንድምህን እንዲህ አድርገህ ለምን ትገፋዋለህ አለው። መኑ ሜመከ መልአከ ወመከሮንነ። በእኛ አለቃ ዳኛ አድርጎ ማን ሾሞሀል ወሚመ ትፈቅድኑ ትቅትለኒ በከመ ቀተልኮ ትማልም ለግብጻዊ አሰው። ምነው አሁን ወነጸረ ሙሴ ለፈ ወለፈ አላልንም ነበር ቢሉ እሱ አላየም አልን /አለ/ እንጂ ሴላ አላየውም አላለም። በዱር በገደል ተጠግቶ ያለ በቅጠል ቀዳዳ ሊመለከተው የነበረ ነው። አንድም ዛሬ ወንድሜ ሙሴ ባይኖር ያ ግብጻዊ ሊገለኝ ነበር ብሎ አመስጋኝ አማሳኝ እንዲሉ፡ ሙሴ ያዳነው ሰው ነው ባለጌን ካሳደገ ያነቀ ጸደቀ እንዲሉ፡ <u>ዮሐንስ</u> አፈወርቅ ግን ወንድሜ ሙሴ ባይኖር /ባይሆን/ ብሎ የተናገረው በትረ ፈሪ ጎሮ ወዳጅ /ብትር ፈሪ ጠብ ወዳጅ/ እንዲሉ፡ ያዳነው ሰው ያው ነው ብሏል። ወኮነ ዝንቱ ነገር ክሡተ ቅድመ አዕያንቲሁ ለፈርያን ይላል። ይህ ነገር በፈርያን ፊት ታውቆ ቢሆንማ ከታች ባቱን ከላይ አንገቴን አይሠራኝም አይቀጣኝም? ብሎ ተለዶ ምድረ ምድያም ሔደ በጎዳነኛ ልማድ ከውሃ ዳር ተቀምጦ ሳለ የካህነ ምድያም የየቶር ፯ ሴቶች ልጆች ነበሩት በግ ሊያለቃቅሙ ዓይቶ ምነው እናንተ አታጠጡም አላቸው። ይህ ደንጊያ የሚከፈት ለሃምሳ ለስልሳ ነው ዘላኖች /አረኞች/ መጥተው አጠጥተው እኛስ የምናጠጣ በመጨረሻ ነው አሉት። ያንን ከፍቶ አየተዳ ሊያጠጣላቸው ዘላኖች መጡ። ምነው እናንተ ወትሮን ዛሬ ከኛ ፊት ማጠጣታችሁ አሏቸው። ምነው ውሃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ /ምርኮ ለጀመረ/ አይደለም? ብሏቸዋል። <u>ፍትሐ ሙሴ</u> ያለኘው ይህ ነው። ይኸውም ጸንቶለት ይኖራል። አጠጥቶላቸው ሄዱ ዮቶር ዮምሰ አፍጠንክን መጺአ አዋልድየ። ልጆቼ ዛሬስ ፈጥናችሁ መጣችሁ አላቸው። አባታችን እንዲህ ያለ ሰው

አጠማጠሙ ግብፃዊ አነጋገሩ ዕብራዊ አግኝተን እርሱ አጠጥቶልን ነው አሉት። እንዲህ ያሰ ሰው ስታዩ ሰምን ትታችሁ መጣችሁ አላቸው። ሲፓራ ይላታል ሚስቱ የምትሆን ናትና አሁንም አላጣውም ብላ ሄዳ ይዛው መጣች። ራት በልተው ሲተሳሰቡ አድረዋል በነገው ሲጨዋወቱ ነገድህስ ስማን ነው ነገርህስ እንደምን ነው አለው። ነገዱም ዕብራዊ ነኝ ነገሬም እንዲህ ያለ ነው አለው። ጎዳና ቢኼዱት ቢኼዱቱ ውሃ ቢቀዱት ቢቀዱት ያልቃል? ከልጆቼ አንዲቱን አግብተህ በጎቼን እየጠበቅህ አትኖርም አለው ሊፓራን አግብቶ ፶ ዘመን በግ እየጠበቀ ኖሯል። ኤልዛር ጌርሳም የሚባሉ ልጆች ወልዷል። ኤልዛር ማለት ረዳኢ ረድኤተ እግዚአብሔር ማለት ነው። ጌርሣም ማለት ነግድ ወፈላሲ ዘወልድከም በስደትየ ማለት ነው። ኤልዛር በአባቱ ሥርዓት ተገዘረ ጌርሳም በእናቱ ሥርዓት ሳይገዘር ቀረ በአርባ ዘመኑ በጎቹን በደብረ ኮራብ አሰማርቶ ሊአበላ /ሊጠብቅ/ በደብረ ሲና ነበልባሉ ከሐመልማሉ ሐመልማሉ ከነበልባሉ ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው አይቶ ወቀርበ ያጠይቆ ይላል። ይህንስ ቀርቦ ሲረዱት ይገባል ብሎ በጎቹን አንድ ወገኑ ከፈረሰ ግንብ አግብቶ /አስጠግቶ/ ዘለሳ /አጥር/ ጥሎባቸው ከአፈረ ነደልም ቢሉ አስጠግቷቸው ይሄዳል። ስጊዜው ሳልረዳው አመለሳለሁ ብሎ ነው። ለኋላ ግን ምሳሌ ነው። ሙሴ የመናንያን፡ ምነና ሲኼዱ ገንዘብን ሰጥቶ መጽውቶ ሕዋሳትን ጠቅሎ መሄድ ይገባል ሲል ከእግረ ደብር ሲደርስ ፶ ከንድ ሲቀረው ሙሴ ሙሴ ፍታሕ ቶታነ አግዕኒከ እምአገሪከ እስመ ዘትከይዳ ምድር ቅድስት ይእቲ የምትቆምባት ደብረ ሲና ከብርት ናትና ጫማህን አውልቅ አለው። ለጊዜው ስንኳን ከሰማያዊ ንጉሥ ሊቀርቡ /ሊገናኙ/ ከምድራዊ ንጉሥ ሲገናኙ /ሊቀርቡ/ ጫማን አውልቆ ባጭር ታጥቆ መገናኘት ይገባል ሲል ነው። ለኋላ ግን ምሳሌ ነው። ደብረ ሲና የቤተክርስቲያን አምሳል፡ ቤተክርስቲያን ሲገቡ ጫማን ፈትቶ በእጭር ታጥቶ መግባት ይገባል ሲል። <u>አንድም</u> የምትሄድባት ግብጽ ጽንፅት ናትና አሣፅነ ፍርሐትን /የልብ ፍርሐትህን/ ተው ሲል ነው። <u>አንድም</u> ፋል የሚባል ጥንቆላ ተምሮ ነበርና ያንን ተው ሲል

www.zeyeneta.com

/ሲሰው/ ነው። <u>ኧንድም</u> ልጆቼን ማን ይመግብልኛል ማለትን ተው ሲል ነው። አንድም ከግብጽ ስትመለስ በደብረ ሲና የምሠራልህ ሕግ ጽንዕት ናትና ልማደ ዮቶርን ተው ሲሰው ነው። ይህም ምሳሌ ነው። ሐመልማል የአሰራኤል: ነበልባል የመከራቸው: ሐመልማሉ ነበልባሉን አንዳላጠፋው እስራኤልም በገዘን መከራውን አላራቁትም: ነበልባሉ ሐመልማሉን አሰማቃጠሉ መከራውም ጨርሶ አላጠፋቸውም ጨርሶማ ካጠፋቸው ከሴት ከሕፃን ሴላ ሰድስት መቶ ሺህ አጋር ይገኛል? ነዐ አፈኑስ ክመገ በሎ ለፈርያን አለው። ፈንዖሙአ ለሕዝበየ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል አለህ በለው አለው። ማን አለኝ ልበለው አለው አኽያ ሸራኽያ ኤልሻዳይ። አኽያ አምላክ ዕብራውያን: ሸራኽያ አምላክ ተለፋ: ኤልሻዳይ ዘሀሎ ወይሄሉ ማለት ነው። ምን ምልክት ይዘህል ቢለኝሳ አለው። ምን ይዘህል አለው ለማናገር ቢሻ ነው። ብትር አለው ጣለው አለው ቢጥለው እባብ ሆነ ሙሴ ሸሸ ተመልሰህ አንሳው አለው። ተመልሶ ቢያነሳው በትር ሆነ ይኸውም ምሳሌ ነው። ብትር የአሰራኤል: እባብ መሆኑ የመከራቸው: መጣሉ ግብፅ የመውረዳቸው: ሙሴ መሸሹ ተሰዶ ምድረ ምድያም የመሄዱ: ተመልሶ ማንሳቱ ተመልሶ አሰራኤልን የማውጣቱ። እባብ ተመልሶ ብትር መሆኑ አሰራኤል የመዳናቸው :: ድገመኝ አለው። እጅህን ከብብትህ አግባው አለው። አገባው አውጣው አለው አወጣው ቢያወጣው ለምፅ ሆነ መልሰህ አግባው አለው አገባው አውጣው አለው ቢያወጣው ደኅና ሆኗል ወርቁ አይለወጥም። ዳግም ክቤተ መንግሥት የሚላክ አከናውኖ የሚናገር ነው። እኔ ምላሰ ዲዳ አፈ ለንባዳ ነኝ አለው። ጸያፍ እ እ የሚል ነው ዲዳ ረን ሰ የሚል ነው። አሮን እጉክ ይኩንክ ነቢየ አፈም ይላል። አሮን ከራምሴ /ከጋምሴ/ ከደብረ ሲና ሙሴ: ተራከቡ በደብረ እግዚአብሔር /በደብረ ሥላሴ/ ይላል። ነገረ እግዚአብሔር ስለተነገረባት ደብረ እግዚአብሔር አላት።

<u>ታሪክ</u> ለዚህ ያበቃቸው ምክንያት ምንድነው ቢሉ ጠግበፅ ላሉ ራሔል የምትባል ሴት ነበረች ባልዋ (ምናሴ/ሮቤል) ይባላል።

መድኃኒት ጠጥቶ ታሞ ይላሉ። በባሷ ተተክታ ኖራ ልትረግጥ ሄደች። ስትረግጥም ምጥ ተሰማት ለሹሙ ወጥቼ

ልውለድ አለችው የንጉሥ ሥራ ይፈታ የለም? ብሎ ጀርባዋን በዘንግ ቢመታት መንታ ጸንላ ነበርና ወጥተው ወጥተው ወደቁ። ባይሆንም አውጥቼ ልቅበር አለችው የሰው ደም ማሸጋ /ጡብ ግንብ/ ያፀናል አንጂ ምን ይጎዳል ምን ይል ብለሽ ነው? አርገጭ ብሎ ጨምሮ /አብሮ/ አስረግጧታል። ያን ጊዜ ደሟን ከእንባዋ ጋራ ቀላቅላ ኢሀሎኑ በዝ ሰማይ አምላክ አስራኤል አዶናይ ብላ ወደሰማይ ብትረጨው ቅድመ እግዚአብሔር ደርሷል /ደርሶላታል/ አብርሃምም በነፍስ ተካሏል። ከጭቃ ተሰውሰው ከናስ ተንሰው ከቀሩማ አበዝጎ ዘርዐከ ያልከው ወዴት ነው ብሏል። ከዚህ በኋላ ሙሴ ሚስቱን ልጆቹን ይዞ ተነሳ ስለምን ቢሉ ተጠራጥሮ። <u>ኧንድም</u> እስከዚያ የሚመግባቸው የለም ብሎ መልእኩ ለይፋን መዞ ለሚሰቱ ታያት ደመ ግዝሮሁ /ግዝረቱ/ ሰወልድየ ይኩን ቤዛ ምትየ ብላ ያልተገረዘውን ጌርሳምን ገዘረችው። ከዚህ በኋላ ያሉትን ይዘህ ትሄዳለህ አለው አስከዘያው የሚመግባቸው የለም ብዬ ነው አንጂ አለው። ከአጠገቡ ባሕር አለ እጅህን ከባሕሩ አግባው አለው አገባው ያገኘኸውን ይዘህ ውጣ አለው ድንጋይ ይዞ ወጣ ከድንጊያው ምታው አለው ቢመታው ውስጠ ግብ /ውስጠ ክፍት/ ሆኖ መንታ ሠርዶ በቅላ ትል አንዲቱን ወገን ሲመገብ አንዲቱ ወገን ስትለመልምለት ደግሞ አንዲቱን ወገን ሲመገብ አንዲቱ ስትለመልምለት አሣይቶ ይህን የመገበ የአንተን ልጆች አይመግብም? ብሎት ትቷቸው ሄዷል። አሮን ከራምሴ ከደብረ ሲና ሙሴ ተራከቡ። በደብረ እግዚአብሔር /ሥላሴ/ ይላል። አዕሩገ አሰራኤልን ለብስብልኝ አለው። ተሰበሰቡ ላወጣችሁ መጥቻለሁ አሳቸው። ምን ምልክት ይዘህል አሉት በትሩን ጥሎ ብትሩን አባብ አድርጎ አሳያቸው አውነት ነው ታወጣናለህ? አሉት አሮንና ሙሴ ከፈርያን ቤት ገብተው ፈንዖሙአ ለሕዝበየ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል አለህ አሉት። ማን አላችሁ አላቸው አኽያ ሸራኽያ ኤልሻዳይ አሉት። ምን ምልክት ይዛችኋል አላቸው። በትሩን ጥሎ አባብ አድርጎ አባቡን በትር አድርጎ አሳየው። ይህንስ የኔም ጠበብቶች ያደርጋሉ አለ። ኢያኔስ ኢያንበሪስ የሚባሉ ጠቢባን ነበሩት። ተጠርተው መጡ አናንተ ሙሴና አሮን ያደረጉትን

www.zeyeneta.com

ማድረግ አይቻላችሁም? አላቸው። በትሩን በምትሐት እባብ አደረጉት አባቡን ግን በትር ማድረግ አልተቻላቸውም። የሙሴ በትር የእነሱን በትር ውጣ ወደ ባሰቤቶች ገሠገሠች በትራችን አንሷት አኛን ልትደርበን ነው አያሱ ወጮዩ በስላቅ ይላል እየተዘባበቱ ሄደዋል። ይህ ፈርዖን ምንም እባቡን በትር ማድረግ ቢሳናቸው በትሩን እባብ በማድረጋቸው ልቡ ፀና። ከዚህ ሁሉ እንጂ እንውጣን ያስቡበት አገዛዝ ብታቀሱላቸው አይደሰም? በሉ እያነደፋችሁ ግሏቸው አለ። መከራ አጸኑባቸው ሙሴ አሮን ወደ አደባባይ ሲያልፉ አይተው አዬ ሙሴ አሮን ላታወጡን እናወጣለን ብላችሁ እንደ ሸቱ ተወደን እንናርበት በነበረ አገር መከራ ታጸኑብን አያሱ ይላቀሱ ጀመር። ሙሴ ወደ ጌታ አመለከተ። ሰዎንት ትጸርሕ ኀቤየ ኵሉ ጊዜ አንሰ አከብድ ልበ ሰፈርዖን ብሎ ዝብጣ ሰባሕር አለው። ውሃውን በብትሩ ቢነካው ተለውጦ ደም ሆኗል። ዘጠኝ መቅሰፍት አሥረኛ ሞተ በኵር አውርዶ ይፈጽማቸው ጀመር። እምበኵረ ፈርዖን ንጉሥ ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ ዓመት ዒውውት ዘትነብር ዲበ ማሕረፅ ያላል። ፈርዖን በኵር ነው /ነበርና/። የግብጽ ሰዎች አንተ በኵር ሚስትህ ልጅህ በኵር አናንተ ካሰቃችሁ መንግሥቱ ሰማን ይሆናል አትስዷቸውምን ብለዋቸዋል። ሙሴ አሮንን ሌሊት አስጠርቶ ያዛችሁልኝ ውጡ አላቸው። ያን ጊዜ ጌታ ሙሴን ሰይትወሀስ ኅር እምሳሩ ወዓመት እምአግዝአታ ወገብር እምእገዚኡ ብለህ አዋጅ ንገር አለው። ፫ ቀን በዓል አድርገን እንመጣለን መሳሪያችሁን አውሱን አሏቸው ገንዘብ ያስወድዳቸው የነበረ ሰያጣንን አሰረው ሌቲቱ ድሪዋን ቀለበቷን ወንዱ ቢትዋውን ጨፋውን /ጋሻውን የራስ ባርኔጣ ጌጡን/ ሳይቀር አውሰዋቸዋል። ይኸውም እዳ እንዳልሆነባቸው ህየንተ ዘተቀንዩ ተቀንዮ ወህየንተ ዘገብሩ ግንፋሰ። ፱፻፲፮ ዘመን ያስ ደመወዝ ስለተገዙ ስለ ደመወዝ ሆኗቸዋል። በ፫ኛው ቀን ሰይጣንን ፈታው አስራኤል እንጂ ሲመለሱ አልሄዱም ወይ ከገንዘባችን ወይ ከባሮቻችን አልሆን አለ። ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብሎ ተከተላቸው። ሦስት ቀን የተጓዙትን በአንድ ቀን ገስግሶ

ደረሰባቸው። እነዚያ ልጅ ከብት ጓዝ ይዘው ነው። እሱ ግን ደረቅ ጦር /አርበኛ ብቻ/ ሆኖ ነው ዞረው /ዘመር/ ብሰው ቢያዩ ደርሶባቸው አዬ ሙሴ አሮን ላተወጡን እናወጣለን ብላችሁ ከዚህ ከምድረ በዳ አንደሻሽ አንጥፋችሁ እንደቅጠል አርግፋችሁ ታስቀሩን ብሰው ይላቀሱ ጀመር። ሙሴ ወደ ጌታ አመለከተ። በሱሙ ሰእስራኤል ይንድኡ እንስኳቲሆሙ ንዱ በላቸው አሰው። ከዚህ ቀደም በዓይነ ሥጋ እንደተያያችሁ ከእንግዲህ ወዲህ በዓይነ ሥጋ አትተያዩም ብሎ በፊታቸው የሚሄድ ደመና ነበር አዙሮ ጋርዷቸዋል። ግብፃውያንና እስራኤላውያን ሳይተያዩ ከአንድ ዛፍ ፊረስ በቅሏቸውን አስረው አድረዋል። ከዚህ ዘኋላ ኤርትራ ደረሱ ዝብጣ ሰባሕር አሰው። ከሦስት ተከፍላለች ያሉ እንደሆነ አራት አራት እየሆኑ ከአራት ተከፍላለች ያሉ እንደሆነ ሦስት ሦስት እየሆኑ ተሻግረዋል። በቀኝ እንደግድግዳ በግራ እንደግድግዳ በላይ እንደጠፈር እንደመስከት ታቹ የሰፋ መስክ ሆኖላቸው ፈረስ በቅሏቸውን እያበሉ ተሻግረዋል። ፈርዖን ቢደርስ ተከፍላ የአገሬ ውሃ አነሱን የሰደደች እኔን የምትከሰክሰኝ ናት? ብሎ ፈረው እንዳያቀር ሰኮ ሰለኮ አያይዞ ገባ። እስራኤል ጨርሰው ሲወጡ ግብፃውያን ጨርሰው ሲገቡ ዝብጣ ሰባሕር አሰው። ከወደፊታቸው ነፋስ ያገናኘው ጀመር። እናንተ እስራኤል እንጂ ፈጣሪያቸው ይረዳቸዋል እንመሰስ አሱ። ከወደኋላቸው /ከኋላ/ ተገዮሞባቸዋል። ያን ጊዜ ሙሴ አሮን የወንዶች አቀንቃኝ፡ ማርያም እኅተ ሙሴ የሴቶች አቀንቃኝ፡ ሆነው ወባረኩ ዘ ቡራኬ በኅብረተ ቃል ይላል። ቃሰ ሸካራ ቃሰ ኦህና ሳይኖር በርትዓት ቃል ዲዳዎች ረትቶላቸው በፍትሐተ ቃል ሕፃናት ፈትቶላቸው አመስግነዋል። ሰዝክረ ነገር ምድራቱ ኅር ሳታበቅል ትኖራሰች ይህም ምሳሌ ነው። ኤርትራ የገዛነም፡ ሙሴ የጌታ፤ ፈርዖን የዲያብሎስ፡ በትር የመስቀል፡ እስራኤል የነፍሳት፡ እስራኤል ወዲያው ወጥተው ምድረ ርስት አልገቡም ፵ ዘመን በምድረ በዳ ኖረዋል። ነፍሳትም ከሲኦል ወጥተው መንግሥተ ሰማያት አልገቡም በገነት የመኖራቸው ምሳሌ። አንድም ግብፅ የኃጢአት፡ ኤርትራ የጥምቀት፡ ደመና የመንፈስ ቅዱስ፡ ሙሴ የቀሳውስት፡ እስራኤል የምእመናን፡ እስራኤል ፊት ደብተራ አሪትን ኋላ

www.zeyeneta.com

ቤተመቅደስን ሠርተው እንደኖሩ ምእመናንም በዚህ ዓለም ቤተ እግዚአብሔር /ቤተክርስቲያን/ ሠርተው የመኖራቸው። ፵ ዘመን መና ከደመና እያወረደላቸው ውሃ ከድንጊያ እያፈለቀላቸው እንደተመገቡ ምእመናንም ሥጋውን ደሙን ተቀብለው የመኖራቸው ምሳሌ። <u>ሚገሺ</u> መጻልዋ ነቢያት ይላቸዋል። መላው እስራኤልን ወላድያነ ነቢያት ናቸውና መጻእያትን ይናገራሉና። አንድም ደጎች ሲል ወይጼሊ ለከ አስመ ከመ ነቢይ ውእቱ እንዲል።

<u>ወጸሎቱ ለሙሴ</u> ሙሴ የተናገረው ይህ ነው። አንድም መጻልዋ ነቢያት የሚላቸው ከሐና እስከ ስምዖን። ወጸሎቱ ለሙሴ ንሴብሖ ብሎ እስመ እላት እስኪል ድረስ ነው። ይህን ፫ቱ፪ ንሴብሖን ከአሪት ዘጸአት፡ አጽምዕ ሰማይን እስመ እላትን ከአሪት ዘዳግም፡ ሐናን ከመጽሐፈ ነገሥት /ላሙኤል/ ሕዝቅያስን በሴሲትን ከመጽሐፈ ኢሳይያስ፡ ምናሴን ከሕጹጸን፡ /ዜና መዋዕል/ ዮናስን ዕንባቆምን ከደቂቀ ነቢያት፡ ስብሐት ዘእምአዛርያን ፫ቱ ደቂቅን ጎበ ባረኩን ከመጽሐፈ ዳንኤል፡ ጸሎተ ማርያምን ዘካርያስን ስምዖንን ከሉቃስ ወንጌል፡ አምጥተው ጠርዘውልናል /ለጥተውናል/። ይህ አርእስት ነው። ፫ቱ፪ ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲለጡ ለዚህም አርእስት ለጥተዋል። እሱ ግን ነገሩን ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ብሎ ያመጣዋል።

<u>ጸሎተ ሙሴ ነቢይ ፩</u>

፩. ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተስብሐ። ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ምስጉን የተመሰገነ አለ። ሰው በሐሰት ሆኖ ይመሰገናል። ንፉገ ሊጋስ፡ ደካማው ኃያል፡ ደሀው ባለጸጋ ተብሎ። እሱ ግን በሊጋስነቱ ንፍገት በኃያልነቱ ደካማነት በባለጸግነቱ ድህነት የለበትም። ስቡሐ፡ ቅድመ ዓለም የተመሰገነ። ወዘተስብሐ። ዛሬም በኤርትራ ግብጻውያንን አጥፍቶ እስራኤልን አድኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

ፈረስ ወመስተፅዕነ ወረወ ውስተ ባሕር። ፈረሱን በፈረስ የተቀመጠውን በባሕር አሰጠመ። አንድም ሠራዊተ አጋንንትን ሊቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አሰጠመ።

፪. ረዳኤ ወመሠውረ ኮነኒ ለአድኅኖተየ። እኔን ለመርዳት /ለማዳን/። ረዳኤ። በደመ በግዕ። ወመሠውረ፡ በደመና። አንድም ረዳኤ። በደሙ። መወሠውረ በመንፈስቅዱስ። ረዳት ሆነኝ።

ውእቱ አምላኪየ ወአምላከ አቡየ እሴብሖ ወአሌዕሎ። ፈጣሪዬ ያባቶቼ ፈጣሪ ነው። አገነዋሰሁ አከብረዋሰሁ። አሁን ፍጡር ፈጣሪውን የሚያገን የሚያከብር ሆኖ አይደለም። ልዕልናውን እናገራለሁ ሲል ነው።

ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ ብሎ እንዲያመጣው።

፫. እግዚአብሔር ይቀጠቅጥ ፀብአ ወእግዚአብሔር ስሙ። ፀባኤ ይላል። አርበኛ ፈርያንን ያጠፈዋል ስሙ እግዚአብሔር ሲባል ይኖራል። <u>አንድም</u> ዲያብሎስን በመስቀል ድል ይነሣዋል። ስሙ አምላክ ወሰብአ ሲባል ይኖራል።

፬. ሠረገላቲሁ ለፈርያን ወሠራዊቶ ወረወ ውስተ ባሕር። የፈርያንን ሠረገላውን ሠራዊቱን በባሕር አሰጠመ። <u>አንድም</u> ሠራዊተ አጋንንትን ሊቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አሠጠመ። ጎሩያን። ለሹመት ለምክር የተመረጡትን። ወመስተፅዕናነ በመሥልስት። ሦስት ወገን ሆነው የተሰለፉትን። ባንድ ሠረገላ ቀስተኛ ጋሻኛ ነፍጠኛ ይቀመጣሉና። አንድም በመካከል ሠረገላ ቀኝና ግራ ፈረስ

www.zeyeneta.com

ይሄዳልና። አንድም ከሦስት በተከፈለች በኤርትራ አሠጠመ። አንድም ሦስት ወገን ሆነው ስመሰለፍ የተመረጡትን ድር እግር ሠረገላ አሠጠመ። /ድር ትንሽ ኀዝና ትንሽ ሰው የሚይዝ እግር በእግር ብቻ የሚሄድ/ እንድም ጎሩያነ። በኢየሩሳሌም ስማያዊት ሲኖሩ የተመረጡትን እጋንንት። ወመስተዕዕናነ በሦስት ወገን የሰፈሩ አጋንንትን በዓየር በዚህ ዓለም በመሠረተ ምድር። ቦ ዘወድቀ ውስተ አየር ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ወቦ ዘወድቀ ውስተ አንጦርጦስ /አንጦርጦስ/ ዘውአቱ መትሕተ ታሕቲት እንዲል። አንድም በነፍስ በሥጋ በልቡና ያደሩትን። አንድም በደቂቀ ሴም በደቂቀ ያፌት በደቂቀ ካም ያደሩትን አሠጠመ።

ወተሰጥሙ ውስተ ባሕረ ኤርትራ። በባሕረ ኤርትራ ተሰጠሙ /ሠጠሙ/ አንድም በባሕረ ገሃነም ተሰጠሙ /ሠጠሙ/።

፭. ወደፈኖሙ ማዕበል። ማዕበለ ኤርትራ ቀበራቸው። አንድም ማዕበለ ገሃነም ቀበራቸው።

ወተሰጥሙ ውስተ ቀላይ ከመ አብን። ደንጊያ ሲጥሉት እንዲሰጥም ስጠሙ።

፮. የማንከ እግዚኦ ተሰብሐ በኃይል። አቤቱ የማንህ ሙሴ ኃይል አድርጎ ተመስገነ። አንድም አቤቱ ሥልጣንህ ኃይል አድርጎ ተመስገነ። አንድም አቤቱ አብ! ልጅህ ኃይል አድርጎ ተመስገነ። አንድም አቤቱ ወልድ! ሥልጣንህ ኃይል አድርጎ ተመስገነ።

የማን እደከ እግዚኦ ሠረወቶሙ ሰፀር። ሰፀር ሠረወቶሙ ስማሰት ደገመው።

፯. ወበብዝኀ ስብሐቲከ ቀጥቀጥከሙ ለጸላእትከ። በብዙ ታምራትህ ጠላቶችህ ግብጻውያንን ጠላቶችህ አጋንንትን አጠፋሀቸው።

ፈኖከ መዓተከ ወበልዖሙ ከመ ብርዕ። መዓትህን ላክህ እሳት ብርን እንዲበላ በላቸው።

፰. ወበመንፈሰ መዓትከ ቆመ ማይ። መዓትህን በምትፈጽምበት በነፋስ ውሃው ተከፍሎ ጸና። አንድም በረቂቅ ሥልጣንህ

ውሃው ተከፍሎ ጸና። አንድም በቅዱስ ሚካኤል ውሃው ተከፍሎ ጸና። አንድም በረቂቅ ሥልጣንህ ገሃነም ተከፍሎ ጸና።

ወጠገዐ ከመ ዓረፍት ማይ። ውሃው ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸና። አንድም ገሃነም ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸና።

ወረገዐ ማዕበል በማእከለ ባሕር። በባሕሩ መካከል ማዕበሉ ረጋ። አንድም በባሕረ ገሃነም መካከል ማዕበለ ገሃነም ረጋ።

፱. ወይቤ ጸላዒ ዴግንየ እስኀሙ። ጠላት ፈርዖን ተከትዬ አይዛቸዋለሁ ብሎ ነበር።

እትካፈል ምሕርካ ወእጸግባ ለነፍስየ። ምርኮውን እካፈላለሁ ስውነቴን እጠግባታለሁ ብሎ ነበር።

እቀትል በመጥባሕትየ ወእኪንን በእዴየ። ወንድ ወንዱን እገድላለሁ ሴት ሴቱን እገዛለሁ ብሎ ነበር። አንድም እንቢ ያለኝን እገድላለሁ እሺ ያለኝን እገዛለሁ ብሎ ነበር። ምንም ቢሆን ነገር ያነቁ ናቸውና ሙሴ አሮንን እገድላለሁ ሠራዊቱን እገዛለሁ ብሎ ነበር።

አንድም ወይቤ ጸላዒ ዴግንየ አእኀሙ ጠላት ዲያብሎስ ግብራቸውን ተከትዬ ዕቄራኛቸዋለሁ ብሎ ነበር።

እትካፈል ምሕርካ ወእጸግባ ለነፍስየ። ምህርካ ነፍስን እካፈላለሁ ሰባሕርዬ አጠግባታለሁ ብሎ ነበር።

እቀትል በመጥባሕትየ ወእኪንን በእዴየ። በሥልጣኔ ነፍስን ከሥጋ እለያለሁ ተቆራኝቼ እኖራለሁ ብሎ ነበር።

፲. ፈኖከ መንፈሰከ ወደፈኖሙ ባሕር። ነፋስን ላክህ ባሕረ ኤርትራ ቀበራቸው። ፊትም የከፈለው ኋላም ያገናኘው ነፋስ ነው። አንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ገለጽከ ኤርትራ ቀበራቸው። አንድም ቅዱስ ሚካኤልን ላክህ ባሕረ ኤርትራ ቀበራቸው። አንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ላክህ ኤርትራ ቀበራቸው።

ወተሰጥሙ ከመ ዐረር ውስተማይ ብዙኀ። እርሳስ ዕሙቅ ስፋሕ በሆነ ውሃ ውስጥ ቢጥሉት እንዲሠጥም ሠጠሙ።

www.zeyeneta.com

፲፮. መኑ ይመስሰከ እምነ አማልክት እግዚኦ። አቤቱ በሰም አማልክት ከሚባሉ ከጣዖታት አንተን የሚመስልህ ማነው።
ወመኑ ከማከ ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን። በቅዱሳን በነቢያት በካህናት ዘንድ እንዳንተ ክቡር ምስጉን ማነው።
መንክር በብሕቲከ ዘትገብር መድምመ። ድንቅ ሥራ የምትሠራ አቤቱ ታምራትህ ድንቅ ነው። አንድም ታምራትህ ድንቅ ነው።
ወትገብር መድምመ። ከእንግዲህ ወዲህም ድንቅ ሥራ ትሠራለህ።

፲፯. ሰፋሕከ የማነከ ወውኀጠቶሙ ምድር። መሌን ላክህ ኤርትራ ቀበረቻቸው። ምድር ይላታል በኋላ ግብሯ። አንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ገለጽክ ኤርትራ ቀበረቻቸው አንድም ልጅህን ላክህ ገሃነም ቀበራቸው።

፲፰. ወመራሕከመ ለሕዝብከ ለአለ ቤዘውከ። በደመ በግዕ የተቤዠሐቸውን በደመና መርተህ አወጣሀቸው። አንድም በደምህ የተቤዠሐቸውን በመንፈስቅዱስ መርተህ አወጣሀቸው።
ወአስተፍኅሓከ በኃይልከ ተረፈ መቅደስከ። የአብርሃምን ልጆች ደስ አሰኘሀቸው። አንድም በዚህ ዓለም ቤተአግዚአብሔር ሠርተው የሚኖሩ ምእመናንን ደስ አሰኘ ሀቸው።

፲፱. ስምዑ አሕዛብ ወተምዑ። አሕዛብ ይህን ስምተው ተበሳጩ። አንድም አጋንንት ይህን ስምተው ተበሳጩ።
ወአኀዙሙ ማሕምም ለአለ ይነብሩ ፍልስጥኤም። በፍልስጥኤም የሚኖሩ ሰዎችን ምጥ ያዛቸው። አንድም አጋንንቶን ምጥ ያዛቸው።

፳፩. ወውኦተ አሚረ መምዑ መላፍንተ ኤዶም። በዚያ ወራት የኤዶም መሳፍንት ተሸበሩ። በኤዶም የነበሩ አጋንንት ተሸበሩ።

፳፪. ወአኀዙሙ ረዓድ ለመላእክተ ሞአብ። የአሞብ አለቆችን ረዓድ እንቅጥቅጥ ያዛቸው። አንድም በሞዓብ ያሉ አጋንንትን ረዓድ እንቅጥቅጥ ያዛቸው።
ወተመስዉ ኩሎሙ አለ ይነብሩ ከነዓን። በከነዓን የሚኖሩ ሰዎች እንደ ሰም ቀለጡ። አንድም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሊኖሩ ተፈጥረው የነበሩ አጋንንት እንደ ሰም ቀለጡ።
ወአኀዙሙ ፍርሐት ወረዓድ። ፍርሐት ረዓድ ያዛቸው።
ኀይለ መዝራዕትከ ፀንዐ እምኩኩሕ። በሥልጣንህ ኃይል የተፈጠረው ውሃ ተከፍሎ ከደንጊያ ይልቅ ጸና። አንድም በኃይለ መዝራዕትከ። በሥልጣንህ ኃይል ውሃው ተከፍሎ ከድንጊያ ይልቅ ጸና።
አንድም ኃይለ መዝራአትከ ጸንዐ በኩኩሕ። የሥልጣንህ ኃይል በፈርዖን ላይ ጸናበት። ኩኩሕ አስው ፈርዖንን ስለ ጸናቱ አንድም ኃይለ መዝራዕትከ የልጅህ ኃይል ገሃነምን

www.zeyeneta.com

በመክፈል ከደንቢያ ይልቅ ጸና። ኃጢአት ኃይሉ መዝራዕትከ ጸንዐ በዙሪሕ። የልጅህ ኃይል በዲያብሎስ ጸናበት።
እስከ የጎልፉ ሕዝብከ አግዚኦ። አቤቱ ወገኖችህ እስኪያልፉ ድረስ። እስከ የጎልፉ ሕዝብከ ዝንቱ ዘቤዘውከ። በደመ በግዕ። በደምህ የተቤዠሃቸው ወገኖችህ ምእመናን እስኪያልፉ ድረስ።

፲፯. ወሰድኮሙ ወተከልከሙ ውስተደብረመቅደስከ። ወስደህ በምሪጋናህ ማደሪያ በኢየሩሳሌም በገነት/በመንግሥተ ሰማያት አኖርህቸው።
ውስተ ድልው ማኅደርከ እግዚኦ ዘገበርከ። በተዘጋጀች በፈጠርሃት።
ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአስተዳለዋ አደዊከ። ክቡር እግዚአብሔር አጾችህ ባዘጋጀኸት ሥልጣንህ በፈጠራት ሥልጣኑማ ያልፈጠረውን አሰ? ብሎ በአዝርዕት በአትክልት ባዘጋጀሃት በዚህ ዓለም። አንድም ለአብርሃም ከዚህ እስከዚህ አወርስሐሰሁ ብሰህ ባዘጋጀሃት /ባዘጋጀህለት/ በስነዓን። አንድም ልጅህ ሕይወትህ መንፈስቅዱስ በጣዕም በመዓዛ በብርሃን ባዘጋጃት በገነት በመንግሥተ ሰማያት አኖርሃቸው።

፲፰. ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም እንዲህ አድርጎ አጥፊ ለጥፋት የሚሰው የለም። ለዘላለሙ ነግሦ /ጸንቶ/ ይኖራል። ወዓዲ ቢል ዘልፊ ያላል። ዘወትር ማለት ነው።

፲፱. እስመ ቦአ ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ምስለ አፍራሲሁ ወመስተፅዕናን ውስተ ባሕር። የፈርዖን ሠረገላው ከፈረሱ ጋር በፈረስ ከተቀመጡት ጋር ወደ ባሕር ገብተዋልና።
ወአስተጋብአ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ማየ ባሕር። ዋዌውን ጥሶ ውሃውን አጠራቀመባቸው።አንድም አጠራቅሞባቸዋልና። ይነግሥ።
ወደቂቀ እስራኤልሰ ኀለፉ እንተ የብስ ማዕከለ ባሕር። አስራኤል ግን በባሕር መካከል በደረቅ አለፉ።
ማይሰ ሎሙ ዐረፍት በይምን ወዐረፍት በጽጋም። ማይኒ። ውሃውም በቀኝ እንደግድግዳ ሆኖ ጸናላቸው። አንድም

ማይሰ። ውሃውስ ትለኝ እንደሆነ ውሃውስ በቀኝ እንደ ግድግዳ በግራ እንደ ግድግዳ ሆኖ ጸናላቸው።
ሰፋሕከ የማነከ ካለውና እግዚኦ ተስብሐ ባለው ሐዲስ ተርጉም የቀረውን ሳይተረጉሙ የመጡ አንደሆነ ይመስሏል። ሙሴ የጌታ፡ ፈርዖን የዲያብሎስ፡ እስራኤል የነፍሳት። ኤርትራ የገሃነም ምሳሌ።

www.zeyeneta.com

ጸሎተ ሙሴ ዘዳግም

ዳግም ሕግ የተራ /ሰተራ/ ያሉ እንደሆነ ሰኦሪት ዘጉልቊ ለ፭ተኛው ብሔር ለ፮ተኛው ዳግም አሰ። በም፡ሠጢር /ሰምበጢር/ ያሉ እንደሆነ ለኦሪት ዘጸአት ሰ፪ተኛው ብሔር ፯ተኛውን ዳግም አሰ። እንድም ሰንሴብሉ ዳግም አለ ሙሴ ፪ተኛ የተናገረው ይህ ነው።

፩. አፅምዕ ሰማይ ወእንግርከ። ሰማይ አድምጥ ልንገርህ።
ውትሰማዕ ምድር ቃለ እፉየ። ምድር ከአንደበቴ የወጣ ቃልን ትስማ። የሰማይ የምድር መስማት እንደምን ነው ቢሉ ጌታ ለውን በተጣላበት ወራት ሰማይን ዝናም ሰዘር ጠል ሰመከር አትስጥ ይሰዋል። ምድርንም የዘሩብሽን አታብቅዪ የተከሉብሽን አታጽድቂ ይላታል። ይህን ማድረግ መስማት ነውና። እንድም ልዑላን መላእክት ትሑታን ደቂቀ አዳምን አታማልዱ ይላል።

፪. ወትስፈም ከመ ዝናም ለነገርየ። ምድር ዝናምን እንድትቀበል ነገሬን ትቀበለው።
ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ። ነቢብን ነቢቦትየ ይላል። ጠል ከመስክ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ ከሰው ልቡና ይስማማ።
ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት። ልዝብ ዝናም ከእርሻ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ ከሰው ልቡና ይስማማ።
ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር። ጠል ከመስክ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ በለው ልቡና ይስማማ። ወፈውለ ኵሉ ፍጡር ጊሜ እንዲል።

፫. እስመ ስመ እግዚአብሔር ጸዋዕኩ። የእግዚአብሔን ስም ጠርቼ ነግሬያቸዋለሁና። እንድም አጽምዕ ሰማይ። ገብርኤል አድምጥ ልንገርህ። ወትሰማዕ። ማርያም በአንተ እድሬ የምነግራትን ቃል ትስማ።
ወትሰፈም ከመ ዝናም ሰነገርየ። ምድር ዝናምን እንድትቀበል ማርያም ነገሬን ትቀበለው።
ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ። ጠል ከሰማይ እንዲወርድ እካላዊ ቃል ሳይሰማ ሰው ይሁን። ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት።

የቢዘን ዝናም ሳይሰማ እንዲወርድ አካላዊ ቃል ሳይሰማ ሰው ይሁን።
ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር። ጠል ሳይሰማ እንዲወርድ አካላዊ ቃል ሳይሰማ ሰው ይሁን። ሰው የሆነበትን ጊዜ ያወቀው የለምና። መልአክኒ ኢያእመረ ዕለተ ትስብእቱ ለቃል ወአልቦ ዘአእመረ እምአለ ሀለዉ ውስተ አርያም ዕሰተ ምጽአቱ ለቃል ወሥርዓተ ዘንብሮ አግዚእ እንዲል።
አንድም ወከመ ዝናም ውስተገራህት። ዝናም ምላሴው እንደመሆኑ ገራህት ምላሴዋ በሆነች /በምትሆን/ በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። ዝናም ምላሴው እንደመሆኑ ገራህት ምበሌዋ በሆነች /በምትሆን/ በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። አንቲ ውስቱ ገራህቱ ሰአብርሃም እንዲል።
ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር። ጠል ምላሴው እንደመሆኑ ፀምር ምላሴዋ በሆነች በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። ፀምር ዘጌዴዎን እንዲል። ፀምር ዘጌዴዎን ያሰኘው እንደምን ነው ቢሉ
ታሪክ የምድያም ሰዎች ፯ኤልን ፯ዓመት እገዛዝ አጽንተው ገዟቸው በዘር በመከር ጊዜ እየመጡ ይወጓቸው ነበር። ከዕለታት ባንድ ቀን ይህ ጌዴዎን ስንዴ ደርሶለት እየሰበረ ሲያሻሽ መልአኩ መጥቶ አ ፅኑዓ ኃይል እግዚአብሔር ምስሌከ። ፅኑዓ ኃይል ጌዴዎን እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር አለ አለው። ባባቶቻችን ዘመን ነበረ እንጂ በኛስ የሰም በረድኤትማ ካሰ የምድያም ሰዎች እንዲህ አድርገው አገዛዝ ሲያፀኑብን መቼ ይተወን ነበር አሰው። አይዞህ ባንተ አድሬ አጠፋቸዋለሁ ብሎሃል አለው። ምን ምልክት ታሳየኛለህ አሰው በግ ሠውተህ ሥጋውን ባገልግል /በቅርጫት/ ደሙን በመንቀል እድርገህ እምጣ አሰው አመጣ። ካጠገቡ ንጽፍ ደንጊያ አለ ሥጋውን ከዚያ ላይ አኑረው ደሙን በላይ አፍስስበት አለው። እንዳለው አደረገ። መልአኩ ዘንግ ይዞ ነበር። ያን ደንጊያ በዘንግ ቢመታው ከደንጊያው እሳት ወጥቶ ሲበላው አይታል /ያያል/ ይህ ምሳሌ ነው። እሳት የሥልጣነ እግዚአብሔር: ዘንግ የኵናተ ጌዴዎን። ሥጋ የአሕዛብ

www.zeyeneta.com

ምሳሌ: ሄዶ ቤተጣያቱን አቃጠለው ተሰብስበው መጥተው ዮአስ አሉት የጌዴዎንን አባት ልጅህ አምላካችንን ተበቅሎብናልና እምጣው አንበቀለዋለን ለጣያቱ እንሠዋዋለን አሉት። ለአምላካችሁ እናንተ ትበቀሉለታላችሁ? አሉ ተበቅሎ ያጥፋው እንጂ ብሎ ዘበተባቸው። ከዚህ በኋላ ፮ ዓመት እንደገሟቸው ለማጠየቅ ሰባት ዓመት የሆነው ወይፈን ነበረው ያን ሠዋ። ፀምር ልዘርጋ በፀምሩ ላይ ጠል ይውረድ /ይውረድበት/ በዳሩ በዳሩ ላይ አይውረድ /አይውረድበት/ አለ እንዳለው ተደረገ። ቢጠምቀው ወመልዐ አይነካ ይላል። መንቀል/ትንሽ የውሃ እንስራ /ማድጋ/ ሙሉ ሆኗል /ሆነ/። ጠጥቶታል። ኃይል ቅሉ የሆነው ይህ ነው። ተፈታተነኝ አትበል። ሁለተኛ ልዘርጋ በዳር በዳሩ ይውረድ በፀምሩ ላይ አይውረድ አለ እንዳለው ተደርጓል። ይህ ምሳሌ ነው ፀምር የእስራኤል: ጠል የረድኤተ እግዚአብሔር: በፀምሩ ላይ መውረዱ በዳር በዳር አለመውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር ለእስራኤል የመሰጠቱ ለእሕዛብ አለመሰጠቱ።

በ፪ተኛ አግርኖ

ጠል የመዓተ እግዚአብሔር: በዳር በዳር መውረዱ በፀምሩ ላይ አለመውረዱ መዓተ እግዚአብሔር በእሕዛብ የመታዘዙ: በእስራኤል አለመታዘዙ: ኧንድም ፀምር የእመቤታችን: ጠል የጌታ: በፀምሩ ላይ መውረዱ ጌታ ከእመቤታችን ሰው የመሆኑ ሥጋ የመልበሱ: በዳር በዳር አለመውረዱ ጌታ ከሌሎች ሴቶች ሰው ያለመሆኑ ሥጋ ያለመልበሱ።

በ፫ኛ አግርኖ

ጠል የዘርዐ ብእሲ: በዳር በዳር መውረዱ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ የመውለዳቸው: በፀምሩ ላይ አለመውረዱ እመቤታችንን ዘርዐ ብእሲ ሩካቤ ብእሲ አላገኛትም።

አሰመ ሰመ እግዚአብሔር ጸዋዕኩ። የእግዚአብሔርን ስም ጠርቼ እነግራቸዋለሁና /ነግሬያቸዋለሁና/።

ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ። ለፈጣሪያችን ዕበይ ስጡ እሰ ዐቢይ አያላችሁ እመስግኑ።

፪. እግዚአብሔር ጻድቅ በምግባሩ። እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ እውነተኛ ነው።
ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊሁ። ሥራው ሁሉ የቀና ነው።
እግዚአብሔር ጻድቅ ወአልቦ ዓመፃ። እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ሐሰት የለበትም ቸር ነው ግፍ የለበትም።
ጻድቅ ወጌር እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ቸር ነው እውነተኛ ነው። ሰው ቸር ቢሆን እውነተኛ እውነተኛ ቢሆን ቸር አይሆንም።

፫. አበሱ ወአከ ሎቱ <u>ትውልድ ርኩሳን</u>። ርኩሳን ትውልድ /ትውልደ ርኩሳን/ ይላል። በደሉ የሱ ወገኖች አይደሉም እሱን የጎዱ አይደለም ሰሱ ምላሹ አይደለም። መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ ሰጣገበ ሰሱ። ትውልድ ዕሱት ወግፍትዕት። አሉተኛ ግፍትዕት ወረተኛ ትውልድ አንድ ጊዜ ወደሕገ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ወደሕገ ጣዖት የምትል።
ከመዝኑ ተዐሥይም ለእግዚአብሔር። ለእግዚአብሔር እንዲህ ያለ ወረታ ትመልሱለታላችሁ? መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ ለመገበ።

፭. ዝ ሕዝብ ዓብድ ወአከ ጠቢብ። ዘአልቦ ጥበብ /ወአልቦ ጥቡብ/። ይህ ወገን ጥበብ የሌለው ሰነፍ ነው። <u>አንድም</u> ወአልቦ ጥበብ ይህ ወገን ሰነፍ ነው። ወአኮ ጠቢብ ብልህ አይባልም።
አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ። ፈጣሪህን ትክድ ለጣዖት ትሰግድ ዘንድግ የፈጠረህ እግዚአብሔር አይደለምን?
ፈጠረከኒ ወንብረከ። ፈጠረከኒ። በነፍስ ወንብረከ በሥጋ። <u>አንድም</u> ፈጠረከኒ በነፍስ በሥጋ። ወንብረከ ወገን ያደረገህ አይደለምን?

፯. ወተዘከር መዋዕለ ትካት። ይህንስ ማሰብ ትተህ የቀደመ ዘመንን አሰብ አለ። የኖኅን ዘመን አስብ።

www.zeyeneta.com

ወጎሊ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ። ለልጅ ልጅ የሚሆን የኖኅን ዘመን አስብ።
ተለአሎ ለእቡከ ወይነግረከ። አንተም ባታውቅ አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል።
ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ። ሽማግሌዎቹን ጠይቅ ይነግሩሃል።

፫. አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ። ደቂቀ ኖኅን በቦታ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል።
ወዘከመ ዘርያሙ ለደቂቀ አዳም። ደቂቀ አዳምን በቦታ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል።
ሠርያሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ። በየአውራጃቸው እንደሠራራቸው፡
ወበበጎልቆሙ ለመላእክቱ እግዚአብሔር። በመላእክተ ዑቃቤያቸው ቍጥር እንደሠራራቸው።

፬. ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር። ያን ጊዜ ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ወገንነት ያለው እድል ሆነ።
ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ። አስራኤልም በርስቱ በኢየሩሳሌም የሚኖር ሆነ። ከማየ ዓይኅ በኋላ ኖኅን ሽማግሌ መልአኩን ዳኛ አድርጎ አካፍሏቸዋል። ያን ጊዜ ቀኝ ቀኙ ለያፌት ግራ ግራው ለካም መካከሉ ለሴም ደርሷል። ኋላ እስ ደብረ ዘይት <u>እስ ቀራንዮ እስ ደብረ ታቦር</u> ጌታ ሥራውን የሚሠራባቸው አህጉር ላንተ እንዲደርሱህ ማድረጉ ቢወድህ አይደለም? እሱን ትተህ ለምን ጣዖት ታመልካለህ ለማለት።
<u>አንድም</u> ተዘከር መዋዕለ ትካት። የቀደመውን ዘመን አስብ አለ የናምሩድን። ወጎሊ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ። የልጅ ልጅ የሚሆን የናምሩድን ዘመን አስብ።

ተለአሎ ለእቡከ ወይነግረከ። አንተ ባታውቅ አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ። ሽማግሌዎችን ጠይቅ ይነግሩሃል።
አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ። ደቂቀ ናምሩድን በቋንቋ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል።
ወዘከመ ዘርያሙ ለደቂቀ አዳም። ደቂቀ አዳምን በቋንቋ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል።
ሠርያሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ። በየአውራጃቸው እንደሠራራቸው ወበበጎልቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር።

www.zeyeneta.com

በአለቆቻቸው ቊጥር እንደሠራራቸው ይነግሩሃል። ወኮነ ያዕቆብ ትርጓሜ እንዳለፈው አይሰወጥም።

ወአስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ። እስራኤልም በርስቱ በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚናገር ሆነ።

ታሪክ እነዚህ ደቂቀ ናምሩድ አንድ ሁነው ወደምሥራቅ ሲጓዙ ሠናዖር ከምትባል ሜዳ ደረሱ። ከዚያ ላይ ሆኖ የውሃ ሻሻቱ አየስደደ የሚያጠፋቸው ያባቶቻችንን ጠላት አናጥፋ ብለው ፣ ግንብ ይሰሩ ጀመር። ፲፫ ምዕራፍ አድርገው ጀምረዋል። ዐ.ይ ምዕራፍ ያሉ አንደሆነ ፮ ገመል ከነሳቢው /ከነመሳቢያው/ ሰኮ አተርትሮ የሚያቆም የሴትና የወንድ መልክ /አካሄድ/ የሚሰይበት፡ የፈረስ አፍታ የሚደክምበት፡ ነዑስ ምዕራፍ ያሉ አንደሆነ የወንጭፍ ደንጊያ የሚደርስበት፡ የፈተና ደንጊያ ተሸክሞ የሚያደርስበት፡ አርበኛ ፍላፃ ወርውሮ የሚያደርስበት ያህል አርቀው ጀምረዋል። አሠሪታ ፲፪ አለቆች ሹመዋል ጡቡ አቆልቋዩ ፲ ክንድ ወርዱ ፪ ክንድ ፭ሺ ከ፬፻፹ ክንድ ከፄ ስንዝር ሠርተው ወጡ። ከዚያ ላይ ሆነው ፍላጻቸውን ሸቅብ ይወረውራሉ በአየር ያሉ አጋንንት በምትሐት ደም እየቀቡ ያሰዱላቸዋል። እኔ ንጉሡን ወጋሁት እኔ ቢትወደዱን ወጋሁት እያሉ ሲዘብቱ /ይዘባበቱ/ ጀመር። ሥላሴ ንዑ ንረድ ወንክዐሙ ነገሮሙ ለከሰዳውያን በነገርነ ብለው፡ ባንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበረ ፍ፩ ቋንቋ ጨመሩባቸው። ጭቃ ሲሰው ደንጊያ ደንጊያ ሲሰው ጭቃ እያመጣ የማይስማሙ ሆነው ወርደዋል። ይህንንም እንዳያመልኩት በነፋስ በትኖታል። ያንጊዜ ፲፭ ሰሴም ፰፭ ለያፌት ፴፪ ለካም ደርሷል። ዕብራይስጥ ቋንቋ ለሴም ደርሷል። ፊትም ዓለምን የፈጠረበት ኋላም ዓለሙን የሚያስልፍበት እንዲደርስህ ማድረጉ ቢወድህ እይደለምን? እሱን ትተህ ሰምን ጣዖትን. ታመልካለህ ስማለት።

፲. ወአጽገቦሙ በምድረ ገዳም። በምድረ በዳ አጠገባቸው መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ።

በብሔረ ጽምዕ ወሐፍ በብሔረ በድው። ጽምዕ ሐፍ ባለበት ቦታ አጠገባቸው።

አንድም በብሔረ ሐሉል በብሔረ ፋሉል ይላል ጥፊ።

መገበሙ ወመርሐሙ። መገባቸው መርቶ አወጣቸው።

ወዐቀቦሙ ከመ ብንተ ዓይን። እንደ ዓይን ብሌን ጠበቃቸው የዓይን ብሌን በሽፋሽፍት እንድትጠበቅ እርሷም ሕዋሳቷን እንድትጠብቅ።

፲፩. ወከመ ንስር ዘያስተጋብእ አዕሲሁ በታሕተ ክነፊሁ። ንስር ልጆቹን በክንፉ ውስጥ እንዲሠውር ሠወራቸው።

ወከመ የሐቅፍ አዕሲሁ በገበዋቲሁ። በሹ እንዲያቅፍ አቀፋቸው። ወሐዘሎሙ በክነፊሁ። በክንፈ ሪድኤቱ አጸናቸው /አዘላቸው/

ወጸሮመ በእንግድዓሁ በረድኤቱ አጸናቸው።

፲፪. አግዚአብሔር ባሕቲቱ መርሐመ። እግዚአብሔር ብቻውን መርቶ አወጣቸው።

ወአልቦ ምስሌሆሙ አምላክ ነኪር። ከነርሳቸው ጋር ጣዖት አልነበረም።

፲፫. ወአዕረጎሙ ዳብ ኃይለ ምድር፡ ጎበ ብዕሰ ምድር ይላል። አወጣቸው ወሴሰዮሙ አክሰ ገራውሀ። እህሉን መገባቸው በታነጸ ግንባቸው በደረሰ አዝመራ መከራቸው ገብተዋልና።

ወሐፀኖሙ በመዓር አምኰኵሕ። ከደበቅና ከማጓ /ከዋሻና ከእንጨት/ ውስጥ የተገኘውን ከዳቦ ቆሎ ከድንጊያ ይልቅ የጸናውን ወግሩን /ግሩን/ ማር አየመገበ አሳደጋቸው።

በቅብዕ እምእብን ፅንዕት። ከድንጊያ ይልቅ የጸናውን ቅቤ እየመገበ አሳደጋቸው የደጋ ላም ጮስኝ የሚባል ሣር /ቅጠል/ ትበላለች ያ ቅቤው ፅኑ ነውና።

፲፬. በቅብዐ እጕለት ወበሐሲበ በግዕ። የጊደሩን ቅቤ የበጉን ወተት እየመገበ አሳደጋቸው።

ምስለ መቅጕዓለ ጠሊ ወላሕም። ከፍየሉ ከላሙ ወረሞ /ጮማ/ ጋራ።

www.zeyeneta.com

ዕጉለ አልሕምት ወአላግዕ። የላሙን ጊደር የበጉን ጠቦት አየመገበ አላደጋቸው። ምስለ ቁቅሐ ሥርናይ። ልጦ ጉርዶ ከወጣው ስንዴ ጋር /ከተፈተገና ከተጣራ/ ወደመ አስካለ ወይን ስትዩ። የወይኑን የዘለላውን ደም ጠምቀው /ፈጨ'ቀው/ ጠጡ። አንድም ወደመ አስካል ስትዩ ወይን። የዘለላውን ወይን ደም ጠጅ አድርገው ጠጡ።

፲፯. በልዐ ያዕቆብ ወጸግበ። ያዕቆብ ያን በልቶ ጠገበ።
ከረዮ ጽጋብ ለምንዘኑ፡ ፍቁር ይላል። ድልድል ቅምጥል ያዕቆብን ረዮጋብ አቀናጣው።
ስብሐ ወገዝፈ ወርኅበ። ስብሐ የወርድ። ወገዝፈ የቁመት። ወርኅበ የወል። ጎደጎ ለእግዚአበሔር ፈጣሪው። ፈጣሪው አግዚአብሔርን ተለየው። አንድም ፈጣሪው እግዚአብሔር ተለየው።
ወርኀቀ አምአግዚአብሔር ሕይወቱ። ከሕይወቱ ከአግዚአብሔር ራቀ። አንድም ሕይወቱ ከእግዚአብሔር ራቀ።

፲፰. ወወህከኒ በዝ ነኪር፡ ሆኩኒ ይላል። በጣዖታቸው አወኩኝ ቅሠፈን ቅሠፈን አሉኝ። አሁን ቅሠፈን ቅሠፈን ብለው አያደለም። ኃጢአት ሠርቶ ነስሓ አለመግባት ቅሠፈኝ ቅሠፈኝ ማለት ነውና።
ወአምረሩኒ በርኩሶሙ። በኃጢአታቸው አሳዛኙኝ በርኩሶሙ በጣዖታቸው አሳዘኑኝ።

፲፱. ሃው ለአጋንንት ወአኮ ለእግዚአብሔር። ለአጋንንት ሠዉ ለእግዚአብሔር የሠዉ አይደለም ለሱ ምላሹ አይደለም። መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከድንጊያ አፍልቆ ለመገበ ለሱ ለአማልክት አለ ኢየአምሩ። ለማያውቋቸው ለጣዖታት፡
ለአማልክተ ግብት አለ ኢይበቍዑ። ለማይረቡ ለማይጠቅሙ ደንገት ለተገኙ ለጣዖታት ሠዉ
ወእለ ኢየአምሩ አበዊሆሙ። አባቶቻቸው ለማያውቋቸው አባቶቻቸውን ለማያውቁ። ጌታ የሆነ እንደሆነ እነ ውእቱ

አምላከ አበዊከ አምላከ አብርሃም አምላክ ይስሐቅ ወአምላክ ያዕቆብ ይላል።

፲፰. ጎደጎ ለእግዚአብሔር ዘወለደከ። በሃይማኖት የወለደህን እግዚአብሔን ተለየኸው።
ወረሳዕከ ለእግዚአብሔር ዘሐፀነከ። በሕግ መጽሐፋዊ ያሳደገህን እግዚአብሔርን ዘነጋኸው።
አንድም ሐደጎ ለእግዚአብሔር ዘወለደከ። ወልድየ ዘበኩርየ ብሎ በሐዲስ ተፈጥሮ የፈጠረህ እግዚአብሔርን ተለየኸው።
ወረሳዕከ። መና ከደመና አወርዶ ውሃ ከድንጊያ አፍልቆ የመገበህ አግዚአብሔርን ዘነጋኸው።

፲፱. ወርአየ እግዚአብሔር ወቀንዐ። እግዚአብሔር ይህን አይቶ ቀና።
ውተምዐ መዓተ ላዕለ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ። በወንዶች በሴቶች ልጆቻቸው ፊጽሞ ፈረደባቸው።

፳. ወይብሉ አመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ። ገጸ ረድኤቴን ከነሳቸው እመልሳለሁ አለ።
ወአፈአዮሙ ዘይከውኑ በደኃራቶሙ። በኋላ ዘመን የሚሆኑትን አያለሁ አለ። አለመ ውሉድ ዓላውያን አሙንቱ። ከዳተኞች ልጆች ናቸውና። ውሉደ ዓላውያን ይላል። የክዳተኞች ልጆች ናቸውና።
ውሉድ አለ አልቦሙ ሃይማኖት። ሃይማኖት የሌላቸው ናቸውና።

፳፩. አሙንቱሰ አቅንዑኒ በዘኢኮነ አምላክ። አምላክ ባይደለ በጣዖት አስቀኑኝ። አንድም ባይደለ አምላክ አስቀኑኝ።
ወአምዕዑኒ በአማልክቲሆሙ። በጣዖታቸው /በጣዖቶቻቸው/ አሳዘኑኝ።
ወእነ አቀንየሙ በዘኢኮነ ሕዝብ። እኔም ባይደለ ወገን አስቀናቸዋለሁ
በዘኢኮነ ሕዝብ፡ ሕዝበ እግዚአብሔር ባይደለ በአሕዛብ አድራ አስቀናቸዋለሁ።

www.zeyeneta.com

ወእምዕያሙ በሕዝብ በዘኢይሌብዉ። ሕዝቡን ሕገ እግዚአብሔርን ልብ በማያደርጉ በአሕዛብ አስቀናቸዋለሁ /አሳዝናቸዋለሁ/ አለ አስማርኬ። አንድም በሕዝብ በዘኢይሌብዉ በና በ የተደራረበ ነው። በሄኖን በቅሩበ ሳሌም እንዲል። አንድም ይገዛናል ብለው ልብ በማያደርጉ ወገን አሳዝናቸዋለሁ አለ። ተርታ ወገን አለነስቼ።

አንድም ለሕዝብ በዘኢይሌዘዉ። እያሁድን ሕገ እግዚአብሔርን ልብ በማያደርጉ በአሕዛብ አሳዝናቸዋለሁ አለ። ሊቃ ጳጳስ ጳጳስ አድርጌ ሹሜ። እንከስ ብኩርና ለነ ወአኮ ለአያሁድ እያሉ ወሰደውባቸዋልና።

፫ ጸሎተ ሙሴ ዘሣልስ

ሣልስ ለንሴብሖ ነው። ሙሴ ሦስተኛ የተናገረው ይህ ነው።

፳፪. እስመ አሳት ትነድድ አመዓትየ። ከመዓቴ የተነሣ እሳት ትነዳለችና ወአምዕያሙ ላለው /ባለው/። አንድም ከመዓቴ የተነሣ እሳት ትነዳለች እኮን። እሳት እባር ቸነፈር ጦር። ወታውዓ እስከ ሲኦል ታሕተ። ሲኦል። ታሕተ አንድ ወገን። አባር። እስከ ታሕተ መሠረተ ምድር ታቃጥላለች። ወትበልዓ ለምድር ወለኩሉ ፍሬሃ። የምድርን ፍሬዋን ሁሉ ትበላለች። አንደሂሞ ወታውዓ እስከ ሲኦልታሕተ። ቸነፈር ሲኦል እናት አባት። ታሕት እያት ቅድመ አያት ታጠፋለች።

ወትበልዓ ለምድር ወለኩሉ ፍሬሃ። ምድር እናት አባትን። ወለኩሉ ፍሬሃ ልጅ የልጅ ልጅን ታጠፋለች።

ወያድለቀልቅ ኩሉ መሠረታተ አድባር። የተራሮች መሠረት በአባር ይነዋወጣል። አንድም የልዑላኑ መሠረት በሞት ይነዋወጣል።

፳፫. ወአስተጋብአ ላዕሌሆሙ እኩየ።መቅሰፍትን አሰበሰብባቸዋለሁ።

ወአንልቅ አሕላየ በላዕሌሆሙ። አሕላ መዓቴን አፈጽምባቸዋለሁ።

ወሖንልቁ በረኃብ። አሕላ ካለው /ካላቸው/ አንዱን አመጣ በረኃብ ያልቃሉ።

ወይዘውኑ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ። ለአዕዋፍ ምግብ ይሆናሉ። በዘመነ ረኃብ አዕዋፍ ይሠለጥናሉ።

፳፬. ወያደክሙ ፅንያሙ። ጉልበታቸው ይደክማል። አንድም አርበኛቸው ይደክማል።

ወአፈኑ ላዕሌሆሙ ስነ አራዊተ ምድር ምስለ ጎምዝ። መርዝ ያላቸው አራዊትን አሰድባቸዋለሁ /አሰዳለሁ/።

በዘመነ ረኃብ አራዊት ይሠለጥናሉና። አንድም ከሠራዊቱ ጋራ ነገሥታቱን አሰዳለሁ። ዘነኪር ጎምዙ እንዲል።

ከመ ይጥየዩ አምድር። ከዚህ ዓለም በሞት ይርቁ /ይለዩ ዘንድ/።

፳፭. በአፍአ ያጸምዖሙ መጥባሕት ለውሉዶሙ። ልጆቻቸውን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል። ጸምታ /ጸሚታ/ እንዲል ትግሬ።

ወወሰተ እብያቲሆሙ ድንጋጼ በቤታቸው ልቅሶ ይሰማል።

ለወራዙቶሙ ሃምለ ደናግሊሆሙ ከቆነጃጅቱ ጋር ጎልማሶችን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል።

ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አዕሩጊሆሙ። ከሽማግሌች ጋራ ሕፃናቱን በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል። አንድም ለወራዙቶሙ ምስለ ደናግሊሆሙ። ከቆነጃጅቱ ጋር ጎልማሶቹን በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል አለ። የማይዘምት ጎበዝ የማትዘምት ቆንጆ።

ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አዕሩጊሆሙ። ከሽማግሌች ጋራ ሕፃናቱን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል። የሚዘምት ሕፃን የሚዘምት ሽማግሌ። አንድም አንድ አንድ ወገንም ይሰጣል።

፳፯. ወእቤ ከመ እዝርዎሙ። አጠፋቸው ዘንድ አጠፋቸዋለሁ። ወአስዐር እምድር ዝክሮሙ። ስም አጠራራቸውን ከዚህ ዓለም ላጥፋ አልሁ።

www.zeyeneta.com

ወእምዕገለእመሕያው። ከለው ለይቼ ሳጥፋ አልሁ።

፳፯. በመዓት ፀረ ኮኑኒ። ጣዖቱን በማምለክ ጠላት ሆነውኛልና። መዓተ አረሚ እንዲል።
ከመ ኢይትዐበዩ ሀር። ሀር እስራኤል እንዳይታበዩ።
ወኢይበሉ እደነ ፀንዓት። ሥልጣናችን በአሕዛብ በረታች እንዳይሉ።

፳፰. እስመ ሕዝብ ነጉላነ ምክር አሙንቱ። እስራኤልም ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና።
አልቦሙ ምልሕ ወኢ ሃይማኖት። የበጀ ምግባር የበጀ ሃይማኖት የላቸውምና በስንቱ ይታበያሉ እንጂ እንዳይታበዩ።
አስኑ እግዚአብሔር ዘንብሮ ለዝ ኵሉ። የአሕዛብን ጥፋት የእስራኤልን ድኅነት ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን ለምን ይታበያሉ።
አንድም ከመ ኢይትዐበዩ ፀር። ፀር አሕዛብ እንዳይታበዩ።
ወኢይበሉ እደነ ፀንዐት። ሥልጣናችን በእስራኤል በረታች እንዳያሉ። ወእምዕገለእመሕያው። በመዓት ተቆጥቼ ከለው ለይቼ ጠላታቸውን ባጠፋላቸው ፀረ ኮኑኒ። እስራኤል ጠላት ሆኑኝ።
አስኑ እግዚአብሔር ዘንብሮ ለዝ ኵሉ። እስመ ሕዝብ ሕጉላነ ምክር እሙንቱ። አሕዛብ ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና።
አልቦሙ ምልሕ ወኢ ሃይማኖት። ምግባር ሃይማኖት የላቸውና የአሕዛብን ጥፋት የእስራኤልን ድኅነት ያደረገ እግዚአብሔር አያደለምን? ተቆጥቶ ከለው ለይቶ ጠላታቸውን ቢያጠፋላቸው ለምን ጠላት ሆኑት።

፳፱. ወኢሐለይዎ ከመ ያእምርዎ ለዝንቱ። አሕዛብ ይህን ያውቁት ዘንድ አላለቡትም።
ወኢየአምርዎ /ወኢየአምሩ/ በመዋዕል ዘይመጽእ። በሚመጣው ዘመን የሚሆነውን አያውቁትም /አያውቁም/።

፴. እፎ ያነትየሙ ፩ዱ ለ፲ቱ ፪። ከእስራኤል አንዱ ከአሕዛብ ሺሁን ድል እንዲነሳ አላወቁም /አያውቁም/። ሶምሶን በተናቀች መንሰክ አድግ ሺሁን ሰው እንዳጠፋ።

ታሪክ ከነገደ ዳን የተወለደ ማኑሄ የሚባል ሰው ነበረ። ሚስቱ እንትኩ ትባላለች ልጅ ባለመውለዳቸው /ስለሌላቸው/ ዘወትር ያዝኑ ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን ይች እንትኩ /እንትኩይ/ ውሃ ለመቅዳት እንጨት ለመስበርም ቢሉ ከውጣች ዘንድ መልአክ አገኛት /አገኘች/። ልጅ ትወልጃለሽና መሥዋዕት የማይሆነውን አትብዪ ራሱን አይላጭ አሳት። ሄዳ ለባሏ ነገረችው ለሚስቱ የነለጽክላትን ለእኔም ግለጽልኝ ብሎ ጸለየ። በነጋው ብትሄድ አገኘችው ሄዳ ያን ሰው እንጂ አገኘሁት አለችው። ሄዶ ትናትና ሚስቱን እንዲህ ያልሃት አንተ ነህ? አለው ያንገራገረው ይመስላል አምን የነገርኋትን ሁሉ አታሰፈርሳት አለው። ምን ምልክት ታሳየኛለህ አለው በግ ሠውተህ ሥጋውን ባገልግል ደሙን በመንቀል አድርገህ አምጣ አለው። አመጣ ካጠገቡ ጎናፍ ድንጊያ አለ ሥጋውን ከዚያ ላይ አድርገው ደሙን በሳዩ አፍስሰበት አለው እንዳለው አደረገ። ከሰማይ እሳት አውርዶ አብልቶለታል እንዲረዳው። መልአኩ አሳቱን ተረግሞ አረገ።
ወአእመራ ለእንትኩ ይላል። በግብር አወቃት ተጸነሰ ተወለደ ሶምሶን አሉት ፀሐይ ማለት ነው። ሸምሽ እንዲል ዓረብ አደን። በዚያ ወራት እስራኤል ለኢሱፍሊ ግብር ይገብሩ ነበር። ይህ ማኑሄ ግብር ይዞ ሲሄድ አብሮ አባቱን ተከትሎ ሄደ። መልክ መልካም ሕፃን አይቶ ተመሰለ አግባ አሉት። አግባ ካሳችሁኝማ እንዲህ ያለች ብላቴና አያጋለሁና እሷን አጋቡኝ አለ። እንዴት ግዙራን ስንሆን ሥርዓት አፍርሰን ከቆላፋን /ካልተገረዙት/ ጋር እንጋባ አይሆንም አሉት። እንግዲያስ እኔም አይሆንም አለ። ምን እናደርጋለን ብለው ሶምሶን ያለውን ነገር ሊያቆሙ /ቃል ሊገቡ/ ሲሄዱ እንበላ መደብ /ዓይነ ምድር ለመቀመጥ/ ወጣ። አንበሳ አፉን ከፍቶ መጣበት። አንድ ጊዜ በጡጫ ቢለው አርፏል። እንድም መንጋጋውን ይዞ ሰነጠቀው ነገር አቁመው /ቃል ተገባብተው/ ተመለሱ። ሊሞሸር ሁለተኛ ሲሄድ ከዚያ ቦታ ንብ ገብቶ ማር ሠርቶ አገኘው። ቀርጠ

www.zeyeneta.com

በልቶ የተረፈውን ስለመዳቹ ይዞላቸው ሄደ። እልነገራቸውም ምንም ቢሆን ኃይሉ ተሰምቷልና ሰላሳ አላማጅ /ሚዜዎች/ ሰጡት። ከጨዋታ የተነሣ ምላሴ መስዬ ነግሬያችሁ በኀዱቱ ቀን ፀሐይ ላትገባ ብትነግሩኝ ፵ መጎናጸፊያ ከነቀሚሱ አለጥ አናንተ ምን ትለጡ አላቸው። እኛም እንሰጣለን ብለው ተወራረዱ። መስል ምሳሌከ አሉ። አምአፊ በላዒ ተረክበ መብልዕ ወአምአፊ ጽኑዕ /ማሩም/ ወጽአ ጥዑም አላቸው። የማይሆነላቸው ሆነ ይህን ሰው እኛን ልታደኸዩ አምጥታችሁታል ጠይቀሽ ንገሪን አሏት። ብትጠይቀው አይሆንም አላት። እንደ ማኩረፍ አለች ምንም ቢሆን ሌት ታሸንፉለችና ከአፈአንበላ ማር አግኝቼ በልቼአለሁ አላት። ሄዳ ነገረቻቸው በሰባተኛዱቱ ቀን ፀሐይ ላትገባ መጥተው ሶምሶን ምላሴህን እንንገርህ አሉት። በሉ ንገሩኝ አላቸው። እምአፈ በላዒ ተረክበ መብልዕ ወአምአፈ ፅኑዕ ወጽአ ጥዑም። ከአንበላ የበረታ አለን? ከማርስ የጣፊጠ አለን? ከአፈ አንበላ ማር አግኝተህ በልተሃል አሉት። ወሶበለ እምኢያሥራኅክምዋ ለዕጉልትየ እምእረከብክምዋ ለምሳሌየ። ሚስቴን ባትዘበዝቢት ምላሌዱን ባላገኛችኋትም ነበር ብሎ ተቆጥቶ በረሀ ወረደ። ከነሱ ወገን ፴ ሰው ገድሎ ልብሳቸውን ገፎ አምጥቶ ጥሎላቸው ሄደ። አሏንም ካላማጆቹ ሳንዱ ድረዋታል። በሦስት ወሩ የበግ ጠቦት እያሳበ መጣ /ሄደ/ ሚስቴን ስጡኝ አላቸው። አሏንስ ለሌላ ሰጥተናታል ትወድ እንደሆነ ክሏ የምታምር ትንሽ እኅቷ እሰች አሏን አግባ አሉት። ሚስቴን እንጅ ሌላ አልሻም /አይሆንም/ አለ። አሏንስ እንድ ጊዜ ሰጥተናታል እይሆንም አሉት። በሩጫ ፫፪ ቀበሮ እያባረረ ይዞ ፪፱ ዳቦት እንደመስቀል እያደረገ ሠራ። ያን እያቃጠለ እንዱን ከሁለቱ ጅራት እየቋጠረ ለደዳቸው። ምን ተስተሰን እያሉ እዝመራቸውን ቁመናውን ከምሩንም እቃጠሉት። ይህን ያደረገ ማነው አሉ። ሶምሶን አላቸው ምን ቢሆን አሉ። እማቾቹ በድለውት አሏቸው። ሄደው ዘረፏቸው ሶምሶን እንተን ደስ ይበልህ ብለን እንዲህ

አደረግን አሉት መልካም እደረጋችሁ ይህን ባታደርጉ ጠቤ ከእናንተ ጋራ ነበር አላቸው። ማን መብት ሰጠውና እንዲህ ይሰናል ብሎው ሲያንጎራጉሩ ሰምቶ ምን ያንጎራጉራሉ ብሎ ጎመዱን እንስቶ ጭን ጭናቸውን ሰብሮ ሄደ። በዓተ ኤጣም /ኤላም/ ተሠወረ። ተሰብስበው ሄደው ዘመዶቹን ያቂቸው ስታመጡ ሶምሶን እምጡ በቀረው እናንተን እናጠፋችኋለን አሏቸው። ፰ኤል ከሦስት መቶ የሚበዙ ሆነው ሄደው ሶምሶን እባክህን ባንተ ምክንያት እንጥፋ አሰኙልን አሉት። በሉ እናንተ ላታጠፉኝ ማሉልኝ አላቸው። እንዲህ ማለቱ ኃይሉ በእሕዛብ እንጂ በ፰ኤል አልታዘዘምና ማሉለት። በ፯ት ላመ ገመድ /ባልደረቀ አርጥብ ጠፍር/ አሥሪው ይዘውት ሄዱ ከእስራኤል እጅ ሊወጣ /ወጥቶ/ በእሕዛብ እጅ ሊገባ ያችን እንደፈትል ክር ቶርሎ ግራ ቀኝ ቢያይ መንሰክ አድግ አገኘ። ያን ቢያምዘገዝግ ሺህ ሰው አርስ በርሱ ተሰጋግቶ አልቋል። ከዘያው ውሃ ፊልቆሰት ጠጥቷል።

ወዲቱ ይሰድድምሙ ሰየየ። ከእስራኤል ሁለቱ ከእሕዛብ አልፋን /አሥር ሺሁን/ ድል እንደነሷቸው አላወቁም። በሳአል ጊዜ ተማምሰው ተሰፋፊሩ /ተሰለፉ/።

ታሪክ እስራኤል እሕዛብን ሳንወጋ እህል ውሃ እንቀምስም ብለው እሕዛብም እስራኤልን ሳንወጋ እህል ውሃ አንተምስም ብለው። የሳአል ልጅ ዮናታን ብላቴናውን አስክትሎ ወጣ። እስራኤል ድሮ ወባት ሊገቡ /እምነው እጅ ሊሰጡ/ እንድ እንድ እያሉ መጡ ያሉን እንደሆነ በእጃችን ጥሏቸዋል ዝም ያሉን እንደሆነ በእጃቸው ጥሎናል አለው። ይህን ሰብላቴናው ሲነግረው እስራኤል ድሮ ወባት ሊገቡ እንድ እንድ እያሉ መጡ አይዞአችሁ ኑ እንነካቸሁም አሏቸው። ያሉበትን ተራራ በአጄም በእግሩም ብሎ ወጥቶ ሃያ ሰው ገደለ። ላአል አሻግሮ በመነጥር ቢያይ እንደወፍ ሲነጣጠቁት እይቶ ክኛ ወደ አሕዛብ ለፈር የሄደ ሰው አለን? እስኪ ሰው ቍጠሩ /ፍቀዱ/ አለ ልጅህ ዮናታን የለም አሉት። ሄደው ገጠሙ ከእሕዛብ ለባት ሺህ ፈረሰኛ

www.zeyeneta.com

ሦስት ሺህ ባለ ሠረገላ አልቋል። ምክንያት መሆናቸውን መናገር ነው።

አሰመ እግዚአብሔር ፈደዮሙ። እግዚአብሔር ፍዳውን አምጥቶባቸዋልና።

ወአምላከነሂ አግብአሙ። ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ጥሏቸዋልና።

፴፩. አሰመ አ.ዘነ አምላክነ ከመ አማልከቲሆሙ። ሆኖም ያ ግን እንደነሳቸው አንደ ጣዖቱ አይደለምና።

ወርነሰ ዐብዳን። ጠላቶቻችን አሕዛብ ሰነፎች ናቸው ይላሉ አሰራኤል። አንድም ወአ.ሐለያዖ። አሰራኤል ይህን ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም።

ወአ.የአምሩ በመዋዕል ዘይመጽእ። በሚመጣ ዘመን የሚሆነውን አያውቁትም /አያውቁም/።

እፎ ያነ-ያሙ አሐዱ... ከአሕዛብ አንዱ ከአሰራኤል ሺሁን ድል እንዲነሣቸው እሳወቁም።

ወክልኡቱ ይሰድድዎሙ ለአልፍ፡ ከአሕዛብ ሁለቱ ከአሰራኤል አልፉን ድል እንዲነሷቸው እሳወቁም።

ወያሜያሙዐ አምድያሙዘ ቆጽል ይላል። ቅጠል ኮሸሸ ባለ ቁጥር አ.ሰ-ነ.ሰ. መጡ አያሉ ገደል ወድቀው ባሕር ጠልቀው ይቀሩ ነበር አይለውጥም።

ወርነሰ ዐብዳን። ጠላቶቻችን አሰራኤል ለነፎች ናቸው ይላሉ ነዘያት ካህናት።

፴፪. አሰመ ከመ ዐዐደ ወይነ ለዶም ዐዘደ ወይኖሙ። የሕግ ማደሪያ ልቡናቸው የለዶም ሕግ ማደሪያ እንደሆነ እንደ አሕዛብ ልቡና ሆኗልና።

ወሐረገሙኒ እምነ ገሞራ። ግብራቸው የገሞራ ነው።

እንድም ትውልዳቸው ከገሞራ ነው። ወሐረገ ሰዶምኒ ትእገዝ በሊዓ እንዲል።

ወእስክሎሙኒ አስካለ ሐሞት። አስካለቸው /ፍሬያቸው/ የሐሞት አስካል ነው። እንድም ግብራቸው መራራ ነው።

ወቀምሐሙኒ መሪር። ግብራቸው መራራ ነው።

፴፫. ጎምዘ አርዌ ምድር ወይናሙ። ወይናቸው የእባብ መርዝ ነው። ያ እንዲያጠፋ የሚያጠፋ ነው።

ጎምዘ አፍዖት ዘይቀትል። ከዚያም ዘንድ የሚገድል የእፉኝት መርዝ ነው። ያ መድኃኒት የሌለው ነው።

፴፬. አኰ ዝንቱ ትእዛዝ ዘአምጎቤየ ውአቱ። ይህ ትእዛዝ ከእኔ የተገኘ እይደለም። የአሕዛብ ጥፋት የአሰራኤል ድኅነት ጠቀ-ነ-ሰ መሳግብትየ። በሣጥን ልቡናዬ ለጥፋት ተቆጠሩ።

፴፭. በዕለተ ኵነኔ እትቤቀሶሙ። በፈረድኩበት ቀን አጠፋቸዋለሁ።

ወበጊዜ ይድሕፅ እግሮሙ። ልቡናቸው በገቢረ ኃጢአት በአምልኮ ጣዖት በተሰነካከለ ጊዜ።

አንድም ወበጊዜ፡ ይድሕፅ እግሮሙ ይላል ሳይናበብ። በጊዜው ጊዜ ለውነታቸው በመቅሠፍት ይሰነካከላል።

አሰመ ቀርበ ዕለተ ጎልቆሙ። ለጥፋት የተቆጠሩበት ቀን ደርሷልና።ጎልቆሙ ባለው ጎልቀቆሙ ይላል። የሚያልቁበት ቀን ደርሷልና።

አሰመ በጽሐ ድልው ውአቱ ለከሙ። በእናንተ የተዘጋጀ መቅሠፍት ደርሷልና።

አንድም አሰመ በጽሐ። መቅሠፍቱ ደርሷልና።

ወድልው ለክሙ። በእናንተም የተዘጋጀ ነውና።

፴፮. አሰመ ይካ.ንን እግዚአብሔር ሕዝቦ። እግዚአብሔር ለአሰራኤል በአሕዛብ ይፈርዳልና።

ወይትናበብ በእንተ እግብርቲሁ። ስለባሮቹ ስለነቢያት ስለካህናት ብሎ ለአሰራኤል ይፈርዳልና።

አሰመ ርእየ ከመ ተመስዉ ወጎልቁ። <u>በመከራው እንደተፈጸሙ አይታቸዋልና</u>።

ወተዘንጉ በጎበ ሀለዉ ባሉበት እገር <u>ግሽግጠጫ</u> /መሸሚጠጫ/ እንደሆኑ እይታቸዋልና።

፴፯. ወሶበ ሠርሑ ይቤ እግዚአብሔር። በመከራው በደከሙ ጊዜ እንዲህ አለ።

www.zeyeneta.com

አይቴ እሙንቱ አማልክቲከሙ እለትትዋከሉ ቦሙ።
የምትታመኑባቸው አማልክቶቻችሁ ወዴት ደረሱ።

፴፯. ወእለ ትበልዑ መሥዋዕተ መሥዋዕቶሙ። ስኩን መሥዋዕት የምትበሉላቸው።
ወትሰትዩ ወይነ ሞግሕቶሙ። ከወይኑ ፍልቅ አድርጋችሁ አፋስላችሁ የምትጠጡላቸው።
ይትነሥኡኬ ወይርድኡከሙ። ይነሷ ይርዷችሁ!
ወይሕንጎከሙ መድኃኒከሙ። ያድኗችሁ!

፴፱. አአምሩ አአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር።
እግዚአብሔር እኔ እደሆንኩ እወቁ እወቁ።
አልቦ ባዕድ አምላከ ዘእንብሌየ። ያለ እኔ ሌላ አምላክ እንደሌለ እወቁ እወቁ።
አነ እቀትል ወአሐዩ። የምገድል የማድን እኔ እንደሆንኩ እወቁ እወቁ።
አቀሥፍኂ ወእሜህል። በመከራ የምገርፍ መልሼ ይቅር የምል እኔ እንደሆንኩ እወቁ እወቁ።
ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ። ከሥልጣኔ የሚያመልጥ እንደሌለ እወቁ እወቁ።

፵. አስመ አሌዕል ውስተ ሰማይ እዴየ። እጀን ወደ ሰማይ ከፋ፡ አድርጌ እምላለሁና።
እምሕል በየማንየ ወአብል ሕያው አነ ለዓለም። አማንየ በርእለየ ብዙ እምላለሁና።

፵፩. ወአበልሓ ከመ መብረቅ ለመጥባሕትየ። ሾተሌን እንደመብረቅ አፍት አፋጥናታለሁና /አቀናጣታለሁና/
ወትቀውም እዴየ በኵነኔየ። በፈረድኩበት ቀን እደ መዓቴ ትፀናለች። ከፍርዴ ጋራ እደ መዓቴ ትፀናለች።
ወእትፈደዮሙ በቀለ ለፀርየ። ከጠላቶቼ በቀልን አከፈላቸዋለሁ። ወእትቤቀሎሙ ለጸላእትየ። ጠላቶቼን ተበቅዬ አጠፋቸዋለሁ።

፵፪. ወአሰክሮን ቢደሞሙ ለአሕዋየ። ፍላፃቼን በደማቸው አሰክራቸዋለሁ። ወትበልዕ ሥጋሆሙ መጥባሕትየ። ሾተሌ

ሥጋቸውን ትበላለች። እምደመ ቅቱላን ወሊውዋን።
ከሞቱት ከተማረኩት ደም።
አሰክሮን ከሞቱትስ ይሁን ከተማረኩት እንዴት ነው ቢሉ የፈሰማ /መለያ ምልክት/ እያሉ ይወጓቸዋልና።
አርእስተ መላእክተ ፀር።
የጠላቶችን የአለቆችን ችብቸቦ ትበልዕ። አንድም የአለቆችን አለቆች ትበልዕ።

፵፫. ይትፌሥሓ ኵሉን ሰማያት ኅቡረ። ሰማያት ተባብረው ደስ ይላቸዋል። አንድም ልዑላኑ ተባብረው ደስ ይላቸዋል።
ወይሰግዱ ሎቱ ኵሉሙ መላእክተ እግዚአብሔር። መላእክት ይሰግዱለታል።
ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስሰ ሕዘቢሆሙ። ሁለቱ ነገድ ከአሥሩ ነገድ ጋራ ደስ ይላቸዋል። ወይብሉ ኵሉሙ ውሉደ እግዚአብሔር ፅኑዕ ውእቱ። ጽኤል ከሃሊ ነው ይላሉ።
አስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ። የአሰራኤልን ደም አስቦ አሕዛብን ይበቀላልና።
ይትቤቀል ወይትፈደይ በቀሰ ሰፀሩ። ከጠላቶቹ ከአሕዛብ በቀልን ይከፈላል።
ወይትቤቀሎሙ ለጸላእቱ። ጠላቶቹን ተበቅሎ ያጠፋቸዋል
ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ። ለወገኖቹ ለእስራኤል ምድረ ርስትን የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል።
ጥንቱንም የሴም ዕፃ ናትና።
አንድም ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስሰ ሕዘቢሆሙ። ሊቃነ መላእክት ተባብረው ደስ ይላቸዋል።
ወይሰግዱ ሎቱ ኵሉሙ መላእክተ እግዚአብሔር። ሠራዊተ መላእክት ይሰግዱለታል።
ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለሕዝቢሆሙ። ኖሎት ከኖሎት ጋራ /እረኞች ከእረኞች ጋራ/ ደስ ይላቸዋል።
ወይብሉ ኵሉሙ ውሉደ እግዚአብሔር ፅኑዕ ውእቱ።
እኑም /ሥሩዕ/ እኑም በሥጋ ስው የሆነ ሥሩዕ ከሀሊ

www.zeyeneta.com

እንደማለት ነው። ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ ወልድ ከሃሊ ነው ይላሉ።

፵፬. አስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ። የምእመናንን ደም አስቦ አጋንንትን ይበቀላልና። ይትቤቀል። ከጠላቶቹ ከአጋንንት በቀልን ይከፈላል። ወይትቤቀሎሙ ለጸላኦቱ። ጠላቶቹ አጋንንትን ተበቅሎ ያጠፋቸዋል። ወያንጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ። ለወገኖቹ ለምእመናን መንግሥተ ሰማይን የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል።

፪. ጸሎተ ሐና እመ ሳሙኤል ነቢይ

ሐና ማለት ፍሥሓ ወሐሤት ማለት ነው።

ወዘሰ ፭ዱ ካህን አምአርማቴም ዘመሲፋ ዘደብረ ኤፍራም ዘስሙ ሕልቃና ይላል።

ታሪክ የኤፍራም ዕፃ የምትሆን መሲፋ የመሲፋ ክፍል የምትሆን አርማቴም አርማቴም ስሙን ሕልቃና የሚሉት አንድ ካህን ነበር።

ወሀሰዋሀ ክልዔቲ አንስት ይላል። ሁለት ሚስቶች ነበሩት።

ለአሐቲ ስማ ሐና ወለካልዕታ ፍናና። አንዲቱ ሐና አንዲቱ ፍናና ትባል ነበር። አሁን ካህን ነበር አለ ሁለት ሚስቶች ነበሩት አሰሳ። እንደምን ቢሉ ጊታ በዚያ ወራት /ጊዜ/ ብዛታቸውን እንጅ ሥርዓት አሳፀናባቸውም ነበርና። እንደ ዛሬም አእምሮ አልሰፋም ነበር።

ወለለዓመት የዐርግ ይተ ጊዜ። ከዓመት ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌም ወጥቶ በዓል ያደርግ ነበር።

ለያስተርኢ ተባዕትነ ይተ ጊዜያተ ለለዓመት ትላለች አሪት። ከተረፈ መሥዋዕቱ አንድ ዕፃ ለሐና ሁለት ዕፃ ለፍናና ይሰጥ ነበር። ምነው ሐናን ጠልቶ ፍናናን ወዶ ነው ቢሉ መውደድስ ሐናን ይወዳል። ያቺ ፍናና ልጆች አሏት ከልጆቿ ጋር ትባላዋለች። ይህቺ (ሐና) ልጅ የላትም። እርሷም ወጥታ እስክትመለስ ድረስ አትበላም ነበር። ይህስ አይቻልም ብሎ ደስ ብሏት አትበላም ነበር። ይህስ ስለምን ልጅ ያልሰጣት ቢሉ የብስጭት ጎዝን ታዝን ነበርና። ይህስ ቢሆን በኋላም ባልሰጣትም ነበር ብሎ አዝና ታማኝው ብሎ። አዝኖ ያገኙት ልጅ ይረባል ይጠቅማልና።

"ካሉ ለእግዚአብሔር በጊዜው እንዲል። ይቅርታውን ያለጊዜው አይሠራውምና ከፅሰታት ባንዱ ቀን ለታዝን አይቶ።

ሐና ለምንት ትቀሥፌ ልበኪ በጎዝን። ልብሽን በጎዘን ጨንገር ለምን ትገርፊያለሽ ኢይኄይስኪኑ እም፲ቱ ትውልድ ከ፲ ልጅ እኔ አልበልጥም /አልሻልምን/? አላት። ኋላ ከቤተ እግዚአብሔር ገብታ አግዚአብሔር ጸባዖት ኤሎሄ አለች። ጸባዖት

www.zeyeneta.com

መዋሚ፡ እግዚአ ኀይላት። አዶናይ፡ ጎዙዕ። ኤሎሄ፡ ፈጣሪዩ ማለት ነው።

ለእመ ነጽሮ ነጸርከ ሳዕለ ሕማማ ለዓመትከ። ኀዘኔን ዓይተህ

ወወህበካ ዘርዓ ብእሲ። ልጅ ብትሠጠኝ፡

እነሂ አሁን ሀብተ በቅድሜከ። እኔም ለጦታ አድርጌ ላንተ እስጠዋለሁ አለች።

ኢይሰቲ ወይነ ወሜሰ። የማር ጠጅ ወይን ጠጅ አይጠጣም። የማር ጠጅስ በአገራቸው የሰም ብሎ ጉሽ የወይን ጠጅ ወይም ደረቅ የወይን ጠጅ አይጠጣም።

ወኢየወርግ ሐኒን ዲበ ርእሱ። ምላጭ ከራሱ አይወጣም ይኸውም ልማድ ነው። የስእሰት ልጅ አይላጭም። ደን ጊዜ ዓሰ. በኖኅተ ደብተራ ወንበር አዘርግቶ ተቀምጦ ነበር። ሰሰምን ቢሰ መሥዋዕተ ነግህ አሰፈ መሥዋዕተ ሠርክ አቅርቡ ሰማሰት። አንድም ኢይባዕ ሞዓባዊ ወዓሞናዊ ደለውን ሰመጠበቅ።

አንድም አሥራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን ለመቀበል በኩራት የለው የአንሰሳ መጀመሪያ የተወሰደው ቀዳምያት የእህል እስቀድሞ የደረሰው በማናቸውም ምክንያት ከተቀመጠ ዘንድ ንብታ ስትጸልይ አይቶ።

ወእምሰላ ዓሊ ከመ ስክርት ይላል። ስካር ሴት እስመለሳት ሥርዓት ብትሰወጥበት። ሰልማዱ ነገር ሊያገኛቸው ለሊቀ ካህናቱ ይነግሩታል ሊቀካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰ ዕጣን እጥኖ ታቦ እግዚአብሔር ጠይቆ ይነግራቸዋል። አሷ ግን ለእሩቅ ብእሲ ቢነግሩት ምን ግዳጅ ይፈጽማል ብላ አንደ ለብስ ሐዲስ ንብታ ስትጸልይ አይቶ።

ወይቤላ ንዒ ጸኢ እምቤተእግዚአብሔር ወእስስሊ ወይነኪ በንዋም። ስካርሽን በእንቅልፍ አሳልፊው አሳት፡ ወይን አሰው በግብሩ። አልቦ አለችው ኢትረስያ ለዓመትከ ከመአዋልድ ርኩሳት። እኔን ባርያህን እንደቅሬ አንደ ደንገጥር አታድርገኝ ቅሬ ደንገጥር ሥርዓት አፍራሽ ናት በልታ ጠጥታ ትገላለች። አንድም አንደ አሕዛብ ልጆች አታድርገኝ። እነዚያ ሥርዓት አልተሠራላቸውም።

አላ አኪተ መዋዕል እነ። ቀን የባሰኝ ወራት ያዋረደኝ ነኝ እንጂ አለችው። ደኅና ከሆንሽ

ሑሪ በሰላም አምላከ አስራኤል የሃሰ ምስሐከ ብሎ ስደዳት።

ነሀ ረከበት ዓመትከ ሞገስ በቅድሜከ ብላለች። ደግ ሰው ሲመርቅ ደስ ያሰኛልና ደግ ሰው የተናገረው አይተርም ብላ ሄዳ አትበላም ቢሉ በላች ደስ ብሏት አብዝታ አትበላም ቢሉ ደስ ብሏት በሳች በበነጋታው ቤተእግዚአብሔር እጅ ነስተው ሄዱ።

ወእእመራ ሰሐና ይላል፡ በግብር አወቃት ተወነሰ ተወለደ ስሙን ሳሙኤል አሰችው።

እሰመ አምኀበ እግዚአብሔር ሰእልኩ ተቤ። ከእግዚአብሔር ሰምኜ አገኘሁት ስትል። ባመቱ እንሂድ አሳት መልሺ እንዳሰመጣው ተሰዞ ወልጀዋሰሁ ትቼውም እንዳልመጣ መዋዕሰ ጥብ አልተፈጸመምና (መዋዕሰ ጥብን አልፈጸመምና) ጡት አልጣሰም አለችው።

"ገበረ ዘይኤድመኪ ሰእሰይንትከ ባሕቱ አትሚ ዘወጽአ እምአፋክ አሳት። ከሴቶች ጽንት አይታጣምና በሦኛ ዓመቱ ፪፻ ዳቦ ፪፫ የበሰስ ቂንጣ ሙዳይ ሙሱ ዘቢብ ማድጋ ሙሱ ስልቅ አድርጋ ሄደች። ፊት ጥንተ መሥዋዕቱን ሠዋ ኋሳ ሳሙኤል በተወሰደ ጊዜ የተወሰደ ወይፈን ነበር ያን ሠዋ ልጇን ከመሥዋዕት ይቆጠርልኝ ሊል ሄዳ ከፊቱ ቆመች።

ለምኅኒ እግዚኦ ሕይወተ ነፍስከ። በረከትህን ስማኝ፡ የስውነትህ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ቢመርቀኝ ልጅ ያገኘሁ እኔ እንደሆንኩ ስማኝ። እንድም ሕያውት ነፍስከ፡ በመንፈስቅዱስ ሕያውት የሆነች ሰውነትህ ብትመርቀኝ ልጅ ያገኘሁ እኔ እንደሆንኩ ስማኝ።

ከመ እንታኩቲ ብእሲት ዘቆምኩ ቅድሜከ ወበዓዕኩ ወጸሰይኩ፡

ወወህበኒ እግዚአብሔር ስእሰትየ እነሂ ወህበክዎ ሀብተ በቅድሜከ። ከመ ይትቀነይ በኵሉ መዋዕሰ ሕይወቱ፡ እስከ አመ ይመውት ብላ ከዚያ ይህን ተናግራለች። በዚህም ሦስት ነገር አሰበት።

www.zeyeneta.com

፩ኛ. ትንቢት፡ እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት እንጕድጕደ፡
፪ኛ. ምዕዳን ኢትትመከሁ ወኢትንብቡ ዐቢያተ።
፫ኛ. አሎቴት፡ አስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር፡ ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ ወአልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚኦ፡
፬ኛ. ፀንዐ ልብየ በእግዚአብሔር። በጎንጽ አብነት ሃይማኖት። የነቢዩ የሳሙኤል እናት ሐና የተናገረችው ነገር ይህ ነው። ጸሎትን ነገር ይሳል ወጸለየ ጦቢት። ጸሎተ ትፍሥሕት ጸሎትስ ተናግሮተ ስብእ ምስለ እግዚአብሔር አንዲል። ነቢይ ቢል ሰሳሙኤል ነቢይት ቢል ሰሐና ይተጽሳል /ይተጸላል/።

፭. ፀንዐ ልብየ በእግዚአብሔር። ሐራ በሰላም አምላክ አስራኤል የሃሉ ምስሌኪ ብለህ በስደድከኝ ጊዜ ልቡናዩ በእግዚአብሔር አምኖ ፀና።
ወተስዐለ ቀርንየ በአምላኪየ ወመድኃንየ። በፈጣሪዩ በመድኃኒቴ አምኜ ሥልጣኔ ከፍ ከፍ አለ።
ወርኀበ አፉየ ዲበ ጸላእትየ። በጠላቶቹ ላይ አፈ ሰፋ አለ በአፍ ላይ አፍ ጨመርክልኝ ማለት አይደለም። ለሁሉ ማሕበሰን ይብስተ አጥባት ኅጥአተበረከት አያሉ ሰሚስድቡኝ ሰሥች ርትተ ማሕበሰን ልሥልምተ አነባት ምልዕተ በረከት ነኝ ብዬ እንደመልስላቸው አደረግሽኝ ስትል ነው።
ወተፈሣሕኩ በአድኅኖትከ። በትድግናህ ደስ አለኝ በሳርታንክ ይሳል። አድኅኖት ማለት ነው።
አስመ አልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ። እንደ እግዚአብሔር ክቡር የለምና።
ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ። እንደ ፈጣሪያችን እውነተኛ የለምና።
አስመ አልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚኦ። አቤቱ ያላንተ ክቡር የለምና ሦስት ጊዜ መላልሳ ተናገረች ሰአፅንዖተ ነገር። አንድም ስእጠይቆተ ፫ቱ አካላት።

፮. አስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር። አብ፡ ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ ወልድ፡ ወአልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚኦ መንፈስ ቅዱስ።

፯. ኢትትመከሁ ወኢትንብቡ ዓቢያተ።

እናንተ የፍናና ዘመዶች እትመኩ ፅኑ ፅኑ ነገር አትናገሩ ዕፁተ ማሕፀን ይብስተ አጥባት ኅጥአተ በረከት አያላችሁ።
ወኢይጸእ ዐቢይ ነገር አምእፉክሙ። ይብስተ አጥባት ኅጥአተ በረከት አያላችሁ ካፋችሁ ፅኑ ፅኑ ነገር አይውጣ።
አስመ እግዚአብሔር አምላክ ማአምር ውእቱ። እግዚአብሔር አዋቂ ነውና አውቆ ያጠፋችኋልና /ይፈርዳልና/።
እግዚአብሔር አስተደለወ መንበሮ። እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ በፍናና ዘመዶች ሊፈርድባቸው ስሐና ዘመዶች ሲፈርድላቸው።

፱. አድከመ ተስተኃያላን። የፍናና ዘመዶች ስልጣንን አደከመ።
ወአትፍነዎሙ ኃይለ ሰድኩማን። ሰሐና ዘመዶች ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው።
ወኃጣነ እክል ርኀቡ። ፪ ዕጣ ተቀብለው ጠግበው ይኖሩ የነበሩ የፍናናና ዘመዶች ተራቡ።
ወርኀቡሳን ወሜጡ። አንድ ዕጣ ተቀብለው ተርበው ይኖሩ የነበሩ የሐና ዘመዶች ጠገቡ።
አስመ መካን ወለደት ፯ተ። መካን ሐና ፍጹም ሳሙኤልን ወልዳለችና።
አስመ ጕልቁ ላብዕ ፍጹም ውእቱ በኀበ ዕብራውያን እንዲል። አንድም ወሐወጸ እግዚአብሔር ለሐና ወወለደት ዓዲ ፫ተ ደቂቀ ወአፍተ አዋልደ ይላል። ሳሙኤልን ስለሁለት ቆጥሮ። ምስፍና የሙሴን ክህነት የአሮንን ይዟል።
ወወላድስ ስእነት ወለደ። ወላድ ፍናና ግን መውለድ ተሳናት በቅናት ማሕፀኗ ደርቋል። አንድም እንደ ሳሙኤል ያለ አንድም ልጅ መውለድ ተሳናት፡ አንድም የወላድ መሐን ሆነች። ልጆቿ አልቀውባታል።
እግዚአብሔር አስተዳለወ መንበሮ። እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ። በግብፃውያን በባቢሎናውያን ሊፈርድባቸው ስአስራኤል ስትሩፋን ሊፈርድላቸው።
አድከመ ቀስተ ኃያላን። የግብጻውያንን የባቢሎናውያንን ሥልጣን አደከመ። ወአቀነቶሙ ኃይለ ሰድኩማን። ሰአስራኤል ስትሩፋን ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው።

www.zeyeneta.com

፳. ፅንሳነ እክል ርኅቡ። ግብጻውያን ተራቡ አንበጣ በልቶባቸው በረድ መትቶባቸው። አንድም ባቢሎናውያን ተራቡ የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ዘርፏቸው።
ወርኅባን ፀግቡ። በግብጽ ተርበው ይኖሩ የነበሩ እስራኤል ጠገቡ። መና ከደመና ወርዶላቸው ውሃ ከድንጊያ ፈልቆላቸው። በባቢሎን ተርበው ይኖሩ የነበሩ ትሩፋን ጠገቡ።
፯ እህጉር ወግተው ብዕለ እሕዛብን ዘርፈው ወጥተዋል።
እስመ መካን ወለደት ፯ተ። መካን ቤተ እስራኤል ፍጹም ሙሴ እሮንን ዮሴፅ ዘሩባቤልን አስገኝታለችና።
ወወላድስ ስእነት ወሊደ። ወላድ ግብጽ ግን እንደ ሙሴ እንደ አሮን ያለ ልጅ ማስገኘት ተሳናት። አንድም የወላድ መሐን ሆነች ባሕር አስጥምባት ቸነፈር ፈጅቶባት ወላድ ባቢሎን እንደ ዮሴፅ ዘሩባቤል ያሰ ልጅ ማሰገኘት ተሳናት። አንድም የወላድ መሐን ሆነች የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ፈጅቶባት።
አንድም እግዚአብሔር አስተዳለወ። እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን /መንግሥተ ሰማይን/ አዘጋጀ። በአይሁድ በአጋንንት ሊፈርድባቸው ሰነፍላት ሰሐዋርያት ሊፈርድላቸው።
አድከመ ቀስተ ኃያላን። የአይሁድን የአጋንንትን ሥልጣን አደከመ። ወአቅነቶሙ ኃይሰ ሰድኩማን። ሰነፍላት ለሐዋርያት መንፈሳዊ ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው።

ፅንሳነ እክል ርኅቡ። አሥራቱን በኵራቱን ቀዳምያቱን ተቀብለው ጠግበው ይኖሩ የነበሩ ሐና ቀያፋ ተራቡ። አንድም እከሰ ሥልጣንን ጠግበው ይኖሩ የነበሩ አጋንንት ከእከሰ ሥልጣን ተራቡ።
ወርኅባን ፀግቡ። ከትምህርት ተርበው ይኖሩ የነበሩ ሐዋርያት ልጅነቱን ትምህርቱን አንድም ከልጅነት ከክብር ተርበው ይኖሩ የነበሩ ነፍሳት ልጅነቱን ክብሩን አግኝተው ጠገቡ።
እስመ መካን ወለደት ፯ተ። መካን ወንጌል ፍጹም ክርስቶስን አስገኝታለችና። መካን አሳት ሥርዓቷ በመልክጼዴቅ ጊዜ ታይቶ ኖራ ኖራ ተሠርታለችና።

ወወላድስ ስእነት ወሊደ። ወላድ አሪት ግን እንደ ክርስቶስ ያለ ልጅ ማስገኘት ተሳናት።
አንድም የወላድ መካን ሆነች። የጥጦስ የአስባስያኖስ ጦር ፈጅቶባት።
፮. እግዚአብሔር ይቀትል ወየሐዩ። እግዚአብሔር ይገድላል ያድናል።
ይቀትል፡ በሥጋ፡ የሐዩ፡ በነፍስ። አንድም ይቀትል ጠላቶቹን፡ የሐዩ ወዳጆቹን። አንድም አንድ አንዱን ሰው ገድሎ ያድናል። እንደ ወልደ መበለት እንደ ወሰተ ኢያኢሮስ ያሰውን።
ያወርድሂ ውስተ ሲኦል ወየዐርግ። ወደ መቃብር ያወርዳል ከመቃብር ያወጣል እንደ አልዓዛር ያሰውን።
፯. እግዚአብሔር ያነዲ ወያብዕል። ያደኸያል ያከብራል እንደ ኢዮብ።
የጎሥርሂ ወያከብር። ያዜጋል /ያዋርዳል/ ያከብራል።
፰. ዘያነሥእ እምድር ሰነዳይ። ደሀውን ከንዴቱ የሚያነሣው እሱ ነው። ማናቸውንም ደሃ።እንድም ሳሙኤልን ሳያልን ዳዊትን።
ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን። ምስኪኑን ከንዴት እንሥቶ ከፍ ከፍ የሚያደርገው እሱ ነው።
ከመ ያንብሮ ምስሰ ዐብያተ ሕዝቡ። በወገኖቹ ከተሾሙ ከአለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ፡
ወያወርሶ መንበረ ክብር። መንበረ ክብርን ያወርሰዋል። ለሳሙኤል መንበሩን ለሳኦል ሰዳዊት ዙፋኑን።
አንድም ዘያነሥእ። ነዳየ አእምሮ አዳምን ከንዴተ ነፍስ የሚያነሳው እሱ ነው።
ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን። ምስኪን አእምሮ አዳምን ከንዴተ ነፍስ አዝቶ ከፍ ከፍ የሚያደርገው እሱ ነው።
ከመያንብሮ ምስለ ዐበይተ ሕዝቡ። ከአለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ።
ወያወርሶ መንበረ ክብር። መንበረ ብርሃንን ያወርስዋል።
ወይሁብ ጸሎቶ ለዘጸለየ።

www.zeyeneta.com

ለጸለየ ጸሎቱን ይሰጠዋል አለ። እንዲጸልይ ያደርገዋል። አንድም የጸሎቱን ዋጋ ይሰጠዋል ሀገኑ። ዘወትር ጸሎተን እንዲል።

፱. ወላረክ ዓመተ ጻድቃኑ። የወዳጆቹን ዘመን አበዛ አከበረ አሰጀ። እስመ ኢኮነ ፅኑዓ ኃይለ ሰብእ። የሰው ኃይሉ ፅኑ አይደለምና አለ። ሰው የገዛ ዘመኑን ማብዛት ማክበር ማበጀት አይቻለውምና። አንድም የሰው ኃይሉ ፅኑ አይደለምና።

፲. እግዚአብሔር ያደከሞሙ ለፀሩ። እግዚአብሔር ጠላቶቹን ያደክማቸዋል።
እግዚአብሔር ባሕቲቱ ቅዱስ። ብቻውን ክቡር ምስጉን የሚሆን እግዚአብሔር ጠላቶቹን ያደክማቸዋል።
ኢይትመካህ ጠቢብ በጥበቡ። ብልህ በብልሀቱ አይመካ ዓየረ ዓየራትን ሙጻአ ነፋሳትን ምሕዋረ ከዋክብትን አውቃለሁ ብሎ አይበል።
ኢይትመካሕ ኃያል በኃይሉ። ኃይለኛ በኃይሉ አይመካ። ብሮጥ እቀድማለሁ ባስር አጠብቃለሁ ብመታ አደቃለሁ ብሎ። ኢይትመካሕ ባዕል በብዕሉ። ባለጸጋ በብዕሉ አይመካ ወርቁ ብሩ በሣጥኔ እህሉ በጎተራዬ ላመ በራው በበረቱ አለ ምን አግኙኝ ብሎ። ፫ አርእስት ተናግሯል። ስሦስቱም ያመጣል። ዘለ ይትሜካሕ በዝ ለይትመካሕ። የሚመካ ስውሰ በዚህ ይመካ በዝ ያለውን ያምጣው።

፲፩. በአእምሮ ወበለብም እግዚአብሔር። እግዚአብሔርን በማወቅ ይመካ ጠቢብ ላለው።
በገቢረ ፍትሕ ወርትዕ በማዕከለ ምድር። የተበደለውን በማስከስ የተቀማውን በማስመለስ ይመካ ኃያል ላለው።
ወጽድቅ። በመመጽወት ይመካ ባዕል ላለው። ይህ ቅሉ ይመኳበት ማለት አይደለም ደስ ይበለው ሲል ነው።

፲፪. እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐደጐደ እግዚአብሔር አንጐደጐደ ውስተ ሰማይ ወዐርገ ይላል። እግዚአብሔር በሳሙኤል ጊዜ በሰማይ ድምፅ አሰማ ልዕልናውን ገለጠ። ሳሙኤል በመሴፋ ጉባዔ ሠርቶ ሲያስተምር ኢሎፍላውያን በጠላትነት ተነሱባቸው። ጸሲ ወኢታርምም በእንቲአነ አሉት።

መሐስዐ እጣሊ ሠውቶ ቃለ እግዚአብሔር ጠየቀ መብረቅ ነጐድጓድ አሰምቶታል። ወአንዙ ይትቃተልምሙ። ወዲያው አሰራኤል ድል አድርገዋል። ጻድቅ ሳሙኤል ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ይገዛል።
ወይሁቦሙ ኃይለ ለነገሥትኑ። ለነገሥት ለሳአል ለዳዊት ኃይልን ይሰጣቸዋል።
ወያሴዕል ቀርነ መሲሑ። ይልቁንም የዳዊትን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ይልቁንም አለ። አንግሥ ለነ አንግሥ ለነ እያሉ ቢዘበዝቡት ዘመነ መሳፍንት ላይፈጸም ዘመነ ነገሥት ላይደርስ ንጉሠ መወት ላያልን አንግሦባቸዋል። ኢያጠፍአ ምስፍና ወምልክና እምአባሉ ለይሁዳ ተበሉ ትንቢት ከተነገረለት ሉባዔ ከተቆጠረለት ነውና።
አንድም እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐደጐደ። እግዚአብሔር በዳዊት ጊዜ በሰማይ ድምፅ አሰማ ልዕልናውን ገለጠ።

ታሪክ ዳዊት በነገሠ ጊዜ ኤሎፍላውያን በጠላትነት ተነሱበት ልሸሽ ልዋጋ? አለው አስከ ቀላውትሞን ሽሽ ከዚያ በኋላ መብረቅ ነጐድጓድ አሰማሃለሁ ዙረህ ግጠም ድል ታደርጋለህ ብሎታል።
ወውእቱ ጻድቅ ይኴንን አስከ አጽናፈ ምድር። ዳዊት ከዳን አስከ ቤርሳቤህ ይገዛል።
አንድም እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐደጐደ።
በ፵ ቀን ሰማየ ሰማያት ዓረገ።
ወውእቱ ጻድቅ ይኴንን አስከ አጽናፈ ምድር። ጻድቅ ክርስቶስ ጽንፍ እስከ ጽንፍ /ከአድማስ እስከ አድማስ/ ይገዛል። እኛ ባወቅን እስከ አድማስ ከዚያ ወዲያ አሉ ባወቀ።
ወይሁቦሙ ኃይለ ለነገሥትኑ። ለሐዋርያት ኃይልን ልጅነትን ይሰጣቸዋል። ነገሥት ይላቸዋል ሐዋርያትን። ነገሥታት ዓይን በፍላት እጅ እግር በስለት እንዲሰሩ እንዲቀጡ ዐይነ ኅፍስ እደ ኅፍስ ይነሳሉ።
ነገሥታት ርስተ ጉልት እንዲተክሉ ሰማያዊ ርስት ይተክላሉ።

www.zeyeneta.com

ወያሴዕል ቀርነ መሢሑ፡ ቀርነ መሢሕናሁ ቢል የክቡርነቱን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል።
ቀርነ መሢሑ ቢል፡ የጴጥሮስን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል።

፩. ጸሎተ ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ

ሕዝቅያስ ማለት አዚዝ ፅኑዕ ኃያል ማለት ነው። አንድም አንበሳ ማለት ነው። ኃያል ካለው ይጣላል።

ወእመ ፲ቱ ወ፬ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ዐርገ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ በአህጉረ ይሁዳ አሰ ሠን ቅስር፡ ጥቅምም ይላል። ሕዝቅያስ በነገሠ በ፲፱ ዓመት ለናክሬም ዘምቷል፡ ሕዝቅያስ በነገሠ በ፮ ዓመቱ ፲ሩ ነገድ ተማርከዋል። ፲ሩ ነገድ በተማረኩ በ፲ ዓመት ለናክሬም ዘምቷል። ሰለምን ዘመተ ቢሉ ባሰጌ ገንዘቡን ለከፈለ አያዝንም ባልንጀራው ለቀረ ነው እንጂ እንዲሉ። የ፲ሩ ነገድ ንጉሥ ሆሴዕ ወልደ ኤላ አባትህ እኛን ማርኮ ንጉሠ ነገሥት ተባለ። አንተስ እነዚህን ማረክህ ንጉሠ ነገሥት አትባልም? አለው። አንድም አራሱ በአባቱ ተንቦ፡ አንድም ጌታ በ፮ቱ ነገድ ቢያዝን እንዲዘምት አደረገው። ይኸውም ሊታወቅ ሚካኤል በነጭ በግ ተመስሎ እየመራ ለኪሶን አደረሰው። ለኪሶን ሊደርስ ተሠወረው።

ቦኑ ግልፎ ዘያድኅና ለኢየሩሳሌም በዝሙ ረሰያክሞ ለሰማርያ ከማሁ እራስያ ለኢየሩሳሌም ወለኮሰ ኀበረ ጣያት፡ ብሎ አግዚአብሔርን ጣያት ብሎ ሰደበ። መልአኩ ሰያፋን መጣ በታየው በ፩ ቀን ሌሊት ፲፰ አልፍ ከአምስት ሺ /አንደ መቶ ሰማኒያ አምሰት ሺህ/ ሠራዊት አልቆበት አድሯል። ይህ ቅስ አበጋዙ ነው። እርሱ /ለናክሬም/ ግን ወዘይኄልቅም ሕፃናት ይላል። ሕፃናት የሚቆጥሩት ሯም ፮ም ሆኖ አጋንንት የፈረስ የሠረገላ ድምፅ እያሰሙት ነነዌ ወርዶ ወአዝ ይሰግድ ውስተ ቤተ ሊድራክ አምላኩ፡ ቀተልም አድራማሌክ ወሶርሶር ደቂቁ። ያን ሁሉ ሠራዊት አስጠፍቶ በማን ፊንታ ሊነግሥ መጥቶአል ብሎው ተቀብሰው ገድሰውታል። ሰለምን ነነዌ ወርዶ እንዲሞት አደረገ ቢሉ በኢየሩሳሌም የመምላኬ ጣያት ደም አይፍሰስባት /አይፈሰባትም/ ብሎ። ምነው ሠራዊቱስ መምላክያነ ጣያት አይደሉም? ቢሉ በሱ ይፀናበታል /ይፀናል/ አጋንንት መከራ

www.zeyeneta.com

ደፅኑበት ብሎ የፈረስ የሠረገላ ድምፅ እያሰሙት የጣዖቱን ደካማነት ለማጠየቅ። ነቢዩ ተናግሮበት ነበርና።
እራስዮ ሰሰብኩከ መቃብሪከ ብሎ።

ወውእቱ እሚረ ደወየ ሕዝቅያስ ወበጽሐ እስከ ለሞት ይላል። በዚያ ወራት ታመመ ስሞት ደረሰ አሁን ጠላት ጠፋሰት አሁን ታመመ እስ እንደምን ነው ቢሉ። ነቢያተ ሐሰት ተነሥተው ድንግል የተባለች ኢየሩሳሌም ናት የአሕዛብ የፈረሳቸው ኮቴ ደልረገጣት አለንጋቸው ያልጮኸባት። ወልድ የተባልህ አንተ ነህ አሉት። አሆን ይሆናል አለ። ከዚህ የተነሳ ታመመ ይህሰ ዳኛው ሳይለወጥ ሸንጎው ሳይመለጥ አንዲሰ ይህን የተናገረ ኢሳይያስ በዘመኑ እሰ አይደለም ይሰዋል ብሎ ሕገ ሰብኅብን በንጉሥ ታመመ። ከሕገ ሰብኅብ ሳልለይ አንዲህ ያለ ሥራ የተሠራልኝ ከሕገ ሰብኅብ ብለይ አንዱት ያለ ሥራ ይሠራልኝ ብሎ ከሰ ምናሴ ከምናሴ አመቤታችን ከአመቤታችን ጌታ የሚወለድ ነውና። ሰዚህም አይታመምም የሕጋውያን ሟ ሲሆን የመነኮሳት ጅ ነው ኩበራቸው ብሎ ቢመካ ታመመ። እንደኔ ያለ ንጉሥ የሌሊት ግሥጋሤ የቀን ዘሰሳ /አጥር/ ሳይመታው ጠላቱን የሚደጠፋ ወዴት ይገኛል ብሎ ቢመካ ታመመ።

ኢሳይያስን ከመዝ በሎ ስሕዝቅያስ ንጉሣሙ ለሕዝብየ ሥራዕ ቤተክ እስመ አንተ ትመውት ወኢተሐዩ ሰሰው አለው። ሄዶ ነገረው። መዞር ቢሳነው ክነአልጋው አዘሩኝ ብሎ ፊቱን ወደ ቤተ እግዚአብሔር መልሶ አለቀሰ።

ተዘከር እግዚኦ ዘከመ ሖርኩ ቅድሜከ በጽድቅ ወበርትዕ ወበፍጹም ልብ ገበርክዋ ለሠናይት አለ። ጌታ የልብን መመለስ እንጂ ብዝኀ ጸሎት አይሻም /አያሻውምና/። ወበጽሐ ኢሳይያስ ማዕከለ ዐፀድ ይላል። ንጉሡና ሲቀ ካህናቱ በአንድ ወጥተው ከድቱ ከጬቱ ቆመ ብእሲ ሲደርሱ የሚለያዩበት አለ። ከዚያ ሲደርስ ተመየጥ አለው። ከመዝ በሎ ለሕዝቅያስ ንጉሣሙ ለሕዝብየ ሰማዕኩ ጸሎተከ ርኢኩ እንብዐከ ወተሐዩ እምደዌከ ወእስከ ለሱስ ዕለት ተዐርግ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አለው ሄዶ ነገረው በምንት እእምር አለ።

ናሁ ይወርድ ጽላሎት ዲበ ፲ቱ መዓርጋት። ፲ኛውን እርከን ጥላ አልብሶታል። ለእመ ይንብእ ፀሐይ ድኅሬሁ ፲ተ ማዓርጋተ። ተመልሶ ፀሐይ ቢሆን አወቅ አለው። አባቱ አካዝ የሠራው ፬ ግንብ ነበር። የቤተ መቅደስም ነው ይላሉ ኢይፈቅድ ዘንተ ትእምርተ። ይህንስ እኔና አንተ ብቻ እውቀነው እንቀራለን ያለኛል።

እመሰ ይትከሀል፡ የሚደረግልኝስ (የሚቻልስ) ከሆነ፡

ሰይባእ ፀሐይ ድኅሬሁ ዲበ ፲ቱ መዓርጋት። ሠርክ ሁኗል ፲ሩን ኬክሮስ ተመልሶ ዘጠኝ ይሁንልኝ አለ።

ይኩን ከመ ትቤ እሰው። ተሰዓት ሆኗል። እንድም ጽላሎት ያለው ፀሐይ ነው። በግብሩ ሠርክ ሆኗል ተሰዓት ቢሆን አወቅ አለው።

ኢይፈቅድ ዘንተ ትእምርተ። ይህስ ያንሰኛል።

እመሰ ይትከሀል፡ የሚደረግልኝ (የሚቻልስ) ከሆነ።

ሰይግባእ ፀሐይ ድኅሬሁ ፲ተ መዓርጋተ። ፲ሩን ወደ ኋላው ትቶ ፱ ኬክሮስ ተመልሶ ፫ ሰዓት ይሁንልኝ አለ።

ይኩን በከመ ትቤ አለው። ፫ ሆኗል። ያን ጊዜ መሮዳህ የሚባል የባቢሎን ንጉሥ ነበር። ዛሬ እንዲህ የሆነበት ምን ቢሆን ነው ብሎ ጠየቀ /እንዲህ ያለ ሥራ የተሠራበት ምንድን ነው/ አለ። እንዲህ ያለ ደግ የአሰራኤል ንጉሥ ከደዌው የተፈወሰበት ቀን ነው አሉት። ለዚህስ ሲገብሩለት ሲቀቅሉለት ይገባል ብሎ ወፈነወ መሮዳህ በልዳንሃ ወልደ በልዳዳን መጻሕፍተ ወተናብልተ ዘምስለ እምኃ ብዙኅ እንዲል ገብሮለታል። እምጽኡ ፍራ በሰለ ቆጽሰ በሰለ ደመ በሰለ እዕቀ በሰለ። ሁሉም አዕቀ ባለው ይክታል /ይካታተል/ ይህን እምጥታችሁ ቅበው ህበጦ ለእግዚአክሙ ብሏቸዋል።

ወናሁ ወሰኩከ ፲ተ ወፅተ ክራማተ በዲበ ክራማቲከ አለው። የሱስ ቢመካ ነው ተኽቶ የነበረ ቢሉ የሱን ጨርሶታል። የሱስ እልቆ ነበር ቢሉ የሰናክሬምን ደርሶታል።

እመ ደወየ ሕዝቅያስ ወሐይወ እምደዌሁ። ሕዝቅያስ በታመመ ጊዜ ከደዌውም በተፈወሰ ጊዜ የተናገረው ነገር ይህ ነው።

www.zeyeneta.com

፩. አንሰ እቤ በኑን መዋዕልየ። ባለ በዘመኔ የማይገባ ነገር ተናግሬ ማለት ዕድሜዬ ይጠር ብዬ
ውስተ እናቅጸ ሲኦል ጎደጉ ዘተርፈ ዐመትየ። የቀረው ዘመኔን በመቃብር እጣሁት ብዬ ነበር፡
ወእቤ ኢይሬኢ ሰብእ እምአዝማድየ። ከዘመዶቼ ሰው አያለሁ አላልሁም ነበር፡
ወጎንልኩ ዘተርፈ ሕይወትየ። የዘመኔን ቅሬታ ሰመቃብር እጣሁት ብዬ ነበር።

፪. ወጽእት ወጎለፈት እምኔየ። ነፍሴ ከሥጋዬ ተሰደደት ሐዲኛ ብዬ ነበር።
ከመ ዘየጎድር ወይተክል ደብተራሁ፡ ከመ ዘይተክል ደብተራሁ ይዱረር ወየጎድር ሲል ነው። ድንኳን ተክሎ ራቱን ተመገበ እድሮ ያ ድንኳኑን ነቅሎ እንዲሄድ።
ከማሁ ኮነት ነፍስየ በሳዕሊየ። ነፍሴ ከሥጋዬ ተሰደደት ሂደች ብዬ ነበር።
ወከመ ዕጡፊ ፀምር ዘአልጸቀ ይገምድዎ፡ ዕጡፍ፡ ፀምር ሲል ነው። ሊቆርጡት የቀረበ ሸማ ዘለሰ /ዘነፍ/ ብሎ ወደጉድጓድ እንዲወድቅ ሥጋዬ በመቃብር ወደቀች ብዬ ነበር። እንድም ቁጢቱ /ዘሀው/ ከሳይ እንዲቀር ነፍሴ ከሥጋዬ ተሰደደት ሂደች ብዬ ነበር።

፫. ወውእተ እሚረ ተሀወኩ ከመ አንበሳ አስከ ይጸብሕ። አንበሳ እስኪጠባ /እስኪነጋ/ ድረስ ምግብ በመሻት እንዲታወክ በዚያ ወራት ታወክሁ እንዘሳ ርሁብ ወተኵላ ጽሙዕ ይለዋል።
ከማሁ ተቀጥቀጣኒ አሰፅምትየ። ሰውነቴ በመከራው ቆሰለች /ኅሰቆለች/።
እኅዘኒ እምነግህ እስከ ሠርክ። ከጧት እስከ ማታ ያዘኝ ቀን ቀን ይጸናበት ነበር። እንድም ከሮቱ ቀን አንዱ ቀን ጸንቶበት ነበር።

፬. ወከመ እድገ መረብ ከማሁ እነቱ። እንደ ምድረ በዳ እሀያ እመሃለሁ ይህ የበዳ /የምድረበዳ/ እህያ ሲርበው ከተራራ ወጥቶ ይሰሃል። ነፋስ መዓዛ ሳዕር መዓዛ ማይ ያሸተዋል። ሄዶ በልቶ ጠጥቶ ስፍራውን አይለቅም።

ወከመ ርግብ እነብብ። እንደ ርግብ እናገራለሁ ይህች ርግብ የምትናገረው በጉሮሮዋ ነው እሱም ውጋቱ አሳናግረው እያለ።

፭. ደክማ እዕይንትየ ወሰዕንኩ ነጽሮ ኀበ እግዚአብሔር ለማየ። ዓይኖቼ ፊዘዙ ወደ ሰማይ ወይም ወደ እግዚአብሔር አትንቡ ማየት ተሳነኝ።

፮. ተሣሃለኒ ወአእትት ሕማማ ለነፍስየ። ይቅር በለኝ ሰሰውነቱ ደዌዋን እርቅላት።

፯. እግዚኦ በእንተአሃ አቤለከ። ስለአሷ እንዲህ አልሃለሁ።
ወአንሣአካ ለነፍስየ። ሰውነቱን ከደዌዋ ፈወስካት አልሃለሁ።

፰. ተፈሣሕኩ ወሐየኩ። ሐየኩ ወተፈሣሕኩ ይላል። ከደዌዬ ተፈወስኩ ወተፈሣሕኩ በዚያው ደስ አለኝ። እንድም ወተፈሣሕኩ በሞተ ለነክራም ደስ አለኝ ወሐየኩ። ከደዌዬ ተፈወስኩ። ወተሣህልካ ለነፍስየ ከመኢትትንሥል። ነፍሴ በመቃብር ፈርሳ በለብሳ እንዳትቀር ሰውነቱን ይቅር አልካት።
ወገደፍከ ድኅሬየ ኵሎ ኀጢአትየ። ኀጢአቱን ሁሉ በኋላዬ ጣልክ በኋላ የጣሉት እንዳይታይ እንዳይታሰብ አላሰብክበኝም።

፱. እስመ አኮ አለ ውስተ ሲኦል ዘይሴብሐከ። በመቃብር ያሉ የሚያመሰግኑህ አይደለምና።
ወአኮ አለ ይመውቱ ዘይባርክከ። የሞቱት ለሥጋ የሚያመሰግኑህ አይደለምና።

፲. ወኢይሴፈዉ ኀሀለከ አለ ውስተ ሲኦል። በመቃብር ያሉ ሰዎች ይቅርታህን ተስፋ አያደርጉምና። ዝናም ሰዘር ጠል ለመከር ይሰጠናል ብለው።
ሕያዋን ክመ ይባርኩከ ከመ እነ ይእዜ። እኔ እንዳመሰግንህ ሕያዋን ያመሰግኑሃል እንጂ።
ዛቲ ተግሣጽ ትኩነኒ እምዮም እግዚእ። ይቺ ተግሣጽ እቤቱ ትሥራኝ ትቅጣኝ ትዝ ትዝ ትበለኝ አልደግምም። እንድም ሕዝቅያስ ቢጨንቅህ ትቀባጥራለህ እንጂ የቀደመ ግብርህን መች ትተዋለህ ትለኝ እንደሆነ እቤቱ ይቺ ተግሣጽ ትሥራኝ ትቅጣኝ ትዝ ትዝ ትበለኝ አልደግምም።

www.zeyeneta.com

እነግር ጽድቀከ በጻገናየ። ባለ በዘመኔ ሁሉ ቸርነትህን እናገራለሁ።

እገብር ደቂቀ ይላል አብነት።

፲፩.ወትረ እሴብሐከ ወእዜምር ለከ። ዘወትር እንተን አመሰግንሃለሁ ለአንተ ምስጋና አቀርባለሁ።

በኩሉ መዋዕለ ሕይወትየ። ባለ በዘመኔ ሁሉ።

በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር። በቤተ እግዚአብሔር ሆኜ።

፮. ጸሎተ ምናሴ ነቢይ

ምናሴ ማለት መርስኤ ኀዘን ማለት ነው፡ የሕዝቅያስ ልጅ ነው። አባቱ የሠራውን አላውርሷል። አባት ቀፎ ቢያበጅ ልጅ ሞገዝ መንሳዛ /የቀፎ ማር የሚበላ አውሬ/። ይዋጅ እንዲሉ ሥዕለ ንስር አቁሟል መንቅሐ /መንሥኤ/ ምውት ነህን አሥነሥኂል። ልጁን ለጣዖት ሠውኂል። አሳይያስ ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ብሎ ቢናገር በኩሳብ አሰቅሎ በመጋዝ አስተርትሮ ገድሎታል /አስገድሎታል/ ከዕሰታት አንድ ቀን ለአደን ዘወጣ ዘንድ አስበቀፈት፡ ሆኒሐርድን፡ አስራዶን፡ ንውስ ሰናክራም ይለዋል። አስልሎ ይዞ ወስዶ በበረት ቀፎ አግብቶ ቀን ዋዕየ ፀሐይ ከሚጸናበት ይጥለዋል ሌሊት ውርጭ /ብርድ/ ከሚጸናበት ይጥለዋል፡ ከዚያው ሆኖ ንስሓ ገባ። መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከነቀፎው ተሸክሞ ወስዶ በአንቀጸ ኢየሩሳሌም ጣለው ለነቢያት ለካህናት ንጉሣችሁ ከዚያ አለላችሁ ሄዳችሁ ልብሱን አልብሳችሁ አምጡት አላቸው። ሄደው ልብሱን አልብሰው አመጡት። ዘመነ መንግሥቱ ሃጅ ዘመን ነው። ሃውን ጣዖት እያመለከ ፎቱን ዘመን ያንን የብረት ቀፎ ከፊቱ አድርጎ እያለቀሰ ገዝቷል። በሚሞትበት ጊዜ ዳዊት ሰሎሞን በተቀበሩበት አትቅበሩኝ በገነተ ዖዛ ቅበሩኝ ብሏቸዋል። እንተ ይእቲ ምቅዋመ እእዱን ይላታል።

ነቢይ ንጉሥ ይላል። ምናሴ የተናገረው ነገር ይህ ነው።

፩. እግዚኦ አጋዜ ኵሉ ዓለም።

ይህን ዓለም የምትገዛ አቤቱ፡ እንድም ይህን ዓለም እንደ ጽና እንደ ጥላ አንጠልጥለህ እንደ አንቁላል ጨብጠህ የያዝክ አቤቱ አምላኩሙ ለአበዊነ። የአባቶቻችን ፈጣሪ፡

ለአብርሃም ወለያስሐቅ ወለያዕቆብ። የአብርሃም የያስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ አቤቱ።

፪. ወለኵሉ ፍሬሆሙ ለጻድቃን።

የልጅነቸው ፈጣሪ አቤቱ።

፫. ዘገበርከ ሰማየ ወምድረ ምስለ ኵሉ ዓለሞሙ። ሰማይና ምድርን ከነለሞኒቸው /ከነለማቸው/ ጋራ የፈጠርክ አዙቱ ሰማይ ከነንሡ ምድር ከነልብሱ አንዲሉ ሰማይን ከዐሐደ ከፈጠረ ከዘዋኩበት ምድርን ከአዘርዕት ከአትክልት ጋራ።

፬. ዘገሠጽካ ለባሕር በቃለ ትእዛዘከ። ውቅያኖስን በቃልህ የገሠጽካት።

እስከ ዝየ ብጽሐ ወኢትትዐደዊ አምዝየንኪ ዳዕሙ ይትከበስ ማዕበልኪ ብለህ።

በአጸከ ቀላያተ ወንተምክ ኀሩመ። ቀላያተ ውቅያኖስን በብሒሎትህ የዘጋህ ኀሩም ብሒሎትን በዚያ የወሰንክ አቤቱ።

፭. ውእቱኒ በስዙሕ ስምከ። ይኸውም ከዙር በሆነ በስምህ ነው አንዲህ ያደረግክ አቤቱ።

አንድም ዘገሠጽካ። ባሕረ ኤርትራን ከሦስት ከአራት ከነፍስህ በቃልህ የገሠጽካት አቤቱ

በዐጸከ ቀላያተ። ኤርትራን በፈርዖን የዘጋህ ኀሩም ፈርዖንን በዚያ የወሰንክ አቤቱ

ውእቱኒ በስዙሕ ስምከ። ይኸውም ከዙር በሆነ በስምህ ነው። አንዲህ ያደረግህ አቤቱ

አንድም ዘገሠጽካ። ባሕረ ገሃነምን በቃልህ የገሠጽካት አቤቱ

አንድም በአጸከ። ቀላያተ ገሃነምን በዲያብሎስ የዘጋህ ኀሩም ዲያብሎስን በገሃነም የወሰንክ አቤቱ ውእቱኒ እይለውሃም።

፮. ዘኵሉ ይርዕድ ወያድሰቀልቅ አም ቅድመ ገጸ ኃይልከ። ከገጸ መሀትህ የተነሳ ሁሉ የሚርድ የሚንቀጠቀጥ አቤቱ።

፯. እስመ አልቦ ጽንፍ ለዕበየ ስብሐቲከ። ለጌትነትህ ጽንፍ፡ ዳርቻ የለውም።

፰. ኀሩም መቅሠፍተ መዐትከ ላዕለ ኀጥኣን። ፈርደህ የምታመጣው መቅሠፍት ኀሩም ነው።

www.zeyeneta.com

አልቦ ጕልቍ ወአልቦ መስፈርት ለሣህለ ትእዛዝከ። እዝዘሀ ለምታደርገው ይቅርታህ ሥፍር ቍጥር የለውም።
አስመ አንተ እግዚአብሔር ባሕቲትከ ልዑል። ገናና ጌታ አንተ ብቻ ነህና መሐሪ ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ሣህል። መዓትህ የራቀ ቸርነትህ የቀረበ አንደም መዓትህ ያነሠ ቸርነትህ የበዛ ቸር ነህ።

፲፪. ወመስተመይጥ ላዕለ ጌጋዮሙ ለዕንሰ አመሐያው። የሰውን ኃጢአት አይተህ እንዳላየህ ከመዓት ወደ ምሕረት የምትመለስ አንተ ነህ።

፲፫. ይእዜኒ እግዚኦ አምላኮሙ ለጻድቃን። ይእዜኒን ያስበዘቀል። የጻድቃን ፈጣሪ አቤቱ
አስመ አኮ ለጻድቅ ዘገበርኮ ለንስሓ። ንስሓን የሠራኸው ለጻድቅ አያደሰምና። አኮ ለአዘርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ አለኢአበሰ ለከ ኪያከ ሲል ነው። አንተን ላልበደሉ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አያደለምና

፲፬.አላ ተመየጥ ንስሓ ዚአየ ለነኃጥኣ። ለኃጢአ ነው እንጂ ለጻድቅ አይደለምና ይእዜኒ ተመየጥ። ባሪም ንስሐዬን አደተህ ከመዓት ወደ ምሕረት ተመለስ።

፲፭.አስመ አበስኩ እምኑልቈ ኖኅ ባሕር። ከባሕር አሸዋ ይልቅ በድያለሁና ወብዙኀ ኃጢአትየ። ኃጢአቴም ብዙ ነውና።
አኮ ድልወት ሊተ እንቃዕዱ ወእርአይ ኑኖ ሰሰማይ። ወደ ሰማይ አቅንቼ የሰማይን ምጥቀቱን ላይ አይገባኝም። ከተበደለ የበደለ ያፍራልና።
እምብዝኀ ጌጋይየ። ከኃጢአቱ ብዛት የተነሣ
ሠራሕኩ በመዋቅሕተ ሐሢን። በግር ብረት ደስምኩ።
ከመ አስሐታ ለነፍስየ እምኀጢአትየ። ለውነቴን ኃጢአት ከመሥራት አሳርፍት ዘንድ።
ወበዝየኒ ኢተስሕትኩ። በዚህም ሆኜ ኃጢአት ከመሥራት አላረፍኩም ወየው ከዚህ ወጥቼ ጠላቴን እንዳደረገኝ አድርጌው እያልኩ።
አስመ ወሀኩ መዓተከ። መዓትህን አነሳስቼአለሁ።
ወአኩየኒ በቅድሜከ ገበርኩ። በፊትህ ክፉ ሥራ ሠራሁ።

፲፫.እንዘ አዐቅብ ከንቶ መአስዝኀ ዘኢይበቍዐኒ። ከንቱ ጣዖትን ስጠብቅ የማያረባኝ የማይጠቅመኝን ነገር አበሳሁ።

፲፰.ወያአዜኒ አሰግድ በብረከ ልብየ። ዛሬም ታሥራአለሁና በአብራክ ሥጋ መስገድ ቢሣነኝ በአብራክ ልብ አሰግዳለሁ።
እንዘ አስአል ምሕረተ ዘአከ። ቸርነትህን እየለመንኩ።

፲፱. አበስኩ እግዚኦ አበስኩ። አቤቱ በደልኩ በደልኩ።
ወንጠአትየኒ እትአመን። አምናለሁ ሠርቼ አልሠራሁም አልልም።

፳.እትመሐሰል ወአስአለከ አለምንሃለሁ
ተሠሃለኒ እግዚኦ ተሠሃለኒ። አቤቱ ይቅር በለኝ ይቅር በለኝ።
ወኢትመጥወኒ ለንዐእትየ። በንጠአቱ ለመጣ መከራ /ፋጅ/ እትስጠኝ እንደ ሰጠሽኝ አትቅር።

፳፩. ወሰዓሰምኦ ኢትዕቀብ ሊተ እዘይየ። ኃጢአቱን አንድ ጊዜ ብትጠብቅ ለዘላለሙ አትጠባበቅብኝ /አትጠብቅብኝ/።
ወኢትትበቀለኒ በማዕምቅቲሃ ለምድር። በምድር በየልቲ አትበቀለኝ በፋርስ በመቃብር በሲኦል።
እንተ እግዚኦ አምላኮሙ ለአለ ይኄስሑ። ንስሓ ለገቡ ሰሠች ፈጣሪያቸው የምትሆን አቤቱ።
ያስተርኢ ኀሩትከ በላዕሌየ። ቸርነትህ በኔ ለሌላው ይገለጥ።
ሊተ ለኔ ይገሥጥ።
ከመ አንዘ አኮ ድልወት ሊተ አድኅንከኒ በብዝኀ ሣህልከ።
መዳን የማይገባኝ ስሆን በይቅርታህ ብዛት እንዳዳንከኝ
ያስተርኢ። አንድም አንዳዳንከኝ መጠን

፳፪. አሴብሖከ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ።
በሚመጣው ዘመን ሁሉ አመሰግንሃለሁ።
አንድም በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ። ባለ ዘመኔ ሁሉ በ፮ቱ በ፲፪ቱ በ፷፬ቱ ጊዜያት አመሰግንሃለሁ።
አስመ ኪያከ ይሴብሑ ኵሉ ኃይለ ሰማያት። ሊቃነ መላእክት አንተን ያመሰግናሉ /ያመሰግናሉና/።
ወለከ ስብሐት ሰዓለመ ዓለም። ለዘላለሙ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

www.zeyeneta.com

፯. ጸሎተ ዮናስ ነቢይ

ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው። ወዘለሙ አሐዱ ወልደ ብእሲት ዘስራጵታ ያሳል። በሕዛንነቱ ሞቶ ኤልያስ አስነሣው የኤልያስ ደቀ መዝሙር ሆኖ አደገ ሀብተ ትንቢት ተሰጠው ነነዌ ወርደህ አስክ ሠሉስ ዕለት ትትገፈታዕ ነነዌ ሀገር በነድ ብለህ አስተምር አለው። አንተ መሐረ ነህ ብትምራችሁ ነዚያ ሐሰት እህል የለም? አለው መሐረ ብሆን ምን ይከሥል ግድ የለም ግድ የለህም/ አለው ይህ ሁሉ አንጂ ነፈቱ ቢያገኝኝ ነው የሚዘገዘገኝ ብሎ ወተነግዮአ ዮናስ እምገጸ እግዚአ ያሳል። ጌታ ከሚያገኘው ቦታ ነብልሎ ሄደ። ርግብ ያለኘው ይህ ነው።

ወተሐሰበ ሐመርሙ ያሳል። መርከብ ዋጅቱ /ለመርከባቸው ዋጋ ለጥቶ/ ተጫነ ማዕበል ሞገድ ተነግባቸው በእብደው እንጂ ነው ብለው ንባቸውን እያነሱ ያነሱ ጀመር። ወዮ የማይልላቸው ሆነ። ከኛ የበደለ ስው አለን? ዕጣ እንጣጣል ብለው ዕጣ ቢጣጣሉ በዮናስ ወጣበት።

ወንነረ ዮናስ ውስተ ከርሠ ሐመር ያሳል። ተኝቶ ሲያንኮራፋ ነበር። ሊቀ ጳጳያው /የመርከቡ ካፒቴን/ ቀሰቅሶ ሁሉ ወደ ፈጣሪው ሲያለቅስ ሲጨነቅ/ አንተ የማታለቅስ የማታዝን ፈጣሪህ ማነው? ነገድህስ ከማነው? አለው። ነገዴም ዕብራዊ ነኝ ፈጣሪዬም ሰማዩን ምድሩን የብሱን ባሕሩን የፈጠረ ፈጣሪ ነው። ይህ መከራ የመጣባችሁ በኔ ነው እኔን ካልጣላችሁ ጸጥ አይልላችሁም አላቸው መጣሉን ተስቅተው ወደ ኋላ ተመለሱ ወዮ የማይልላቸው ሆነ።

ኢትሬሲ ደሞ ለዝ ብእሲ ደመ ጻድቅ ብለው ጣሉት። ዓሣ ዐንበሪ ቀለመው/ ተቀብሎ ዋጠው/ ባሕርም ድርጎዋን ተቀብላ ጸጥ አለች። ሶስት ቀን ወስዶ በአንቀጸ ነነዌ ተፋው እንደ ጸዳ ነለች ቦታ ደርሶ ይህች ሀገር ማን ትጣላለች ብሎ ጠየቀ ነነዌ ትጣላለች አሉት። በፈቃደ እግዚአብሔር መጥቻለሁ ብሎ ከዚያ ገብቶ እስከ ሠሉስ ዕለት ትትገፈታዕ ነነዌ በነድ ብሎ አስተማረ። ሰልምናሶር ነበር ንጉሡ አዋጅ ነገረ ጥጃ ከእናቱ ልጅ ከጡቱ ላይገናኙ አዘኑ። እሱም ኃዘናቸውን አይቶ አዘነ እሳቱ ይቀራል ብሎ።

እሱም ኀዘንክኑ ዮናስ፡ እሳት ባለማዝነሜ አዘንክ? አለው እምን አለ። ይህን ብሎት ተሰወረ። የሸማግሌ ልጅ መታየቱ መቀሳወጡ እንዲሉ እንዲህ ማለቱ ሊያዘንም ነው ብሎ። እንደ ካይላ ሜዳ ካለ ወጥቶ ጎጆ ሠርቶ ተኛ። ቢነቃ /ቢነሳ/ ቅል በቅሳ ጎጆውን አልብሳለት ሰውነቱን ደሰ ብሎት አገኘ። መልካም ብሎ ሁለተኛ ብንን ቢል ያችን ቅል ትል/ ቆማምጦ/ ቆራርጦ/ በልቷት። ሀሐይ ራሱን መትቶት አዳኒት የምትባል ራስ ጥልጠት ቀፎን ሰፕር ውጋት ተነስቶበት አገኘ እንዲያውም ነቢየ ሐሰት እየተባለ ከመኖር መሞት ይሻላል አለ።

ኀዘንክኑ ዮናስ በእንተ ካቲ ሐምሐም ዘኢተክልካ ወዘኢስቀደካ ዘሌሊተ በቀለት ወሌሊተ ማስነት። ሌሊት ያለው መዓልቱን ነው። የሌሊት ሥራ ስለተሠራበት። እንደም ሰኖ ለማክለሞ በቅሳ አድራ ማክለሞ ለረቡዕ ደርቃለት አምን አለው። እንሰኑ ኢያምሕካ ለነነዌ ሀገር ዐብይ ዘሀለዉ ውስቴቱ እለ ይበዝኑ እም ፲፪ ወቄቶየ እለ ኢፈለው የማኖሙ ወጸጋሞሙ። ከመቶ ሃያ ሺሕ የሚበዙ ከሙቱ ሃያ ሦስት ሺህ የሚያንሱ ቀኝ ግራቸውን የማይለዩ ሕፃናት ላሉባት ለነነዌ ማዘን አይገባችኁም አለው።

እንድም ቀኝ ግራ ብለው የሚወረውሩ አርበኞች ላሉባት ለነነዌ ማዘን አይገባችኁም? አለው። እውነት ነው ጌታዬ ይገባል አለው። ይህችም ነነዌ ወምዕዋደ ቅጽራ እምእንቀጽ እስከ እንቀጽ ምሕዋረ ፫ቱ ዕለታት ይላታል፡ የሶስት ቀን ጎዳና ናት። ነቢየ ሐሰትም እንዳይባል ረቡዕ በሠርክ እንደ ደመና እንደ ደመና ሆኖ ታይቶ ተመልሷል ይህም ምሳሌ ነው። ዮናስ የወልደ እግዚአብሔር፡ ከርሠ ዓንበሪ የመቃብር፡ ከዚያ ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት አድሯል። ጌታም በከርሠ መቃብር ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት አድሮ ተነሥቷል። ይህንንም እስከ ሠሉስ ዕለት ያለውን ጠቢት በሶስተኛው ትውልድ ትጠፋለች ማለት ነው ብሎ ተርጉሞታል። በእስራኤል የቆጠሩ እንደሆነ በኢኮንያን ተማርከው በሰላትያል ተስፋ ሰምተው በዘሩባቤል ወጥተዋል። በአሕዛብ የቆጠሩ እንደሆነ በናቡከደነፆር ተማርከው በኢዮርማሮዴቅ ተሰፋ

www.zeyeneta.com

ስምተው በብልጣሶር ወጥተዋል። ነቢዩ ዮናስ የተናገረው ነገር ይህ ነው።

፩. ጸራሕኩ በምንዳቤየ ጎበ እግዚአብሔር አምላኪየ። በመከራዬ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኼ ለመንሁ

፪. ወሰምዐኒ በውስተ ከርሠ ሲኦል። በባሕር ውስጥ ሆኜ የሰመንኩት ልመናዬን ሰማኝ። አንድም በባሕር ውስጥ ባለ በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ የለመንኩት ልመናዬን ሰማኝ።
ወሰምዐኒ ቃልየ። ልመናዬን ሰማኝ።
ወገደፈኒ ውስተ ማዕምቀ ልበ ባሕር። ማዕምቅ ልብ የተደራረበ ነው። በጥልቁ ጣለኝ
ወአፍላግኒ ዐጥቡኒ።
ፈላሾች ከበቡኝ ነቢይ ነውና በላይ የሚሄደውን ያያል።

ከዚያው ውስጥ የሚገባውን።
ኵሉ ማዕበልከ ወሞገድከ አንተ ላዕሌየ ነለፈ። ማዕበል ሞገዱ ተመላለሰብኝ።

፫. ወአቤ ተንጉልኩኑ አንጋ አምቅድመአዕይንቲከ። ከባለሟልነትህ እንደተለየሁ ቀረሁ ይሆን አልኩ።
ሀሉኩኑ እርአይ ጽርሐ መቅደስከ።
ከዚህ ወጥቼ ቤተ መቅደስን እይ ዘንድ አለኝ? ይሆን አልኩ።

፬. አሕዘዘኒ ማይ እስከ ነፍስየ። ሰውነቴን እስከ ማጥፋት ደርሶ ውሃው አነዘዘኝ ሲጥሉት እንዘዞታልና
ወቀላይኒ መልዐኒ። ውሃው መላብኝ።
ናሁ ርእስየ ውስተጥንቃቃተደብር። ራሴ በምሽጉ/በባሕር እዝዋሪ /አለ። እንደ ንዋየ ውስጥ ነው። ንቅዓታተ ደብር ቢል በክፍልፍሉ አለ። ነቢይ ነውና በተራራና በተራራ መካከል ሲወስደው ያያል።
ወወረድኩ ውስተምድር ከመመልሕቅ ታሕተ። መልሕቅ ጨጥሉት ወደ ታች እንዲወርድ እንደዚያ ወረድኩ።

፭. ትዕርግ ሕይወትየ ዘእንበለ ሙስና ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ። ስውነቴ ጥፋት /ጉዳት/ ሳያገኛት ወደእንተ ትምጣ።

፮. ሶበ ኀልቀት ነፍስየ ተዘከርክዎ ለእግዚአብሔር። ነፍሴ ከሥጋዬ አለይ አለይ /ልለይ ልለይ/ ባለች ጊዜ እግዚአብሔርን በጸሎት አሰብኩት።
ትብጸሕ ጸሎትየ ቅድሜከ ጽርሐ መቅደስከ።
በፊትህ ሆኜ የጸለይኋት ጸሎት ወዳንተ ትድረስ?

፯. አስሰ ዐቀቡ ከንቶ ወሐሰተ ገዳፉ ሣህሎሙ። ከንቱ ጣዖትን የተጠባበቁ ሰዎች ይቅርታቸውን አጡ። አንድም ይቅርታቸው እግዚአብሔርን አጡ። አንድም ገንዘባቸውን አጡ። ሐሰትም ያሰው ጣዖቱን ነው። አንድም ሐሰተ ይላል። በሐሰት ይቅርታቸውን አጡ።

፰. አነስ ምስለ ቃለ ስብሐት በተጋኦኦ አሠውዕ ለከ። በመገዛት ከምሰጋና ጋራ ላንተ መሥዋዕትን አቀርባለሁ።
መጠነ ጸለይኩ በሕይወትየ እዐስዮ ለእግዚአብሔር። በሕይወቴ የጸለይኩትን ያህል በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ አቀርባለሁ። አንድም በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ የጸለይኩትን ያህል ከከርሠ ዓንበሪ በወጣሁ ጊዜ አቀርባለሁ። እንድም መጠነ በዓዕኩ። የተሳልሁትን ያህል እሰጣለሁ። ከዚህ ብታወጣኝ ይህን እደርጋለሁ ብዬ።

www.zeyeneta.com

፭. ጸሎተ ዳንኤል ነቢይ ስብሐት ዘእምአዛርያ

ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው። የዳንኤል እናትና ቤቱ ደቂቅ ካንድ ሆድ ይወጣሉ።። ጻድቃንን ከኃጥአን ጋራ ያለማርካቸዋል። ስለ ምን ቢሉ መከራ ቢበዛ ጸጋ ክብር ይበዛላቸዋል ብለ። ተሹመው ተሽልመው እሰራኤልን ሊጠብቋቸው መከረው አስተምረው ከገቢረ ኃጢአት ከአምልኮተ ጣዖት ሊያድኗቸው። ከምርኮ በኋላ ናቡከደነፆር ጎረዩ ሲተ እምደቂቀዔዋ አለ። ቢቆም የማይታከተውን ጥበብ የሚለማማውን እያያችሁ ምረጡ። መርጣችሁ ፈላስፋ ሕሙግ መብልዕ የሐምግ ልበ ይላልና። ጽሩይ ጽሩይ ምግብ እየመገባችሁ መሐርዎመ መጽሐፈ ወነገረ ፋርስ። መጽሐፈ ወግ ታሪክን። ወነገረ ፋርስ ቋንቋን። አንድም መጽሐፈ ፍልስፍናን። ወነገረ ፋርስ ጥንቆላን። አስተምሯቸው አለ። አስፋኒዝ ይለዋል። ቢትወዳዱ እነዚህን መርጦ አምጥቶ ከፊቱ አቆማቸው። ወወለጠ ለሞሙ ይላል። ስማቸውን ለውጦታል ሲለውጥም በአንጻር በአንጻር ይለውጣል። ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነበር። ብልጣሶር ብሎታል /አለው/ አምኃ ቤል ሲል። አናንያ ማለት በግዕ ደመና ማለት ነበር። ሲድራቅ ብሎታል /አለው/ ጸሐፊ ጸሐቂ ፍንው ትጉሕ ለግብረ ንጉሥ ሲል ነው። አዛርያ ማለት ረዳኢ ረድኤተ እግዚአብሔር ማለት ነበር። ሚሳቅ ብሎታል /አለው/ ሠቃዬ አትክልት አሠናዬ አትክልት ሲል። ሚላኤል ማለት ለምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነበር።

አብደናጎ ብሎታል፡ ገብረ ዳጎን ሲል። አሚሳድ ይለዋል መምህሩ ለሱ ስጣቸው ሀበነ ዘርዓ ምድር አሉት ለለምን ቢሉ ተጸይፈው ዛሬ እኛ የእለላምን አንጀራውን እንድንጸየፈው ጥሬውን እንዳንጸየፈው። ደግሞም በተድላ በደስታ ከተማሩት በመከራ የተማሩት ትምርት ይበልጣልና። ይህስ ዘርዐ ምድር ያለው ምንድን ነው ቢሉ ሽምብራ ይህስ ተድላ ደስታ ይሆናል። ባቄላ ነው።

ለእመ ርእየክሙ ንጉሥ ድግዱጋኒክሙ እምእለ ይሴለዩ አማእደ ንጉሥ ኢይኬንነኒኑ ርእስየ አለ። ከንጉሥ ማዕድ ከሚመገቡ ይልቅ እናንተ ጠቁራችሁ ከሰታችሁ ቢያያችሁ ከታች ባቴን ከላይ አንገቴን አይሠራኝም አይቀጣኝም? አላቸው። ፍትነነ አሥረ መዋዕለ ለአግብርቲከ። አሥር ቀን ፈትነኸን የከላን የጠቆርን እንደሆነ እንዳልከን እንሆናለን አሉት። አሰር ቀን ሙሉ ባቄላ ሲለጣቸው ለነበተ።

ጎየለት ነፍሶሙ ወሠነየት ራእዮሙ እምእለ ይሴለዩ አማዕደ ንጉሥ ይላል። እንደ ብርሌ ጠርተው እንደብርጭቆ አንጸባርቀው አገኛቸው። እኔ ትክላላችሁ ትጠቁራላችሁ ብዬ ነው እንጂ ብሎ ለነሱ የመጣውን እሱ እየተመገበ ሶስት ዓመት ሙሉ ባቄላ ሲለጣቸው ኖረ።

በሶስተኛው ዓመት ንጉሥ እስኪ አምጣቸው ጥበብ ኣመረምራቸዋለሁና አለው። ቢመረምር ወሰበጎሠሠ ንጉሥ በጎቤሆሙ ረከበ ትዕሥርተ እድ እምኩሉሙ ጠቢባነ ባቢሎን ይላል። አስር እጽፍ ጥበብ አገኘባቸው መልካም ነው ተቀመጡ አላቸው። ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ንጉሡ ከሰገነት ላይ ተቀምጦ ሁሉ ሲፈታ ሲታጠቅ አይቶ እኔ ሁሉን እንደ ሰም አቅልጬ እንደገል ቀጥቅጬ ገዛሁት ከኔ በኋላ የሚነሳው ከኔ የበለጠ ይሆን ከኔ ያነሰ? ብሎ አሰበ። ቀን ያሰበውን ሌሊት ያሳየዋል ቀን የለቀሙ ሌሊት ይቅሙ እንዲሉ። ርእሱ ዘወርቅ እንግድዓሁ ዘብሩር ሐቋሁ ዘብርት ቍየጺሁ ዘሐጺን መንፈቀ እግሩ ዘልሕኵት ወዘሐሚን። ሽቅብ ነው ያሉ እንደሆነ እንደ አፍራኔቆ /አፍራኒቆን/ ድንኪን/ ክብ ድንኪን/። ግድም ነው ያሉ እንደሆነ እንደነፍጥ መሸቢያ /እንደ ጥይት ካርታ/ እንደ አልጋ ሽንኮር። እሱ ጣዖቱን ጣዖቱ እሱን ሲመለከት ከረጅም ተራራ የሰው እጅ ላይነካው ደንጊያ ተፈንቅሎ ወርዶ ያን ቀጥቅጦ ደንጊያው ተራራ ሲያህል ተራራው በዓለም ሲመላ አይቷል። ብንን ቢል ጠፋው ለለምን ቢሉ የንጋት እንቅልፍ ነበረበትና። አንድም ራእዩ ግሩም ነውና። የዳንኤልን ክብር ለመግለጽ ሲነጋ ከበላው አብልቶ ከጠጣው አጠጥቶ የሚያኖራቸው ብዙ ማእምራን ጠቢባን

www.zeyeneta.com

ነበሩት። እነዚያን እስጠርቶ ሕልም አይቼ ጠፍቶኝ ሕልሜን ከነትርጓሜው ትነግሩኝ ብዬ አላቸው። ንጉሥ ሥርዓት ለወጥክብን ዮሴፍ ለፈርያን ቢተረጉምለት ሕልሙን ነግሮት ነው። ሕልሙን ንገረን እንተርጉምልህ አሉት ቢጠፋኝ ነው እንጂ አላቸው። ባይሆንም ቀን ስጠን አሉት አይድዑኒ እንበለ ይሕልፍ ጊዜሁ። ይህን ጊዜ ትዝ ትዝ ብሎኝ ሳለ ንገሩኝ ድኅረሰ ትፈጥሩ ካልዐ ነገረ ኂሳማ ልብ ወለድ አምጥታችሁ ይህ ነው ልትሉኝ አያደልምን? አላቸው። የማይሆንላቸው ሆነ እንኪያ ፈረሰ አይደላችሁ አልጋልባችሁ በቅሎ አይደላችሁ አሳስግራችሁ በሰይፍ በላቸው አለ።

ወወጽአ አርዮክ /ያርክ/ ሰያፊ ወአጎዘ ይቅትሎሙ ለጠቢባነ ባቢሎን ይላል። ሁለቱን ሶስቱን እንደነሳላቸው /እንደነሣሣላቸው/ ዳንኤል ፫ቱ ደቂቅ ከስተማ በአፍአ ነበሩ። ዳንኤል ቀረብ ብሎ ይጠይቃል። በይነ ምንት ወጽአ ዝንቱ ፅኑዕ ትእዛዝ እምቅድመ አዕይንቲሁ ለንጉሥ አለው። ኧረ ይህስ ሰአናንተም አይቀርላችሁም ንጉሥ ሕልም አልሞ ሕልሙን ከነትርጓሜው የሚነግረው እጥቶ አለው። እነሱንም አትጨርሻቸው ተዋቸው ሕልሙን እኔ እነግረዋለሁ አለው።

ነገር ግን ቀን አሰጠኝ አለው ገብቶ ከምርኮ ልጆች እንዲህ የሚል እለ አለው። ሦስት ቀን ሰጥቼሀለሁ በለው አለው ሱባዔ ገቡ በሶስተኛው ቀን ተገለጸላቸው። ለዳንኤል ግን ዕለቱን ተገልጾለታል። ሰለምን ቢሉ ጥራ እንበላ ውሀ እንጠጣ በማለት ጸንቶ ይኖር ነበርና። ሰለተገለጸለት ዕለቱን ልውጣ አላለም ዛሬ ሱባዔ የገባ ሰው ነገሬ ከቀናልኝ ብሎ ሱባዔውን ሳይፈጽም መውጣት እንዳይገባው ሰያጠይቅ። በሶስተኛው ቀን ለሁሉም ተገለጸላቸው ሂዱ ንገሩልኝ አለ። ነገሩለት ግባ በሉት አለ ገባ።

ትክልኑ ትንግረኒ ሕልምየ ወፍካራሁ አለው። ይህ ዳንኤል እጥር ምጥን ያለ መልከ መልካም ነበረ። እኔ በጥበብ ከሁሉ እበልጣለሁ ብዬ አይደለም ነገር ግን ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር እንጂ የገለጸለት ነው ብሎ አምልኮተ

እግዚአብሔርን ሰበከለት። አስኪ በል ንገረኝ አለው። እንዲህ እንዲህ ያለ አላየህምን አለው።

ሕልምየ ውእቱ ንግረኒ ፍካሬሁ፡ አለው። እንኪያስ ቀን ያሰብከውን ሌሊት አሳይቶሃል ባንተ ጊዜ የሚሆነውን ካንተ በኋላ የሚደረገውን። ርእሱ ዘወርቅ፡ የተባልህ አንተ ነህ። ወርቅ መክብበ ንዋያት ነው። እንተም ንጉሠ ነገሥት ነህ። እንግድዓሁ ዘብሩር የተባለ ዳርዮስ ነው። ብር ከወርቅ በታች ከሌሎች ንዋያት በላይ ነው። ዳርዮስም ካንተ በታች ከሌሎች ነገሥታት በላይ ነውና። ሐቂሁ ዘብርት የተባለ ቂሮስ ነው። ብርት ቢመቱት ከሩቅ ይሰማል ቂሮስም ዜና መንግሥቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይሰማልና። ቍየጺሁ ዘሐፂን የተባለ አስክንድር ነው። ብርት ጽኑዕ ነው አስክንድርም ኃያል ንጉሥ ነው። መንፈቀ አግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን የተባሉ አስክንድር በጊዜ ሞቱ የሚያነግሣቸው ድኩማኑ ኃያላኑ ነገሥታት ናቸው። ድኩማኑ ሰልፎስ ድማጥርያኖስ፡ ኃያላኑ አንጥያኮስ ሰጥሊሞስ። አንድም ወዘመዋዕሊሆሙ ሰአሊ ይመጽእ እምሳህ ለማይ ይላል ብሎ፡ በመንግሥት ያወርዱታል። ርእሱ ዘወርቅ፡ መንግሥተ ባቢሎን። እንግድዓሁ ዘብሩር፡ መንግሥተ ሜዶን። ሐቂሁ ዘብርት፡ መንግሥተ ፋርስ። ቍየጺሁ ዘሐጺን፡ መንግሥተ ጽርዕ። መንፈቀ አግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን፡ መንግሥተ ሮም። አንድም ጽርዕን ከፋርስ ደርቦ ቍየጺሁ ዘሐፂን መንግሥተ ሮም። መንፈቀ አግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን፡ በሮም ያሉ ድኩማኑ ኃያላኑ ነገሥታት ናቸው። ይህ ምሳሌ ነው። ደብር የሰማየ ሰማያት፡ አብን የጌታ። ከረጅም ተራራ የሰው እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ መውረዱ ያለ አንብሮ /ያለ መገደድ/ ከሰማየ ለሰማያት የመውረዱ፡ አንድም ደብር የእመቤታችን፡ አብን እይለወጥም የጌታ። የሰው እጅ ሳይነካው ከረጅም ተራራ ተፈንቅሎ መውረዱ ያለ ዘር ከእመቤታችን የመወለዱ። ያን ቀጥቅጦ ደንጊያው ተራራ ሲያህል ማየትህ ይህን ሁሉ አጥፍቶ ልዕልናውን የመግለጹ፡ ተራራው በዓለም ሊመላ ማየትህ ሕማሙ ሞቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ የመስበኩ አምላክ ነው ብሎ ተርጉሞለታል። አሙን ሕልሙ ወርቁዕ ፍካሬሁ ብሎ አድንቆ ራስ ቢትወደድ ሾሞታል ይህንንስ

www.zeyeneta.com

ሌላ ይዞታል ብሎ ሊቀ ጠቢባንነት ሾሞታል። ፫ቱ ደቂቅም ወግዴ በዘመኑ እንዲሉ ቀኝአዝማች ግራአዝማች ከንቲባ እየሆኑ ተሾመዋል። ሹመታቸውም የዳንኤል በስተማ፡ የ፫ቱ ደቂቅ በአፍኣ ነው። ጥበበ እግዚአብሔር ነው። ዳንኤል በስተማ ያሉ እስራኤልን ሊጠብቃቸው፡ ፫ቱ ደቂቅ በአፍኣ ያሉ እስራኤልን ሊጠብቋቸው። ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ፫ቱ ደቂቅ ከሹመቱ ያስለቀቁት ነው ይላሉ ሌላም ነው ይላሉ ዳንኤል ሰንኒን ርእሱ ዘወርቅን የተረጕመልህ ላንተ ነው የወርቅ ጣያት አቁመህ አታስግደውም? አለው። እውነት አንጂ ነው ብሎ ፮ ክንድ ቁመቱ፡ ፮ ክንድ ደረቱ፡ ጣያት በሐቅለ አዱራን ይቁም ብሎ አዘዘ ቆመ። ዘኢሰገደ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርኩ በእዴየ ይትበርበር ቤቱ ወይትሐየድ ንዋየ ወይትከነን ነፍሱ ብሎ አዋጅ ነገረ። ጸርዕ ሚደን ፋርስ ባቢሎን ሰገዱ። ፫ቱ ደቂቅ ሳይሰግዱ ቀሩ ያው ለው ሂደ ኧረ ቀኝአዝማች ግራአዝማች ከንቲባ አድርገህ የሾምካቸው ሊድራቅ ሚሳቅ አብደናጎ ሳይሰግዱ ቀሩ አለው /ብለው ነገሩት/። ወአዘዘ በመዓት ያምጽእሙ። ተቆጥቶ ያመጣቸው ዘንድ አዘዘ። አንድም እያጣደፋቸው አምጣቸው አለ መጡ /አመጣቸው/። አማንከሙኑ ሊድራቅ ወሚሳቅ ወአብዳናጎ ዘኢትሰገዱ ለምስል ዘገበርኩ በእዴየ ወኢታመልኩ አምላኪየ አላቸው።

አ ንጉሥ ኢንፊቅድ ንሰጠውከ በዝንቱ ግብር ሀሎ አምላክነ ዘናመልክ ኪያሁ በሰማይ አሉት።

መኑ ያድኅነከሙ እምእዴየ ወእምአቶን አሳት አላቸው። ሀሎ አምላክነ ዘፈጠረ ኪያከ ወኪያነ ውእቱ ያድኅነነ እምእዴከ ወእምአቶን አሳት አሉት። ያን ጊዜ ሰይፍ ጦር ቃጣባቸው። ኋላ ያን ትቶ ጉድንድ አሰቆፍሮ አሳት አስነድዶ ከነቁንጽል/ ከአጭር / ቀሚላቸው በተራዳ እየገፋ ጣላቸው /እየገፉ ጣሏቸው/ ስለምን ቢሉ አላልቦ ይግደላቸው ብሎ። ለዚህስ አሳቱ ይበቃል ብሎ ውሉደ መንግሥት ናቸውና አንዳይዋረዱ ብሎ። ፫ቱ ደቂቅ በውስጥ ዳንኤል በአፍኣ ሆነው ተናግረውታል፡ ከአዛርያ የተገኘ ዳንኤል የተናገረው ነገር ይህ ነው። ምነው አነዚያስ ተናግረው የለም? ቢሉ አነዚያ መከራውን እንደመለቀቅ ብለዋል፡ ይህ አዛርያ

አጸንቷቸዋል አንድ ሰዓት አይደለም ምን ቁም ነገር አለው ብሎ። ዳንኤል ጥሬ አንብሳ በማለት እንደጸና።

፩. ይትባረክ አግዚአብሔር አምላክ አበዊነ። ያባቶቻችን ፈጣሪ አግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ። አንድም ለሙሴ ባሕር የከፈለለት ለኢያሱ ፀሐይ ያቆመለት ዛሬም ለኛ አቶነ አሳትን ያበረደ አግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።
እኩት ወስቡሕ ስምከ ለዓለም
ስምህ ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው። እኛ ብናመሰግነው ክብር የሚጨመርለት እኛ ባናመሰግነው ክብር የሚጎድልበት ሆኖ አይደለም።

፪. አስመ ጻድቅ አንተ በኵሉ ዘአምጻእከ ላዕሌነ፡ ብነ ሲል።ነው ባመጣህብን ሁሉ እውነተኛ ነህና እውነት ፈርደህ አምጥተህብናልና።
እሙን ኵሉ ግብርከ። ሥራህ ሁሉ የታመነ ነው።
ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊከ። ሥራህ ሁሉ የቀና ነው።
ወጽድቅ ኵሉ ኵነኔከ።
ፍርድህ ሁሉ እውነት ነው።
አንድም እሙን ኵሉ። ኢታምልክ የታመነ ነው። ኵሉ አለ ፍጹም ሲል ነው።
ኢ በሰማይ ወኢ በምድር ብሎ ከፍሎታል።
ወርቱዕ። ይኽ ቃላት።
ወጽድቅ ኵሉ ኵነኔከ። ፍጹም ወነበቦ አለ። ያ እውነት ነው
አንድም እሙን ሚጠት። ወርቱዕ። ዓዋዊ።
ወጽድቅ ኵነኔከ። በሀገራችን ሳለን ያመጣኸው አባር ቸነፈር እውነት ነው አለ የሚገባ ነው።

፫. ወገሰርከ ፍትሐ ወርትዐ በኵሉ ዘገበርከ ለነ ብነ ሲል ነው። /ይላል/ በኛ ባደረግኸው ሁሉ ፍትሕ ርትዕን አደረግህ አለ። እውነት ፈርደህ አመጣህብን።
ወዲበ ሀገረ አበዊነ ኢየሩሳሌም ቅድስት።

www.zeyeneta.com

ብነ ወበሀገረ አበዊነ። በአባቶቻችን እገር በኢየሩሳሌም ሳለን ያመጣኸው አባር ቸነፈር እውነት ነው አለ፡ እውነት ፈርደህ አመጣህብን።

እስመ በኵነኔ ጽድቅከ አምጻእከ ዘ ኵሎ በእንተ ኃጢአትነ። ስለኃጢአታችን ይህን ሁሉ በእውነተኛ ፍርድህ አምጥተህበናልና አለ፡ እውነት ፈርደህ አምጥተህብናልና።

፱. እስመ አበስነ ወጌገይነ ዘንደግናከ ያ ግን የጣልኽህ እኛ በድለናል ስሑታን ሆነናልና። ዐመፅነ በኵሉ ወኢሰማዕነ ትእዛዘከ። ያሩ ቃላትን አፈረስን።

ኢሰማዕነ። ፎፎፎ ወነበቦ አለ፡ ያን አልሰማንም።

አንድም ዐመፅነ በኵሉ። ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ዕፀው አእባንን በማመን (በማምለክ) በደልንህ።

ወኢሰማእነ። ኢታምልክ ያልከውን አልሰማንም።

፲. ኢዐቅብነ ወኢገበርነ በአመ አዘገዘከነ። ያዘዘከንን አልጠበቅንም እንዳዘገዘከን አላደረግንም።

ከመይኩን ሠናየ ላዕሌነ። መጠበቁ በጎ ይሆንልን ዘንድ፡ ሠናይ. ይላል በመጠበቁ ክብር ሬድኤት ይሰጠን ዘንድ።

፲፩. ኵሎ ዘአምጻእከ ላዕሌነ ወኵሎ ዘገበርከ ዲቤነ በኵነኔ ጽድቅ ገበርከ። በኛ ላመጣኸው በኛ ባደረግኸው ሁሉ በእውነተኛ ፍርድህ አደረግህ አለ፡ እውነት ፈርደህ አመጣህብን።

፲፪. ወመጠውኩነ ውስተ እደ ዘርነ ጎጥአን ወዓላውያን። ጎጥአን ዓላውያን ነሚሆኑ በጠላቶቻችን እጅ የጣልከንን መጣል ኃጥአን የሚላቸው ምግባር የሌላቸው፡ ዓላውያን የሚላቸው ሃይማኖት የሌላቸው ናቸው። እሊህ ግን ሁሉም የላቸውምና ኃጥአን ዓላውያን አላቸው።

እለ ርትዕን ወግሑሣን እምኔክ። ኃጥአን ያለውን ርትዕን ዓላውያን ያለውን ግሑሣን ብሎ ደገመው።

ወንጉሥ ዐማዊ ወእኩይ እምኵሉ ምድር፡ ወውስተ እደ ንጉሥ ይላል። ከሰው ሁሉ በሚከፋ በናቡከደነፆር እጅ የጣልከንን መጣል። ቢከፋ ቢከፋ ከፈርያን ይከፋል? ቢሉ ለጊዜው አምን ይከፋል። ፈርያን ለእግዚአብሔርኒ እየአምሮ

አለ እንጂ አነ ውእቱ አላለም። እሱ ግን አነ ውእቱ ዘእሠርቅ ፀሐየ ብሏል።

፲፫. ወይእዜኒ አኮ፡ ድልወት ለነ ንከሥት አፉነ። አሁንም አድነን ብለን አንለምንህ ዘንድ አይገባንም ኃጥአን ነን።

ሐፍረት ወዝንጋጌ ኮኖሙ ለአግብርቲከ ለእለ ይፈርሑከ። በሚያመልኩህ በሚፈሩህ በባሮችህ በነቢያት በካህናት የመጣውን ሽሙጡን ተግዳሮቱን አይተህ ሰምተህ ይቅር በለን አንጂ።

፲፬. ኢትመጥወነ፡ ለግሙራ በእንተ ስምከ። ስምየኒ መሐሪ ወመሥተሣህል ስላልከው ስለስምህ ብለህ ለመከራው አትስጠን አንደሰጠኸን አትቅር።

ኢትሚጥ ኪዳነከ ወኢታርሕቅ ምሕረተከ እምኔነ። መሐላሕን ቸርነትህን ከእኛ አታርቅ ኪዳነነ ምሕረተነም ይላል።

በእንተ አብርሃም ፍቁርከ። ብየ ዓርከ አብርሃም በዲበ ምድር ስላልከው ሰለ አብርሃም ብለህ።

ወበእንተ ይስሐቅ ቊልዔከ። እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርዕ ስላልከው ስለይስሐቅ ብለህ።

ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ። እምይእዜለ ኢይሰመይ ስምከ ያዕቆብ አላ ይሰመይ ስምከ እስራኤል ስላልኸው ስለ ያዕቆብ ብለህ ይቅር በለን።

፲፭. አለተናገርኮሙ ወትቤሎሙ ከመታብዝኅ ዘርዖሙ ከመ ኮከበ ሰማይ። ልጅ የልጅ ልጃቸውን እንደ ሰማይ ኮከብ።

ወከመ ኖኅ ባሕር ዘድንጋገ ባሕር። እንደ ባሕር እሸዋ ታበዛላቸው ዘንድ ስለተናገርካቸው ስለእነሱ ብለህ ይቅር በለን።

እስመ ውጥዣን እሙንቱ አምኵሉ አሕዛብ። ከአሕዛብ ይልቅ ጥቂቶች ላሉ አብርሃም ኮኃራ፡ ይስሐቅ ከርብታ፡ ያቆዕብ ከራሔል ከልያ።

ወኮነ ኀሡራነ በኵሉ ምድር ዮም በእንተ ኃጢአትነ። ስለኃጢአታችን በባቢሎን የኀሰቆልን ሆን።

፲፮. አልዮ በዝ መዋዕል መልእክ ኢ ነቢይ ወኢ ንጉሥ። አለቃችሁ አያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ እንደ ኢያሱ ያለ

www.zeyeneta.com

ክፉውን ተመራምሮ አጥፍቶ የሚያድን አለቃ የለንም (የለንምና)።

<u>ታሪክ</u> ይህ ኢያሱ ተሳለ ለብአ ኢያሪኮን በእጁ ብትጥልልኝ ከዚያ ያገኘሁትን ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር አለጣለሁ ብሎ ሕዝቡም ተሳሉ። ይህች ኢያሪኮ ፮ ቅፅር ያላት ናት ፯ ቀን እየዞረ ሊሰፍር ሰነበተ በ፯ኛው ቀን የነጋሪት ድምፅ አለማባት ሻ / ናድ ፡ ወለል/ ብላ ፊረለች። እክሌን ወልደ ከርሚ ይለዋል። ሀምሳ ወቂት የምትሆን ልሳነ ወርቅ ሁለት መቶ ምዝምዝ ብር አራት ጎሞር አምስተኛ ወርቀ ዘቦ ያላት ግምጃ አገኘ ያን ከድንኳኑ ወስዶ ጉደጓድ ቆፍሮ በታች ወርቁን በላይ ብሩን ከዚያ በላይ ግምጃውን አድርጎ ቀበረው ካጠገቡ ጋደ የምትባል አገር ነበረች ሰላይ ሰደደ /ሰዶ/ ይህችስ አንተንም የምታስጭን አይደለችም ቢሆን ሁለት ሺ ባይሆን ሶስት ሺ ጦር ይበቃታል አሉት። ሶስት ሺ ጦር ሰደደ አሰራኤል ድል ሆኑ። ከአሰራኤል ፴፮ ሰው ሞተ። ኢያሱ በኖነተ ደብተራ ወደቀ።

በይነ ሃንት አዕድም አዕደሥሙ ገብርከ ዮርዳኖስ ናሁ እስራኤል ሜጠ ዘባኖ ቅደመ ፀሩ። እስራኤል ጀርባውን መልሶ ፊቱን ቀልሶ ሸሸ ብሎ ፪ ሊቃናትም ወደቁ ጌታ ስሠርክ መጥቶ አንተስ ሰባ ሊቀናትስ ለምን ወደቃችሁ ለኔ ክተሳልከው ገንዘብ ያስቀረ አለ። ያን ተመራምረህ ነሰጠፋህ በረድኤት ካንተ ጋራ አልኖርም አለው። ሊቀ ካህናቱ አልዓዛር ነበር አልዓዛርን /ካህናቱን/ ልብሰ ተክህና አልብሰ በየነገዳችሁ እለፉ ሂዱ አላቸው። ነገደ ዛራ ሊያልፍ ምልክት ታየ። ምልክቱም ልብሱ ይጠቁራል ይነፋል እነዚያን ደግሞ አንድ አንዳችሁ እለፉ አላቸው። ይህ አክለን ሊያልፍ ጭራሽ ጠቆረ ቃልም ተሰማ ይላሉ።

እመኖ ወልድየ። ልጄ አላዋቂ አታድርገው። ምን ምን ወሥደሃል አለው። እንዲህ እንዲህ ያለ ወስጃለሁ አለው። ሚስቱን ልጆቹን ከብቶቹን እሱን አድርጎ በቆላተ ኤሜቃኮር በአላት አንጠቅጥቆ ገድሎታል። እንዲህ አድርጎ ክፉ ክፉውን ተመራምሮ አጥፍቶ የሚአድን አለቃ የለንም።

ኢ ነቢይ። ነቢያችሁ አያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ እንደ ሙሴ ያለ። እምትጥስዮሙ ለእሱ ሕዝብክ ጠስዮኒ ሊተ አመጽሐፊ. ሕይወት ዘጸሐፍከኒ ብሎ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ የሚያድን ነቢይ የለንም።

ወኢ ንጉሥ። ንጉሣችሁ አያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ እንደ ዳዊት ያለ፡ ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እነ ናላዊ /እንዘ እነ/ ናላዊ ብሎ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ የሚያድን ንጉሥ የለንም።

ታሪክ ዳዊት የእስራኤልን ብዛት ሊያይ ቢሻ አስቆጠራቸው። ነገደ ይሁዳ አምስት መቶ ሺሕ ሆኑ። ፲ሩ ነገድ ተኩል ስምንት መቶ ሺሕ ሆኑ። ፪ቱ ነገድ ተኩል ክረምት ገባና ሳይቆጠሩ ቀሩ። በዚህ ቢያዝን ጋድን በልማደ ነቢያት ላከበት። ብዛታቸውንስ ልታይ ብትወድ ግባት አለኝተህ/ስብለባ ጠርተህ/ ባሮሃቸው ነበር እንጂ። አሁንም ከረኃብ ከጦር ከቸነፈር ከሊህ ከሰሳቱ ምረጥ ብሎሃል አለው።

እምእደት ውስተ እደ ሰብእ ይኄይሰኒ ወዲቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር አለ። ረሀብንስ አላነሳውም ከሁለም ይጸናልና። ከዚህ በኋላ መልአክ መደምሰስ በዓውደ አርና ሲቀስፍ ታየው።

ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዘ እነ ናላዊ ዘአበሰኩ። በግ አረኛው ሊቆጥረው አልቆጠርም ይላል?

ዛቲ እደከ ትኩን ላዕሌየ ወላዕለ ቤተ አቡየ ብሎ ወደቀ። ቸነፈሩ ፀጥ አለ ያንጊዜ ያለቁት ሰባ ሺሕ ከሶስት ናቸው እስከ ቀትር።

ኢ ቊርባን ወኢ መሥዋዕት። ቊርባናችሁ መሥዋዕታችሁ አያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ ቊርባን መሥዋዕት የለም። መሥዋዕት የላሙ የበጉ፡ ቊርባን የሰንዴው የእህሉ እንድም መሥዋዕት ተረፉ ቊርባን የሚፈስሰው ደሙ የሚጤሰው ስቡ።

ወኢ ንበ እለ ያጸነሐሑ ዕጣነ። ሊቀ ካህናቱ አያድናችሁም ትለን /ትለኝ/ እንደሆነ እንደ አሮን ዕጣን አጥኖ የሚያድን ሊቀ ካህናት የለንም። አንድም ዕጣን የሚያጥንበት ማዕጠንት የለም። ኤርምያስ ቀብሮት ሄዷል። አንድም ዕጣን ይላል። ዕጣን በባቢሎን የሰም ማለት አይደለም መሥዋዕቱ ሲቀር ዕጣኑም ቀርቷል።

www.zeyeneta.com

ወኢ ብሒር ገበ እለ ይፈርዩ በቅድሜከ ይርከቡ ሚህለከ። ይቅርታህን ሊያገኙ ምግባር ትሩፋት የሚሠሩበት አገር የለም። ለሥራ ቦታ ያግዛልና።

፲፪. ዘእንበለ በነፍስ የዋሕ ወበመንፈስ ትሑት ተወከፍ ለነ። በትሑት ለብእና በየዋሕ /በቅን/ ልቡና ያቀረብንልሕን ተቀበልልን እንጂ። እንደ መሥዋዕቱ ጸሎታቸውን፡ እንደ ምሥዋዕ ብርቱ ልቡናቸውን፡ አንደ ሊቀ ካህናቱ አንደበታቸውን፡ እንደ ቤተ መቅደስ ሰውነታቸውን፡ እድርገው ይናገራሉ።

፲፫. ከመ ዘመሥዋዕተ ሐራጊት ወእልሕምት። ሐራጊት የዳዊት የለሎሞንን። እልሀምት፡ የሙሴ የእሮንን መሥዋዕት እንደተቀበልከ ተቀበልልን።
ወከመ ዘአዕላፍ አጣፃዕ ስቡሐን። የኢዮስያስን መሥዋዕት እንደተቀበልከ ተቀበልልን። አልቦ ዘገብረ በዓለ ዘከመ ገብረ ኢዮስያስ ይለዋልና።
ከማሁ ይኩን መሥዋዕቲነ በቅድሜከ ዮም። ጸሎታችን በፊትህ አንዲህ ይሁን አለ ወደህ ተቀበልልን።
ወፍጹመ ይኩን በጎቤከ። ባንተ ዘንድ ፍጹም ይሁን።
ከመ ኢይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ ይትዊከሱከ። ባንተ ያመኑ ሁሉ መከራ መጥቶባቸው እንዳያፍሩ።

፲፬. ወይእዜኒ ንተልወከ በኵሉ ልብነ ወንፈርሐከ። አሁንም በፍጹም ልቡናችን እንፈራሃለን እናመልክሃለን።
ወነኀሥሥ ገጸከ ዳዕሙ ኢታስተሐፍረነ። አታሳፍረን እንጂ ረድኤትህን እንሻለን።

፲፭. ወግበር ምስሌነ በከመ ተመይጦትከ። ከመዓት ወደ ምሕረት እንደመመለስህ መጠን ቸርነትህን እድርግልን።
ወበከመ ብዝኀ ምሕረትከ እድኅነነ በተአምሪከ። እንደ ቸርነትህ ብዛት መጠን በተአምራትህ እድነን።
ሀብ ስብሐተ ለስምከ እግዚኦ። ለስምህ ምስጋናን ስጥ አለ።
አቤቱ እኛን አድነህ ስምህ እንደሚመሰገን እድርግ።

፲፮. ይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ እርእይዎሙ ሥቃየ ለአግብርቲከ። በባሮችህ በነቢያት በክናት መከራ የሚያፀኑባቸው ይፈሩ ይጎስቁሉ።
ይትሐፈሩ በኵሉ ትዕግልቶሙ ወይትቀጥቀጥ ጎይሎሙ። የሰው ገዝዙ በመቀማታቸው አምልኮትህን በመቀማታቸው ይጎስቁሉ ይትሐፈሩ ይድክም ጎይሎሙ ይሕልቅ ብዕሎሙ ይላል። ጎይላቸው ይድከም። ብዕላቸው ይለቅ።

፲፯. ወያእምሩ ከመ አንተ እግዚአብሔር አምላከ ባሕቲትከ።
አንተ ብቻ አምላክ እንደሆንክ ያወቁ።
ሰዘኩሕ ዘኵሉ ምድር ወበኵሉ ዓለም፡ በኵሉ ምድር፡ በዚህ ዓለም።
ወዘበኵሉ ዓለም፡ በሰማይ።
አንድም ዘበኵሉ ምድር፡ በኢየሩሳሌም።
ወዘበኵሉ ዓለም፡ በባቢሎን።
አንድም በዘኵሉ ምድር፡ በባቢሎን።
ወዘበኵሉ ዓለም፡ በክላውዲዎስ። ክሁር ሥስጉን አንተ ብቻ እንደሆንክ ያወቁ።

፱ ጸሎተ ፱ቱ ደቂቅ

ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባል ወኮነ ከመ ነፋስ ቁሪር ይላል። ቅዱስ ጉብርኤል ወርዶ ቢባርከው ቀዘቀዘ በምትሐት ያጠፋት መስሏቸው ወወደዩ ውስተ እሳቱ ተየ ወፒሳ ወሰጠጽዮን ወቀለሞጲዳ ይላል።
ተየ ድኝ ፒሳ ስም አደሮማር ስጠጽዮን የወይን ሐረግ ዶግ ቀለሞጲዳ ቅንጭብ ቁልቋል የሚያናድደውን ሁሉ ጨምረዋል /ጨምረውበታል/።
ወተለዐለ ነበልባሉ መጠነ ፱ ወ፱ቱ በእመት ይላል። በምን ታውቂል ቢሉ ካጠገቡ ዛፍ ነበረ ያንን ወጥቶ በልቶታል። ቢስፍሩት ፺፱ ክንድ ሆኗል። እንድም ነበልባሉ አልፎ የወደቀበት

www.zeyeneta.com

መስከ። አንድም ዳንኤል በእመተ ጸጋ ስፍሮታል /በጸጋ አውቆ ቆጥሮታል/ በመከራ ላይ መከራ ቢያጸኑባቸው በምስጋና ላይ ምስጋና ይጨምራሉ ፫ቱ ደቂቅ የተናገሩት ነገር ይህ ነው።

፩. ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ። ያባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ። አንድም ለሙሴ ባሕርን የከፈለለት ለኢያሱ ፀሐይን ያቆመለት ባራም ለኛ አቶነ አሳትን ያበረደልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።

ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም። ስምህ ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው። እኛ ብናመሰግንህው ክብር የሚጨመርለት እኛ ባናመሰግንህው ክብር የሚጎድልበት አይደለም።

ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ። ክቡር ልዩ የሆነ የጌትነቱ ስም ይክበር ይመስገን።

በቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ በኩሉ ዓለም። ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው።

፪. ዙሩክ አንተ በጽርሐ ትድሳተ ስብሐቲከ። በጽርሐ አርያም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን ክቡር ምስጉን አንተ ነህ።

ስቡሕኒ አንተ ወእኩት አንተ ለዓለም። ለዘላለም ክቡር ምስጉን ነህ።

፫. ዙሩክ አንተ ዘትራኢ ቀላያተ ነበረከ ላዕለ ኪሩቤል። በኪሩቤል ላይ ሆነህ ቀላያተ ውቅያኖስን ቀላያተ እቶነ እሳትን ቀላያተ ገሀነምን የምታይ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ።

ስቡሕኒ አንተ ወልዑል አንተ ለዓለም። ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ።

፬. ዙሩክ አንተ በዲበ መንበረ መንግሥትከ። በጌትነትህ ዙፋን ክቡር ምስጉን አንተ ነህ። ስቡሕኒ አንተ ወዙሩክ አንተ ለዓለም። ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ።

፭. በሩክ አንተ በመልዕልተ ሶማያት። በሊቃነ መላእክት ክቡር ምስጉን አንተ ነህ።

ስቡሕኒ አንተ ወክቡር አንተ ለዓለም። ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ።

ስለምን ከፍ ብለው ፮፡ ፰፡ ዝቅ ብለው ፬፡ ፭፡ ያልተናገሩ ፮ የተናገሩ ስለምን ነው ቢሉ ለውስ ከፍ ብለው ፮፡ ፰፡ ዝቅ ብለው ፬፡ ፭፡ ቢናገሩም ስለምን ነው ግለቱን አይተውም ብሉ መንፈስ ቅዱሰ እንደመጻቸው ተናግረዋል። እኛ ለአቶነ እሳት በወደቅን በ፮፱ ዘመን ሰው ይሆናል ሥጋ ይለብሳል ሲሉ። በዘመናቸው የነበረ ዳንኤል ፬፻፯ አሉ፡ እነሱ ፮፱ አሉ፡ እንደምን ነው ቢሉ እሱ ከሚጠት እስከ ጽንስ ቆጥሮ እነሱ ከአቶነ እሳት እስከ ዕርገት ቆጥረው ነው። የሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥቱ ፲፩ ዓመት ነው። በአሥኛው ወድቀዋል። ከሴዴቅያስ ፮ የናቡከደነፆር ጽሕ። የዮርማሮዴቅ ፭፻ የብልጣሶር ፵፫ ይህን ቢያገናኙት /ቢገጥሙት/ ፸፮። የጌታ ፴፫። በጠቅላላ ፻፱። ፬፻፯ን እና ፻፲ን ቢያነሩ /ቢገጥሙት/ ፮፻ ይሆናል። ወተለዐለ ነበልባሉ መጠነ ፵ወ፬፡ በእመት ያለው ግን የዘሩባቤል ዘመነ መንግሥቱ አምሳል። ፵፬ ዘመን ገዝቷል። ፮ን እና ፵፬ን ቢያገናኙ (ቢቆጥሩ) ፯፩ ይሆናል። በ፰ ሺህ ከ፭፻ ዘመን ሰው ይሆናል ሥጋ ይለብሳል ሲሉ።

፮ ጋብ ባረኩ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል።

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል ምስጋና ካቀረቡ ዘንድ፡

፮. ይባርክም ኩሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር። ፍጥረቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል አሉ። ፫ቱ ደቂቅ አሉ። ፫ቱ፮። ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም። ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው።

፯. ይባርክም ሶማያት ለእግዚአብሔር። ኩሉ ያለውን ይተረትራል። ፯ቱ ሰማያት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ስቡሕኒ፡ አይለውጥም።

፰. ይባርክም መላእክተ እግዚእ ለእግዚአብሔር። ሰራዊተ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ስቡሕኒ፡ አይ።

www.zeyeneta.com

፱. ይባርክም ኵሉ ማያት ዘመልዕልተ ሰማያት ለእግዚአብሔር። ከጠፈር በላይ ያለ ሐናሰ እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል። ማያት ሰማያት ብሎ አበላ በ፱ቱ ማዕዘን ጸንቶ የሚኖር ሰለሆነ ሰቡሕኒ፡ አይ።

፲. ይባርክም ኵሉ ኃይለ እግዚእ ለእግዚአብሔር። ሊቃነ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ሰቡ አይ።

፲፩. ይባርክም ፀሐይ ወወርኀ ለእግዚአብሔር። ፀሐይ ጨረቃ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ሰቡ አይ።

፲፪. ይባርክም ከዋክብተ ሰማይ ለእግዚአብሔር። በሰማይ ያሉ ከዋክብት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፫. ይባርክም ጠል ወዝናም ለእግዚአብሔር። ጠል ዝናም እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፬. ይባርክም ኵሉ መንፈስ ለእግዚአብሔር ፷ቱ ነፋሳተ መዓት ፬ቱ ነፋሳተ ምሕረት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፭. ይባርክም እሳት ወላህብ ለእግዚአብሔር። እሳት አካሉ ላህብ ዋለዩ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፮. ይባርክም ሌሊት ወመዓልት ለእግዚአብሔር። ፲፪ቱ ሰዓተ መኃልት ፲፪ቱ ሰንተ ሰሰት እግዚአብሔር ያመሰግኑታል።

፲፯. ይባርክም ጠል ወዐውል ለእግዚአብሔር። ጠል ዓውል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ምነው ጠልንማ ተናግሮት አልነበረም? ቢሉ ጠሰ ሐጋይ ጠሰ ከረምት ጠሰ መዓት ጠሰ ምሕረት አሰና። አውልዕ ዋግ ነው።

፲፰. ይባርክም ቊር ወአሰሐትያ ለእግዚአብሔር። ቊር አሰሐትያ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ቊር ብትኑ አሰሐትያ ግግሩ። ወይትፈሰጥ ከመ ሰባረ ማሕረጽ /ማጎው/ የሚለው።

፲፱. ይባርክም በርህ ወጽልመት ለእግዚአብሔር። ጨለማ ብርሃን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳. ይባርክም ደደከ ወመርቂ ለእግዚአብሔር።
ደደክ ደጋ መርቂ ቆላ። እንድም ደደከ ቀቅ/ብርድ/ መርቂ ዋዕዩ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፩. ይባርክም በረድ ወጊሜ ለእግዚአብሔር። በረድ ጊሜ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። በረድ የሚለው መገብተ ደመናት ወሰደው ደመናውን ይዘረጋሉ። ማያት ይቋጥራሉ። መገብተ ነፋሳት ቊነው ይወጣሉ። ከዚያ ሲያማታው ይወርዳል። አንድም ሄኖክ ወርኢኩ መዝገበ በረድ ይላልና፡ ቦታ አሰው። ጊሜ ላህበ ምድር ነው።

፳፪. ይባርክም መብረት ወደመና ለእግዚአብሔር። መብረቅ ሰያፉው መላእክት ድኛ አሸዋ ጨምረው ቊነው ይወጣሉ። ከዚያ ሲያጋጩት ይወጣል ቡላድ/ደንጊያና ደንገያ/ ሲያጋጩት አሳት እንዲወጣ። ደመና፡ ርጡብ ጢሰና ይቡስ ጢሰ በፀሐይ ሞቀው አንድ ደመና ይሆናሉ። ወይመውቀ ጀሆሙ በፀሐይ ወያከሠት አሐደ ደመና እንዲል።

፳፫. ትባርኮ ምድር ለእግዚአብሔር። ምድር እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች። አስነ አሁን በወንድ አንቀጽ ሲናገር መጥቶ አሁን በሴት አንቀጽ ተናገረ። ሴት ከባሏ ዘር ተቀብላ ልጅ እንድታሰኝ ምድርም ከሰማይ ዝናምን ተቀብላ እትክልትን አዝርዕትን ታስገኛለችና።

፳፬. ይባርክም አደባር ወአውግር ለእግዚአብሔር። አድባር ተራሮች /ተራራዎች/ አውግር ኮረብቶች /ኮረብታዎች/ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፭. ይባርክም ኵሉ ዘይበቍል ውስተ ምድር ለእግዚአብሔር። በምድር የሚበቅለው ሁሉ እዝርዕት አትክልት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፮. ይባርክም ቀላያት ለእግዚአብሔር። ቀላያት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ። በሀገራችን ጣና በሀገራቸው ምጥዋ።

፳፯. ይባርክም ባሕር ወአፍላግ ለእግዚአብሔር። ባሕር በፈሳሹ መካከል ያሰው፡ አፍላግ ፈሳሹ እንደ ዓባይ እንደ በሽሎ ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፰. ይባርክም ዐንበር ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማይ ለእግዚአብሔር። ዓሣ ዐንበሪ በውሰጡ ያሉት አዞ ጉማሬ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

www.zeyeneta.com

፹፩. ይባርክዎ ኩሉ አዕዋፈ ሰማይ ለእግዚአብሔር። አእዋፍ እግዚአብሔርን ያመሰግናኑታል።

፹፪. ይባርክዎ ኩሉ አራዊት ወእንሰሳ ለእግዚአብሔር። አራዊት እንሰሳት እግዚ ያመሰግኑታል።

፹፫. ይባርክዎ ደቂቀ ፅንለእመሕያው ለእግዚአብሔር። ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ቤት ሠርቶ ጉልላት እንደ መሥራት ጥቁር ጥሎ ነጭ እንደመጣል ስውን በላይ እየረገፈ /እመጣ/።

፹፬. ይባርክዎ እስራኤል ለእግዚአብሔር። ከዚያውም ዘንድ ምእመናን ይበልጣሉና፡ እስራኤል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፹፭. ይባርክዎ ካህናተ እግዚእ ለእግዚአብሔር። እንደ ዲያቆናት ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፹፮. ይባርክዎ አግብርተ እግዚእ ለእግዚአብሔር። እንደ ሠላውስት ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፹፯. ይባርክዎ መንፈስ ወነፍሰ ጻድቃን ለእግዚአብሔር። የጻድቃን ለውነታቸው ልቡናቸው እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል።

፹፰. ይባርክዎ ጻድቃን ወትሑታን ልብ ለእግዚአብሔር። ጻድቃን ወጣንያን፡ ትሑታን ፍጹማን፡ ወይራስዩ /ወይራእዩ/ ርእሶሙ ከመ ነፍስ/መንፈስ/ እንተ ትማልም ኅሰፈትእንዲል/ የሚሉቸው/ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፹፱. ይባርክዎ አናንያ፡ ወአዛርያ፡ ወሚሳኤል ለእግዚአብሔር። ከዚያውም ዘንድ ሰማዕታት ይበልጣሉና አናንያ አዛርያ ሚሳኤል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

ንባርኮ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እናመሰግነዋለን። አንድነታቸውን ሲያዩ ንባርኮ፡ ሦስትነታቸውን ሲያዩ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉ። አንድም የ፫ቱ ደቂቅን ቃል ፫ቱ ይተረጕማሉ ይባርክዎ ማለታቸው። ንባርኮ ለእግዚአብሔር ማለታቸው፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሊሉ ነው ብለው።

አንስ ሶበ እቤ እግዚአብሔር አብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል።

ታሪክ፡-

ያህ ናቡከደነፆር ከሰንነት ላይ ሆኖ እይቶ

አሰኑ አሚረነ ፫ተ እደወ ወደይነ ውስተ እሳት ናሁ እፈኢ ፬ተ እደወ እንዘ ያንሰንዉ ኅቡሐንሆሙ ውስተ እቶነ እሳት።

ወራብዑሰ ያመስል ገጹ ከመ ገጸ ወልደ እግዚአብሔር አለ። ዛራ ስለው መልክ መልካም ሕግን ያየ እንደሆነ የንጉሥ ልጅ መልክ ያመሰላል እንዲል ወሐያ ያመስላል አለ። አንድም ሙሴን ያመስላል አለ። በፈተ ብርሃን ተሥለጠጠ ተወለደ ሲሉ ያሰሚልና። አንድም መልአክ ፈተን ጻፍዮ አፋን ከፍቶ አናገሮታል። ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ወልደ እግዚአብሔር ማለት ነውና። ከዚያ ወርዶ አንትሙ ሲድራቅ ሚሳኤል በአብደናጎ አንብርቱው ሰልውል፡ ንዑ ጸኡ ዝየ አላቸው። ተራዳ ተከሰልን ነመድ ላሉልን ሳይሉ አንደሳዚሳ ብር ብር እያሉ ወጥተዋል። አሞጽን ዘአሞጽ መልሶታል።

ዘኢሰንደ ለአምላክ ሲድራቅ ወሚሳኤ ወአብደናጎ ይትበርበር ዜቱ ወያትሐየድ ንዋዩ ወያትከሱን ነፍሱ ብሏል። ይህ ምሳሌ ነው። በወሰወ ያሉት የጻድቃነ ብሉት፡ ከዚያ ሆነው እሳቱ እንዳላገኛቸው ጻድቃነ ብሉትንም ሥጭየ ዝህንም አላገኛቸውም።

ነፍሶሙሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢሰከሮሙ ሥቃየ /እሳተ/ ዝህንም እንዲል።

እደ እግዚአብሔር እንደ ድንኳን እንደ አሽበር ሆና ትወዘቃቸው ነበር።

በእሳት /በውጭ/ ያሉት የጎጥአነ ብሉት። ናቡከደነፆር የወልደ እግዚአብሔር፡ ከዚያ ወርዶ ጸኡ ዝየ እንዳላቸው በእሳለ ነፍስ ወርዶ እሰ ውስተ ሲኦል ጸኡ ወእሰ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ ብሏቸዋልና። ይህንም መሥመሩን ቢቆጥሩት ፴፪፡ እንድ ስቡሕኒ ፊኒምሮ ፴፫ ይሆናል። በዚህ ዓለም ለው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ፴፫ ዘመን የመኖሩ ምሳሌ።

www.zeyeneta.com

፲፪. ጸሎተ ዕንባቆም ነቢይ

ዕንባቆም ማለት ማእምር ጠቢብ ለባዊ ማለት ነው። ዒዋዊ እንደደረሰ ተገልጸለት ፍልሰጥኤም ወጥቷል። ከዚያ ሲኖር ለሰንደ. ሰባሪዎች /አጫጆች/ ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ይህን ባቢሱን ወስደህ ለዳንኤል ስጠው አለው። ዞግበ እንበላ /እናብስት/ ወድቶ ነበርና አይቱት ባቢሱን ወስደቱት ዳንኤል አለው። ወጸሮ በሥእርተ ርእሱ ይላል። በራስ ጠጉሩ አንበልጎሰ ወሰዶ እንደተገጠመች ገብቶ መግቦት እንደተገጠመች ወሮንጂል፡ ይህ ምሳሌ ነው። ዕንባቆም የወልደ እግዚአብሔር፡ ዳንኤል የአዳም፡ ገብ የእመቤታችን፡ ምገቡ የምግበ ነፍስ፡ እንደተገበመች ገብቶ እንደተገጠመች መወጣቱ በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና የመወለዱ ምሳሌ። ዕንባቆም የተናገረው ነገር ይህ ነው።

፩. እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ። አቤቱ ቀድሞ ይህን ነሰም እምነበ አልቦ ነበ ቦ አምኮተከ ፈጠርከ ሲሉ ሰማሁ ሰምቼ ፈራሁ

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ። ዛሬም እምነበ ቦ ነበ አልቦ ስታሳልፈው አይቼ ሥራህን አደነቅሁ።

፪. በማዕከለ ክልኤ እንሰሳ ርኢኩከ። በጻድቃንና በኃጥአን መካከል ንዑና ሐሩ ብለህ ስትፈርድ አየሁህ

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ። ዘመነ ምጽአት ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ

ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሴብወከ። ጊዜ ምጽአት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ሰበ ትትሐወክ ነፍሰየ እመንሱት በምሕረትከ ተዘከረኒ። ከኃጥአን ጥፋት የተነሣ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ አሰ። እጸድቃን ተዳርጎ /አጽድቃንን መሰሎ/ ይናገራልና።

እንድም እግዚኦ ሰማዕኩ አቤቱ ቀድሞውን ጀውን ፹ /ሰድስት መቶ ሺ/ አጋርን በምድረ በዳ እንደሻሸ አንዮፊህ እንደቅጠል አርግፌህ አስቀረሃቸው ሲሉ ሰማሁ ሰምቼ ፈራሁ። ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ። ዛሬም ፲ሩን ነገድ ፪ቱን ነገድ ስታሰማርክ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ።

በማዕከለ ክልኤ እንሰሳ ርኢኩከ። በሰልምናሶርና በናቡከደነፆር መካከል አየሁህ።

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ። ዘመነ ዒዋዊ ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሴብወከ። ጊዜ ዒዋዊ ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ሰበ ትትሐወክ ነፍሰየ እመንሱት በምሕረትከ ተዘከረኒ። ካሥሩ ነገድ ከዘሰብ ነገድ ጥፋት የተነሣ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ ዘቸርነትህ አሰበኝ ከነቢያት ተዳርጎ ይናገራል።

አንድም እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሀኩ። አቤቱ ቀድሞ ሰብአ ትካትን ሰብአ ሰዶምን አጠፋሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ ሰምቼም ፈራሁ።

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ። ዛሬም የባቢሎንን ሰዎች ስታጠፋ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ።

በማዕከለ ክልኤ እንሰሳ ርኢኩከ። በዳርዮስና በቂሮስ መካከል አየሁህ።

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ። ዘመነ ሚጠት ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ወከመ ከመ ይበጽሕ። ጊዜ ሚጠት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ሰበ ትትሐወክ ነፍሰየ እመንሱት። ከባቢሎናውያን ጥፋት የተነሳ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ፡ በትሩፋን ተተበየ ይናገራል።

አንድም እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ። አቤቱ ቀድሞ ከአብ ያለ እናት ተወለድክ ሲሉ ሰማሁ ሰምቼም ፈራሁ።

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ። ዛሬም ከቅድስት ድንግል ደለ እባት ሰትወለድ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ።

በማዕከለ ክልዔ እንሰሳ ርኢኩከ። በአድግና በሳህም መካከል በጎል ተጥለህ አየሁህ። አስተማወቅም እስትንፋሰ አድግ ወሳህም በመዋዕለ ቍር ወአስሐትያ እንዲል።

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አአምረከ። ዘመነ ሥጋዌ ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ።

www.zeyeneta.com

ወከመ ከመ ይብጽሕ። ጊዜ ሥጋዊ ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ሰብ ትትሀወክ ነፍስየ እመንሱት። ከአይሁድ ጥፋት የተነሳ ሰውነቱ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ። በምእመናን ተገብቶ ያናገራል። እንድም እግዚኦ ስማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ። አዜቱ ተድሞ ዲያብሎስ በአደ ፈጼለማ አጥናጽፊህ ዕመቀ ስሚቀት አወረድከው ሲሉ ሰማሁ። ስምዃም ፈራሁ።

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ። ዛሬ በመስቀል ድል ስትነሳው አደነቅ ሥራህን አደነቅሁ።

በግዕዝሰ ዝልኁ እንስሳ ርኢኩከ። በፈያታዊ ዘየማንና በፈያታዊ ዘጸጋም መሳክል ተሰቅለህ አየሁህ። እንድም በዮሴፍና በኒቆዲሞስ መሳክል ገንዘው መታቡር ሲያወርዱህ አየሁህ።

ከመ ከመ ይተርብ ዓመቲሁ አአምረከ። ጊዜ /ዘመነ/ ስቅለት ሳያቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ወከመ ከመ ይብጽሕ። ጊዜ ስቅለት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ።

ሰብ ትትሀወክ ነፍስየ እመንሱት። ከአ/ንጎንት ጥፋት የተነሳ ሰውነቱ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ። ከነፍሳት ተዳርጎ ያናገራል።

፫. እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ። እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል። ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወአምአህጉረ ይሁዳ። ከደብረፋራን ከአህጉረ ይሁዳ ይመጣል። እነዚህ ሁሉ ቀድሞ ከንብጽ ሲወጡ ታምራት አድርጎባቸዋል። ያን ጊዜ ታምራት ሲያደርግ እንደመጣ ዛሬም ታምራት ሲያደርግ ይመጣል። አንድም እግዚአብሔርሰ እንተ የማን ይላል። በየማናዊ ኃይል ይመጣል። እንድም ታምራት በሚያደርግበት በሥጋ ማርያም ይመጣል።

ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወአምአህጉረ ይሁዳ። ከድንግል ይወለዳል ወደብረ ፋራን ዘዕንባቆም እንዲል። ወአም አህጉረ ይሁዳ ከነገደ ይሁዳ ይወለዳል ይሁዳ ዕጓለ እንስሳ ተብሎ ከተነገረለት።

ከደነ ሰማያተ ሥኑ። ሥኑ /ሥልጣኑ/ ሰማያትን ከደነ።

ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ። ጌትነቱ ምድርን መላ። አንድም ሥልጣኑ ሰማይን ምድርን ፈጠረ። የእስራኤል ልዑላኑን ትሑታኑን አስማረከ። አንድም የባቢሎናውያንን ልዑላኑን ትሑታኑን አጠፋ። አንድም የእስራኤል ልዑላኑ ትሑታኑን መሰሰ።

<u>አንድም</u> ከደነ ሰማያተ ሥኑ። በዕሰተ ልደት መላእክት አመሰገኑት።

ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ። ኖሎት አመሰገኑ።

አንድም ከደኑ ሰማያተ ሥኑ። በዕሰተ ስቅስት ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ከዋክብት ረገፉ።

ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ። አዕባን ተፈተቱ፡ መቃብራት ተከፈቱ፡ ሙታን ተነሡ፡ መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ከሁለት ተከፈለ ኋሳም ያሳልፋቸዋል።

፬. ወፀዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ። ጸዳለ ረድኤቱ እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛል ኃጥአንን እጥፍቶ ለጻድቃን፡ አሰሩን ነገድ አስማርኮ ለሁሰቱ ነገድ፡ ሁለቱን ነገድ አስማርኮ ለነቢያት ለካህናት፡ የባቢሎንን ለምች አጥፍቶ ለትሩፋን፡ አይሁድን አጥፍቶ ለምእመናን፡ አጋንንትን አጥፍቶ ለነፍሳት፡ ያደረገው ፀዳለ ረድኤቱ እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛል። ፀዳልናሁ ቢል ብርሃንነቱ እንደ አብ ብርሃን ነው። ብርሃን ዘእምብርሃን አንዲል።

አቅርንት ውስተ እደዊሁ። አቅርንት በእጆቹ ተይዘዋል ማለት ሥልጣን የባሕርዩ ነው። አንድም ሰልምናሶር ናቡከደነፆር በሥልጣኑ ተጠብቀዋል። አቅርንት አላቸው። አስራኤልን ይቀጣቸዋልና፡ አንድም ቂሮስ ዳርዮስ በሥልጣኑ ተጠብቀዋል አቅርንት አላቸው። አሕዛብን ይቀጣቸዋልና አንድም በሰውነቱ ሥልጣን የባሕርዩ ነው። ቅንዋት በእጆቹ ተቸንክረዋል። አንድም ሄናክ ኤልያስ በሥልጣኑ ተጠብቀዋል።

ወረሰየ ፍቁረ በፅንዐ ኃይሉ፡ በፅኑዕ ኃይሉ ይላል። በፅኑ ኃይሉ ወዳጅ አደረገ። ኃጥአንን አጥፍቶ ጻድቃንን፡ አሥሩን ነገድ አስማርኮ ሁለቱን ነገድ፡ ሁለቱን ነገድ አስማርኮ ነቢያት

www.zeyeneta.com

ካህናትን፡ የባቢሎንን ሰዎች እጥፍቶ ትሩፋንን፡ አይሁድን አጥፍቶ ምእመናንን፡ አጋንትን አጥፍቶ ነፍሳትን።

፫. ወየሐውር ቃል ቅድመ ገጹ። በፊቱ ቃል ይሄዳል ማለት ይማረኩ ብሎ፥ ያዝዛል ይማረካሉ። ይውጡ ብሎ ያዝዛል ያወጣሉ። እንድም በሩባቤል ከባቢሎን በወጣ ጊዜ ሳንቲ ዛጉፍ ዲቦ አንበሳ /አምቢልታ ቀንደ መለከት ነጋሪት/ እያሰመታ ወጥቷልና። አንድም ቃለ ዓዋዲ ዮሐንስ በፊቱ ይሄዳል አለ። መንፈት ጽንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል። እንድም ቃለ ወንዔል ዜጌሎ ፊት ትነገራለችና።

ወያዐወጽእ ውስተገጸም እምድኅረአገሪሁ። በአገሪሁ በስልምናሶር በናብከደነፆር አድሮ፡ ወደ እስራኤል ከተማ ይሄዳል።

ድኅረ አገሪሁ፡ እስራኤል ስልምናሶርን ናብከደነፆርን ይከተላሉ ይማረካሉ። አንድም በአገሪሁ፡ በቂሮስ በዳርዮስ አድሮ ወደ አሕዛብ ከተማ ይሄዳል። ድኅረ አገሪሁ እስራኤል ቂሮስ ዳርዮስን ይከተላሉ አለ ይወጣሉ። አንድም በአገሪሁ፡ በአግሩ ከሲቶስዮራ ወደ ቀራንዮ ይሄዳል። እንደጌትነቱ ፈረስ ሳቡልኝ ሠረገላ ጥረቡልኝ አይልም። ድኅረ አገሪሁ ጻድቃን እስጉ አብነት አድርገው ይመንናሉ። ተስቅለ አፍኣ እምተዕይንት እንዲል። ጥንቱን ከከተማ አፍኣ መስቀሉ እኔን አብነት /ምሳሌ/ አድርጋችሁ መንኑ ሲል ነውና። አንድም በአገሪሁ፡ በሐዋርያት አድሮ ወደ አሕዛብ ከተማ ይሄዳል። ድኅረ አገሪሁ፡ አሕዛብ ሐዋርያትን ይከተላሉ አለ ያምናሉ። አንድም በአገሪሁ በሄኖክ በኤልያስ አድሮ ወደ ሐሳዊ መሢሕ ከተማ ይሄዳል።

፮. ወሶበሂ ይቀውም ታድለቀልቅ ምድር። በመዓት በተነሳ ጊዜ ምድር ትናወጣለች። በዓዋዊ ኢየሩሳሌም፡ በሚጠት ባቢሎን በዕሰተ ዓርብ በቁሙ ኋላም ታልፋለች።

ወእመሂ ነጸረ ይትመሰወ አሕዛብ። በዓይነ መዓት በተመለከተ ጊዜ አሕዛብ እንዳሰም ይቀልጣሉ። በዓዋዊ ኢየሩሳሌም፡ /እስራኤል/ በሚጠት ባቢሎን /አሕዛብ/፡ በዕሰተ ዓርብ አይሁድ፡ በምጽአት ታጥአን።

ወይትቀጠቀጡ አድባር እምኃይሉ። ከኃይሉ የተነሣ ተራራዎች ይቀጠቀጣሉ አለ፡ የእስራኤል ነገሥታቱ ይማረካሉ።

ወይትመሰወ መኳንንቱ ይማረካሉ።

<u>አንድም</u> ወይትቀጠቀጡ። የባቢሎናውያን ነገሥታቱ ይጠፋሉ ወይትመሰወ መኳንንቱ ይጠፋሉ።

<u>አንድም</u> ወይትቀጠቀጡ። በዕሰተ ዓርብ ሐና ቀያፋ በጌቱ ታምራት ይቀጠቀጣሉ።

ወይትመሰወ፡ አውግር ዘአምዓለም። ሄሮድስ ጲላጦስ ድል ይነሣሉ ኋላም ያልፋሉ።

ወፍናቶሂ ዘእምዓለም ርኢኩ። ዛሬም ይህን ዓለም እምጎበ ቦ ጎበ አልቦ ስታሳልፈው እንዳየሁ ቀድሞ እምጎበ አልቦ ጎበ ቦ ፈጠርከው ሲሉ ሰማሁ። ዛሬ እሥሩን ነገድ ሁሉቱን ነገድ ስታስማርክ እንዳየሁ ቀድሞም ፷፱ /ስድስት መቶ ሺሁን/ አጋር በምድረ በዳ እንደሻሽ እንጥፊህ እንደቅጠል እርግፊህ እስቀረሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ፡ ዛሬ የባቢሎንን ሰዎች ስታጠፋ እንዳየሁ ቀድሞም ሰብእ ትካትን ሰብእ ሰዶምን እጠፋሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ። ዛሬ ስድንግል ያለ አባት ስትወለድ እንዳየሁህ ቀድሞም ከአብ ያለ እናት ተወለድክ ሲሉኝ ሰማሁ። ዛሬ በመስቀል ድል ስትነሳ እንዳየሁህ ቀድሞም ዲያብሎስን ቢከድ ጨለማ አጎናጽፈህ ዕመቀ ዕመቃት አወረድከው ሲሉኝ ሰማሁ።

፯. <u>አዕፃዳቲሆሙ</u> ኢትዮጵያ ይደነግጻ። የምድያም ነገሥታት ይደነግጣሉ።

አዕፃዳቲሆሙ ለብሔረ ምድያም። ምድያም ሰማስት ደገመው። በላዕሰ አፍላግስ ኢትትመዐዕ እግዚኦ። አቤቱ በአፍላግ በእስራኤል እንድ ጊዜ ብትፈርድባቸው ዘወትር አትፍረድባቸው አፍላግ ይላቸዋል፡ ፈሳሽ ውኃን እየተካፈሉ እንዲወስዱት እየማረኩ እየተካፈሉ ይወስዷቸዋልና።

፰. <u>ወኢይኩን</u> መዓትከ በላዕሰ አፍላግ። በአፍላግ በእስራኤል መዓትህ አይፅና

www.zeyeneta.com

ወኢ መቅሠፍትከ ዲበ ባሕር። በእስራኤል ከተማ መቅሥፍትህ አይፅና።
እስመ ተፅዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በስልምናሶር በናቡከደነፆር አድረሀ መጥተሃልና።
አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ስልምናሶር ናቡከደነፆር ሕይወት ናቸው። ለነቢያት ለካህናት። ሕያዋን ቢል እስከ ጊዜ ሞታቸው።
አንድም እስመተፅዕንከ ዲበአፍራሲከ። በቂሮስ በዳርዮስ አድረሀ መጥተሃልና።
አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ቂሮስ ዳርዮስ ሕይወት ናቸው። ለእስራኤል። ሕያዋን ቢል እስከ ጊዜ ሞታቸው።
አንድም እስመተጽዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በሐዋርያት አድረሀ መጥተሀልና አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ሐዋርያት ሕይወት ናቸው ሰምእመናን። ሕያዋን ቢል በነፍስ። አንድም እስመ ተጽዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በኪሩቤል ላይ ተቀምጠሀልና።
አፍራሲከኒ። ኪሩቤል ሕይወት ናቸው አሰ፡ ሰፍጡራን። ሕያዋን ቢል የባሕርይ።

፱. ወተርከ ወወሰቀ ቀስተከ ዲበ አብትር ይቤ እግዚአብሔር። እስራኤል ይሆንልኛል መስሎህ? /መስሎሃል/? በእሕዛብ ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ።
ፈለግስ ይሠጥቃ ሰምድር። ነገር ግን አንተ እንዳልከው አይደለም ፈለግ አሕዛብ ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።
አንድም ወተርከ ወወሰቀ ቀስተከ ዲበ አብትር አሕዛብ ይሆንልኛል መስሎህ? በእስራኤል ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ ፈለግስ። ነገር ግን እንተ እንዳልከው አይደለም።
ፈለግስ ይሠጥቃ ለምድር። ፈለግ እስራኤል ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።
አንድም ወተርከ። አሕዛብ ይሆንልኛል መስሎህ? በሐዋርያት ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ ፈለግስ ነገር ግን አንተ እንዳልከው አይደለም ፈለግ ሐዋርያት ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።

፲. ይሬእይክ ወይፄዐሩ አሕዛብ። አሕዛብ አይተውህ ይጸጸራሉ /ይቸገራሉ/ በዒዋዊ እስራኤል፡ በሚጠት አሕዛብ በምጽአት ኃጥአን።
ወይዜከሩ ማየ በውስተ ፍኖት። በጎዳና ውሃ ያስባሉ በዒዋዊ ደርቆባቸው ነበር።
ወአሥጡ ቀሳውቲሆሙ ዕራቆ እንዲል። በሚጠት ፈልቆላቸው ጠጥተዋል። አንድም ወይዘረዉ ከመ ማይ ይላል። ቀድሞ ደርቆብን ነበር ዛሬ ግን ፈልቆልን ጠጣን አያሉ።
ወመህበት ቀላይ ቃላ። ቤተ አስራኤል ቃሏን ሰጠች አለ። አመሰገነች
ወአልዐለት ግርማሃ። መፈራቷን አበዛች።

፲፩. ተንሥኡ ፀሐይ ወወርኀ ወቆሙ በሥርዐትከ። ፀሐይ ጨረቃ ተፈጠሩ በሥርዓትህ ጸንተው ኖሩ። አንድም የእስራኤል ፀሐይ ሲቀ ካህናቱ ወርኀ ንጉሡ ተማረኩ። በዒዋዊ ጸንተው ኖሩ። አንድም የባቢሎን ፀሐይ ንጉሡ ወርኀ ቢትወደዱ ጠፋ በጥፋቱ ጸንተው ኖሩ። አንድም የእስራኤል ፀሐይ ሲቀ ካህናቱ ወርኀ ንጉሡ ተመለሱ በሚጠት ጸንተው ኖሩ። እንድም በዕለተ ዐርብ ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ወቆሙ በሥርዓትከ እስከ ጊዜ ቀትር። ወፍናሠርከ ይበርህ ብርሃነ ፀሐይ አንዲል። ኋላም ያልፋሉ።
በብርሃነ ማዕበልከ የሐውሩ። ዓረብ ቅራ ጭሆ /እንደተሳለ ሰይፍ/ በሆነ ረድኤትህ ጸንተው ይኖራሉ።
ወበፀዳለ መብረቅ ወልታከ። እንደ ፀሐይ ደስ በሚያሰኝ ጋሻ ረድኤትህ ጸንተው ይኖራሉ።

፲፪. በመዓትከ ውኅደት ምድር። በፈረድክበት ቀን ምድር አነስች በዒዋዊ ኢየሩሳሌም፡ በሚጠት ባቢሎን፡ ኋላም ታልፋለች።
ወታጸድፎሙ ለእሕዛብ በመዓትከ። አሕዛብን ፈርደህ ታጠፋቸዋለህ።

፲፫. ወወጻእከ ለአድኅኖ ሕዝብከ። ወገናችህን ለማዳን ወጣህ።
ከመታድኅኖ ለመሲሕከ። ይልቁንም ቀብተህ ያነገሥከው ዘሩባቤልን ታድነው ዘንድ ወጣህ።

www.zeyeneta.com

አንድም ወወጻእከ ከመታድኅኖ ይላል። ልጅህን ታስነሳው ዘንድ ወጣህ።
ለአድኅኖ ሕዝብክ። ወገናችህን ሊያስነሳቸው ወጣ ድኂኖ እሞት አድኅኖሙ እንዲል።
ወወደይከ ውስተ አርእስቲሆሙ ለኃጥአን ሞተ። በኃጥአን ቸብቸቦ ሞትን አመጣህ።
ወአንሣእከ ማእሰረ ውስተ ክሣውዲሆሙ ለዝሉፋ። ከአንገታቸው ዛንጅርን አነሣህ አለ። አገዛዝን አጠፋህላቸው።
፲፬. ወመቲርከ አርእስተ ኃያላን እንዘ በድንጋጼ ይላል። በድንጋጼ ሳሉ የኃያላኑን ቸብቸቦ ቆረጥክ። ወይትሐወኩ ባቲ። በዚችም ያዝኑባታል አ ንድም ይትሐወኩ ባቲ። ይ ታወኩባት ዘ ንድ የኃያላኑን ቸብቸቦ ቆረጥክ። ምነው አንድ ብልጣሶር እይደለም ቢሉ ንጉሣዊ አነጋገር ከመዝ ይብሉክሙ ንጉሥ እንዲል። አንድም አሱ ከሞተ በኋላ ብዙ ሰዎች አልቀዋልና።

ታሪክ፦

እነዚህ ቂሮስ ዳርዮስ ተስለው ገጠሙ። ብልጣሶርን ድል ብናደርግ አስራኤልን ነፃ እናወጣለን ቤተእግዚአብሔር እንሠራለን ብለው። ሁለት ጊዜ ድል አደረጋቸው ሰለምን ቢሉ ኃይል የባሕርያችን ነው ባሉ ነበርና።
አንድም ኋላ ድል የሚያደርግ በፊት ድል መሆን ልማድ ነውና። እነዚህን ድል አድርጎ አዳራሽ ተገኘ። ከመኳንንቱ አንዱ ዛራ እንጂ አስራኤል ሳያረዱን ዋሉ /ቀሩ/ ልበ አበር /ግብረ አበር/ ቢሆኑ ነው አለ። አስራኤል ቢረዱስ ምን ሊጠቅሙ ባያረዱስ ምን ሊጎዱ ብሎ ናቡከደነፆር የአምላክ ዕቃ ለአምላክ ነው ብሎ አክብሮ ንዋየ ቅድሳቱን ከቤተ ጣዖት አኑሮት ነበር ጥንቱንም አባቱ አጥፍቷል ብሎ አስመጥቶ በጽዋው ቀድቶ ጠጣበት አጠጣበት በጻሕሉ ፈትፍቶ በላበት አበላበት። በዚህ ምክንያት ማኔ ቴቄል ፋሬስ እያለች እጅ ክንብን ስትጽፍ አይቶ /ታየች/ ይህን አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረኝ ሲሶ መንግሥት እሰጠዋለሁ አለ። የሚተረጉምለት ጦዱ አዝኖ ላለ የናቡከደነፆር ሚስት አያቱ ነበረችና ዛሬ

የልጂ ምላ ተመለገነለት ይሆን? ብላ ጠየቀች። ምላውስ ተመስግኖለት ነበር ነገር ግን አንዲህ ያለ ጽሑፍ ተገኝቶ አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረው አጥቶ አዘኗል አሏት። ሴት ችኩል ናትና ልብሷን /ልብሴን/ ልልበስ አላለችም ሄዳ ዛራ ምላው ተመለገነልህ? አለችው ምላውስ ተመለግኖልኝ ነበር ነገር ግን እንዲህ ያለ ጽሑፍ ተገኝቶ አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረኝ አጥቼ አላት። ለዚህማ ምን ይቸግርሃል ለአያትህ ለናቡከደነፆር ርእሱ ዘወርቅን የተረጉመለት ዳንኤል አለ እሱን አታስመጣውም አለችው ዳንኤል ተጠርቶ መጣ ይህን አንብበህ ተርጉመህ ብትነግረኝ ሲሶ መንግሥት እሰጥህለሁ አለው። ዳንኤልም መፍቀሬ ሚመት አይደለምና ሹመቱም ላንተ ይሁን አንብቤ ተርጉሜ እነግርሃለሁ። ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንዲሉ ለአዳም ከለማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን እንዳስገዛለት ለአባትህ ፀቱን መዓዝን ቢያስገዛለት አነ ውእቱ ዘአሠርቅ ፀሐየ አለ። በዚህ እስከ የአምር ልዑል ከመይኬንን መንግሥተ ደቂቀ ዕጓለ አመሕያው ወለዘፈቀደ ይሁብ /ወይሁብ ለዘፈቀደ/ ይላል። በጠለ ለማይ ተነክሮ ለባት ዓመት ዕሪያ ሆኖ ኖረ። አንተኒ ብልጣሶር ወልዱ አንተም የአራቢ /የፋቂ/ ልጅ አጥባቂ የአበያ ልጅ ወዳቂ የዘማ ልጅ ሳቂ የትዕቢተኛ ልጅ ናቂ እንዲሉ። አባትህ የአምላክ እቃ ለአምላክ ነው ብሎ አክብሮ ያኖረውን አምጥተህ በጽዋው ቀድተህ ጠጣህበት አጠጣህበት በጻሕሉ ፈትፍተህ በላህበት አበላህበት በዚህ ተጽፎብሃል ንባቡ በዕብራይስጥ ነው ማኔ ቴቄል ፋሬስ ትርጓሜው በሱርስት ነው ማኔ ማለት ለፈራ እግዚአብሔር ለመንግሥትክ ወሠለጣ ቴቄል ማለት ደለዋ ለመንግሥትክ ወተረክበት ሕጽጽተ ፋሬስ ማለት ተሥዕረት መንግሥትክ ወተውህበት ለፋርስ ወለሜዶን ማለት ነው። አለው ምንም ቢተረጉምበት አሕዛብ የተናገሩትን አያስቀሩምና ቢትወደድነት ጌትነት ለጥቶታል። ይህን ሲተረጉም የለማ ነው ይላሉ ጠጅ አሳላፊውም ነው ይላሉ ሲበጠብጠው ውሎ ነበርና ሌላ ከሚመለገንበት እኔ ልመለገንበት ብሎ ክተኛበት ቸብቸቦውን

www.zeyeneta.com

ቆርጦ ወስዶ ግዳይ /ምርኮ/ ጣለላቸው። አንተ ለጌታህ ያላዘንክ ብለው ተቀብለው ገድለውታል።
ወይከሥቱ እፋሆሙ ከመ ዘይበልዕ ነዳይ በጽሚት። ሁለት ሦስት ቀን ጦሙን ያደረ ደሀ ቀለ ብሎ እንዲያዋውጥ ቀለ ብለው ይናገራሉ የንጉሥ ሞት ደርሶ በለፍኣ አይነገርምና።

፲፮. አኬድክ ውስተ ባሕር አፍራሲክ። ስልምናሶር ናቡከደነፆርን በእስራኤል ከተማ አመላለስክ።
እንዘ የንሞጉ ማያተ ብዙኃ። ይኸውም ውሃውን እያደፈረሱ ነው አለ እስራኤልን እየማረኩ /እያጠፉ/ ነው።
አንድም አኬድክ ውስተ ባሕር አፍራሲክ። ቂሮስ ዳርዮስን በአሕዛብ ከተማ አመላለስክ።
እንዘ የሐጎምጉ ማያተ ብዙኃ። ይኸውም አሕዛብን እያጠፉ ነው። አንድም አኬድክ ውስተ ባሕር አፍራሲክ። ሐዋርያትን በአሕዛብ ከተማ አመላለስክ
እንዘ የጎምጉ ማያተ ብዙኃ ይኸውም አሕዛብን እያሳመኑ ነው።

፲፯. አስተሐየጽኩ ወደንገፀኒ ልብየ። ያህን ሁሉ ተመልክቼ ልቡናዬ ደነገጠብኝ።
እምቃለ ጸሎተ ከናፍርየ። ግለጽልኝ ብዬ ከጸለይኩት ጸሎት የተነሣ ለዚህ ብሎ ገብቶ ኮሯል ቢሉ አምን። አንድም ለሌላ ከነባ ዘንድ ተገልጾለታል።
ወበአ ረዓድ ውስተ አዕፅምትየ። በሰውነቴ ረዓድ እንቅጥቅጥ አደረ።
ወተንሥጣ ኵሉ ፈቃድየ በመትሕቴየ። በሰውነቴ ውስጥ ያሰ ልቡናዬ በኃዘን ደፈረስ
ወአዐርፍ በዕለተ ምንዳቤየ። በመከራዬ ቀን አርፋለሁ።
ለዐሪግ ውስተ ሕዝበ ፍልስጥኤም። ወደ ፍልስጥኤም ለመውጣት መክሬሃለሁና። ዐሪግየ ቢል ወደ ፍልስጥኤም ወጥቼ አርፋለሁ።

፲፰. እስመ በለስኒ ኢትፈሪ። በለስ አታፈራምና
ወኢይከውን ፍሬ ውስተ ዐጸደ ወይን። በወይን ቦታ ፍሬ አይገኝምና ትሑሱ ግብራ ዘይት። ዘይት ቅብዕነቷን ታብላለች

ወምድርኒ ኢትገብር ሲሳተ። ምድርም አዝርዕትን አትከልትን አታስገኝምና።
ተጎድሷ አባግዕ አመብልዕ። አምተበልያ ሲል ነው። አባግዕ ከመበላት ርቀዋልና የድርቅ በግ አይብሳምና
ወአልህምትኒ ኢይትረከቡ በውስተ ጎል። አልህምት ክበረት አይገኙምና እንዲህ ያለ ጽኑ መከራ ይመጣልና ወጥቼ አርፋለሁ።
አንድም አስመ በለስኒ ኢትፈሪ። በለስ ዘይቤ ቤተ እስራኤል አሙንቱ እንዲል። እስራኤል ምግባር ሃይማኖት አያስገኙምና
ወኢይከውን ፍሬ ውስተ ዓፀደ ወይን። ዓፀደ ወይኑስ ለእግዚአብሔር እስራኤል አሙንቱ አንዲል። በእስራኤል ልቡና ምግባር ሃይማኖት አይገኝምና ትሑሱ ግብራ ዘይት። መምህራን አያስተምሩምና
ወምድርኒ ኢትገብር ሲሳተ። እርድኣት አይማሩምና ተጎጉሉ አባግዕ አመብልዕ። እስራኤል ከመሥዋዕትነት ርቀዋልና አለ ደስ ከማለኝት።
ወአልህምትኒ ኢይትረከቡ በውስተጎል። መምህራን በጉባኤ አይገኙምና እንዲህ እንዲህ ያለ ጽኑ መከራ ይመጣልና ወጥቼ አርፋለሁ።

፲፱. አንስ እትፌሣሕ በእግዚአብሔር። ስለነዚያ /ለነዚያ/ ነው እኔ በእግዝአብሔር አምኜ ደስ ይለኛል።
ወእትሐሠይ በአምላኪየ ወመድኃንየ። በፈጣሪዬ በመድኃኒቴ አምኜ ደስ ይለኛል።

፳. አግዚአብሔር አምላኪየ ወኃይልየ። እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ኃይሌ ዘይሠርፆን ለእገርየ ወለፍጸሜየ። እግሮቼን ፈጽሞ የሚያቅናናቸው /የሚያቀናቸው/ እሱ ነው።
ወዲበ ልዑላት ያጸዕነኒ። በኃያላኑ ላይ ያሠለጥነኛል። ፩ቱን ነገሥተ ፍልስጥኤም ይዞ፡ ፪ቱን ነገሥተ አሕዛብን ፪ቱን ነገሥተ ፍልስጥኤም ይዞ አምስቱን ነገሥተ አሕዛብ ድል አድርጓል።
ከመ አማዕ በመኃልይሁ። እሱን በማመስገን ድል አነሳ ዘንድ በፍኖቱ ቢል ሕጉን በመጠበቅ ድል አነሣ ዘንድ።

www.zeyeneta.com

፲፪. ጸሎተ ኢሳይያስ ነቢይ

ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። ኢያሱ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት እንደሆነ። ይኸውም መድኃኒት መባሉ አንደ ኢያሱ ባሜር ታጥቆ ዘገር ነጥቆ የእስራኤልን ጠላት አጥፍቶ እንደ ጌታ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ዓለምን አድኖ አይደለም። መክሮ አስተምሮ ነው። ይህን ስሙንም እናት አባቱ በ፰ ቀን ኢሳይያስ ብለውታል። አንድም ነቢያት ካህናትን ማን እንበለው ብለዋቸው መክሮ አስተምሮ መድኃኒት እንዲሆን ተገልጸላቸው ኢሳይያስ በሉት ብለዋቸዋልና ኢሳይያስ ብለውታል። አንድም ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው። በዚህ በተሰጠው ትንቢቱ ሕዝቡ በሕገ ሲና አሕዛብ በሕገ ልቡና ረብህ ጥቅም እንዳላገኙ ሲያጠይቅ በእስራኤል ፫፡ በእሕዛብ ፪፡ ነገር ይናገራል። በእስራኤል ሦስት ነገር። አባር ቸነፈር፡ ፄዋዌ ሚጠት። እሊህ ሦስቱ ሥጋውያን ለሦስቱ መንፈሳውያን አምሳል መርገፍ፡ ናቸው። እንደአባር ቸነፈር ርኂቅ እምእግዚአብሔር፡ እንደ ፄዋዌ ፄዋዌ ነፍስ፡ እንደሚጠት ሚጠተ ነፍስ፡ ፄዋዌ ሚጠት አንድ ወገን ነው ብሎ፡ ሦስተኛ ሥጋዌወልደእግዚአብሔርን ተናግሯል። በአሕዛብ አራት፡ ትእምርት አፍርሆ። ትእምርት አሕዛብን ሲያጠፋ አይተው እስራኤል ምልክት ያደርጋሉ አፍርሆ ሕግ ያልሠራላቸው አሕዛብን እንዲህ ሲያደርግ እኛን እንዴት ያደርገን ብለው ይፈራሉ፡ ሦስተኛ አምላካችን አይደለም ይላሉ የግድ አምላካቸው እንደሆነ። አራተኛ በደባያት /በወንፈል በተራ/ እንዲጠፋ። ትእምርትና አፍርሆ ይጎራብታሉ ብሎ። ሁለተኛ አምላካችን አይደለም ይላሉ። የግድ አምላካቸው እንደሆነ። ሦስተኛ በደባያት እንዲጠፋ። አራተኛ ላያናግር /ላይናገር/ እንዳያጠፋ ሠረይነ ስብአ ወኢያሕየውነ /ወኢያሕዮነ/ ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢተፈወስት እያሉ። ይህ ሲነበብ ሲተረጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደረስ ሐዋርያትም ፸፩ መጻሕፍትን ቆጥረው ለቀሌምንጦስ ሲሠጡ አንድ መጽሐፈ ኢሳይያስ ብለው ቆጥረዋል። ይህም ለስንቱ የተጻፈ አይደለም። እኛ ልንመክርበት ልንገሠጽበት ነው እንጅ።

ወኵሉ ዘተጽሕፈ ሰተግሣጸ ዚእነ

ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወከሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ እንዲል። ይህ ተራው ከሕዝቅያስ ነው። የአመቤታችን ባለሟል እንደሆነ ለማጠየቅ ከዚህ አምጥተው ጠርዘውታል። ኢሳይያስ የተናገረው ነገር ይህ ነው።

፩. በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ አግዚኦ አምላኪየ። አቤቱ ፈጣሪዬ በሌሊት ልቡናዬ በጸሎት በአምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች።

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር። በመንፈቀ ሌሊት ተነሥታችሁ አመስግኑ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና ጨለማ አይከሰከሰውምና።

አንድም በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ አግዚኦ አምላኪየ። ሕዝቅያስ ነው በሌሊት መከራ ተይዤ ሳለሁ ልቡናዬ በጸሎት በአምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች።

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር። ሕዝቅያስ ይዳን ሠናከሬም ይጥፋ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደብርሃን ደስ ያሰኛልና።

አንድም በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ አግዚኦ አምላኪየ። ትፋፍ ነው። ፎ ዘመን ልቡናዬ በጸሎት በአምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች። እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር። ትፋፋን ይዳኑ ባቢሎናውያን ይጥፉ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛልና።

አንድም በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ አግዚኦ አምላኪየ። አዳም ነው አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ልቡናዬ በአምልኮት ወዳንተ ትገሠግሣለች።

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር። ነፍሳት ይዳኑ አጋንንት ይጥፉ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛልና።

ተመሐሩ ዝሪረ ጽድቅ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም። በዚህ ዓለም የምትኖሩ አስሩ ነገድ ሁሉቱ ነገድ ዝሪረ ጽድቅን ተማሩ።

፪. እስመ ኀልቀ ኀጥአ ዘኢይትሜሀር ዝሪረጽድቅ በዲበ ምድር። በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር

www.zeyeneta.com

ወኢይገብር ሠናየ። በጎ ሥራ የማይሠራ ስድስት መቶ ሺህ አጋር በምድረበዳ እንደሻሽ ተነጥፎ እንደ ቅጠል ረግፎ ቀርቷልና።
አንድም ተመሐሩ ገቢረጽድቅ እስ ትነበሩ ውስተ ዓለም። በዚህ ዓለም የምትኖሩ እስ ሕዝቅያስ ገቢረ ጽድቅን ተማሩ።
እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜህር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር። በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር
ወኢይገብር ሠናየ። በጎ ሥራ የማይሠራ ሰናክሬም ጠፍቷልና።
አንድም ተመሀሩ ገቢረጽድቅ እስ ትነብሩ ውስተ ዓለም። ትሩፋን ገቢረ ጽድቅን ተማሩ። እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜህር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር። በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር
ወኢይገብር ሠናየ። በጎ ሥራን የማይሠራ ብልጣሶር ጠፍቷልና።
አንድም ተመሀሩ ገቢረ ጽድቅ እስ ትነብሩ ውስተ ዓለም። ምእመናን ገቢረ ጽድቅን ተማሩ።
እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜህር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር። በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር
ወኢይገብር ሠናየ። በጎ ሥራን የማይሠራ ዲያብሎስ በመስቀል ድል ተነስቷልና።
የአትትዎ ለጎጥእ። አሥሩን ነገድ በዔዋዊ ያርቁታል።
ከመ ኢይርእይ፡ ስብሐተ እግዚአብሔር። ስሁስቱ ነገድ የተደረገውን ታምራት እንዳያይ። አንድም የእትትዎ ለጎጥእ። ሠናክሬምን ከለኪሶን ያርቁታል።
ከመ ኢይርእይ ስብሐተ እግዚአብሔር። እለ ተቅዋመ ወርቅን እለ ማዕጠንተ ወርቅን እንዳያይ አንድም አበውን በሞት ያርቁታል።
ከመ ኢይርእይ። ስውሉድ የተደረገውን ታምራት እንዳያይ።

አንድም የእትትዎ ለጎጥእ። ይሁዳን ከደብረ ታቦር ያርቁታል።

ከመ ኢይርእይ። ብርሃነ መለኮቱን እንዳያይ። ምነው ጌቱስ ቀርተው የለም ቢሉ ስምንቱ ቅሉ የቀሩ በሉ ምክንያት ነውና። አንድም ሥላሴ ጎጥኦን በሐሩታ ያርቁታል። ከመኢይርእይ ኢይረስ ይላል። ክብሩን እንዳይወርስ ኢይራእያ ያለውን ኢይወርሳ ብሎ እንደተረጐመው።

፫. እግዚኦ ልዑሰ መዝራዕተከ ኢያእመሩ። አቤቱ አስሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም
እምከመስ አእመሩ ይትሐፈሩ። ለልሳውን እልፍ አጋር በምድረ በዳ እደሻሽ አንጥፎ እንደቅጠል አርግፎ አስቀራቸው ሲሉ እየስሙ ምነው አያውቁም ትለኝ እንደሆነ ካወቁማ /ስ/ ያዋቂ አጥፊ ናቸውና ይጥፉ።
አንድም እግዚኦ ልዑሰ መዝራዕተከ ኢያእመሩ። አቤቱ የባቢሎን ለምኞ ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም።
እመከመስ አእመሩ ይትሐፈሩ። ሰብአ ትካትን ሰብአ ሲዶምን አጠፋህ ሲሉ እየስሙ ምነው አላወቁ ትለኝ እንደሆነ ካወቁስ /ማ/ ያዋቂ በዳይ ናቸው፡ ይጥፉ
እግዚኦ ልዑሰ መዝራዕተከ ኢያእመሩ። አቤቱ አብ አይሁድ ልዑል ልጅህን የባሕርይ አምላክ እንደሆነ እላወቁም ። ከልሙዕ ግንባር /ከደረቅ ግንባር/ ዓይን ሊፈጥር የአራት ቀን ራሳ ሲያስነሳ አያዩ ምነው አያውቁ ትሰኝ እንደሆነ ካወቁስ አዳለፈው።
አንድም እግዚኦ ልዑሰ መዝራዕተከ ኢያእመሩ። አቤቱ ወልድ አይሁድ ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም።
እምከመስ አእመሩ ይትሐፈሩ። በልሙዕ ግንባር ዓይን ሊፈጥር የአራት ቀን ራሳ አልዓዛርን ሲያስነሳ አያዩ ምነው አያውቁ ትለኝ እንደሆነ ካወቁስ እንዳለፈው።
ቅንዓት አጎዘሙ ለሕዝብ አብዳን። ስነፍች ወገኖችን ቅናት ያዛቸው በዔዋዊ አለራኤልን፡ በሚጠት አሕዛብን፡ በዕለተ ዓርብ አይሁድን፡ በዕለተ ምጽአት ኃጥአንን።
ወይእዜኒ አሳት ትበልያሙ ለፀር። አሁንም ጠላቶችህን መቅሠፍት ታጠፋቸዋለች።

www.zeyeneta.com

፱. እግዚኦ አምላክነ ስላመ ሀበነ። እቤቱ ፈጣሪያችን ፍቅር አንድነትን ስጠን።
እስመ ኵሉ ወህበከነ መከራውን ሁሉ አምጥተህብናልና።
፳. እግዚኦ አምላክነ አጥርየነ። እቤቱ ወገኖችህ አድርገን
እግዚኦ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር። እቤቱ ያለ አንተ ልዩ ጣዖትን እናውቅምና።
ወስመ ዚአከ ንጼውዕ። ስምህንም በጸሎት በአምልኮት እንጠራሰን።
፳፩. ሙታንሰ ኢይራእይዋ ሰሕይወት። ሙታን ልቡና አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ሕይወትን እያይዋትም።
ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ነቢያተ ሐሰት አንተ የገደልከውን ማዳን /ማንሳት/ አይቻላቸውምና።
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ። ስለዚህ ነገር ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን አምጥተህ አጠፋሀቸው።
አንድም ሙታንስ ኢይራእይዋ ሰሕይወት። መታን ሕሊና /ልቡና/ አሰ ሠናክሬም ሕይወትን እያይዋትም።
ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ካህናተ ጣዖት አንተ የገደልኸውን ማዳን አይቻላቸውምና
በእንተዝ። ስለዚህ ነገር ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን አምጥተህ አጠፋሃቸው አንድም ሙታንሰ ኢይራእይዋ ለሕይወት። ሙታን ሕሊና አሰ ሠናክሬም ሕይወትን እያይዋትም።
ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ካህናተ ጣዖት አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውምና
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ። ስለዚህ ነገር ቅዱስ ሚካኤልን አምጥተህ አጠፋሃቸው አንድም ሙታንሰ ኢይራእይዋ ለሕይወት። የባቢሎን ሰዎች ሕይወትን አያይዋትም። ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ካህናተ ጣዖት እንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም።
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ። ስለዚህ ነገር ቂሮስ ዳርዮስን አምጥተህ አጠፋሀቸው። አንድም ሙታንሰ ከሥጋቸው የተለዩ ነፍሳት አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ሕይወተ ነፍስን አያይዋትም

ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ነቢያተ ጽድቅ ስብ አጢሰው ደም አፍስሰው አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም።
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ። ሎሙ ይላል። ስለዚህ ነገር አምላኪየ እምላኪየ ብለህ ጸልየህ ዲያብሎስን አቅርበህ ድል ነሣህላቸው።
አንድም ሙታንሰ ኢይራእይዋ ለሕይወት። ሙታነ ልቡና አይሁድ ሕይወት ወልድን አያዩትም። ወትፈትዉ አሐተ ዕሰተ እመዋዕሊሁ ሰወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዲል ወየው ከሟቹቱ ዘመን አንዲቱን ቀን አግኝተናት ብለዋል።
ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ። ካህናተ ኦሪት አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም።
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ። ስለዚህ ነገር ጥጦስ አስባስያኖስን አምጥተህ አጠፋሀቸው።
ወአእተትከ ኵሉ ትዕቢቶሙ። ትቢታቸውን ሁሉ አራቅህ
ወለኮሙ እግዚኦ እኪተ። እቤቱ በመከራ ላይ መከራ አምጣባቸው።
፳፪. ወለኮሙ እግዚኦ እኪተ ለከቡራን ምድር። ከቡራን ምድር በሚሆኑ በነዚህ በመከራ ላይ መከራ አምጣባቸው። ከቡራን ምድር ይሳቸዋል። በወዲያው ዓሰም ከብር የሳቸውምና።
፳፫. እግዚኦ በምንዳቤየ ተዘከርኩከ። እቤቱ በመከራዬ ጊዜ አሰብኩህ ወበጎዳጥ ሕማም ገሠጽከኒ። በጥቂት መከራ ገሠጽከኝ።
፳፬. ከመእንተውስተማሕምም እንተአልጸቀት ሰወሊድ። ለመውሰድ የቀረበች ሴት እንድትጨነቅ
ወአውየወት በሕማማ። በምጣ ጊዜ እንድትጮህ
ከማሁ ኮነ ለፍቁርከ።
ከማሃ ኮነ ለፍቁርከ። ለወዳጅህ ለሕዝቅያስ ተጨነቅንለት አንድም ከማሃ ኮነ ፍቁርከ። ወዳጅህ ሕዝቅያስ እንደሷ ተጨነቀ። አንድም ከማሃ ኮነ ለፍቁርከ። ለወዳጅህ ለትሩፍ እንደሷ ተጨነቅንለት።
ከማሃ ኮነ ፍቁርከ ወዳጅህ ትሩፍ እንደሷ ተጨነቀ አንድም ከመሃ ኮነ ለፍቁርከ። ለወዳጅህ ለአጣም አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን እንደሷ ተጨነቅንለት። አንድም ከማሃ ኮነ

www.zeyeneta.com

ፍቁርከ፡ ወዳጅህ እዳም እምሰት ሺ ክአምሰት መቶ ዘመን እንደሷ ተጨነቀ።።

፲. በእንተ ፈሪሆትከ እግዚኦ ጸነሰነ።። እምልኮትህን ስለጣልን /ስላልጠበቅን/ ዒዋዊ አለ ሲሉ ሰማን።።
ሐመምነሂ ወወሰድነ።። በአባር በቸነፈር ተያዘን ዒዋዊ አገኘን።።
አንድም በእንተ ፈሪሁትከ እግዚኦ ጸነሰነ።። እምልኮትህን ስለጠበቅን ሚጠት አለ ሲሉ ሰማን።።
ሐመምነሂ።። ሰባ ዘመን በመከራ ተያዘን
ወወልድነ።። ሚጠትን አገኘን አንድም በእንተ ፈሪሁትከ እግዚኦ ጸነሰነ እምልኮትህን ስለጣልን ዒዋዊ ነፍስ አለ ሲሉ ሰማን
ሐመምነሂ።። ርኀቅ እም እግዚአብሔር አገኘን።።
ወወሰድነ።። ዒዋዊ ነፍስ አገኘን።። አንድም በእንተ ፍሪሆትከ አምልኮትህን ስለጠበቅን ሚጠተ ነፍስ አለ ሲሉ ሰማን።።
ሐመምነሂ።። እምሰት ሺ ክአምሰት መቶ ዘመን በመከራ ነፍስ ተያዘን ወወሰድነ።። ሚጠተ ነፍስ አገኘን።።
መንፈስ እድኅኖትከ በዲበ ምድር።። ትድግናህን የምትፈጽምበት ረድኤትህ በዚህ ዓለም ሰምእመናን ይደረግ።።

፲፩. ሙታን ይትነሥኡ።። ሙታን ይነሣሉ ሁሰቱ ነገድ
ወየሐይዉ አለ ውስተ መቃብር።። አሰሩ ነገድ
ወይትፈሥሑ አለ ውስተ ምድር።። ስልምናሶር ናቡከደነጾር መጣ መጣ ሲሏቸው ሰምተው ሸሽተው የሔዱት።። ወይነግሩ ሠናይቶ ለእግዚአብሔር ለደሰያት ወሰግብጽ የሚሳቸው።።
አሰመ ጠል ዘአምኃቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።። ካንተ የተገኘ ጠሰ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና።።
አንድም ሙታን ይትነሥኡ።። ሙታን አለ ሕዝቅያስ ይነሣሉ።።
ወየሐይዉ አለ ውስተ መቃብር።። በለኪሶን ያሉት
ወይትፈሥሑ አለ ውስተ ምድር።። ሠናክሬም መጣ መጣ ሲሏቸው ሸሽተው የሄዱት
አለመ ጠል ዘአምኃቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።። ካንተ የተገኘ ጠለ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና።።
አንድም ሙታን ይትነሥኡ፡ እንደ ወልደ መበለት እንደ ወስተ ኢያኢሮስ ያሉት ይነሣሉ።።

ወየሐይዉ አለውስተ መቃብር።። አንደ አልዓዛር ያሉት
ወይትፈሥሑ አለ ውስተ ምድር።። ድውያን ደሰ ይሳቸዋል።።
አንድም አሰመ ጠል ዘአምኃቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።። ካንተ የተገኘ ጠል ወልድ ሕይወታቸው ነውና።።
አንድም ሙታን።። በራሳቸው ፍዳ የተያዙት
ወየሐይዉ።። በራሳቸው ፍዳ ላይ በአናት ባባታቸው ፍዳ የተያዙት
ወይትፈሥሑ አለ ውስተ ምድር።። ምአመናን ደስ ይሳቸዋል።።
አሰመ ጠል ዘአምኃቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።። ካንተ የተገኘ ጠል ወልድ ሕይወታቸው ነውና።።
አንድም ሙታን ይትነሥኡ።። ያልተቀበሩት ይነሣሉ እንደ አርማጌዶን /የጥፋትና የጦርነት ቦታ/።።
ወየሐይዉ አለ ውስተ መቃብር።። የተቀበሩት ይነሳሉ።።
ወይትፈሥሑ።። ገብር እምገብር ተሰውጠው /ወዲያው አርፊው የሚገቡት/።።
ንሕነሰ ንትዌለጥ በምዕር ከመ ቅጽበተ ዓይን ወእንበጸ፡ሐመ ሰምዉታን የሚላቸው።።
አሰመ ጠል ዘአምኃቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ።። ካንተ የተገኘ ጠል ሕይወታቸው ነውና።። በዕሰተ ምጽአት ጠሰ ምሕረት አሰ።። የሚያርከፈከፍ /የሚያከፈከፍ/።።
ወታጠፍዕ ምድርሙ ለነጥአን።። የንጥአን ምድራቸውን ታጠፋሰህ።። በዒዋዊ ኢየሩሳሌም፡ በሚጠት ባቢሎን፡ ኋላም ሀገረ ነፍሳቸውን ታጠፋሰህ።።

፲፪. ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ።። ወገኔ ሁሰቱ ነገድ ወደ ቤትህ ግባ።።
ወዕፁ ኖኅተከ።። ደጅህን ዝጋ።።
ወተንባዕ ጎዳጠ ምዕረ።። ጥቂት ሰዓት ተሠወር ስአስሩ ነገድ እረዳሰሁ አትበል።።
አስከ የኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር።። የእግዚአብሔር መዓቱ በአስሩ ነገድ እስኪያልፍ ድረስ።። እግዚአብሔር ሰፈረደበት ሰው እረዳሰሁ ማስት መከራው ይትረፈኝ ማስት ነውና።።
አንድም ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ።። ወገኔ ሕዝቅያስ ወደ

www.zeyeneta.com

ቤትህ ግባ። ወዕፁ ኖኅተከ። ደጅህን ዝጋ። ወተኅባዕ ኅዳጠ ምእረ። ጥቂት ስዓት ተሠወር ከስናክሬም ጋር እዋጋለሁ አትበል
እስከ የኀልፍ። የእግዚአብሔር መዓት በሰናክሬም እስከሚያልፍ ድረስ
አንድም ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ። ወንጌ ምእመን ወደ ቤተ ልቡናህ ግባ
ወዕፁ። ህዋሳትህን ስብስበህ ጸልይ
ወተኅባዕ ኅዳጠ ምእረ። ጥቂት ስዓት ተሠወር
እስከ የኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር። የእግዚአብሔር መዓቱ ይህ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ። መዓት አለው ይህን ዓለም። መዓቱም ምሕረቱም የሚደረግ /መደረጉ/ በዚህ ዓለም ነውና።

፲፫. ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም

ማርያም ማለት ጸጋ ወሀብት ማለት ነው። ለጊዜው ለእናት ለአባቷ ጸጋ ሀብት ሆና ተሰጥታለች። ለኋላው ግን ላመነባት ሁሉ ጸጋ ክብር ታሰጣለችና። አንድም ፍጽምት ማለት ነው። ስጊዜው መልክ አቀናን ከደም ግባት ጋራ አስተባብራ ይዛ ተገኝታለች ለኋላው ግን ድንጋሌ ሥጋ ከድንጋሌ ነፍስ አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና። አንድም ልዕልት ማለት ነው። መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናትና። ወአልቦ ዘይከብር እምኔሃ እምታሕተ እግዚአብሔር እንዲል። አንድም ተለአኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው። ስውንና እግዚአብሔርን የምታስታርቅ። ወአምጽኡ ማሬ ዘድዮስ እንዲል። ተፈሥሒ ቤተ ይሁዳ ወተሐሠዪ ቤተ እስራኤል። በሷ መወለድ እስሩን ነገድ ሁለቱን ነገድ ደስ ብሷቸዋልና። አንድም መርሕ ለመንግሥተ ስማያት ማለት ነው። ያመነባትን ሁሉ አስከትላ ፌታውራሪ ሆና ይዛ ገነት መንግሥተ ስማያት ታገባለችና /ታስገባለችና/ አንድም ማኅበረ ማሄያምናን ወመሄያምናት ማለት ነው። ሕዝቡን አሕዛቡን አንድ የምታደርግ አንድም ፀሐይ ማለት ነው። አስቴር ማለት ፀሐይ ማለት እንደሆነ ሠረገላ ፀሐይ ማለትም ነው። ማሪሃም የሚል አብነት ይገኛል። እመ ብዙኃን እግዝእተ ብዙኃን

ማለት ነው። አብርሃም ማለት አበ ብዙኃን ማለት እንደሆነ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ።

ታሪክ፦

ሐና ኢያቄም የሚባሉ ባልና ሚስት ነበሩ ልጅ አልነበራቸውም ልጅ ባለመውለዳቸው ያዝኑ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ቤተ እግዚአብሔር ደጅ ለመጸናት /እጅ ለመንሳት/ ከሄዱ ዘንድ ወርአዩ አርጋበ አንዘ ይትፌሥሑ በውስጠዮሙ ይላል። አርጋብ በልጆቻቸው ተድላ ደስታ ሲያደርጉ አያተው ሁሉ እንዲህ ይበዛል የኛን ተፈጥሮ ከደንጊያ አድርገኸዋል? ብለው አዘኑ ራአይ ያያሉ ለሷ የብርሃን መቀነት ሲሰጣት ለእሱ የብርሃን መቋሚያ ሲሰጡት። ተስለው ይሄዳሉ ወንድ ቢሆን እኛን ይረዳን ያጥባን ያገልግለን እንልም ሴትም ብትሆን እኛን ትርዳን ታጥባን አንልም መሶበ ወርቅ ስፍታ ግምጃ ፈትላ ለዜናእግዚአብሔር ታገለግላለች ብለው ተስለው ወጡ። ወአአመራ ለሐና ይላል። በግብር አወቃት አመቤታችን ተጸነሰች ተወለደች በተወለደችም ጊዜ ነዳያንን ምስኪናንን ጠርተው ምሳ አድርገዋል። በተወለደች በሦስት ዓመት ይህችን ሕፃን ተስለን ወልደናታል ዘመድ ሳትወድ እህል ሳትለምድ እንስጥ ብለው ሄዱ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ነበር ተቀበለን አሉት የስእለት ልጅ እኔ ለብቻዬ እንዴት እቀበላለሁ መጥቅዕ ይመታ ሕዝቡ ይሰብሰቡ የምግቢ ነገር ይመከር እንጂ አላቸው። ከዚህ መሀል ያች ሕፃን ተራበች መልአኩ ፋኑኤል ጉብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዞ መጣ ዘካርያስ ዛሬስ ክብሬን ባደባባይ ሊገልጽልኝ ነው ብሎ ሊቀበል ተነሣ ወደ ላይ ለቀበት /ራቀበት/ ሐና ልትቀበል ተነሣች ወደ ላይ ለቀቀባት /ራቀባት/ የጌታ ነገር አይታወቅም ይህችን ሕፃን ትታችኋት ፈቅ በሉ አላቸው። ትተዋት ፈቅ አሉ /ቢሉ/ አንድ ክንፉን አከናንቦ /አጎናጽፎ/ አንድ ክንፉን አንጥፎ አብልቷት አጠጥቷት ዓረገ። እኛ መጥቅዕ ይመታ ሕዝቡ ይሰብሰቡ ያልን ለምግቢ ነበር፡ ጌታ የማይጨርሰውን ይጀምራል? ምግቢ ሰማያዊ ከሆነ አግብታችሁ ከቤተመቅደስ አትሯት አለ። ፲፪ ዓመት ዕልተርቢዝ ዕልተግቢጥ /የዘመድ ፍቅርና ልማደ ሰብእ/ ጠፍቶላት ኖራለች። ጥንቱንም ኑሮባት አይደለም ከእናት ከአባቷ ቤት ፫ ዓመት ከቤተ

www.zeyeneta.com

መቅደስ ፲፪ ዓመት ፲፩ ዓመት ሲሆናት ካህናቱ ተሰብሰበው ልማደ እንስት አላት /ያለባት/ መስሏቸው ይህች ሕፃን አቅመ ሔዋን እደረሰች ቤተ መቅደስ ታስተራኩሳለች /ታሳድፋለች/ ብለው (ላቲ ስብሐት) ሄደው ታገቢ በድንግልና ትኖሪ አሏት። እንደእላችሁኝ አንጂ አሰቻቸው /አሰች/ እንዲህ ማለቷ እንኳን ገቢር ጎልዮ ኑሮባት አይደለም ፈጻሚተ ፈቃድ ናትና። እነሱም እኛማ ከሕገ እንስሳ ሕገ ሰብእ ከሕገ ሰብእ ሕገ መላእክት አንዲበልጥ አናውቅ የለም? በንጽሕና ልትኖሪ /ብትኖሪ/ እንወዳለን አሏት። ካላችሁስ ስንኳን ገቢር ጎልዮ የሰብኝም አለቻቸው። የዚች ሕፃን ነገር ከንቱ የሚቀር አይደለም ልብሰ ተክህኖ ለብሰ ዕጣን አጥነህ ቃለ እግዚአብሔር ጠይቀህ ንገራት አሉት። ዘካርያስም ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ዕጣን አጥኖ ቃለ እግዚአብሔር ቢጠይቅ ከቤተ ይሁዳ ሚስቱ የሞተችበትን ሰው ብትር ለብስብ ከብትሩ ምልክት የተገኘበት ይጠብቅ አለው ለሁለት ሺህ አሥራ አምስት የጎደለው (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስማኒያ አምስት) ብትር ተለበለበ። አራት ሺህም የሚል አለ። በነረ ማርያም። ሞተ አንስት የበዛበት ወራት ነውና /ነበርና/ ኋላ ከዮሴፍ ብትር ዕቀባ ለማርያም ፍሕርትከ የሚል ጽሑፍ በግብር አምላካዊ ተጽፎ ተገኘ። አንድም ርግብ ከብትሩ ወርዳ ከራሱ ላይ ተቀመጠችበት /ስትቀመጥ ታየች/። አንድም እጣ ቢጣጣሉ ለእርሱ ደረሰ እንደ ሦስት ምስክር፡ ጠብቅ አሉት። እኔ እናት የሌላቸው ልጆች የማሳድግ ነኝ ወዲያውስ ሞፈር ድግር ጠርቤ ያንን ሸፎ የማድር አንደምን አድርጎ ይሆንልኛል አላቸው። የኛ ትእዛዝ አይደለም ትእዛዘ እግዚአብሔር ነው። አይሆንም ብትል አንተ ሰራስህ ታውቃለህ አሉት፡ ይሟት ሄደ ።

ወበሳድስ ወርኅ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ አምላክ እግዚአብሔር ኀበ አሐቲ ሀገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት። በስድስተኛው ወር ገብርኤል የገሊላ ክፍል የምትሆን ናዝሬት ወደምትባል አገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። ሳድስ ወርኅ ለኤልሳቤጥ ጽንስ ነው። ወእምዝ ጸንሰት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ ይላል። ዮሐንስ የመስከረም አመ ፴ ተጸንሳል መጋቢትን ለመስከረም ሳድስ አለ። ስለምን በስድስተኛው ወር ተላከ ቢሉ

በስድስተኛው ቀን የተፈጠረ አዳም በድሉ ነበርና እሱን ለማዳን በሱ የሄደችውን ልጅነት ለመመለስ እንደመጣ ለማጠየቅ። ስለምን በዚህ ወራት ተላከ ቢሉ በዚያ ወራት የተፈጠረ አዳም በድሉ ነበርና እሱን ለማዳን በእሱ የሄደች ልጅነትን ለመመለስ እንደመጣ ለማጠየቅ። እንድም በስድስተኛው ሺ ለምን ተላከ ቢሉ በሐሙስ ዕለት ወነመንፈታ ለዕለት እትወለድ አምወለተ ወለትከ ያለው አንደደረሰ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ። ስለምን ሺሁን ወር አለው ቢሉ ዕለት ያለ ወርኅ ቢል ድንቅ ነው? ለማለት። ስለምን ገብርኤል ተላከ ቢሉ ሲላክ የለመደ ነው። ከዘካርያስ ከኤልሳቤጥ ሲላክ የነበረ ነው። ከቅዱሳን አያንዳንዱ የማይላክ የለም ብሎ ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነው አምላክ ሰው ሰው አምላክ የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ ሲል። አንድም መጋቤ ሐዲስ ነውና ማን ይላክለት በዘመኑ። አንድም በጥንተ ተፈጥሮ ጌታ መላእክትን ሕያዋን ለባውያን ነባብያን አድርጎ በፍሉማ ፈጥሯቸው ተሠወረ። መላእክትም ምንት ንሕነ እምነበ አይቴ መጻእነ ወመኑ ፈጠረነ ውሚመ በበርእስነት ተፈጠርነ አሉ። ያንጊዜ ዲያብሎስ ቅሩበ እግዚአብሔር አኃዜ መንጦላዕት ሆኖ ተፈጥሮ ነበር። ከፍ ብሎ ቢያዳምጥ ድምፅ አጣ። ዝቅ ብሎ ቢያዳምጥ እንዲህ ሲሉ ሰማ። ዝም ብዬ መንግሥት አሰዳለሁ? እኔ ፈጠርኋችሁ ልበል ብሎ አሰበ፡ አስቦም አልቀረ። አነ ፈጣሪየሙ ለአሉ ፍጡራን ወአነ ገባሪየሙ ለአሉ ግቡራን ብሎ ተናገረ። ያን ጊዜ በመላእክት ከተማ ሽብር ጸና። ወአኅድየሙ መልአክ ሰላም ዘሰሙ ገብርኤል ይላል። ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለእምላክነ ብሎ አጽንቷቸዋል። ይህ ቅሉ ለብሥራት አብቅቶታል። ወበእንተዝ ደለም ይጹር /ይሰብክ/ ዜናሃ ለማርያም አንዲል።

ኀበ ድንግል እንተ ተፍሕረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ። ከዳዊት ወገን ለሚሆን ስሙን ዮሴፍ ለሚሉት ወደታጨች ወደ ድንግል ተላከ። ዘእምቤተ ዳዊት አለ። እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ ያለው እንደደረሰ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ።

ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም። የዚያች ብላቴና /ሕፃን/ ስሟ ማርያም ይባል ነበር። ቦአ መልአክ ኀቤሃ። ወደሷ ገባ ከዚያ

www.zeyeneta.com

ከቤተ ዮሴፍ ሳለች ቋንጤ ወንበሯን ዘርግታ ወእንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ ይላል። ወርቁን ከሐሩ ሐሩን ከወርቁ አስማምታ ስትፈትል መጥቶ ቃል ሥጋ ኮነ አላት። ደንግጥ ብላ ወደ ቤቷ ገባች። ተከትሎ ገባ ገብቶም ወቆመ ገሀደ በአንጻረ ዘትራአዮ ይላል። ፊት ለፊት ቆመ። አንድም ቦአ፡ ወደሷ ባሕርይ ገባ። በአምሳለ መልአክ የታየችበት እንደሆነ ትደነግጣለች ብሎ። በአምሳለ ብእሲ ከዚያውም ዘንድ በአምሳለ ብእሲ ዘሰያብ /ሽበት የቀላቀለበት መካከለኛ ሰው መስሎ ታይት/ ለጊዜው እንዳትደነግጥ ነው። ምሰጢሩ ግን ብሉየ መዋዕል አምላክን ትጸንሻለሽ ሲል ነው።

ወይቤላ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተጸጋ እግዚአብሔር ምስሊኪ። እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ቢሆን የእናትነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል። ይህስ ጊዜው ገና ነው ብሎ እንደ ሐዋርያት በጸጋ ቢያደርብሽ የእናትነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል። ይህም ጊዜው ገና ነው ብሎ እንደነቢያት በረድኤት ቢያድርብሽ የባሰ ጸጋነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል።

ቡርክት አንቲ አምአንስት። ከሴቶች ይልቅ ንዕድ ክብርት ነሽ። ወርአያ ደንገጸት አምቃሉ። ቃሉን ሰምታ ደነገጠች። ርእየን ሰምዐ ይላል። ወርአዮ ሕልመ አቡሁ ገብአ ማቴ፩፡፳። አጽንን ርእስከ /አጽምዕ/ እዝነከ ሰርእየ ሕልመ አቡከ። ስምዒ ወሰትየ ወርአዩ፡ እንዲል። አንድም ቃሉን ሰምታ መልኩን አይታ ደነገጠች። ወጎለየት ወተቤ። አስበች አንዲህ አሰች እፎኑ ከመዝ ኑ አምኃ ይትአምኑ። እፎና ኑ አንድ ጊዜ /አንድነት/ አይተረጉምም ሰቤት እንዲህ ያለ ለላምታ እንዴት ይሰጣታል። አናቱ ሔዋንን ያሳተ ሰይጣን ነው እንጂ ሌላን ነው አሰች።

ወይቤላ መልአክ ኢትፍርሒ ማርያም። ማርያም አትፍሪ አንችም እንደ እናትሽ አንደ ሔዋን ኩሕት አይደለሽም /ሰሕተት የሰብሽም።/ እኔም እናትሽ ሔዋንን እንዳሳተ ሰይጣን አይደለሁም አላት። ኢትፍርሂ አላት ፍርሃቷን ካሰራቀላት ነገሩን አትሰማውምና ማርያም ብሎ ጠራት። አይወልዳትምና ዳዊት ግን

ይወልዳታልና ወሰትየ ይላታል አለ። አስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር። ስእግዚአብሔር ዘንድ የእናትነት ባሰሚልነትን አግኝተሻልና ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ። ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድን በድንግልና ጸንሽሽ በድንግልና ትወልጅዋለሽ አላት። ኢሳይያስ አርቆ ትጸንስ ትወልድ ብሎ ነበር። ፈከረ ሳቲ ሰድንግል ያሰኘው ይህ ነው። ራሰ ቆርቶ ሰም ጠርቶ እንደ መናገር።

ውትሰምዩዮ ሰሞ ኢየሱስ። ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ። ውእቱ ዓቢይ። የአብ ዐቢይ ኃይሉ ነው። ወያሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አለ በተዋሕዶ። ወይሁበ እግዚአብሔር መንበረ ዳዊት አቡሁ። የዳዊትን መንግሥት ይሰጠዋል። ለጊዜው ሰሎሞን ነው። ፍጻሜው ግን ክርስቶስ ነው። ምነው የዳዊት የጸጋ የጌታ የባሕርይ የዳዊት ሥጋዊ የጌታ መንፈሳዊ አይደለም? ቢሉ የጸጋውን የባሕርይ፡ የሥጋዊውን መንፈሳዊ፡ አድርጎ ገዝቷል፡ አንጂ መንግሥቱስ አንድ ነው። አንድም የመለኮቱን ሥልጣን ይሰጠዋል። መንበረ ዳዊት አለ። መንበርከ አግዚኦ ሰዓለመ ዓለም ብሎ ሰሰተናገረለት። አንድም መሰቀልን ይሰጠዋል አለ አንዲሰቀል ያደርገዋል። መንበረ ዳዊት አለ። አርትዕ ተሠራህ ወንገሥ ብሎ ሰሰተናገረለት። አንድም ምአመንን ይሰጠዋል አለ። አንዲዋሐድ ያደርገዋል። መንበረ ዳዊት አለ ሰምዒ ወሰትየ ብሎ በሰመሰከረለት። ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም። ለዘላለሙ ለያዕቆብ ወገን ይነግሣል። ምነው ለአሕዛብ አይነግሥምን ቢሉ እመቤታችንን ዮሴፍን ደሰ ለማሰኘት። የተሰፋ የሃይማኖት መሠረት ናቸውና። አንድም ያመኑበትን ሁሉ ቤተ ያዕቆብ አለ። አሕዛብ ቢሆኑ ካመኑ ቤተ ያዕቆብ ይባላሉ። አስራኤል ቢሆኑ ካላመኑ ቤተ ያዕቆብ አይባሉም። ወአልበ ማሕሰቅት ለመንግሥቱ። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም። ዳዊት ሰሎሞን ፸፡፸፪ ዘመን ነግሦው ገዝተው አልፈዋል። አሱ ግን ቅድመ ዓለም ማዕከለ ዓለም ድኅረ ዓለም ነግሦ ይኖራልና። ትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ አንዘ ኢያአምር ብእሴ። አሷም ይህ ወንድ ሳላውቅ እንዴት ይሆንልኛል፡ እምአይአቴ ረከብከ

www.zeyeneta.com

ዘከመዝ ብሥራተ ዘእንበለ ዘርዕ እምድር እትወተ ወዘእንበለ ምት እምድንግል ጽንሰተ። ምድር ያለዘር ታፈራ ዘንድ ሴት ያለወንድ ትጸንስ ዘንድ እንዲህ ያለ የምሰራች ከየት አገኘህ አለችው። እንዲህ ማለቷ ነገሩን ሽታው አይደለም ጥንቱን እንደ ምን ይሆንልኛል ነገሩን አላደርገውም ስትል ነው። ይህም እንደ ዘካርያስ ተጠራጥራ እንደ ኒቆዲሞስ ተሰራክራ አይደለም ልረዳው ብላ ነው እንጅ። መልካም ደቀመዝሙር የጸነነውን ቀስም ከመምህሩ ተከራክሮ እንዲረዳ።

እውሥኣ መልእክ ወይቤላ።

መሰሰቱት እንዲህ አላት።

መንፈሰ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ። ያንቺማ ነገር እንደሌሎች ሴቶች መሰለሽ? አላት።

ወኃይለ ልዑል ይጼልሰኪ። መንፈስቅዱስ ያለውን ኃይለ ልዑል። ላዕሌኪ ያለውን ጸለለኪ ብሎ ደነመው። ከኃጢአት ይጋርድሻል። ይለብሰ ሥጋ ዚእኪ የእብ ኃይሉ ወልድ ሥጋሽን ይዋሐዳል።

ዝኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ።

ይህ ካንቺ የሚወለደው ከሃስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው አላት። ወይለመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አለ፡ በተዋሕዶ። ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተእምአዝማድኪ ይእቲኒ ጸንስት ወረከበት ወልደ በልሕቃቲሃ ወበርሰዓቲሃ። ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥስ ስንኪን ካረጀች ከመከነች በኋላ ጸነሰች ወንድ ልጅን አገኘች። ምነው በድንግልና ጸንሶ በድንግልና ከመውለድ ካረጄ ከመከኑ በኋላ መውለድ ይበልጣልና እንዲህ አለ ቢሉ እመቤታችን ከሙቀት ከልምላሜ ናት። እሷ ግን ሙቀት ልምላሜ ተለይቷታልና። ደግሞም መጽሐፍ የደረሰበትን ማጽናት ልማድ ነው። <u>አንድም</u> ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥም ካረጀች ከመከነች በኋላ ጸነሰች ወንድ ልጅን አገኘች። እንተእምአዝማድኪ ያለኸው እንደምን ነው ቢሉ ሌዊ ማጣትን ይወልዳል። ማጣት ሶፍያን ሐናን ማርያምን ይወልዳል። ሶፍያ ኤልሳቤጥን ሐና እመቤታችንን ማርያም ስሎሜን ትወልዳለች።

ወናሁ ሳድስ ዝንቱ ወርኀ ለኢንተ ይብልዋ መካን እስመ እልቦ ነገር ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር። ካረጄ ከመከኑ በኋላ እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው እይደለምና እነሆ መካን ስሚሏት ለኤልሳቤጥ ከጸነሰች ስድስት ወሯ ነው አላት። ገብርኤል ያየው ምሥጢር ያሰኘው ይህ ነው። እሷ ሠውራው ነበር። እሷም እንጂ ከባሏ እንዳትወልድ በድንግልና ጸንሶ በድንግልና እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው እይደለም እኮን አለ። አውሬ የፈራ ያጥራል ነገር የፈራ ቀን ይቀጥራል እንዲሉ እሷ አየጠየቀች እሱ እየመለሰ ነገር በዘዘ ነበርና።

እስመ እልቦ ነገር ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር። ብሎ ነገሯን ወሰነባት። ያን ጊዜ የደረቀ ዕፀ ዘይት ከፈቱ ነበር አሰምልሞ አላይቷታል።

ትቤሎ ማርያም ለመልእክ ነየ ዓመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ። እነሆ በነፍስ በሥጋ የማገለግለው ባሪያው አሰሁለት እንደቃልህ /አንዳልኸው/ ይደረግልኝ አለችው። ለእግዚአብሔርማ ይላነዋል ብዙ ብል ክህደት ይሆንብኝ የለም? ብላ ይኩነኒ ብላለች። እስካሁን አልተዋሐደም ነበር። የኢአማኒት ሥጋ መዋሐድ በሆነበት ነበርና። አሁን ግን ይኩነኒ ያለችው ቃሏን ምክንያት እድርጎ በምልዓት ያለ ቃሰ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በአምላነ ሕዛናት ተጸነሰ። ስፍሐ ገብረ ዘእምጥንተ ሥጋሁ ለአዳም ወየእርፋ /ወየእርፍ/ አልባቢነ ዘበጥንተ እግዚአብሔር ነጽርኬ ኀበ ሰዐሌ ሕዛናት ዘበጥንተ ሙላዱ ወጠነ ፍኖተ ነኪረ እሜሃ ተስእለ በጥንተአካል ሥጋሁ ለወልደ ዕጓለ እመ ሕያው እንዘ ይትወሐድ ምስለ ቃል እንዲል።

ረቂቁ ግዙፍ፡ ግዙፉ ረቂቅ፡ ምሉው ውሱን፡ ውሱኑ ምሉዕ ሆነ። የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ። እንቲእሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲእሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል ዘእንለ ኃጢአት ባሕቲታ እንዲል። ተዋሕዶ ፀና ምንታዌ ጠፋ። እስመ ተዋሕዶ አለተታ ለምንታዌ እንዲል።

ሐረ ወንለፈ እምኔሃ መልእክ።

www.zeyeneta.com

ሖረ ከሳ ተለየ። ጎለፊ ከሳ አልፎ ተሰይቶ ብዙ ጎዳና ሄደ። ደርሼ የጠፊኋት እንደሆነ ትደነግጣለች ብሎ እያየችው ብዙ ጎዳና ሄዷል። አንድም ሖረ ከሳ ተሰይቶ ብዙ ጎዳና ሄደ ወንበፊ ሄዶ ሄዶ ረቀቃ የርቀት ያይደለ የርሕቀት አሞራ ወጥቶ ወጥቶ እንዲረቅ።

ወተንሥአት ማርያም ፍጡነ በውስቱ መዋዕል። በዚያ ወራት ፈጥና ተነሣች ፈጥኖ በጾሮ የስሙትን በዓይን እስኪያዩት ያስቸኩላልና። ዘካርያስ ታሟልና እሱን ለመጠየት፡ ምስክር ሦስት ሰማድረግ፡ መሐረት ደወሰ ዓይነ ከርም። የነረምት ንብር ባሰበት ቦታ ሄደች አለ። ደመናው በሚረገረገበት ጉሙ በሚሰብበት። አንድም ሰብክል የሚያጠጡት ምንጭ /ውሀ/ ባለበት ቦታ ዘያስመይ ሀጥሚ ያላል። አበነት። ወበጽሐት ፍጡነ ሀገረ ዳዊት ዘያሁዳ። የይሁዳ ዕፃ ክፍል ወደምትሆን ወደ ዳዊት ሀገር ፈጥና ደረሰች። በቅርብ ጎዳና ሄዳ ጸጋ አግዚአብሔር አድርባታልና። አንድም ፍጡነን አይሻም። ወበጽሐት ኀበ ሀገረ ዳዊት ዘይሁዳ ይላል። ወቦአት ቤተ ዘካርያስ ወደ ዘካርያስ ቤት ገባች ወአምጽአ ሰኤልሳቤጥ። ኤልሳቤጥን ቸር አለሽን? አሰቻት።

ወሰበ ሰምዐት ኤልሳቤጥ ቃሰ አምኖታ ለማርያም። ቸር አለሽን ስትላት በስማች ጊዜ።
አንፈርዐፀ ዕንል ሰውስተ ከርሣ በፍሥሓ ወበሐሤት። በማሕፀኗ ያሰ ጽንስ ደስ እያላት ደስ እያሰው ስገደ። አንፈርዐፀን ሐዋርያት በሲኖዶስ ስገደ ብለው ወሰደውታል። ቅዱስ ያሬድም አምከርሠ አሙ አለማሮ ስገደ ወልደ መካን ለወልደ ድንግል ብሎ ወሰዶታል /ተርጉሞታል/። በእመቤታችን ማኅፀን ያለ ጽንስ በኤልሳቤጥ ማኅፀን ባለው ጽንስ መንፈስ ቅዱስ አሳድሮበት ስግዷል። ዮሐንስ ኤርምያስ በማሕፀን አግኝተዋል ደስ እያላት አለ። ሴቶች ሲነዋወጽ ያማቸዋል ሲፈዝ ደስ ይላቸዋል ልማድ አፍርሶ ይህስ ሲነዋወጽ ደስ ይላቸዋል ብሎ ከወትሮው ደስታዋ ይልቅ ደስ አያላት። ወመልዐ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኤልሳቤጥ። መንፈስቅዱስ በኤልሳቤጥ መላበት ተለይቷት አይደለም። ምስጢር ገልጸላት ትንቢት ቋንቋ አናገራት የሚል ነውና። ወከልሐት በዐቢይ ቃል። ቃሏን አሰምታ ተናገረች ጮሃ ተናግራ

አይደለም ጮሆ የተናገሩት ከሩቅ እንዲሰማ ነገሯ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ስለተሰማ።
ወትቤ ቡርክት አንቲ አም አንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተጸንሷልና ይህን አተረፈች የማኅጸንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቡር ምስጉን ነው። ወሀቤ በረከት ነው ርስሐተ ሕጻናት /ልማደ ሕፃናት/ የሌለበት ነው። መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ በረከተ ነፍስን የሚያድል የባሕርይ አምላክ ነው።

<u>ምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ</u> ንቡየ አሙ ሰአግዚአየ። የጌታዬ እናቱ ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንደነኝ ገረድ ወደ አመቤቷ ትሄዳለች እንጂ አመቤት ወደ ገረዷ ትሄዳለች? አሰች ይሄውም የሚያለኝ ቃል ነው። ዳዊት ቢሄድበት ምንት አምጽዖ ለአግዚአየ ኀበ ንብሩ ብሏል። ዮሐንስም ጌታ አጥምቀኝ ብሎ ቢሄድበት አንሰ አፈቅድ አምኀቤከ አጠመቅ ወአንተኑ ትመጽኦ ኀቤየ ብሏል። ጴጥሮስም ጌታ ሊያጥበው ቢሄድ አንተኑ ተሐፅበኒ አገርየ ብሏል።

<u>አስመ ናሁ</u> ሶበ ሰማዕኩ ቃሰ አምኖትኪ። አንፈርዐፀ ዕንል በውስተ ከርሥየ በፍሥሓ ወበሐሤት። ቸር አለሽን ስትይኝ በሰማሁ ጊዜ በማኅጸኔ ያለ ጽንስ ደስ እያለኝ ደስ እያለው ሰግዷል። <u>ወብጽዕት</u> አንቲ አንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ አምኀበ አግዚአብሔር። ከአግዚአብሔር ታዝዘው የነገሩሽ ቃል እንዲደረግ የምታምኚ።

አንድም ቃለ። ከአግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽን ነገር እንዲደረግ የምታምኚ አንቺ ንዕድ ክብርት ነሽ። አንደ እኔ ባል ላትከራከሪ /ተጠራጥረሽ/ መክራ ያላገኘሽ አለች። ምነው ዘነገሩኪ አለ አንድ መልአኩ አይደለም? ቢሉ መጽሐፍ ስም ካልጠራ አንድና ብዙ አይጠነቅቅም። በተአምኖ አመ ነገርዎ ሰኖኅ። አየ ገቦ ረዝሙ ሐራሁ ለጲላጦስ (ሐራ ጲላጦስ) እንዲል።

ወትቤ ማርያም ተዐብዮ ነፍስየ ለአግዚአብሔር። ከዚህም በአንድ መልአክ በአንዲት ባልቴት ቃል ብቻ ተመስግኜ አልቀርም። ትውልድ ዘይመጽእ ትውልድ ዘየኀልፍ ትውልደ ሴም ትውልደ ያፌት ትውልደ ካም ያመሰግኑኛል ስትል ታመጣዋለች።

www.zeyeneta.com

ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር

ለውነቱ እግዚአብሔርን ታገነዋለች ታከብረዋለች። አሁን አመቤታችን ጌታን የምታገን የምታከብር ሆና አይደለም። ልዕልናውን ትናገራለች ሲል ነው። ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ እንዲል።

ወትትሐሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃንየ። በፈጣሪዬ በመድኃኒቴ አምኜ ልቡናዬ ደስ ይላታል። መድኃኒየ አለች ከምን አድኗታል ቢሉ ከርደተ ገሃነም አሉን ባትጸንስ እንደ አባቶቿ ርደተ ገሃነም ባልቀረላትም /ባገኛት/ ነበርና። አንድም በዘርዕ በሩካቤ ከመውለድ ከሰስሎተ ድንግልና። ውእቱስ ንጹሕ እምነ ፫ቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርዕ ወሩካቤ ወስስሎተ ድንግልና አሰ ሥሩዓን በዕገለ አመሕያው ወአሙራን ቦሙ እንዲል።

አሰመ ርእየ ሕማማ ሰአመቱ።

የባሪያው የሔዋንን ኃዘን አይቷልና ኃዘኗን አይቶ ሰው ሆኗልና። ትሕትናሃ ቢል በመንፀፊ ደይን መውደቋን በአግረ አጋንንት መጠቅጠቋን አይቶ። አንድም የኔን ኀዘኔን አይቷልና ኃዘኔን አይቶ ሰው ሆኗልና። ባባቶቿ ርደት ታዝን ነበርና። ትሕትናየ ቢል ትሕትናዬን አይቶ። ከዕሰታት አንድ ቀን መጽሐፊ ኢሳይያስ ለትመለከት ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ኮሚሰው አንቀጽ ብትደርስ /ስትደርስ/ መየው ከዚያ ሰዓት ደርሼ ውሀ ቀድቼ እንጨት ለቅሜ /ሰብሬ/ አገልግያት እያለች ትመኝ ነበር። ይህ ትሕትናዋ ራሷ ሰመሆን አብቅቷታል።

ናሁ አምይእዜሰ ያስተብፅዑኒ ኵሉ ትውልድ። እንግዲህ ወዲህ በሷንድ መልአክ በአንዲት ባልቴት ቃል ተመስግኜ አልቀርም ብላለች። ትውልድ ዘይመጽእ ትውልድ ዘየኀልፍ ትውልደ ሴም ትውልደ ያፌት ትውልደ ካም ያመሰግኑኛል። አንድም ፍጥረት ሲል ነው። አሪት ዘልደት እንዲል። ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑኛል።

እሰመ ዝኩረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ። አብ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና የኳሕርይ ልጁን በኳሕርዬ እንድወልደው አድርጎኛልና ወቅዱስ ስሙ። ስሙ ልዩ ነው አለች። አብ ቢባል እንጂ ወልድ መንፈስቅዱስ አይባልም።

እንድም እሰመ ዝኩረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ። ወልድ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና በድንግልና ጸንሼ በድንግልና እንድወልደው አድርጎኛልና ወቅዱስ ስሙ ስሙ ልዩ ነው አለች። ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስቅዱስ አይባልም።

እንድም እሰመ ዝኩረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ። መንፈስ ቅዱስ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና አጽንቶኛልና ወቅዱስ ስሙ። ስሙ ልዩ ነው አሰች። መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ አይባልም።

ወሣህሱኒ ለትውልደ ትውልድ ሰአለ ይፈረሐም። ለና ለ የተደራረበ ነው። ለካህናት ለደቂቀ አሮን ለብአሲት ለመርዓተ በግው እንዲል። ይቅርታው ለሚፈሩት ለሚያመልኩት ከትውልድ ለተወለዱ ትውልድ ነው።

ለአለ ይፈርሐም ያ ግን ለሚፈሩት ለሚያመልኩት ነው እንጂ ሰሁሉ አይደለም። እንደ አባቷ እንደ ዳዊት። ኀሀሉ ለእግዚአብሔር እምዓለም ወእስከ ለዓለም ብሎ ዲበ እለይፈርሐም እንዲል።

ወገብረ ኀይለ በመዝራዕቱ። ዛራም ብቻ አይደለም በግብጽ በባቢሎን ታምራት አደረገ።

መዘረዎሙ ለአለ የዐብዩ ኀሊና ልቦሙ። ልቡናቸውን የሚያስታብዩ ግብጻውያንን ባቢሎናውንን በተናቸው።

<u>ወነሠቶሙ</u> ለኃያላን እመናብርቲሆሙ። ኃያላን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ከሹመታቸው ሻራቸው።

አዕበዮሙ ለትሑታን። በግብጽ ተዋርደው የነበሩ እስራኤልን ከፍ ከፍ አደረጋቸው። አንድም ትሑታን ሐዋርያትን አሥራት በዙራት ሰጥቶ ትሑታን ነፍሳትን ልዕልና ነፍስን ሰጥቶ አክብራቸው።

ወእጽገቦሙ <u>እምበረከቱ</u> ለርኁባን። በግብጽ ተርበው የነበሩ እስራኤልን አጠገባቸው። መና ከደመና አውርዶ ውሀ ከደንጊያ አፍልቶ። <u>አንድሆ</u> በባቢሎን ተርበው የነበሩ ትሩፋንን አጠገባቸው። ፮ አህጉር ወግተው ብዕለ አሕዛብን ዘርፈው ወጥተዋልና።

www.zeyeneta.com

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዉላን። ግብጻውያንን ባዶዋቸውን አስናበታቸው። በረድ መትቶባቸው አንበጣ በልቶባቸው ባቢሎናውያንን ባዷቸውን አስናበታቸው። የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ዘርፏቸው።

ወተወከፎ ለእሰራኤል ቍልዔሁ። ወዳጁ እስራኤልን በረድኤት ተቀበለው።

ወተዘከረ ሣህሎ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ። ለአባቶቻችን የተናገረው ይቅርታውን አሰበ አለ ፊጸመ።

ለአብርሃም ወለዘርዑ አስከ ለዓለሃ። ለአርብሃም የተናገረውን ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላስያነ ውስተ ምድረ ነኪር፡ ፬ተ ፻ተ ዓመተ ያለውን።

ወለዘርዑ። ለልጆቹ የተናገረውን። ወጎሊቆ ፫ዐ ዓም እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኩሉ ሰብእ ያለውን። አንድም ወገብረ ኃይለ አብ በወልድ ህልው ሆኖ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ታምራት አደረገ።

ወዘረዎሙ ለእለ የዐብዩ ጎሊና ልቦሙ። ልቡናቸውን የሚያስታብዩ አይሁድን በተናቸው። ወነሠቶሙ ለንያላን። ሐና ቀያፋን ከሸመታቸው ሻራቸው።

አዕበዮሙ ለትሑታን። ልብደ ሠረ /መረብ ሠሪ/ ዓሣ አሥጋሪ /ወጋሪ/ የነበሩ ሐዋርያትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው።

አንድም መልስ። ወአጽገበሙ እምበረከቱ ለርጉባን። ከልጅነት ከትምህርት ተርበው ለነበሩ ለሐዋርያት ልጅነትን ትምህርትን አጠገባቸው።

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዉላን። አሥራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን ተቀብለው ከብረው ገነው ይኖሩ የነበሩ ሐና ቀያፋን ባዷቸውን አስናበታቸው።

ወተወከፎ ለእሰራኤል ቍልዔሁ። ይህን ለማድረግ ልጹን አሰራኤላዊ ሥጋን እንዲዋሐድ አደረገው። ኀበ ያዕቆብ ኀድረ ወነበ እሰራኤል ተዋረሲ እንዲል።

አንድም ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ። ወልድ በሥልጣኑ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ታምራት አደረገ።

ወዘረዎሙ ለእለ የዐብዩ ጎሊና ልቦሙ። ልቡናቸውን የሚያስታብዩ አጋንንትን በተናቸው። ሥጋትን በመቃብር አፍርሰን አበስብሰን ነፍሳትን በሲኦል /በገሀነም/ ተቆራኝተን አንኖራለን ይሉ የነበሩትን።

ወነሠቶሙ ለኀያላን አመናብርቲሆሙ። ከሰው ልቡና ለሰወጣቸው ልቡናቸውን እንደ ዙፋን ሰውነታቸውን እንደ አዳራሽ እንደ ድንኳን አኩያት ፍትወታት ኃጣውእን እንደ አጥር እንደ ቅጥር አድርገው ይኖሩ የነበሩትን። አዕበዮሙ ትሑታን። ነፍሳትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው።

ወአጽገበሙ እምበረከቱ ለርጉባን። ከልጅነት ከክብር ተርበው የነበሩ ነፍሳትን ልጅነትን ክብርን አጠገባቸው።

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዉላን። አጋንንትን ባዷቸውን አስናበታቸው።

ወተወከፎ ለእሰራኤል። ይህን ለማድረግ መጥቶ እሰራኤላዊ ሥጋን ተዋሐደ።

ወተዘከረ። ለአዳምና ለሔዋን የተናገረውን ቃሉን አሰበ አለ። በሐሙስ ዕለት ያለውን። ለአብርሃም። ለአብርሃም የተናገረውን በዘርዕከ ይትባረኩ ኩሉሙ አሕዛበ ምድር ያለውን።

ወለዘርዑ። ለልጆቹ የተናገረውን።

እስመ እምፍሬ ከርሥከ እንብር ዲበ መንበርከ ያለውን።

ወነበረት ማርያም ኀቤሃ መጠነ ፫ቱ አውራኀ ሶስት ወር ያህል ኖረች ወእምድኅረዝ አተወት ቤታ። ከዚህ በኋላ ወደ ቤቷ ሄደች። ስለምን ቢሉ መኖር ፈቃዷ ቢሆን ኖረች፡ መሄድ ፈቃዷ ቢሆን ሄደች። አንድም ሰው ሁሉ በየሀገሩ ይኮር ተብሎ አዋጅ ተንግሮ ነበርና። እመቤታችን ክብርት ቤተ መቅደስ ናት ክቡር ቤተ መቅደስ እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስን ጸንሳለች። ማስተራከስ በሆነባት ነበርና። ኤልሳቤጥ የምትወልድበት ጊዜ ደርሷል። ተቀንዮ በሆነባት ነበርና። ዮሐንስ ባልተወለደም ነበርና። አንበላ ክደጅ አስረው አንበላ ይፈታሉ? /ይፈቷል?/።

www.zeyeneta.com

፲፬. ጸሎተ ዘካርያስ ካህን

ዘካርያስ ማለት ዝኩር ዝክረ እግዚአብሔር ማለት ነው።

ወሀሎ አሐዱ ካህን ዘሰሙ ዘካርያስ በመዋዕል አብያ። በአብያ ዘመን ሰሙን ዘካርያስ የሚሉት አንድ ካህን ነበረ። ዘካርያስ መሉዕ አብያ ዱግ ነው። /የበላይና የበታች/። ምነው ምሉውን በዱግ ዘመን ነበረ አለ ቢሉ ምሉው ቢሰነካክል ዱኑ የምሉውን ሥራ ይሠራዋልና። በአጢነ ዕጣን በአብኦ መሥዋዕት ይፈራረቀዋልና። ወብአሲቱኒ አምአዋልደ አሮን ወሰማ ኤልሳቤጥ። ሚስቱም ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች፡ ስሟም ኤልሳቤጥ ይባል ነበር። ይህ አሮን የነአሶን ወልደ አሚናዳብ እኅት ኤልሳቤጥ ትባላለች እሷን አግብቶ አልዓዛርን ይወልዳል። የዚያች ልደቷ ከዚያች ነው። ይህን ለምን ይሻዋል ቢሉ የዮሐንስ ልደቱ ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ነው ለማለት። የቀደመውን ሊቀ ካህናት የቀደመችውን ኤልሳቤጥ አነሳ። በቀደመው ሊቀ ካህናት በቀደመችው ኤልሳቤጥ ሕገ ሥጋ አሮት ተሠርታለች ለማለት። የኋለኛውን ሊቀ ካህናት የኋለኛዪቱን ኤልሳቤጥ አነሳ በኋለኛው ሊቀካህናት በኋለኛዪቱ ኤልሳቤጥ ሕገ ነፍስ ወንጌል ተሠርታለች ለማለት።

ወክልዔሆሙ ጻድቃን አሙንቱ በቅድመ እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ባወቀው ነገር ሁሉቱ ደጎች ነበሩ።

ወየሐውሩ በኵሉ ትእዛዘ። በኵሉ ትእዛዙ በኢታምልክ።

ወሕጉ። በፀኙ

ወኵነኔሁ። በፎደፎ ወነበቡ። ጸንተው ይኖሩ ነበር። አንድም ያዘዋውራል። ብኩሉ ትእዛዙ። ፎደፎ ወነበቡን።

ወሕጉ። ፀኙን

ወኵነኔሁ። ኢታምልክን ጠብቀው ይኖሩ ነበር።

ወንጹሐን አሙንቱ ዘእንበለነውር። ነውር ነቀፋ የሌለባቸው ንጹሐን ነበሩ። ምግባራቸውን እበዛዝቶ ተናነረ። በደጎቹ ቃል አምላክነቱ ተመስክሯል ለማለት። ደግሞ ወባሕቱ አልቦሙ ውሉድ ብሎ የሚያመጣ ነውና። ልጅ አለመውለዳቸው በኃጢአታቸው እንዳይመስል። ወባሕቱ አልቦሙ ውሉድ። ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም ልጅ ባለመውለዳቸው እሰመ መክን

ይእቲ ኤልሳቤጥ። ሚስቱ ኤልሳቤጥ የባሕርይ መካን ነበረችና። አነ እግዚአብሔር ዘአፈጥር መክነ ወዘአወልድ እንዲል። ይህስ ምክንያሰ ኢተውህባ ሰብእሲት ዳዕሙ ትማስን /ትመውት/ በግብረ አደዊሃ ዘእንበለ ውሉድ ይላል ብሎ አስከ ጊዜዋ ድረስ መክን አላት። ለለምን አዘገያት ቢሉ አዝና ታግኝው ብሎ። አዝነው ያገኙት ልጅ ይረባል ይጠቅማልና። ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ አንዲል። ይቅርታውን ያለጊዜው አይሠራውምና። ለወንጌል አምሳል መርገፍ ልትሆን አሷ ኖራ ኖራ እንደወለደች፡ ወንጌልም ሥራቷ በመልከጼዴቅ ታይቶ ኖራ ኖራ ተሠርታለች /የመሠራቷ ምላሴ/።

ወክልኤሆሙ ልሂቃን አሙንቱ ወሐለፊ መዋዕሊሆሙ። የሁለቱም ዘመናቸው ገፍቶ ነበር።

ወአምዝ አመ ይገብር ግብረ ክህነት። በዕብራቱ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ ይገብሩ ካህናት። በከመ ልማደ ካህናትም ይላል። እንደ ካህናቱ ልማድ ካህናት እንዲሠሩ። በስሞኑ የክህነት ሥራ በሚሠራበት ወራት

በጽሐ ጊዜ የአጥን። የሚያጥንበት ጊዜ ደረሰ። በደረሰ ጊዜ ቦአ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር። ወደቤተመቅደስ ገባ ይህስ ምን ቀን ነው ቢሉ ወአሕምዖዋ ለነፍስክሙ ያላት ዕለተ ዮሴፍ ናት። በዚህ ቀን አባቶቻቸው ወንድማቸው ዮሴፍን ሸጠው አባታቸውን አሳዝነው ነበርና፡ ያን ዕዳ አታድርግባቸው ሲሉ፡ ካህናቱ በውስጥ ሕዝቡ በአፍአ ሆነው ሲያለቅሱ /ሊጨነቁ/ ነበር። አንድ ቀን ባለቀሱት ዓመት ይጠበቁ ነበር /ይጠቀሙበታል/ አንድም ዕለተ ሮቤልም ናት ይላሉ። ከአባቱ ዕቅብት ደርሶ አባቱን አሳዝኖ ነበርና፡ እዳ አታድርግበት ሲሉ። ወንብሩ ላሕመ በኮሬብ አንዲል። ጣያትም ያቆመበት ቀን ነው ይላሉ።

ወሕዝብስ ሀለዉ ይጼልዩ በአፍአ። ሕዝቡም በአፍአ ሆነው ይጸልዩ ነበር። ምን ብለው ይጸልዩ ነበር ቢሉ የወትሮ ጻሎታቸውን ልጅ ስጠው ብለው በጎ ራእይ ግለጥለት ብለው። ስቡ ከአትርጉተ ምሥዋዕ እንዲመላለት አድርግ ብለው።

ወአስተርአዮ መልአክ እግዚአብሔር ቀዊሞ መንገለ የማነ ምሥዋዕ ዘዕጣን።

www.zeyeneta.com

በዕጣኑ በምሥዋዑ ቀኝ በኩል ሆኖ ታየው ተነጋገረው። ዘዕጣን አሰ ዘመሥዋዕት ዘብርት አለና። በቀኝ ሆኖ ታየው ተናገረው አለ የመልአክ ግብሩ የማናዊ ነውና። ሰው ሁሉ ከግራ ወደቀኝ የሚያልፍበት ጊዜ ደረሰ ሲል። አንድም መክሮ አስተምሮ ከግራ ወደ ቀኝ የሚመልስ ልጅ ትወልዳለህ ሲል።

ወሶበ ርእዮ ደንገጸ ዘካርያስ። ዘካርያስም መልአኩን ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርሃት ረዓድ አደረበት። ድንጋጼ የናላ ፍርሃት የልቡና ረዓድ የጉልበት። የመልአክ ራእዩ ግሩም ነውና። ከቅድስተ ቅዱሳን ያሰ አሱ የሚገባ የሰምና ገብቶ ቢያየው ደነገጠ። ናዳብ አብዩድን ባሳወቁት ኃጢአት እንደቀሰፋቸው እኔንም ባሳወቅሁት ኃጢአት ሊቀሥፈኝ መጣ ብሎ። የአክዮ አሦር በዕብራውያን ወዕብራውያን የአክዮ በአሦር እንዲል።

በአፍአ ያሉትን ጨርሶ እኔን ሊያጠፋኝ መጣ ብሎ።

ወይቤሎ መልአክ ኢትፍራህ ዘካርያስ። መልአኩም ዘካርያስን አትፍራ አለው። ኢትፍራህ አለው ፍርሃቱን ካላራቀሰት ነገሩን አይሰማውምና፡ ዘካርያስ ብሎ ጠራው ሥጋዊ ጠላት አይደለምና።

እስመ ናሁ ተሰምዐ ጸሎትከ ቅድመ እግዚአብሔር። ጸሎትህ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሳልና ምን ብሎ ይጸልይ ነበር ቢሉ የወትሮ ጸሎቱን ልጅ ስጠኝ ብሎ በጎ ራእይ ግለጽልኝ ብሎ። ስቡ እንዲመላ አድርግልኝ ብሎ። ወብእሲትከኒ ኤልሳቤጥ ትወልድ ሰከ ወልደ። ሚስትህ ኤልሳቤጥም ጸንሳ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች። ለከ አሰው አርጅቶ ነበርና ከሴላ እንዳይመስለው፡ ልጅ ስጠኝ ብሎ ይጸልይ ነበር ብሎ ገለጠው። ሴላ ጸሎት ይጸልይ ነበር ቢሉ ሁለተኛ ምልክት ይነግረዋል።

ወትሰምዮ ስሞ ዮሐንስ። ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ትሰዋለች። ወይከውነከ ዐቢየ። ደግ ደስታ ይሆንልሃል።

ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ። በመወለዱ ብዙ ሰዎች ደስ ይላቸዋል። በሙያው በግብሩ። መካን ዘመዳቸው ብትወልድ /ስትወልድ/።

እስመ ዐቢየ ይከውን ውእቱ በቅድመ እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ባወቀው ነገር ደግ ሰው ይሆናልና። ኢይሰቲ ወይነ

ወሜሰ። የማር ጠጅ የወይን ጠጅ አይጠጣም። የማር ጠጅስ በአገራቸው የለም ብሎ ዘያስክር፡ አረቂ አይጠጣም። ወዘኢያለክር፡ ቀሀ /ቡና/ አይጠጣም።

አላ ይመልዕ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ አምከርሠ እሙ። በአናቱ ማኅጸን ሳለ በወይኑ ባረቂው ቦታ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል እንጂ። ዮሐንስ ኤርምያስ በማኅጸን አግኝተዋል።

ወሰብዙኃን እምደቂቀ አስራኤል ይመይጦሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላኮሙ።

ከአስራኤል ብዙዎቹን መክሮ አስተምሮ ወደ ፈጣሪያቸው ይመልሳቸዋል።

ውእቱሰ የሐውር ቅድሜሁ በመንፈስ ቅዱስ ወበኀይለ ኤልያስ። በመንፈስ ቅዱስ በኤልያስ ግብር አንቶ ያኖራል። ኤልያስን በምን ይመስለዋል ቢሉ ኤልያስ አዋጊ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ድንግል ነው። ዮሐንስም አዋጊ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ድንግል ንጹሕ ነው። ኤልያስ አንር ነው። ዮሐንስም አንር ነውና። ኤልያስ ቀይ ዓረብ ታጥቆ ነበር። ደሜን በስማዕትነት አፈሳስሁ ሲል። ዮሐንስም ቀይ ዓረብ ታጥቆ ነበር። በስማዕትነት አሞታስሁ ሲል። ኤልያስ መገሥጻ አክአብ ወኤልዛቤል ነበር። ዮሐንስም መገሥጻ ሄሮድስ ወሄሮድያዳ ነውና። ኤልያስ ለደኃራዊ ምጽአቱ ፈታውራሪ /ግንባር ቀደም ሆኖ/ ይመጣል ዮሐንስም ሰቀዳማዊ ምጽአቱ ፈታውራሪ ሆኖ መንፈቅ ቀድሞ መጥቷልና። አንድም ዘውአቱ ኃይለ ኤልያስ ይላል። የኤልያስ ኃይል በሚሆን በመንፈስቅዱስ እየተቃኘ በጌታ ፊት ይሄዳል አለ። መንፈቅ ጽንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል። ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኀበ ውሉድ። የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብን ዕውቀት ወደሐዋርያት ይመልስ ዘንድ።

ወኀሊና ከሐድያን ውስተ አእምሮ ጸድቃን። የሐዋርያትን ልቡና ወደ አብርሃም ወደ ይስሐቅ ወደ ያዕቆብ ዕውቀት ይመልስ ዘንድ። አንድም ከመ ይሚጥ የአይሁድን ዕውቀት ወደ ሐዋርያት ዕውቀት ይመልስ ዘንድ። ወኀሊና ከሐድያን ውስተ አእምሮ ጸድቃን። የከሐድያን የአይሁድን ልቡና ወደ ሐዋርያት ወደ ቀደመ ዕውቀታቸው ይመልስ ዘንድ። ወደ ድንቁርና ማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ስመ ይሥራዕ ሕገ። ሥርዓትን ይሠራ ዘንድ።

ወሕዝበ ዘድልው ለእግዚአብሔር። ለእግዚአብሔር የተዘጋጀ ሕዝቡን ይሠራ ዘንድ። ድልው የተዘጋጀ አድርጎ ይሠራ ዘንድ

ወይቤሎ ዘካርያስ ሰመልአክ በምንት አእምር ስመ ይስሙን ዝንቱ እስመ እነሂ ልሕቁ ወለብእሲትየ ኀለፈ መዋዕሊሃ። እኔ አርጅቻለሁ የሚስቴም ዘመኗ ገፍቷል ይህ እንዲደረግ በምን አውቃለሁ እለው። ሣራ ካረጀች ከመከነች በኋላ እንደወለደች በአሪት የተጻፈውን ገድፍ።

ወተሠጥዎ መልአክ ወይቤሎ አነ ውእቱ ገብርኤል ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር። በእግዚአብሔር ፊት የምቆም እኔ ገብርኤል ነኝ። በእግዚአብሔር ፊት የማይቆም ዲያብሎስ ሐሰት ይናገራል እንጂ እኔ ሐሰት እናገራለሁ?አለው አነ ውእቱ አለው።በምን አውቆ ቢሉ መጽሐፈ ዳንኤልን ሲመለከት ያውቀው ነበርና። ተፈኖኩ ኀቤከ ዘንተ እንግርከ ወአዜንቱ ዘንተ። ጽንሱን ልደቱን እነግርህ ዘንድ ወዳንተ ተላክሁ።

ወናሁ ትከውን በሐመ። እነሆ ድዳ ትሆናለህ። ወትሰዕን ነቢበ። መናገር ይሳንሃል። እስከ አመይከውን ዝንቱ። ይህ እስኪደረግ ድረስ።

እስመ ኢአመንከኒ ነገርየ ዘይከውን ወይትፈጸም በጊዜሁ /በእድሜሁ/። በጽንሱ የሚጀመር በልደቱ የሚፈጸም ነገሬን አላመንክኝምና /አላመንክምና/። አንድም ኩን በሐመ ወሰዐን ነቢበ ብሎ ረገመው። አንደበቱ ታሠረ

ወሕዝብሰ ሀለዉ ይጸንሕም ለዘካርያስ። ሕዝቡ ግን በእፍኣ ሆነው ዘካርያስን ደጅ ይጸኑት ነበር። ዛሬ ስረዩ ቂስ ወጥቶ ካላሰናበታቸው እንዳይሄድ። ወአንክሩ እስመ ጕንደየ ውስተ ቤተመቅደስ። በቤተመቅደስ ዘግይቷልና ተጠራጣሩ ሸማግሌ ነውና፡ አቃ ሲያዘጋጅ ወድቆ ይሆን፡ ራዕይ በዝቶበት ይሆን ናዳብ አብዩድን እንደቀሠፋቸው ቀሥፎት ይሆን እያሉ ተጠራጠሩ።

ወወጺአ እፍኣ ኀቢአሙ ስእነ ተናገሮቶሙ። ወደ ውጭ በወጣ ጊዜ መነጋገር ተሳነው።

ወአእመሩ ከመ ዐ ዘአስተርአዮ በቤተመቅደስ። በቤተመቅደስ ሳለ የታየው የተነጋገረው ነገር እንዳለ አወቁ፡ ጠቅሶ አሳይቷቸዋል። እንደበቱ በመታሰሩ። ወነበረ ኮሚሁ እንዘ ዐሐም ውእቱ። እንዲሁ ድዳ ሆኖ ኖረ። ወይኤምሮሙ በአዴሁ ሰዚህ ውጡ በዚህ ግቡ እያለ በእጁ ሲያመላክታቸው ኖረ።

ወፈጸሞ መዋዕለ አገልግሎቱ አተወ ቤቶ። ሰሞኑን ጨርሶ ወደቤቱ ሄደ በዓመት አንድ ቀን ነው ያሉ እንደሆነ ደብረዘይት ነው ቤቱ። ሳምንት ነው ያሉ አንደሆነ የከተማ /ከስተማ/ ቤት ነበረው።

ወእምድኅረ ከልዔ መዋዕል ጸንሰት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ። ከሁለት ቀን በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ሰሰምን አስከዚያ ሰነበተ ቢሉ ሰለ አስብሮተ ዕባን። ዛሬ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ዕለቱን መድረስ እንዳያገባ ሲያጠይቅ። ወከበተት ጽንሳ ፫ተ አውራኃ እንዘትብል ከመዝ ኑ ረሰየኒ እግዚአብሔር አመ ሐውጸ ሐወጸኒ ያለትት ዝንጓጌየ አምሰብእ። ከሰው ተግዳሮቴን ያርቅ ዘንድ በምሕረት በነበንኝ ጊዜ እንዲህ ያለ ሥራ ሠራልኝ እያለች አምስት ወር ያህል ጽንሷን ሰወረች። ሴቶች ሦስት ወር መሠወር ልማዳቸው ነውና። ትርፉ ሁለት ወር ነው። በላች በላችና ሆዷ ቢስማች አረገዝኩ ትላለች። ሲያረጁ አምባር ይዋጀ ይሉኛል ብላ፡እንድም ደግ ሰው ናትና ጊዜው ይግሰጠው ብላ። ምን አያሉ ይሰድቧት ነበር ቢሉ።

ዕፁተ ማሕፀን ይብሉተ አጥባት ኀጥእተ በረከት። በቅሉ ከወለዷት በኋላ ወልዳ አታውቅ እያሉ ይገደሯት ነበርና።

ወበጽሐ ወርኃ ሰኤልሳቤጥ ከመ ትለድ። ኤልሳቤጥ ትወልድ ዘንድ ወራቷ ደረሰ ወወለደት ወልደ። ወንድ ልጅን ወለደች።

ወሰምዑ አዝማዲሃ ወአግዋሪሃ ከመ አዕበየ እግዚአብሔር ሣህሉ ላዕሌሃ። ኅቲ ሲል ነው። ይቅርታውን አንዳበዛላት ሰሙ። ወተፈሥሑ ምስሌሃ። ከሷ ጋራ አንደሷ ደስ አላቸው በሙያው በግብሩ። መካን ዘመዳቸው ብትወልድ።

ወእምዝ አመ ሰሙን ዕለት መጽኡ ከመ ይግዝርዎ ለሕፃን። በስምንተኛው ቀን ዮሐንስን ይገዝሩት ዘንድ መጡ።

www.zeyeneta.com

የሊቀ ካህናት ልጅ ነውና መጡ አሉ። ጌታን ግን ወሰድም ይላል። ይህንም ወሰድም ይላል።

ወሰመይም በሰመ አቡሁ ዘካርያስ። በአባቱ ስም ዘካርያስ አሉት በፋሲል ፋሲል በኢያሱ ኢያሱ እንዲሉ።

ወእወሥአት እመ። እናቱም መለሰች።

ወትቤ አልቦ አሳ ዮሐንስ ይሰመይ ስመ። ስሙ ዮሐንስ ይባል እንጂ አይሆንም አለች።

ወይቤልዋ አልቦ እምአዝማድኪ ዘዘመገ ስም። ከዘመዶችሽ እንዲህ ያለ ስም ያለው ሰው የለምን? አሏት። አንድም ከዘመዶችሽ እንዲህ ያለ ስም ያለው ሰው የሰም‍ና መልካም ነው አሏት።

ወቀጸብዎ ሰአበሁ ሴት ብታውት በወንድ ያልት እንዲሉ ዘካርያስን ጠየቁት።

መነ ትፈቅድ ይሰምዮ። ማን ይሉት /ይባል/ ብንድ ትወዳለህ አሉት ወስአለ ሰውህ ብራና ጻምጣችሁ ብዕር ተርጓችሁ ሰጡኝ ብሎ ለመነ /ጠየቀ/። አልፈው። እ ነው ያሉ እንደሆነ ለመነ። ዐይኑ። ዐ ነው ያሉ እንደሆነ ደመጸ ጸፈ።

ወጸሐፈ እንዘ ይብል ዮሐንስ ይሰመይ ስመ። ስሙ ዮሐንስ ይባል ብሎ ጻፈ።

ወእንከሩ። አደነቁ ቃሏና ቃሉ አንድ በመሆኑ።

አንድም የሚቀድመው ቀለም አለ። ዮሐንስ ይሰመይ። ስምንቱን ቀለም ጽፎ ሲጨርስ። አንድም ዮሐንስ ይሰመይ ስመ። አሥሩን ቀለም ጽፎ ሲጨርስ እንደበቱን ፈትፍሰታል። የአሥሩ ቃላተ አሪት ምግብና (ሥርዓት) ሲፈጸም ስው ሁሉ ከማዕሠረ ኃጢአት እንዲፈታ በሐዲስ ቂንቂ እንዲናገር ለማጠየቅ።

ተከሥተ አፋሁ ወነበበ ልሳኑ። አንደበቱ ረትቶለት ተናገረ።

ወባረከ ለእግዚአብሔር። እግዚአብሔርን አመሰገነው። ከዚህ ሰዓት ያደረሰኸኝ ከደዌዬ የፈወስከኝ ልጅ የሰጠኸኝ ብሎ።

ወእንከሩ። እደነቁ እንደበቱ በመፈታቱ።

ወኮነ ፍርሐት ላዕለ ሰብእ ውእቱ ብሔር። በዚያ አገር ባሉ ሰዎች ፍርሐት አደረባቸው። ወተናገርም ለዝንቱ ነገር ውስተ

ኵሉ ብሔረ ይሁዳ። በይሁዳ አውራጃ ሁሉ ይህን ነገር ተጨዋወቱት።

ወዐቀብም ውስተ ልቦሙ። በልቡናቸው አስተዋሉት።

ወይቤሉ ምንትኑ እንጋ ይኸውን እምዝንቱ ሕፃን። ከዚህ ሕፃን የተነሣ ምን ይሠራ ይሆን አሉ።

እስመ እግዚአብሔር ላዕሌሁ። ሥልጣነ እግዚአብሔር አድሮበታልና። ጌታ እንጂ ለነገሩ መስላል ይፈልግለታል ኖሎ አበ እንጋድ ሲሆን በመወልዲቱ ፊት ቆሞ አመሰገነ። ዓይኑን ሲገልጠው በቤቱ ብርሃን መላ። መሴ ለቀ ነቢያት ሊሆን በፊቱ ብርሃን ተስሎበት ተወለደ። ዳዊት ሥርወ መንግሥት ሲሆን አንበሳ በርግጫ ነብር በጡጫ ይገድል ነበር። ይህም ሲጸነስ ያባቱን አንደበት አሠረ። ሲወለድ ያባቱን አንደበት ፈታ ብለው።

ወመልዐ መንፈስቅዱስ ላዕለ ዘካርያስ። ተሰይቶት አይደለም ተናገረ የሚል ነውና።

ተነበየ ወይቤ። ተነበየ ብሎ አንድ አርእስት። ይቤ ብሎ ሁለት አርእሰት። ተናገረ። ሰሁለቱም ያመጣል።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል። የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ሰቀረበው አመጣ። ይቤ ሳለው።

ዘተሣህለነ ወገብረ መድኃኒተ ሰሕዝበ ዚአሁ። ይቅር ያለን ሰወዳጆቹ /ሰወገኖቹ/ ድኅነትን ያደረገልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። በኃላፊ ተናገረው ዕርቅ ተጀምሯልና።

አንሥአ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ አምቤተ ዳዊት ገብሩ። ከባርያው ከዳዊት ወገን የምንድንበትን ንጉሥ አሰነስቶልናልና /ያሰነሣልን/ ይትባረክ። ቀርን። ንጉሥ ሥልጣን በቁሙ። ቀንድ ይሆናል። ቀንድ አለው እንስሳት በቀንዳቸው ከአራዊት እንዲጠበቁ እኛም የሱን ስም ጠርተን ከኢጋንንት እንጠበቃለንና። ብከ ንወግያሙ ለኵሉሙ ፀርነ አንዲል።

በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለእምዓለም። በዚህ ዓለም ባሉ በነቢያት ቃል እንደተናገረ። እለ እምአማም ከአዳም ቡተወለዱ። እለ እምቅድም /እምጥንት/ ከጥንት ጀምረው በነበሩ በነቢያት በከህናት እንደተናገረ።

www.zeyeneta.com

ከመ ያድኅነነ እምአደጸርነ። ከሠራዊተ አጋንንት ያድነን ዘንድ ወእምአደኵሎሙ እለያጸልኡነ። ከሠራዊተ አጋንንት ከሊቃነ አጋንንት ያድነን ዘንድ።

ከመ ይግበር ሣህሉ ምስለ አበዊነ። ከአባቶቻችን ጋር እንደ አባቶቻችን ላባቶቻችን እደርገዋለሁ ያለው ይቅርታውን ያደርግ ዘንድ።

ወከመይዘክር ኪዳኖ ቅዱስ። ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ።

መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም አቡነ። ይኸውም ለአብርሃም የማለው መሐላ ነው። ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ።

ከመ የሀበነ በዘኢንፈርሕ እምእደ ጸርነ። ከጠላቶቻችን እጅ በማንፈራ ገንዘብ አለመፍራትን ይሰጠን ዘንድ። አንድም በጠላቶቻችን እጅ የተወረወረ ፍላጻ ያገኘናል ብለን በማንፈራ ገንዘብ የማንፈራበትን ይሰጠን ዘንድ። አንድም የሀበነ መድኃኒተ ይላል። ከጠላቶቻችን ከአጋንንት እጅ አስለቅቆ ሥጋውን ደሙን ይሰጠን ዘንድ።

ያድኅነነ ናምልኮ በጽድቅ ወበርትዕ። ያድነን ዘንድ በአሪት በወንጌል ጸንተን እናገለግለው ዘንድ።

በቅድሜሁ ወለኵሉ መዋዕለነ። ባለ በዘመናችን አሱ ባወቀው ነገር ጸንተን በአሪት በወንጌል እናገለግለው ዘንድ። ከአጋንንት እጅ አስለቅቆ ሥጋውን ደሙን ይሰጠን ዘንድ።

መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም አቡነ። ይኸውም ለአብርሃም የማለው መሐላ ነው። ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ። ከሠራዊተ አጋንንት ያድነን ዘንድ። በዚህ ዓለም ባሉ በነቢያት ቃል እንደተናገረ። ከባሪያው ከዳዊት ወገን የምንድንበትን ንጉሥ ያስነሣልን ይቅር ይለን ዘንድ ስወገኖቹ ድኅነትን ያደረገ አግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ። ይቤ ያለውን ጨርሶ። ተነበየ ሳለው አመጣ። አንተም ማሞ (ልጅ) ልዑል አግዚአብሔር የሾመህ መምህር ትባላለህ አለ።

አስመ ተሐውር ቅድመ አግዚአብሔር ከመ ትጹሕ ፍኖቶ። ጎዳናውን ትጠርግ ዘንድ በአግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና። ፍኖት

ልበ አስራኤል። መጥረግ ከእኩያት ከፍትወታት ከኃጣውእ። ቅድመአግዚአብሔር። መንፈቅ ፅንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል።

ከመተህበሙ ለአሕዛብ ያአምሩ መድኃኒቶሙ። መድኃኒታቸው ክርስቶስን ሊያውቁ ታስተምራቸው ዘንድ። ወህብከምሙ ቃስ ዘወህበከኒ እንዲል።

አንድም ነዋ በግዕ። ብለህ ትዳርጋቸው ዘንድ።

በዘያትኀደግ ሰሙ ኃጢአቶሙ። ኃጢአታቸው በሚሠረይበት (በሚሠረይላቸው) ገንዘብ ክርስቶስን ሊያውቁ።

በሣህሉ ወበምሕረቱ ለአምላክነ። በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ። ለዘሐወጸነ እምአርያም። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጎበኘን በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ።

ወሠረቀ ከመ ያርእዮሙ ብርሃኖ። ብርሃንነቱን ብርሃነ መለኮቱን ይገልጥ ዘንድ።

ለእስ ይነብሩ ውስተ ጽልመት በድንቁርና።

ወጽላሎተ ሞት። በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ስዎች ዕውቀትን ልጅነትን ይገልጥላቸው ዘንድ።

አንድም ውስተ ጽልመት። በራሳቸው ፍዳ የተያዙትን።

ወጽላሎተ ሞት። በራሳቸው ፍዳ ላይ በእናት ባባታቸው ፍዳ ለተያዙት ለዎች ብርሃንነቱን ብርሃነ መለኮቱን ይገልጥላቸው ዘንድ።

ከመ ያርትዕ አገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም። እግረ ልቡናችንን ወደ ወንጌል ጎዳና ያቀና ዘንድ። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጎበኘን በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ ኃጢአታቸው በሚሠርይላቸው ገንዘብ ይሠረይላቸው ዘንድ ክርስቶስን ሊያውቁ። ነዋ ስግዕ ብለህ ትዳርጋቸው ዘንድ። ጎዳናውን ትጠርግ ዘንድ በአግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና። እንተም እንጂ ማሞ /ብላቴና/ ልዑል እግዚአብሔር የሾመህ መምህር ትባላለህ።

www.zeyeneta.com

፲፩. ጸሎተ ስምዖን ነቢይ

ለምዖን ማለት ለምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው።

ታሪክ በጥሊሞስ የሚባል የጽርዕ የፋርስ ንጉሥ ነበር። ልጅ አልነበረውም ከሞቱ በኋላ ስም የሚያስጠራ ምን አለ ብሎ ጠየቀ የአይሁድ ሽማግሌ ብሉያት መጻሕፍት አሏቸው ያንን በጽርዑ ምላሽ አጽፊው አሉት። ጥበበ እግዚአብሔር ነው። አይሁድ ሥጋዌ ወልደ እግዚአብሔር አልያረሰም ብሰው ቢፍቱት በጽርዑ ምላሽ አንዲገኝ መጻሕፍቱንም ጸሐፍቱንም ስደዱልኝ ብሎ ላከ። ንጉሠ ነገሥት ነውና ለደዱለት። ፵ ናቸው ቢሉ ፵፩ ድንኳን ሰጣቸው። የሁሉቱንም ቋንቋ የሚያውቅ አንድ ሰው በመካከላቸው አኖረ። በዕጣ (በክፊል) መጽሐፈ ኢሳይያስ ለሰምዖን ደረሰ። አንድም መምህሩ ነውና የእጎቱ ልጅ ነውና ያባትህን መጽሐፍ ማን ይጽፍልህ አሉት። ሲጽፍ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ከሚሰው ደረሰ። ይህን ንጉሥ ፈላስፋ ነው፡ ይነቅፈኛል ብሎ። ወሰት ትጸንስ ብሎ ጻፈ። መልአኩ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ብሎ ጻፈበት ጸሐፊ የጻፈውን ዘወር ብሎ ማየት ልማድ ነው። ዞሮ ቢያይ ድንግል ትጸንስ ብሎ ጽፎበት አገኘው። ማነው እንዲህ የሚያደርግብኝ ብሎ ወቅለምቱን /ምላጩን ቢለዋውን/ አንሥቶ አፍቃሰሁ ሲል አንደ እንቅልፍ ወደብ አደረገው። ይህን የተጠራጠርከውን ሳታየው አትቀርም /አትሞትም/ ተወው አለው። ከዚያ በፊት ፪፻ ዘመን ነበረው ቢሉ ከዚያ በኋላ ፫፻ ዘመን ነበረው ቢሉ ከዚያ በኋላ ፪፻ ዘመን እንደ ትኋን ካልጋ ተጣብቆ ኖሯል። ጌታ በተወለደ በ፵ ቀን ዮሴፍ ሰሎሜ እመቤታችን ይዘውት ወደ ቤተ መቅደስ ዝ። ያ ሳታየው አትሞትም ያልኩህ ከቤተ መቅደስ አለልህ አለው። እንደ ትኋን ካልጋ ተጣብቆ የነበረ የ፵ ዘመን ጎልማሳ ሆኖ ተነሥቶ ፎቱን ፮ቱን ቆመ ብእሲ መር መር አያለ /እየተራመደ/ መጥቶ ከእመቤታችን ክንድ ሕፃኑን ተቀብሎ ይህን ተናግሯል። ስምዖን የተናገረው ነገር ይህ ነው።

ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ። ሰዐሮ ሊል ነው። ወትገብራ ለደብተራ ያለውን ግበራ ብሎ እንደተረጐመው። አኔን ባርያህን በሞት አለናብተኝ።

በሰላም አግዚኦ በከመ አዘዝከ። መራት አንተ ወትገብዕ ውስተ መራት ብለህ እንዳዘዝክ በፍቅር ሳለሁ አስናብተኝ። ከዋሉ ካደሩ ጸብ አይቀርምና /አይታጣምና/። አንድም ዛር ጋር ሳይበዛብኝ። ሽማግሌ ሆኖ ከዋሉ ካደሩ ዛር ጋር አይታጣምና። አንድም ሳታየው አትሞትም እንጂ ማለት የፍቅር አንጋገር ነው። ሳታየው አትሞትም ብለህ እንደተናገርህ።

እስመ ርእያ አዕይንትየ አድነኖተከ። ዓይኖቼ ልጅህ ክርስቶስን አይተዋልና፡ አድኅኖት አለው በግብሩ።

ዘአስተዳለሖከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ። በኵረ ምእመናን አድርገህ ያዘጋጀኸውን።

አንድም አስመርአያ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ። በዮሴፍ በሰሎሜ በእመቤታችን ፊት አይተዋልና። አንድም አንገዲህ ወዲህም በሚነሡ ምእመናን ፊት አይተዋልና።

ከመ ትክሥት ብርሃነ ለአሕዛብ። ሃይማኖትን ለአሕዛብ።

ወክብረ ሰሕዝብከ እስራኤል። ልጅነትን ለእስራኤል ትገልጥ ዘንድ። አንድም ከመ ትክሥት ብርሃነ ለአሕዛብ። አሪትን ለአሕዛብ።

ወክብረ ለሕዝብከ እስራኤል። ወንጌልን ለእስራኤል ትገልጥ ዘንድ። ይህ መለያየት አይደለም።

ከመ ትክሥት ብርሃነ ወክብረ ለአሕዛብ ወለእስራኤል ማለት ነው።

ተፈጸመ ትርጓሜ መኃልየ ፩ቱ መጽቱ ክሊያት በሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

www.zeyeneta.com

ከዚህ ቀጥሎ ከአንድምታው ትርጉም የወጡ ጥቅሶችን ይመልከቱ።

፩. ወአንዘ ቆው ተመስጠ ሕሳኮ፡- ልጁ ሕሳን ላለ ፈጥኖ በሞት ተነጠቀ።
ወአንዘ በቆውም ይላል፡- ልጁ በሕሳንነቱ ላለ በሞት ተነጠቀ ጥበብ ፲፬፡፲፭-፲፮።

፪. ወይጼሊ ለከ እስመ ከመ ነቢይ ውእቱ። ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልይልሃል ትደናነህም ዘኁ ፳፫፡፯።

፫. ቦ ዘወድቀ ውስተ እየር ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ወቦ ዘወድቀ ውስተ አንጦርጦስ /አንጦርጦስ/ ዘውእቱ መትሕተ ታሕቲት። በአየር ላይ ተንሳፎ የወደቀ አለ። በምድርም ላይ የወደቀ አለ በአንጦርጦስ ውስጥም የወደቀ አለ። ይህም የታች ታች ። /ከጥልቆች በታች ያለ ጥልቅ ነው/ አንዳለ አክሲማሮስ /ሥነ-ፍጥረት/።

፬. ወፊውስ ኵሉ ፍጡር ጊሜ። የለው ሁሉ ሕያውቱ ዝናብ ፈጥኖ ቢዘንም ነው። ዝናብም ወደ ምድር በወረደ ጊዜ ደስ ያለኛል፡ አንዳለ ሲራክ ፵፫፡፭፪-፭፫።

፭. መልአክኒ ኢያአመረ ዕሰተ ትስብእቱ ለቃል ወአልቦ ዘአአመረ እምአለ ሀለዉ ውስተ አርያም ዕሰተ /ምሥጢረ/ ምጽአቱ ለቃል ወሥርዓተ ዘንብሮ አግዚእ። መልአክም ጌታ ሰው የሆነበትን ቀን ለውንም ስለመውደዱ ጌታ ሰው ሆኖ የሠራውን ሥራ በአርያም ካሉ መላእክትም ማንም ሰው መሆኑን አላወቀም እንዳሉ ኤጲፋንዮስ እና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት /ዘአንዚናዙ/ በሃይማኖት አበው።

፮. ወይሜምዑ ፲ቱ፪ እምኔከሙ እምድምፀ አሐዱ። ከአንድ ሰው ድምፅ ወይም ዛቻ የተነሣ ሺህ ሰዎች ይሸሻሉ፡ ኢሳ ፴፡፲፯።

፯. ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ። አቤቱ በመልካሙ ጊዜ ጸሎቴ ወደ አንተ ነው እንዳለ ክቡር ዳዊት መዝ ፷፱፡፲፫።

፰. ኢይብእ ሞዓብዊ ወአሞናዊ። አሞናዊና ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ ዘዳ ፳፫፡፪-፬፡ ዘፍጥ ፲፱፡፴፯-፴፰።

፱. አስመ ጎልቄ ላብዕ (ጀቱ) ፍጹም ውእቱ በጎበ ዕብራውያን። በዕብራውያን ሰባት ቍጥር ፍጹም /መጨረሻ/ ነው፡ እንዳለ ሳዊሮስ፡ ዘአንጾኪያ በሃያማኖተ አበው።

፲. ዘያነሥኦ እምድር ለነዳይ ወያሌዕሎ አመራት ሰምስኪን። ችግረኛውን ከመራት የሚያነሣ ምስኪኑንም (ጦም አዳረ ደሀውን) ከፍ ከፍ የሚያደርግ አንዳለ ክቡር ዳዊት በመዝ ፻፲፪፡፯-፱

፲፩. ኢይጠፍእ ምስፍና ወምልክና አምአባሉ ለያሁዳ። በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም ዘፍ ፵፱፡፲

፲፪. አስክዝየ ብጽሒ ወኢትትዐደዊ አምወስንኪ ዳዕሙ ያትከውስ ማዕበልኪ በውስቴትኪ። አስከዚህ ድረሺ አትለፊ ማዕበልሽ ገደብ ይሁን አልሁ፡ ሰባሕርም ዳርቻዋን በወሰነ ጊዜ ውሃ ከትዛዙ እንዳያልፍ። ኢዮ ፴፰፡፲፩-፲፪ ምሳሌ ፰፡፳፱ ኤጲፋንዮስም፡ ይህንን ቃል በመጽሐፉ ቅዳሴው ወስዶታል።

፲፫. አነ ውእቱ ዘአሠርቅ ፀሐየ። ናቡከደነፆር ያስ እኔ ሌላ ንጉሥ የለም በዚህ ዓለምም ፀሐይን የማወጣ ፈጣሪ እኔ ነኝ ብሎ ኮራ ክትዕቢቱም ብዛት የተነሣ እንዲህ አለ። መጽ መቃ ቀዳ ፩፡፫-፬።

፲፬. እምትጥሰዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ጠለየኒ ሲተ እመጽሐፈ ሕይወት። ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ፡ ዘጸአ ፴፪፡፴፪-፴፫።

፲፭. አልቦ ዘንብረ በዓለ ዘከመ ገብረ ኢዮስያስ። ከነቢዩ ከሳሙኤል ዘመን ጀምሮ እንደ ኢዮስያስ ያለ ፋሲካን ያደረገ የለም መጽ፡ ዜና መዋ፡ ካልዕ ፴፭፡፲፰-፲፱።

፲፮. አንሰ ሶበ እቤ አግዚአብሔር አብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። እኔ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ ስለ አብ

www.zeyeneta.com

ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ እንዳለ ባለልዮስ በሃይማኖተአበው። ተናጋሪው ግን ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ነው።

፲፯. ነፍሰሙሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለክሮሙ ሥቃየ /እሳተ/ ዝየንም። የደጋግ ሰዎች ነፍስ ግን በእግዚአብሔር እጅ ናት። የኃጢአተኞች መከራ አላገኛቸውም፡ ጥበ ፫፡፩-፪።

፲፰. እለ ውስተ ሲኦል ጸኡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተዝሠቱ /ነጽሩ/። በሲኦል ውስጥ ያላችሁ ውጡ በጨለማ ውስጥ ያላችሁም ውጡ ተገለጡ። ኢሳ ፵፱፡፱ እንዳለ ባስልዮስ ዘአንጾኪያና ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በሃይማኖተአበው።

፲፱. ወእሥጡ ቀሳውስቲሆሙ ዕራቆ። ታላላቆችም ብላቴናዎቻቸውን ወደ ውሃ ለደዱ ወደ ጉድጓድ መጡ ውሃም አላገኙም እቀዎቻቸውንም ባዶውን ያዘው ተመለሱ እንዳለ÷ኤር ፲፬፡፫።

፳. ወፍናሠርክ ይበርህ ብርሃነ ፀሐይ። በዚያም ቀን በረዶና ውርጭ እንጂ ብርሃን አይሆንም አንድ ቀንም ይሆናል እርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ይሆናል ሌሊትም አይሆንም ሲመሽም ብርሃን ይሆናል። ዘካ ፲፬፡፮-፯

፳፩. ሠረይነ ለብእ ወኢያሕየውነ /ወኢያሕዮነ/ ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢትፈወስት። ባቢሎን በድንገት ወድቃ ጠፍታለች አልቅሱላት ትፈልግም እንደሆነ ለቁስሏ መድኃኒት ውሰዱላት ባቢሎንን ፈወስናት እርሷ ግን አልተፈወሰችም ኤር ፶፩፡፰-፱።

፳፪. ወትፈትዉ አሐተ ዕለተ እመዋዕሊሁ ለወልደዕንስ እመሕያው። ከሰው ልጆች ቀኖች አንዱን ልታዩ የምትመኙበት ወራት ይመጣል አታዩትም ሉቃ ፲፯፡፳፪

፳፫. ንሕነሰ ንትዋሰጥ በምዕር ከመ ቅጽበተዓይን ወኢዝክዕሙ ለሞዉታን። የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገትእንደ ዓይን ጥቅሻ እንለወጣለን /እንነሣለን/ መለከት ይነፋልና።

ሙታንም የማይዘሰበሰቡ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን፡ ፩ ቆሮ ፲፭፡፶፪-፶፫

፳፬. ወርእየ ሕልመ አዘዙ ገብአ ማቴሳላ። ማቱሳላም የአባቱ የሄኖክን ነገር በለማ ጊዜ ሥራውን ሁሉ በሥውር ገለጠለት፡ልና ነገሩን ሰምቶ ተመለሰ። ሄኖ ፶፩፡፳፭-፳፱።

፳፭. አጽንዖ /አጽንን/ ለዝንከ ወልድየ ለርእየ ሕልመ እቡከ። ልጄ ማቱሳላ ነገሬን ስማኝ። የእኔን የአባትህንም ህልም ለመስማት ጮርህን አቅርብ ሄኖ ፶፡፪-፬

፳፮. ነጽርኩ ኀበ ሰኑሲ ሕዛናት ዘሰዮንቱ መላዱ ወጠነ ፍናተ ነዚረ። ሕዛናትን የፈጠረ ጌታ ትሕትናን የዕለት ጽንስ ዘመሰገን እንደጀመረ እወቅ እንዳለ አረጋዊ መንፈላዊ።

፳፯. ምንት አምጽአ ለእግዚአየ ኀበ ገብሩ። አርናም ጌታዬን ገብሩን ወደ ባረያው ያመላው ምክንያት ምንድር ነው ፪ ሳሙ ፲፬፡፳-፳፪

፳፰. ውእቱሰ ንጹሕ እምነ ይቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርዕ ወሩካዜ ወሰከሰሙተ ድንግልና እሰ ሥሩዓን በዕንስ እመሕያው ዘእሙራን ይሙ። ከሰው ዘንድ ከተወሩ ከታወቁ ከሦስቱ ግብራት ንጹሕ ነው። እነዚህም ዘር ሩካቤ የድንግልና መሰወኖ ናቸው እንዳለ ሰዑትዩ በሃ አበው።

፳፱. ወሐሊቆ ፍ ዓም እትዜቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኩሉ ሰብእ። ሰባው ዓመትም በተፈጸመ ጊዜ የባቢሎንን ንጉሥና ያንን ሕዝብ ሰለ ኃጢአታቸው አቀጣሰው ኤር ፳፭፡፲፪-፲፭።

፴. ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላለያነ ውስተ ምድረ ነኪር ፬፻ ፪፻ ዓመተ። እግዚአብሔር አብርሃምን አለው። ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፡ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል። ዘፍ ፲፭፡፲፫።

፴፩. ኀበ ያዕቆብ ጎድሪ ወገበ እስራኤል ተዋረሊ። የያዕቆብን ሥጋ ተዋሐጂ ከእስራኤልም በነሳሽው ሥጋ ሁሉን ግዢ አለኝ። ሲራክ ፳፬፡፳-፳፪።

www.zeyeneta.com

ቁጽ. በዘርዕክ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛብ ምድር። የሃምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። ዘፍ ፲፪፡፪-፬።

ቁጽ. አስመ እምፍሬ ከርሥከ እነብር ዲበ መንበርከ። ከወገብህ የሚወጣው ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ መንግሥቱንም እጸናለሁ ፳ኛ ሳሙ ፯፡፲፪-፲፮።

ቁጽ. እነ እግዚአብሔር ዘእፈጥር መካነ ወበአወልድ። በሠራ ወደ መውለድ የማደርስ እኔ አላስወልድምን? ማሕፀንን እኔ አዘጋለሁን? ኢሳ ፷፮፡፱-፲።

ቁጽ. ምክንትለ ኢተውህባ ለብእሲት ዳዕሙ ትማስን /ትመውት፡ በግብረ እደዊሃ ዘእንበለ ውሉድ። በእጅዋ በሠራችው ሥራ ልጅ ሳትወልድ ትሞሸለት እንጅ ለሌት ምክንት አልተሰጣትም ነበር፡ ሄናክ ፹፯፡፲፱-፳።

ቁጽ. ብከ ንወግዖሙ ለኵሉሙ አርኃ። በአንተ ጠላቶቻችንን እንዋጋቸዋለን መዝ ፵፫፡፭

ቁጽ. ወዘከክሙሙ ቃለ ዘመሀበክኒ። የለጠፍኸኝን ቃል ለጥቻቸዋለሁና እነርሱም ተቀበሉት፡ ዮሐ ፲፯፡፰።

ከአንድምታው ትርጓሜ በምዕራፍና በቍጥር የተዘጋጁ ጥቅሶች በዚህ ተጠቃልለዋል።

ክፍል ፪

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኃዱ አምላክ አሜን

አዋጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ጽሑፈ ሐተታ መጽልየ

፲ቱ ወፍቱ ነቢያት

በአብ ስም አምኔ አብን ወላዲ ብዬ፡ በወልድ ስም አምኜ

ወልድን ተወላዲ ብዬ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ

መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ብዬ፡

የ፲ቱ ነቢያት መጽልይን ማብራሪያ መጻፍ እጀምራለሁ

www.zeyeneta.com

መጋልያ ዝደያት ወጸሉቱ ሰሙሴ
አንተጽ ፩
ስለ መጋልይ

መጋልይ፦ ማለት ምስጋና ግጥም ቅኔ ማለት ነው። ምስጋናውም በሁለት ይከፈላል። በዜማ በግጥም /በስንኝ/ ምስጋናውንም የሚያቀርብ ሁሉም በየቋንቋው ነው። ሁሉም በየቋንቋው ሸንል በእግዚአብሔር ምሳሌ ከተፈጠረው የሰው ዘር የመጀመሪያ አባት ከሆነው ከአዳም በፊት ቀድመው ከተፈጠሩ ከአዕዋፍ ዘሮች መጥቀስ ይቻላል። ዜማቸው /ድምጻቸው/ ያማረና ደስ የሚያሰኝ አዕዋፍ እንዳሉ መጻሕፍት ያስረዳሉ።

አዕዋፍ ዘሠናይ ዜማዘሙ አንዲል። ጥበ ፲፮፡፲፮። በድጋሚም ያፍ ዘይብልዎ አሮድዮን /አልአሮድዮን/ አንዲል።

ታሪክ አሮድዮን የሚባል ወፍ አለ። እጅግ ድምፀ መልካም ነው። ሰው ከሚኖርበት ወደ በረሀ ሔዶ ይኖራል። እሱም ከዜማው ደስ ማሰኘቱ የተነሣ ምግብ መልቀሙን እስኪዘነጋ ድረስ ድምፁን ያሰማል። መንገደኛውም ሁሉ የየራሱን መንገድ /ጉዞ/ ይዘነጋል። ማር ይሥ አንቀጽ ፭፰ ምዕ።

ነቢያትም ብዙዎች በዓለም የተወለዱ ቢሆኑም ወይም በዓለም ተወስነው ልጆችን ወልደው ቢኖሩ እነሱ ከሰው ዘር ተገኝተው ዘርን /ልጅን/ ለዓለም ቢተኩ የዚህን ዓለም መንገድ ብቻ ሳያከተሉ ሰብአ ዓለም ከገቢረ ኀጢአት ወደ ዝቢረ ጽድቅ እንዲመለሱ ከእግዚአብሔር የታዘዙትን መልእክት ከመፈጸምና ትእዚትን ከመናገር ወደ ኋላ አላሉም።

በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለ እምዓለም እንዲል። ሉቃ ፩፡፸ ስለዚህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በየዘመናቸው በመንፈሳዊ ዜማ /ምስጋና/ እንዲሁም በግጥም እግዚአብሔርን አመሰግነዋል። ለምሳሌ፦

፩. እስራኤል ኦባርነት ወደ ነፃነት ሲሸጋገሩ ዝኬብሉ ብለው አመሰግነዋል። ዘጸ ፲፭፡፩-፳። ይህ በዘመነ መሳፍንት ነው። ከካህናት ሙሴና አሮን ሙሴ መሰፍን ሲሆን አሮን ካህን ነው።

፪. በዘመነ መሳፍንት፡ ከመሳፍንት ባርቅና ነቢይት ዲቦራ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን በተቀዳጁ ጊዜ የተቀኙት ቅኔ አለ። ነገሥታት ዘያ ስሙ መኳንንት ዘይ አድምጡ እኛ ለእግዚአብሔር አንቀኛለን። ለአስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔርም እንዘምራለን ብለው በምስጋና ተቀኝተዋል። መሳ ፭፡፩

፫. በዘመነ ነገሥት፡ ከነገሥታት ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን አመሰግነዋል። የእግዚአብሔርን ሰም አመሰግናለሁ። በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ። መዝ ፻፵፰፡፩ ንጉሡ ሰሎሞንም ከፍ ያለ ምስጋናን አመሰግኗል። መኃ ፩፡፩ የመኃልይን ሐተታ ማብራሪያ በዚህ አጠቃለን ነቢይ የሚለውን እንቀጥላለን።

ስለ ነቢይ /ነቢያት/

ነቢይ ማለት ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለንጉሥና ለሕዝብ የሚናገር ማለት ነው። ለዚህ ማስረጃ አንድ የእግዚአብሔር ሰው በዚች ከተማ አለ። አርሱም የተከበረ ሰው ነው። የሚናገረውም ሁሉ በእውነት ይፈጸማል ይህም ሳሙኤል ነው። ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ቃልን ተቀብሎ ለሳዖል ሲናገር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትመራ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል ብሎ አንገሠው ፩ኛ ሳሙ ፱፡፮። ፩ኛ ሳሙ ፲፡፩-፪ ነቢያትም ትንቢት ሲናገሩ እግዚአብሔር አንዲህ ይላል አያሉ ነው። እግዚአብሔር አንዲህ ይላል። ማዴ ሊመጣ ጽድቁም ሊገለጽ ቀርቧልና ፍርድን ጠብቁ ጽድቅንም አድርጉ ኢሳ ፶፮፡፩-፪።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የነገርኩህን ቃል ሁሉ በመጽሐፍ ጻፍ። ኤር ፴፡፪።

የሰው ልጅ ሆይ ይህን መጽሐፍ ብላ አለኝ። አፌንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጎረሰኝ። እኔም በላሁት መጽሐፉም እንደ ማር ጣፈጠኝ ሕዝ ፫፡፩-፫።

www.zeyeneta.com

ስለ ጸሎት /ታት/
የጸሎት ዝርዝርና ጥቅሙ

ጸሎት፡- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንደሚገልጸው ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእግዚአብሔር ስለተፈጠረ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መገናኘት ይገባዋል። መገናኛውም ጸሎት ስለሆነ ይጸልያል። የክርስቲያን ጸሎት ወደ ክርስቶስ ነው። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና ማጽኛ ነው።

ጸሎት፡- ሁሉ ኀብረትን ምስጋናን ስግደትን ንስሐን ልመናን ምልጃን ያጠቃልላል። በጸለየ ዕጣን ጊዜ ሕዝቡ ይጸልዩ እንደነበር ካህኑ ዘካርያስም ጸሎትህ ተሰማ የሚል መልካም መልስ ማግኘቱን እንረዳለን። ሉቃ ፩፡፲-፲፩። ክርስቶስም በቃልና በሥራ የጸሎትን መንገድ አስተምሮናል። ሰምሳሌ ክርስቶስ በአንድ ቦታ ይጸልይ በነበረበት ወቅት ከደቀ መዛሙርቱ እንዱ በጠየቀው መሠረት አባታችን ሆይ የሚለውን ጸሎት አስተማረ። ሉቃ ፲፩፡፩-፲፫።

እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት በደስታ ይሰማልና ጸሎት ብዙ ኃይል አለው። ፭ ጴጥ ፫፡ ፲፪። እርስ በእርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ። የጸድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች ብሎ የጸሎትን ጥቅም መጽሐፍ ያስረዳናል። ያዕ ፭፡፲፮-፳።

አለመጸለይ ኃጢአት ነው። መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ ብሎ ነቢዩ ሳሙኤል ስሕዝቡ አስተማራቸው። ፩ኛ ሳሙ ፲፪፡፳፫

ስለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ልደት መመረጥና የግብጽ ተልዕኮ

ሙሴ፡- ለወላጆቹ ሦስተኛ /የመጨረሻ/ ልጅ ነው። አባቱ እንበረም እናቱ ዮካብድ ይባላሉ። በሶስት ሺሕ ሰባት መቶ ሰልሳ ሦስት ዓመተ ዓለም ሙሴ በግብፅ ተወለደ። ሰሟ ዘመንም ያህል

በግ ሲጠብቅ ከኖረ በኋላ ሙሴ እንደልማዱ በጕቹን ሲጠብቅ እግዚአብሔር ሙሴን መርጦ በሲና ተራራ /በኮሬብ/ ተገልጦ በግብጽ አገር በባርነት የሚሠቃዩት እስራኤልን እንዲያወጣ አዘዘው። ከብዙ መቅሠፍት በኋላም ፈርዖን እስራኤልን ለቀቀ። እስራኤል የኤርትራን ባሕር በደረቅ ምድር ተሻገሩ። እስራኤል ከግብጽ የወጡት ስድስት መቶ ሺሕ ሆነው ነው። ይህ ቍጥር ሕፃናትንና ሴቶችን አይጨምርም ዘጸ ፲፪፡፴፯-፴፱።

እስራኤል በግብጽ የኖሩበት ዘመን ፬፻፴ ዓመት ነው። ዘጸ ፲፪፡፵-፵፩። ይህም ቍጥር የእስራኤል ልጆች እነሱም አባቶቻቸውም /አብርሃም ከነቤተሰቡ/ በከነዓንና በግብፅ የኖሩበት ዘመን ነው።

በተጨማሪም እግዚአብሔር አብርሃምን ከተነጋገረበት ቀን ጀምሮ ያዕቆብ ወደ ግብፅ እስከ ወረደበት ዘመን ድረስ ፪፻፲፭ ዓመት ይሆናል። ያዕቆብ ከግብጽ ከወረደበት ቀን እስከ ሙሴ ልደት ፻፷፩ ዓመት ይሆናል።

ከሙሴ ልደት እስራኤል ከግብጽ እስከ ወጡበት ጊዜ ፹ ዓመት ይሆናል። በጠቅላላው ፬፻፴ ነው። ሙሴም ከእግዚአብሔር ጋር ፭፻፫ ቃላተ ሕግን ተነጋግሯል። ማለትም እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው የሚለው ቃል ፭፻፫ ይሆናል።

ወእምድኅረሁ በፅቱ ፪ ወፀ ክረምት መጽአት ኦሪት እንዲል። አብርሃም ከሞተ በኋላ በ፬፻፴ ዘመን ኦሪት ተሠራች። ገላ ፫፡፲፯

ሐተታ፡ አብርሃም ተስፋውን በሰማ በ፸፭ ዓመት ይስሐቅን ወለዲል። ይስሐቅ መሰከረም ፴ ተጸንሶ ሰኔ ፮፭ ቀን ተወለደ። ይስሐቅ በተወለደ በ፷ ያዕቆብን ወልዲል። ፹፭ ይኾናል። ያዕቆብ በተወለደ በ፻፴ ርደተ ግብጽ ሆኗል። ይህንም ገብተው ይቆጥሩታል። ያዕቆብ በተወለደ በ፹፫ ሌዊን ይወልዳል። ሌዊ በተወለደ በ፵፬ ቀዓትን ይወልዳል። ቀዓት በተወለደ በ፹ ርደተ ግብጽ ሆኗል። ፻፻፲፭ ይኾናል። ርደተ ግብጽ በሆነ በ፷፭ ቀዓት እንበረምን ይወልዳል። እንበረም በተወለደ በ፰ ሙሴን ይወልዳል።

www.zeyeneta.com

ሙሴ በተወለደ በ፹ እስራኤል ከግብጽ ወጥተዋል። ፪፻፲፭ና ፪፻፲፩ ፱፻፹ ይሸናል። በ፱፻፹ ዘመን አሪት ተሠራች ያለኘው ይህ ነው።

ስለ እስራኤል ከግብፅ አወጣጥ

እስራኤል ከግብጽ የወጡበት ምክንያት ጌታ ለአብርሃም የነገረው ተስፋ ሲፈጸም ነው። ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላስያን ውስተ ምድረ ነኪር ወይቀንይሙ ግብጽ ፬፻ ፱፻ ዓመተ ወእምዝ ይወጽኡ። /ልጆችህ በባዕድ አገር ይኖራሉ ግብጻውያንም አራት መቶ ዓመት ይገዟቸዋል። ከዚህ በኋላም ይወጣሉ ባለው ቃል ኪዳን መሰረት ሲሆን አራት ነገሮችንም በመጠበቃቸው ነው።

፩. ግዝረትን ስለአልተው
፪. ስማቸውን ስላልለወጡ
፫. ቋንቋቸውን ስላላጠፉ
፬. ተስፋቸውን ስላልገሰጡ ነው

እስራኤል ከግብፅ የወጡበት ዘመን በሦስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሦስት ዓመተ ዓለም ነው። መጋቢት ፳፫ ረቡዕ ቀን እስራኤል በጉን በልተው መጋቢት ፳፬ ቀን ሐሙስ ከግብጽ ወጥተዋል። በዕብራውያን አቆጣጠር ሚያዚያ ፲፬ በጉን በልተው በ፲፭ ወጥተዋል።

ስለ ኤርትራ

ኤርትራ በግብጽና በዐረብ መካከል ያለ ባሕር ነው። ከብርቱሳይድ እስከ ባብአልመንደብ ያለ ባሕር ቀይ እላት የሚመስል ቀይነት /ቅላት/ ያለው ባሕር ነው። መሬቱ ቀይ ስለሆነ ቀይ ሰልባቦት ይንሳፈፍበታል። ቀያይ ዓሣ ይወለድበታል። በዙሪያውም ቀያይ ሣር ቅጠል ያበቅላልና ቀይ ያለኘው ይህ ነው።

ባሕርንቱ ከሜዲተራኒ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ገጥሞ ተያይዞ በስተምሥራቅ አሰያንና አፍሪካን ይለያል። ዘጸ ፲፡፲፱። ፲፫፡፲፰። ፲፭፡፬።

ስለ ፈርዖናውያን

ፈርዖን ግሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት አዜ ይባሉ እንደነበር ከጥንት ጀምሮ የድሮ ዘመን የግብጽ ነገሥታት ፈርዖን ይባሉ ነበር። የሮም ነገሥታት ቄሳር የጣሊላ ሄሮድስ እንደሚባሉ በብሉይ ኪዳንም የተጠቀሱት ፈርዖኖች በመጠሪያ ስማቸው ሳይለዩ በዚህ ማረግ ይጠሩ ነበር።

የደቱ ፈርዖኖች ልዩ ስም እንደሚከተለው ነው

፩. በአብርሃም ጊዜ /ዘመን/ የነበረው ፈርዖን ልዩ ስሙ ሳኖሪስት /ሌስስትሪስ/ ይባላል። አብርሃም በረሃብ ምክንያት ከግራ ጋራ ወደ ግብጽ ወርዶ ያወቀው ፈርዖን ይህ ነው። ዘፍ ፲፪፥፲፩-፳። በዚህ ጊዜ ፍቅር ጸንቷል።

፪. በያዕቆብና በልጁ ዮሴፍ ዘመን የነበረው ፈርዖን የግብጽ ተወላጅ ነው። ልዩ ስሙ አህሞሲስ /አሜንሆቴፕን/ ይባላል። በዚህ ጊዜ ፍቅር ተከፍሏል።

፫. ሙሴ በተወለደ ጊዜ የነበረው ፈርዖን እስራኤል በሥራ የደከሙበትና ነፃነት ያጡበት ሙሴም ያደገበት ጻግሜኖ ራምሲስ ነው። ልዩ ስሙ መኔፕታህ /መሬንፕታህ/ ይባላል። እስራኤልን አልለቅም ብሎ በሀገሩ ላይ መቅሠፍት እንዲወርድ ያደረገና ከነሠራዊቱ በኤርትራ ባሕር የሠጠመ ይህ ፈርዖን ነው። ስማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስም በሐዲስ ኪዳን ዘመዶቻችንን ተነኮሰ ያለው ይህን ፈርዖን ነው። በዚህ ጊዜ ፀብ ጸንቷል። የሐዋ. ፯+፲፯-፳፪።

አንቀጽ ፪
ስለ ስማይ /ያት/

የኪዳን ወልድ ክፍሌ የግእዝ መዝገበ ቃላት እንደሚተነትነው ስማይ /ያት/ ማለት ሰፊ ሆኖ የተዘረጋ መጥቆ የሚታይ የማየት መጨረሻ ወሰን ድንበር ከእርሱ በላይ ሌላ የማያላይ መጋረጃ የምድር ባጥ /ጣራ/ መዋቅር ከእላት ከውሃ

www.zeyeneta.com

የተሠራ በነፋሳት ምለሶዎች የቆመ ከበላዩ የውቅያኖስ ውሃ ሆኖ የሰፊረበት ከበታቹ ታላላቅ ብርሃናት /ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት/ እንደፋናስ የተለቀሱበት ነው።

ሰማይ ሁለት ቃል ነው። ሰ፡ማይ ትርጕሙ እሳትና ውሃ ማለት ነው። ከፍ ማለቱና ርቆ መታየቱ የጋራ ሆኖ ለጠፈርም ለላይኞቹ የብርሃን ስማያት ለተባሉት ለኀቱ ሁሉ ይነገራል። አሳትና ውሃ ግን ለጠፈር ብቻ ነው።

ስለ ምድር /ምድራት/

ምድር ምድራት አምዳር አምዳራት አምዳሮት ማለት፡ ስፌ ዝርግ ደንዳና ወፍራም ከነ ባሕሩና ከነ የብሱ ከነ ልብሱ የብስ የባሕር ርቦ /ፀኖ/ ነው። ከየብስ የተፈጠሩ የዐርብ ፍጥረቶችም የሚኖሩበት ነው። ወስመዮ ለየብስ ምድሪ፡ ወለምእላደ ማይ ባሕረ። ለታብቍል ምድር ሐመልማለ ሣዕር፡ ለታውጽእ ምድር ዘመደ እንስሳ ወአራዊት እንዲል ዘፍ ፩፡፲-፳፬

ምድር ርሒባት። ርሒብ ይላል። ምድሪቱም ስፊና ጸጥተኛ ለላም ያላት ነበረች። ፩ኛ ዜና ፬፡፵፬። አድባር ወአምዳር። የምትገቡባት ምድር ኮረብታና ሸለቆ ያለባት አገር ናት ዘዳ ፲፩፡፲፩። ወዘረወከምሙ በአምዳሮት። ወደአገሮችም በትኖ ቸዋለሁ። ሕዝ ፲፩፡፲፭-፲፯። ይበውእ ውስተ አምዳሮት። ወደ መልካሚቱ ምድር ይገባል ዳን ፲፩፡፵።

በተጨማሪም ምድር የሰው ባሕርይ ሥጋ ጠፊር መሬት የሚል ትርጕም አለው። ዘምድረ ለብለ እንዲል። ኪዳ። ምድርንም በእራቱ እፍላጋት አጽንቷታል። ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ እንዲል። መዝ ፻፴፫፡፮ ወይም ከውሃ ጋር አቀላቅሎ ፈጥሯታልና። ወበአፍላግኒ ውእቱ አጽንዓ። መዝ ፳፫፡፪። በአራቱ ወዝቦች እጽንቷታልና ውስጥ ለውስጥ ባያጠጧት እንደሪቅ እንደጎታ እንደ ጎተራ ሆና በፈረስች ነበርና። ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ በል። መዝ ፳፫፡፪።

የአራቱ ወንዞች ስምና መነሻ መድረሻ

፩. ኤፌሶን /ፊሶን/፡- የወተት ወንዝ ነው። ርስትነቱም የሕፃናት ነው። ማቴምስ ይመስልበታል። አስመ ኩሉ ዘይትወጋዕ ሐሊበ ሕፃን ውእቱ። ወተትን የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፡ ወኩነ ከመ ሕፃናት ወአፍቅሩ ሐሊበ ነባቤ። አሁንም እንደተወለዱ ሕፃናት ተዝክል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ ዕብ ፭፡፲፫። ፩ ጴጥ ፪፡፪።

፪. ግዮን፡- የወይን ወንዝ ነው። ለሚጸሙ ለሚጸልዩ በመልካም ሥራቸውም ደስ ለሚላቸው ርስት ነው። በማርቆስ ይመሰላል።

፫. ጤግሮስ፡- የማር ወንዝ ነው። ርስትነቱ ነገርን መሸከም ለሚቻላቸው /ለትግሥተኞች/ ስዎች ነው። ሉቃስ ይመስልበታል።

፬. ኤፍራጥስ። የዘይት ወንዝ ሲሆን ርስትነቱ የሰማዕታት ነው። ዮሐንስ ይመሰልበታል። በተጨማሪም የ፬ቱ ወንዞች መነሻንና መድረሻን በአጭሩ እንገልፃለን።

፩ኛው ኤፌሶን /ፊሶን/ ሲሆን ዘፍ፡-፪፥፲፩-፲፪። በህንደኬ ያሉትን የወንዝ ውሃዎችን ሁሉ አሰባሰቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ውቅያኖስ ይገባል።

፪ኛው ግዮን ሲሆን ። ዘፍ፪ ፲፪-፲፬ ። በኢትዮጵያና በግብፅ ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ ሰብስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ኢያሪኮ ይገባል።

፫ኛው ጤግሮስ ሲሆን ዘፍ ፪፥፲፬-፲፭ ። በዮናናውያን ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ አሰባስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ባሕረ ኤርትራ ይገባል።

፬ኛው ኤፍራጥስ ነው። ዘፍ ፪፡፲፭-፲፯ በአውሮፖ በፋርስ በባቢሎን ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ አሰባስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ባሕረ ኤርትራ ይገባል።

ሐተታ፡- ምድር ምንን ትመስላለች ቢሉ ሰውን ትመስላለች። እንደ ደሙ በውሃ፡ እንደ አጥንቱ በደንጊያ፡ እንደሥሩ በእንጨት፡ ጸንታ ትኖራለች። ሰማያትን የፈጠረ

www.zeyeneta.com

ምድርንና በውሰጧ ያለውን አጸና አለ። ኢሳ ፵፪፡፭-፮። በመዝሙር ፻፵፰፡፰ ላይም አንተ እግዚኦ አቅደምከ ሣርሮታ ለምድር። አቤቱ አንተ ምድርን አስቀድመህ ፈጠርህ። ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድር በእግዚአብሔር ቃል ከውሃ ተጋጥማ በውሃ መካከል ነበረች፡ የሚል ይገኛል። ፪ኛ ጴጥ፡፫፡፭

አትደምከ አለ። ከማን ቢሉ ከስማይ ምነው የሰማይና የምድርማ ተፈጥሯቸው በቀዳሚ ጊበረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ስማይንና ምድርን ፈጠረ ባለ ጊዜ አንድ ጊዜ አይደለምን ቢሉ በመታየት አቅደምከ አለ። ባሬ ትሉ ስማይ አይታይምና። አንድ ወገን ለምድር ሰጥተህ ከመታየት መፈጠሯን ብቻ አቅደምከ በል። ከዚህ ብሩህ ሰማይ መልቶ ነበርና።

አንቀጽ ፫
ስለ እሳት /እሳውት/

እሳት፡- ከአራቱ ባሕርያት /ነፋስ እሳት ውሃ መሬት/ ከሊህ አንዱ በሁሉ የሚገኝ ነው በድርቀቱ ከነፋስ፡ ስሙቀቱ /በማቃጠሉ/ ከመሬት። በብርሃኑ ከውሃ፡ የሚስማማ ነው። በአምጣነ ዕፁ ለእሳት የወጢነዱ። በእንጨቱ ልክ የእሳቱ ነዲድ ይበዛል። ሲራ ፵፰፡፲

እሳት በላዓ ለዓማጽያን እንዲል። ቅዱ ማር እሳተ እሳት የሰማይ እሳት። እሳተ ገሞራ እሳተ ገሃነም ብርቱ ቅጣት። አበራኤል ልጆቻቸውን ለሞሎህ /ሞሎህ/ ለተባለ ጣዖት/ ሠውተው ያቃጥሉበት የነበረ የሰማያዊ እሳት ምሳሌ ነው። በወንድሙ ላይ የተቆጣ ሁሉ የገሀነም ፍርድ ይገባዋል። እሳት ዘለዓለም፡ የማይጠፋ የማያልፍ፡ ሥቃይ ያሰበት ማቴ ፲፰፡፰-፱።

እሳተ ሕይወት። መንፈስ ቅዱስ እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል። ማቴ ፫፡፲፩-፲፫።

ስለ ሲኦል

ሲኦል፡- ማለት ታች ዝቅተኛ መቃብር ማለት ሲሆን በዓመተ ፍጻ ሰአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል ነፍሳት የኖሩበት ነው። ከዚህ በኋላም በሕገ እግዚአብሔር ያልሄዱና ሥርዓቱን ያልጠበቁ የከፉ ሥራ ክፉ ውጤት መኖሪያቸው ነው። ከምጽአት በኋላ ግን የጥሞኑን የፍርድ ቦታ ገሃነም ነው። ሙታን ስዎች ከውሃዎች በታች በውሃዎች ውሰጥ ከሚኖሩ በታች ይንቀጠቀጣሉ። ሲኦልም በፊቱ ራቁትኖን ናት። ኢዮ ፳፮፡፭-፮

ስለ አሪት አጻጻፍ

አሪት አራት አይነት ነው/አራት ጊዜ ተጽፋሰች።

ሰ. በሙሴ ዘመን ነው። ይህ አሪት ዘሌዋውያን /አሪተ ሌዋውያን/ ይባላል።

፪. አሪት ዘሊቃውንት /አሪተ ሊቃውንት/ ይባላል። ይህ እንደምን ነው ቢሉ በግብጽ ንጉሥ በበጥሊሞስ ዘመን በአምስት ሺሕ ሁለት መቶ አርባ አምስት ዓመተ ዓለም ፵ ሊቃናትን ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ አሪት ዘሌዋውያንና መጻሕፍተ ነቢያትን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ በተረጐመ ጊዜ ነው።

፫. አሪት ዘሳምራውያን /አሪተ ሳምራውያን/ ይባላል። በዚኖው ኢዮርብዓምና በአሶር ንጉሥ በሰልምናሶር ዘመን ምናሴ የሚባል ካህን አሪትን አስተምሮ ስለጻፈላቸው ከላይ የተጠቀስውን ሥያሜ ይዟል። ፪ ነገ ፲፯፡፳፭-፳፱

፬. አሪት ዘአይሁድ /አሪተ አይሁድ/ ብጡል ይባላል። የዚህ ምክንያት ደግሞ ሰማዕቱ አስጢፋኖስ የሄኖክ የትውልድ ሱባዔንና የኤርምያስን የዕለት ሱባዔ እየቆጠረ ለአይሁድ ሲያስተምር ባለማመናቸው ጊዜው ክልደረሰም ሥጋ ክልሰበሰም እያሉ ከአዳም ፫ኛ ትውልድ ከሆነው ከሄኖ ዘመን ጀምረው እየቀነሱ አሰክ አብርሃም ድረስ ሰንድ ሺሕ አምሰት መቶ ዘመን አውጥተው ስለጻፉ ጊዜው አልደረሰም አሰኝቷቸዋልና አሪተ አይሁድ ተባለ።

www.zeyeneta.com

ስለ ሙሴ አገልግሎት

ሙሴ፡- እስራኤልን በምድረ በዳ ለ፵ ዓመታት ያህል ሊመግብና ሊመራ ኖረ።

ታሪክ፡- ከዕለታት አንድ ቀን እስራኤል ሙሴ ውሃ ሙሉ ውሃ እያሉ ዘበዘቡት። ደክሞት ነበርና ንሴብሐን ዘጸ ፲፫፡፩ ላይደግም ስጣቸው እነርሱም ላያመለማኑ ጠጥተውታል። እግዚአብሔር ሙሴን በእንተዝ ኢትበውኣ ለኪየሩሳሌም በእንተ ዘኢቀደስክኒ። ለዘርሀ እሰጣታለሁ ያልኳት ምድር ይቺ ናት። በዓይንህ እንድታያት አደረግሁህ። ነገር ግን ወደዚያች አትሻገርም ብሎት ነበርና። በዚህ ምክንያት ኢየሩሳሌም አልገባም። ምድረ ናባው ቀርቷል። አገሩ ሞዓብ የተቀበረበት ተራራ ናባው ፍስጋ /ፒስጋ/ ይባላል። ዘዳ ፴፬፡፩-፯

አንቀጽ ፩
ስለ ነቢይት ሐና ዘመን

ሐና፡- ማለት ሀብት መልካም ስጦታ ዕድል ፈንታ ማለት ነው። የሕልቃና አንደኛ ሚስት ናት። እምነቷም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው። መካንም ነበረች። ሐና የተወለደችበት ዘመን በአራት ሺሕ ሦስት መቶ ዓመተ ዓለም ገደማ ነው።

ስለ መካን /ናት/

መካን፡- ማለት የማይወልድ /የማትወልድ/ የማያፈራ/ የማታፈራ ማለት ነው።
ወሶራለ መካን ይእቲ ወኢትወልድ። ሶራም መካን ነበረች ልጅ አልነበራትም። ዘፍ ፲፩፡፴/፲፱፡፴፩-፴፪

እስመ መካን ይእቲ ኤልሳቤጥ። ኤልሳቤጥም መካን ነበረች። ሉቃ ፩፡፯-፳

ብፁዓት መካናት እለ ኢወለዳ። መካኖችና ያልወለዱ ማሕፀኖች ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓት ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ ሲል ክርስቶስ ለኢየሩሳሌም ልጆች ተናገረ። ሉቃ ፳፫፡፳፱-፴።

ነቢይት ሐናም ልጅ ባለመውለዷ ታዝን ነበር። በእግዚአብሔር መቅደስ ፊት ጸለየች። ወንድ ልጅ ብትሰጠኝ ዕድሜውን ሁሉ ለእንተ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ ብላም ስእለትን ተሳለች ፩ኛ ሳሙ ፩፡፩-፲፪።

ስለ ስእለት /ስእለታት/

ስእለት፡- የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስእለትን እንደሚከተለው ይተረጉማል። ሰው በፊቃዱ አንድ ነገር ለእግዚአብሔር ለማድረግ ወይም ለመስጠት ቃል መግባት ነው። ብዙ ጊዜ ሰው ወደፊት ከእግዚአብሔር በረከትን ለመቀበል ስእለትን ይሳላል። ማስረጃ ያዕቆብም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆንና ቢጠብቀኝ ከሰጠኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ከአሥር እጅ አንዱን አሰጣለሁ ብሎ ተሳለ። ዘፍ ፳፰፡፳-፳፪። ዘሌዋ ፳፯። ዘኍ ፳፩፡፩-፫። መሳ ፲፩፡፴-፴፩።

ሰው ስእለቱን ባይፈጽም ኀጢአት ነውና በችኮላ መሳል አይገባም። ዘዳ ፳፫፡-፳፩-፳፫፡- ምሳ ፳፡፳፭። መክ ፭፡፬-፮። እግዚአብሔርም የሐናን ጸሎትና ስእለት ሰምቶ ወንድ ልጅ ወለደች ከእግዘአብሔር ለምኜ አግኝቸዋለሁ ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው። ፩ኛ ሳሙ ፩፡፩-፲፪።

ሕፃኑም ጡትን በተወ ጊዜ ሐና ወደ እግዚአብሔር ቤት ወሰደችው። በእግዚአብሔርም ቤት አደገ። ከዚህ በኋላም ሦስት ወንዶችንና ሁለት ሴቶችን ወለደች ፩ኛ ሳሙ ፪፡፳፩።

አንቀጽ ፬ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፭
ስለ ሕዝቅያስ ጸሎትና ዘመን

ሕዝቅያስ ማለት የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር ኃይሌ ነው ማለት ነው። በአራት ሺሕ ስባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ዓመተ ዓለም ተወለደ። ፲፫ኛው የይሁዳ ንጉሥ ነው።

www.zeyeneta.com

ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እሱን የሚመስል አልነበረም ፪ ነገ ፲፰:፭። ባዕድ አምልኮትን አጠፋ። ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ስበረ ቤተ መቅደስንም አሠራ። ታሞ ለሞት ከደረሰ በኋላ በዘመኖቹ ላይ ፲፭ ዓመት የተጨመረለት ጸሎቱም ቅድመ አግዚአብሔር የደረሰለትና የሠመረለት ንጉሥ ነው። ይህም የሆነው በነቢዩ በኢሳይያስ ምክንያት ነው። ምናሴንም የወለደ ከዘ.ሀ በኋላ ነበር። አሳ ፴፰:፩-፯ በተወለደ በሸሸ ዓመቱ ነገሠ የመነገሥቱ ዘመን ፵፱ ዓመት ሲሆን መላ ዘመኑ ፶፱ ዓመት ነው። አንቀጽ ፭ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፮
ስለ ንጉሡ ምናሴ በደልና ንስሓ

ምናሴ፡- ማለት ማስረሻ ወይም መከራዬን አስረሳኝ ማለት ነው። ከይሁዳ ነገሥታት አሥራ አራተኛው ንጉሥ የሕዝቅያስ ልጅ ነው። ፪ ነገ ፳:፳፩።

በአራት ሺሕ ስምንት መቶ አንድ ዓመተ ዓለም ተወለደ። በተወለደ በ፲፪ ዓመቱ ነገሠ። ባዕድ አምልኮትን እየተከተለ ከአሞራውያን ይልቅ ክፉ ሥራ ሠራ። በኢየሩሳሌም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲመጣ አደረገ። ፪ ነገ ፳፩:፩-፲፮። ፪ ዜና ፴፫:፩-፲። ኤር ፲፭:፬።

የአሶር ንጉሥ አስራዶን /ንውስ ስናክራም/ ወደ ባቢሎን ማረከው። በዚያም ጊዜ ጸለየ። እግዚአብሔርም ምሕረትን አደረገለት፡ና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አዘዘ። ፪ ዜና ፴፫:፲፩-፳

ስለ ውቅያኖስ

ውቅያኖስ ውሃ የሚኖርበት የውሃ መኖሪያ ታላቅ ባሕር ስፋ ጥልቅ ሲሆን ባራቱ ማዕዘን የሞላ ነው ውሃ የሌለበት ከደረቁ ምድር ፫ እጅ የሚበልጥ እንደየብሱ ፯ ክፍል ያለው ነው። ባሕር ለታላቁ ለታናሹ ሲሆን ውቅያኖስ ግን ለታላቁ ብቻ ነው።

ስለ ብሔሞት

ብሔሞት ጉማሬ የወንዝ አውራ የባሕር ፈረስ በአፍሪቃ ወንዞች በሐይቆች የሚገኝ ከውሃ አየወጣ ሣርና ቅጠል የሚበላ ታላቅ ጎናና ቆርበቱ ወፋራም አንገቱ ደንዳና የባሕር የበረሃ ጉሽ ጠባዩ ያውራ መልኩ የበሬ ነው። ጉማሬ አንደ በሬ ሣር ይበላል ኢዮ ፵:፲፭

ስለ ንስሓ

ንስሓ ማለት ነዘን ጸጸት ቁጭት ምላሽ መቀጫ ቅጣትና ቀኖና የነጠአት ካሳ ማለት ነው።

ምናሴ በኢየሩሳሌም የነገሠበት ዘመን ፶፭ ሲሆን መላ ዘመኑ ፷፯ ነው። አንቀጽ ፮ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፯
ስለ ነቢዩ ዮናስ የትውልድ ዘመን

ዮናስ ማለት የዋህ ሰላማዊ ገርና ንጹሕ ማለት ነው። አባቱ አማቴ እናቱ ማቀሲ ይባላሉ። በአራት ሺሕ ስድስት መቶ አርባ ዓመተ ዓለም ተወለደ። ነቢዩ ኤልያስም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ከሞት ያስነሣው ነው። ኤልያስንም ደገለግለው ነበር። የትንቢት ጸጋ የተሰጠው ነው። መኖሪያውም በገሊላ በጋትሔፌር ከተማ ነበር።

ስለ ወንበሪ /ዐናብርት/

ታላቅ ዓሣ እንደ ዘንዶ ያለ ዮና ፪:፩ ወንበሪ ምሥጢሩ ታላቅነትና ነባርነት ያለው ማለት ሲሆን አምባ እንደማለት ነው።

www.zeyeneta.com

ስለ መልሕቅ /ቃት/ መላሕቅ/

የመርከብ ልኑም እንዳይሔድ እንዲይናውጥ የሚገታው እንደ አልጋ እግር አራት ሆኖ ሁለቱ በፊት ሁለቱ በኋላ ባራት ማለዘን የሚወርድ ታላቅ ዘናና ብረት ነው። ዮና ፪:፮

አስመ ዘውስተ መርሶ ያንቀለቅል። በወደብ የተጠጋ መርከብ ይነዋወፃልና። ወባሕቱ መርሶ ወመልሕቅ ኢየነድግም ይትህበክ።

ነገር ግን ወደብ መልሕቅ ቢታውን ለቆ እንዲሄድ እያደርጉትም አንዳስ ዮሐአፈ.ድር ፲፩።

ስለ ነነዌ

ይህ ጥንታዊ ከተማ በጢሮስ ወንዝ ዳር በናምሩድ የተመሠረተ ነው። ዘፍ ፲:፲፩-፲፪። ለአሶር መናገሻ ከተማ ሆነ። የነነዌ ሰዎች ንስሓ እንዲገቡ ዮናስ ወደ ነነዌ ከተማ ተላከ። ንስሓም ገብተው ከመጥፋት /ከሞት/ ድነዋል። እንቀጽ ፯ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፰

ስለ ነቢዩ ዳንኤል እና የትንቢቱ ፍጻሜ

ዳንኤል ማለት እምላክ የሚፈርድልኝ ፈራጂዬ ዳኛዬ ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው። አባቱ ዮአኪን፡ ይባላል እናቱ ሚሊናስ፡ ትባላለች።

በይሁዳ ከፍል ውስጥ በምትገኝ በኢየሩሳሌም በእራት ሺሕ ስምንት መቶ ሰባ አምስት ዓመተ ዓለም ተወለደ። በምርኮ ጊዜ ዳንኤል ወጣት ነበር። የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሲማርክ ከተማረኩት ከአሥር ሺሕ ሰዎች ጋር እንዱ ዳንኤል ነበር። ፪ ነገ ፳፬:፲፬-፲፭። ሕልም ተርጓሚ መሆኑ የታወቀ ነው። ዳን ፪:፲፱-፵፱። ትንቢትም ሀብቱ ሆነ። ንጉሡ ናቡከደነፆር ከሰው ተሰይቶ ከአራዊት ጋር በዱር ፯ ዓመት እንደሚኖር እንደ አንስሳም ሣር እንደሚበላ ከ፯ ዓመትም በኋላ ወደ መንግሥቱ እንደሚመለስ ትንቢት ተናገረ። ትንቢቱም ተፈጸመ። ትንቢቱንና

የትንቢቱን ፍጻሜ ዳን ፬:፲-፴፯ ይመልከቱ። ማንም ያልተረጐመውን ተረጐመ። ማኔ ቴቄል ፋሬስ የሚለውን ማለት ነው። ዳን ፭:፳፭። የዘሀ ትርጕምና የትንቢት ፍጻሜ በጊዜው ጊዜ ተፈጸመ።

በተ መቅደስም ከሮ ዓመት ማለት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ አስራኤል ሲመለሱ ዘሩባቤል በ፬፻፺፫ ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ ተናገረ ተፈጸመ። ዕዝ ፫:፮-፲፫ ደህም እንደሚፈርስ /እንደሚታጠል/ ተናገረ። በግሪክ መንግሥት በታሳቱ አስክንድር ፈረሰ። ዳን ፰:፳፩። ትንቢቱም በ፪፻፭፮ ዓመት ከልደት በፊት ተፈጸመ። ትንቢቱም ከ፪፻፶፱-፪፻፷። ዓመት ከልደት በፊት የነገሠው የአሶር ንጉሥ አንጥያኮስም ቤተ መቅደስን እንደሚያረከስና እንደሚያጠፋ ተናገረ። ደህም ተፈጸመ። ዳን ፰:፳፬-፳፮። ክርስቶስም ወደዘሀ ዓለም እንደሚመጣና እንደሚገደል ተናገረ ተፈጸመ። ዳን ፱:፳፭-፳፮። ከክርስቶስ ስትሰት በኋላም ኢየሩሳሌም ተቃጠለች። ይህ የሆነው በ፸ ዓ.ም ነው። ቤተ መቅደሱን አሰፋፍቶ ያሠራው ሄሮድስ አግሪጳ ከልደት በፊት በ፲፱ ዓመት ነበር። ያፈረሱትም ሮማውያን ናቸው። ዳንኤል ቤተ መቅደስ ትሠራለች ከዚህ በኋላም ትጠፋለች ብሎ ትንቢት የተናገረ ክርስቶስ ሲወለድ ፬፻፯ ዓመት ሲቀረው ነው።

ስለ ኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም ስመ ሀገር የዳዊት ከተማ መዲና የልጆች ሁሉ መናገሻ የሆነች በምድረ ይሁዳ ያለች ጥንታዊት ከተማ ናት ዘፍ ፲፬:፲፰።

የሩ፡ ሀገር ሳሌም ስላም ሲናበብ ሀገረ ስላም ማለት ነው። ሳሌም ከመባሏ በፊት ሌዱ ስሳቀናት ሳይዳ ቤተ ሳይዳ ትባል ነበር። ቤተ ጸጋ ወማህል ማለት ነው። ዮሐ ፩:፪። ከሌዱ በኋላ ልጁ ሳሌም ስስነገሠባት ሳሌም ኢየሩሳሌም ተብላለች። ከዚያም በኋላ ስሟ አልተለወጠም መዝ ፸፮:፪ ኢያ ፲:፩። ከሳሌም በኋላም የነገሡት ንጉሠ ሳሌም በመባል ላይ መልከጼዴቅ አዶንጼዴቅ አየተባሉ በምሳሌ ስም ተጠርተዋል። ኢያ ፲:፩-፬ ይኸውም የእውነት ንጉሥና ጌታ ማለት ነው። እማናዊው

www.zeyeneta.com

ንጉሠ ጽድቅና እግዚአ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰውነቱ ንጉሠ እይሁድ ተብሎ በመካከሏ ተሰቅሎ ደቂቀ አዳምን ከአብ፡ ሕዝብን ከእሕዛብ፡ ሰውን ከመላእክት፡ ነፍሳትን ከሥጋት አንድ የሚያደርግባት /የሚያስታርቅባት/ ስለሆነች ስሟ እንደ ትንቢት ሆኖ ከነቢያት በፊት በዘመነ አበው ተነግሯል። ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባምና ዛሬና ነገ ልሄድ ያስፈልገኛል አሰ ክርስቶስ። ሉቃ ፲፫፡፴፫-፴፭።

ነቢያት ግን በእስራኤል ከፋት ሰዶም ገሞራ ብለዋታል። ከሰዶምም ያከፋትና ያበሰጣት እሉ። እናንተ የሰዶም አለቆች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡ ኢሳ ፩፡፲። ነቢዩ ሕዝቅኤልም ስለ ኢየሩሳሌም ሲናገር ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ከክፋትሽ ሁሉ በኋላ የምንዝርናን ስፍራ በየአደባባዩ ከፍ ያለ ቦታ ሰራስሽ ሠራሽ እለ። ሕዝ ፲፮፡፴፯-፶። እንቀጽ ፰ ተፈጸመ።

እንቀጽ ፱

ስለ አናንያ አዛርያ ሚሳኤል ምርኮና ዘሰዓሰማዊ ምስጋና

እባታቸው ኢዮአቄም (ሴምዩ፡ ሴንዩ) ይባላል፡ እናታቸው ሐና ትባላለች። ኢዮአቄም ማለት እግዚአብሔር አቆመ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ስመናቅ የነቢዩ ኤርምያስን መጽሐፍ አቃጠለ። ኤር ፴፮፡፳፫-፳፱ በዚህ ምክንያት ኢየሩሳሌም እንደምትማረክ ኤርምያስ ትንቢት ተናገረ። የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄምን እንዲህ በለው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የባቢሎን ንጉሥ በእርግጥ ይመጣል ይህችንም ከተማ ያፈርሳታል ከሰውና ከእንስሳም ባዶ ያደርጋታል ሲል። ኤር ፴፮፡፳፱-፴፪ ነቢዩ ኢሳይያስም ከኤርምያስ አስቀድሞ በኢየሩሳሌም ላይ ምርኮ እንደሚመጣ ተናግሮ ስለነበር። ኢሳ ፳፪፡፩-፭ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ኢየሩሳሌም ተማረከች። ስትማረክም አናንያ አዛርያ ሚሳኤልም በወጣትነታቸው ተማርከው ወደ ባቢሎን ወረዱ። ንጉሡ ናቡከደነፆር በቤቱ ውስጥ እሳድጉ በባቢሎን ሀገሮች ውስጥ ሾማቸው። በእሳቱ ውስጥም የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤልም ፬ተኛ ሰው መስሎ ታየ። የእግዚአብሔር

መልአክም የእሳቱን ነበልባል ከቮቱ ደቂቅ ላይ እጥፍቶ አዳናቸው እንደ ሳጥ ጤዛም ሆነ። ንጉሡም በፊታቸው ሰገደ።

በዚያን ጊዜም ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ። የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን እያሉ በ፮ ቃላት ምስጋናን አቀረቡ። በዚያም ጊዜ ከ፮፱ ዓመት በኋላ ክርስቶስ እንደሚወለድ ትንቢት ተናገሩ። አንቀጽ ፱ ተፈጸመ።

እንቀጽ ፲

ከዚህ በመቀጠልም ይባርከው ኩሉ ግብረ እግዚአ ለእግዚአብሔር። የአታ እግዚአብሔር ሥራዎቹ ሁሉ ያመሰግኑታል። እርሱ ለዘላለሙ ምስጉን ልዑልም ነው። እያሉ ፴፫ ጊዜ አመሰገኑት።

ይባርክሠ ብለው ያመሰገኑትን ምስጋና መሥመር በቁጥሩ ፴፫ ይሆናል። የቮቱ ደቂቅ አሉት በዘመናቸው በታሪክነት ብቻ ተጽፎ ሳይቀር ከአንድ ሺሕ አንድ መቶ ሃያ ዓመት በኋላ በቅዱስ ያሬድ ድርሰት በሰማያዊ ዜማ እንደገና ተቃኝቷል። ከላይ እንደጠቀስነው ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነንና ያባርከው ኩሉ ግብረ እግዚአ ለእግዚአብሔር የሚለውን የቮቱ ደቂቅን አሉት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከሰቱ አዋጥቀ ዜማዎች /የዜማ ከፍሎች/ አንዱ በሆነው ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ በዘወትርና በዓበይት በዓላት ስብሐተ ነግህ /የጳጉሜ ምስጋና/ ተብሎ በሚጠራው ምስጋና ውስጥ በሦስት ዜማዎች ማለት ግእዝ ዕዝል ዓራራይ ተሰባስቦ ይገኛል።

ከዚህ ላይ ስብሐተ ነግህን ብቻ የጠቀስንበት ምክንያት ከዓመት እስከ ዓመት በታላላቅ አድባራት ሳይቋረጥ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ስለሆነ ለማለት እንጅ የይትባረክና የይባርከው ምስጋና ከላይ በተጠቀሰው ስብሐተ ነግህ ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን እናሳስባለን።

ቃሉ እንዴት ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተካተተ /ተዘጋጀ/ የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ የሚከተለው ይሆናል። ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍም ውስጥ የሚገኘው ቃል በብዛት

www.zeyeneta.com

ከመዝሙረ ዳዊት መሆኑ ሰሊቃውንቱ ግልጽ ነው። ሆኖም ምክንያቱ ዳዊት ይትባረክ ይባርከም የሚለውን ቃል በመዝሙሩ /በምስጋናው/ ውስጥ በብዛት ጠቅሶት ይገኛል /ተጠቅሶ ይገኛል/። ነቢዩ ዳዊት ሰሰ ሕዝቅያስ ሲናገር አባርኮ ለእግዚአብሔር በኩሉ ጊዜ። እግዚአብሔርን በኃጉ በ፲፪ቱ በሽዑቱ ጊዜያት አመሰግነዋለሁ ብሎ ተናግሮ ነበር። መዝ ፻፲፰።

፪ኛ ሰሰ ትሩፋኑም ከሮ በመን በኋላ እግዚአብሔር ያደረገውን ድንቅ ሥራ ትንቢት በተናገረበት በመዝ ፺፯፡፩ ወይትባረክ እግዚአብሔር። ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በማለት ተናግሮ ነበር።

፫ኛ በመዝ ፹፭፡፲፪ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አሰራኤል፡ አሰራኤልን የፈጠረ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሎ ነበር።

፬ኛ በመዝ ፻፲፰፡፳፩ ይባርከም ለእግዚአብሔር ኩሉ ኃይሉ። ሠራዊተ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ብሏል።

፭ኛ በመዝ ፻፴፬፡፲፬-፳ ቤተ-አሰራኤል ባርከም ለእግዚአብሔር። የአሰራኤል ወገኖች እግዚአብሔርን አመሰግኑት። ቤተ አሮን ባርከም ለእግዚአብሔር። የአሮን ወገኖች ካህናትም እግዚአብሔርን አመሰግኑት። ቤተ ሌዊ ባርከም ለእግዚአብሔር። የሌዊ ወገኖች እግዚአብሔርን አመሰግኑት።

፮ኛ በመዝ ፻፲፬፡፭ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኪየ። ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሎ የራሱን አመሰጋገኑት ከላይ የተጠቀሱትንም እግዚአብሔርን እንደአመሰገኑና እንዲያመሰግኑ ገልጿል። ይህን በማያያዝም ነቢዩ ዳንኤል በምዕ ፱፡፭ ላይ ይትባረክ ስመ እግዚአብሔር፡ ካለ በኋላ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ የሚለውንም በምዕ ፪፡፳፯ ላይ ተናግሯል። ይህ በምዕ ፪፡፳፯ ያለው ከአዛርያ ምስጋና ጋራ የተያያዘ ነው።

እግዚአብሔር ለአናንያ ለአዛርያ ለሚሳኤልም አውቀትንና ጥበብን መጻሕፍትን ከማንበብ ሁሉ ማስተዋልን ሰጥቷቸው ነበር። ንጉሡም ናቡከደነፆር እንደ አራቱ ያለ ሰው አላገኘም።

ስለሀ በኋላም በሥጋ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩበት ለዓት በደረሰ ጊዜ በአሰት ቤታቸው ማለት አሰራኤል ጊዜና ነፃነት ስለሌላቸው ባሉበት ያጸልዩ ነበር።

ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ። ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት። ዓለምም በእርሷም የሚኖሩ ሁሉ። መዝ ፳፫፡፩-፪። እየአሰዩ ሳሉ ለገደው ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ። ዘዲያው ንዑጽዘጽ በባቢሎን አገር ሆነ። ንጉሡም ፈርዖ ዳንኤልን ጠየቀው። ነቢዩ ዳንኤልም ያህ ይቱ ደቂቅ ስላረፉ ነው አለው። ንጉሡም አዝኖ ይ ሳዮኖችን እንዲሠሩላቸው በሐር ግምጃ ልብሶችም ገንዘው ቅዱሳኑን በግዮን ውስጥ እንዲያኖሩአቸው አዘዘ። ንጉሡም እንዳዘዘ አደረጉ። ንጉሡም በሚሞትበት ጊዜ ሥጋውን በውስጡ አድርገው በነበሩ በሶስቱ ልጆች አፅም መካከል እንዲያኖሩት አዘዘ። እንዲሁም እደረጉለት። ከዘዘ ዘመን በኋላ ማለት አንድ ሺሕ ዘመን ሲፈጸም አባ ቴሞፋኑስ በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስና በተሾመበት ወረት በቹ ደቂቅ ስም ቤተ ክርስቲያን ሠራ። አባ ዮሐንስ ሐፃርን አፅማቸውን እንዲያመጣለት አዘዘ። አባ ዮሐንስ ሐፃርም ዘያዘዘው መሠረት ባቢሎን ደረሰ። ወንዞችንም ብቻ አየ። ዘውስጣ ከተ /ፈጽሞ/ ስው አልነበረም። የወርቁ ምስል ብቻ ከዚያ ነበር። አባ ዮሐንስ ሐፃርም አፅማቸው ባለበት ሰገደ። እንዲህ ብሎ አለየ። የከበራችሁ አባቶቼ ሆይ የከበረ አባት አባ ቴሞፋኑስ በስማችሁ ቤተ ክርስቲያንን ሠርቶ አፅማችሁን በውስጣ ሲያኖር አኔን ልኮኛልና ከእኔ ጋር ትሔዱ ዘንድ ፈቃዳችሁ ይሁን አለ። በዚያን ጊዜ እንዲህ የሚል ቃል ከአፅማቸው ወጣ። ለሃያማኖት አባት ለአባ ቴሞፋኑስ እንዲህ በሰው። የድካምህን ዋጋ እግዚአብሔር ይስጥህ። ነገር ግን እኛን እስከ ፍርድ ቀን /እስከ ዳግም ምጽአት/ ድረስ አፅማችን ከንጉሡ አፅም ጋራ እንዳይሰይ እግዚአብሔር ስላዘዘን ከዚህ እንወጣም። ድካመንም ከንቱ እናደርግም ቤተ ክርስቲያኒቱ በምትከብርበት ዕለት በሴሊት መብራቶችን ይሰቅሉ ዘንድ እንዲያዝዝ በውሰጣቸውም ዘይትና ፈትል እንዲያደርጉ በእሳት ግን እይለኩሷቸው። እኛም ከዚያ ደርሰን በእኛ የእግዚአብሔር ኃይል በዚያ ይገለጣል፡ ብለህ ንገረው

www.zeyeneta.com

አሉት። እባ ዮሐንስ ሐዊርም እንደነገሩት ሁሉንም ለእባ ቴምፍሎስ ነገረው እርሱም ፫ቱ ደቂቅ እንዳዘዙት አደረገ። በግንቦት ወር በ፲፭ኛው ቀን በግብጽ ሀገር ቤተክርስቲያኒቱ በምትከብርበት ሌሊት የከበሩ ፫ቱ ደቂቅ በተአምር ተገለጡ። ሊቀ ጳጳሳቱ እባ ቴምፍሎስና ለዚህ ጸጋ የታደሉ ሁሉ ዘቤተክርስቲያኒቱ እርከን ሳይ ሲሆሩ ፫ቱ ደቂቅን እዩአቸው በየሳይነቱ በሆነ ደዌ የታመሙ ብዙ በሽተኞችም ከቅዱሳን ፫ቱ ደቂት መገልጥ የተነሣ ያን ጊዜ ተፈወሱ።

ታሪክ

የእስክንድርያ ፳፫ኛ ሊቀጳጳሳት የሆነው ቴምፍሎስ በ፲፪፻፱ ዓ.ም በማርቆስ ወንበር ተሾመ። ከዚህ በኋላ ቤተክርስቲያንን ለማሠራት ይተጋ ነበር። ቤተክርስቲያንን ለማሠራት የተነሣሣበት ምክንያት የእርስ መምህር የነበረው ሐዋርያው የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት አትናቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ይመኝ ስለነበር። የመምህሩ የአትናቴዎስን መልካም ምኞት በተግባር ለመተርጉም ሲል መጠኑ ሰፊድእ ከመ ሲቁ። ደቀመዝሙር እንደመምህሩ መሆኑ ይበቃዋል የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ በዚህም ሳይ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ።

፩ኛ. በነቢዩ በኤልሳዕና በመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ስም፡
፪ኛ. በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፡
፫ኛ. በ፫ቱ ደቂቅ ስም በግብጽ አገር በ፴፪ ዓ.ም ገደማ ቤተክርስቲያንን አሠራ።

ስለ አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የስም መጠሪያ

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የመጀመሪያ ስማቸው ሲሆን ሲድራቅ ሚሳቅ አብደናጎ የሚሰው ስም ደግሞ የንጉሡ ናቡከደነፆር የጻንደረቦቹ አለቃ የሆነው አስፋኔዝ /አስፋኔስ/ ያወጣላቸው ስም ነው። ዳን ፩፡፮-፰።

፩. ፫ቱ ሲል ቍጥራቸውን መናገር ነው።

፪. ደቂቅ ሲል በዕድሜ ታናናሽ ሆነው ከወጣትነት ጀምረው ለእግዚአብሔር አገልጋዮችና ታማኞች ሲሆኑ ቤተሰብና የአንድ ሰው ልጆችም /ወንድማማቾችም/ በመሆናቸው ነው።

፫. ዳቴራን አነው ሲልም የተወደዱ የከበሩና የእግዚአብሔር ወዳጆች ባለሟሎች ማለቱ ሲሆን ወንድማማች መሆናቸውን የነሰጠ ያስረዳል። በሥጋ ዝምድና በሃይማኖትም የተስማማ ስም ነው።

፬. ፫ቱ ዕደው ሲል የጸጉ ስም ማለት የወንድነት ተፈጥሮ መኖርን ያሳተው መሆኑን ያስረዳል።

፭. ስማዕት /ሰማዕታት/ የሥራ የተጋድሎ ስማቸው ነው። ከላይ የጠቀስናቸው ስምች ሁሉ በቅዱስ ያሬድ ድርሰት ውስጥ የተገለጸ ናቸው።

አንቀጽ ፲፩
ስለ ነቢዩ ዕንባቆም

ዕንባቆም፡- ትውልዱ ከነገደ ስምዖንና ከነገደ ዮሴፍ ነው። አባቱ ዳህር /ናኮር/ ይባላል። እናቱ ሱራፋ ትባላለች። በአራት ሻሕ ስባት መቶ ዘጠና ስምንት ዓመተ ዓለም ገደማ ተወለደ። በአረጀና በሸመገለ ጊዜ የእስራኤል ልጆች ከተማረኩበት ስባቢሎን ተመልሰው ኢየሩሳሌም ንብተው በዘሩባቤል ዘመን ቤተ መቅደስን ሠሩ። ዕንባቆምም ኢየሩሳሌም ደርሶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ በታላቅ ደስታም ተቀበሉት ትንቢቱንም የሰሙ ወደአርሱ ተሰበሰቡ አፉንም ከፍቶ በመንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለ።

አቤቱ ድምፅህን ሰማሁ፡ ሰምቼም። ፈራሁ ሥራህንም አይቼ አደነቅሁ አለ። ስለ ጌታችን መድኃኒታችንና መውረድና በደሁዳ ከፍል በሆነች በቤተልሔም ስለመወለዱ ሲናገር የተመሰገነ እግዚአብሔር ከፋራን ተራራ ከቴማን ከይሁዳ አውራጃ ይመጣል ብሎ እስከመጨረሻው ያለውን ቃል ተናገረ። ከነቢያት መጻሕፍትም ጋራ ቆጠሯት።

ከዚህ በኋላ ከእስራኤል ልጆች አንዲት ሴት ወደ እርሱ መጣች እያለቀሰችም እንዲህ አለችው። ሁለት ልጆች ነበሩኝ ጣያት እንዲያመልኩ ፈለጉአቸው። እምቢ ባሉ ጊዜም ገድለው

www.zeyeneta.com

በጎዳና ላይ ጣሏቸው። ተገድለው ወደ አሉበትም አብሯት ሄደ። ነፍሳቸውንም ያለነሣ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነ ልመናውንም ተቀብሎ በሕይወት አለነሣቸው። ዕረፍቱም በቀረበ ጊዜ ዘመዶቹን ጠራቸው እንደሚሞትም ነገራቸው። አንዲት ሰዓት ያህል ወደ ላይ እየተመለከተ ተቀመጠ። እነሆ እንደለው ከንድ ያለች ታላቅ ከንድ የቤቱን ጣሪያ ለጉጥቃ ወረደች ወደ አፉም ተዘርግታ ነፍሱን ወሰደች።

ስለ ቴማን

ቴማን፡- የቦታ ክፍል ነው። መጀመሪያውን ምሥራቅ ቢሉ አንጻሩ ምዕራብ ማለት ነው። ሰሰዚህ ቴማን ማለት ዕንባ ፫፡፲፫። ናጌብ ደቡብ የደቡብ ነፋስ በደቡብ ያለ አገርና ሕዝብ ማለት ነው። ሣይም ገጸክ መንገለ ቴማን ሲተረጉም ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አቅና ማለት ሲሆን ቴማን ኢየሩሳሌም ተብሎ ተተርጉሟል። ሕዝ ፳፩፡፭-፱።

ስለ ፋራን

ፋራን፡- ከቤርሳቤህ በሰተደቡብ በሲና ውስጥ የሚገኝ ምድረ በዳ ነው። እስማኤል በፋራን ተቀመጠ። ዘፍ ፳፩፡፳፩ አሰራኤላውያንም በዚህ ተገዙ። ዘጉ ፲፡፲፪። ፲፪፡፲፮። ፲፫፡፳፮። የፋራን ተራራ ኤልፋራን ተብሎአል። ዘፍጥ ፲፬፡፮። ዕንባቆም ክርሰቶስ ከፋራን እንደሚመጣ ተናገረ። ዕን ፫፡፫ ይህም ኤፍራታን ያመለክታል ሚክ ፭፡፪

ስለ መብረቅ /መባርቅት/

መብረቅ፡- ማለት የእሳት ሰይፍ የእሳት ፍላጻ ማለት ሲሆን፡ በዝናም ጊዜ ከደመና አፎት የሚመዘዝ የሚወረወር ነው። ራእ ፬፡፭። ሲራ ፵፭፡፲። ኤር ፲፡፲፫ ማቴ ፳፰፡፫።

ጩቲታ፡- የመብረቅ ተፈጥሮ እንደምን ነው ቢሉ ውሃው በደመና አይበት /በአቆማዳ በሸራ/ ተቋጥሮ በነፋስ ወደል ፫ዝ /በሦስት እንስሳና በመጪኛ/ ተጭኖ ሲመጣ ደመናና ደመና በተጋፊዔ ጊዜ እንደ አረቄ ከውሃ ይወጣል። ወተት ሲገፋ ቅቤ እንዲወጣው። አንቀጽ ፲፩ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፲፪
ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ

ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ነው። አባቱ አሞጽ ይባላል፡ እናቱ ኑራንስ /ሶፍያ/ ትባላለች። በአፉት ሺሕ ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመተ ዓለም ገደማ እንደተወለደ በንባቡ ፫ገያን እደሚያመለክት ነው።

ጊታ ዘዘፋት ላይ እያለ ሱራፌል ከፍቤል እያመሰገኑት በአዘሩ በፈትነቱ ተገልጸለት አያት ነው። ኢሳ ፮፡፩-፰።

ኢሳይያስም በያሁዳ በነገሡ በአምስቱ ነገሥታት ዘመን ትንቢት ተናገረ። እሰሀም አገሪን ኢዮአታም አካዝ ሕዝቅያስና ምናሴ ናቸው። በአካዝ ዘመን እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረ። እነሆ እግዚአብሔር ምልክትን ይሰጣችኋል።

፩. እነሆ ድንግል ትጸንሰሰች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከኛ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው። ኢሳ ፯፡፲፬-፲፮። አርሱም በነገሠታቸው ከሚመጣባቸው ፍዳ ወገኖቹን የሚያድናቸው ወደሃይማኖቱም የሚመልሳቸው እንደሆነ የአሰራኤልንም ልጆች መሥዋዕታቸውንና ክህነታቸውን /የአሪቱን ሥርዓት/ እንደሚሽር ከሐዲስ ወገኖችም የሚያመሰግኑት ካህናትን /ሐዋርያትን/ እንደሚሾም ተናገረ።

፪. ስለ እስራኤል መማረክና ከምርኮ መመለሳቸውን ትንቢት ተናገረ። ኢሳ ፳፱፡፭-፮። ኢሳ ፭፡፯-፳።

፫. ክብር ይግባውና ስለ መድኃኒታችን ክርስቶስ መከራ ትንቢት ተናገረ። ኢሳ ፶፫፡፩-፲። እንዲህም አለ። እርሱም በመከራው ጊዜ ነገርን አልተናገረም፡ እንደ በግ ይታረድ ዘንድ መጣ በግ

www.zeyeneta.com

በሚሸልተው ስው ፊት እንደማይናገር እንዲሁ በመስራው ጊዜ ነገርን አልተናገረም ብሎ። የሐዋ ፰፡፴፪-፴፭።

በሕዝቅያስ ልጅ በንጉሡ ምናሴም ትንቢት ተናገረ። ጣዖትን ስለማቆሙና ስለማምለኩ ገሠጸው። ስለዚህም ንጉሡ ምናሴ ተቆጥቶ በእንጨት መሠንጠቂያ በመጋዝ በራሱና በእግሮቹ መካከል ለነጠቀው። ምስክርነቱንም በዚህ ፈጸመ። እንቀጽ ፲፪ ተፈጸመ።

እንቀጽ ፲፫
ስለ ድንግል ማርያም ልደት

በአምስት ሺሕ አራት መቶ ስማኒያ አምስት ዓመተ ዓለም እመዚታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባቷ ኢያቄም ከእናቷ ሐና ተወለደች። በተወለደች በሦስተ ዓመቷ እግዚአብሔር በቃሉ እንደተናገረና እንደ ነቢያት ትንቢት በድንግልና ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድን እሑድ መጋቢት ሰባ ቀን በሦ ስዓት ጸነሰችው። ወዲያው በዚሁ ወር ወደ ቅድስት ኤልሳቤጥ ቤት ሔዳ ሰላም ካለቻት በኋላ።

ተውበሎ ነፍስየ ለእግዚአብሔር። ስውነቱ ጌታን ታከብረዋለች የሚለውን ምስጋና ተናገረች አመሰገነች። እንቀጽ ፲፫ ተፈጸመ።

እንቀጽ ፲፬
ስለ ካህኑ ዘካርያስ እና የልጁ ዮሐንስ ልደት

ዘካርያስ- ማለት እግዚአብሔር ያስባል ማለት ነው። ካህኑ ዘካርያስ በአምስት ሺ አራት መቶ ዓመተ ዓለም ተወለደ።

ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ለሦ ወር ያህል ማለትም ከመስከረም ፳፮ - ስኔ ፴ ቀን ዘካርያስ መናገር አልቻለም። ዮሐንስ ሲወለድ እንደበቱ ተከፈተ /ተናገረ/። ነቢዩ ዳዊትና ነቢዩ ዳንኤል እንዲሁም አናንያ አዛርያ ሚሳኤልም ያመሰገኑትን ምስጋናና ለፈጣሪያቸው ያቀረቡትን ጸሎት። ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል። የእስራኤል ጌታ አምላክ ይክበር

ይመስገን እያለ አመሰገነ። ሉቃ ፩፡፷ ደግሞም እንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱንም ልትጠርግ በእግዚአብሔር ፊት ትሔዳለህ አያለ ትንቢት ተናገረ። እስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስም ተነግሮ ስለነበረ ኢሳ ፵፡ ሚል ፫፡፩-፪። ለልጁ ለዮሐንስ ተገልጸለት መንገሥቱ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ እያለ ከማስተማሩም በላይ ማቴ ፫፡፩-፱። ለዮሐንስ ፴ ዓመት ከሞ ወር ስጒኑ ፴ ዓመት ሲሆነው ፈጣሪውን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው። ማቴ ፫፡፲፫

ስለ ልደቱ

ለጻ ዮሐንስ የቸ ዓመት ሕፃን እያለ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፴፮ ዓመት የነገሠው የመጀመሪያው እንቲጳስ ሄሮድስ ሕፃናትን በሚያስገድልበት ጊዜ ዮሐንስን ደዛ እናቱ ኤልሳቤጥ ወደ በረሀ እንድትሸሽ ዘካርያስ እገዘ ወደ በረሀ ይዛው ሄደች። በሄሮድስ የሚፈለገው ክሕፃኑ አንዱ ዮሐንስ ነበርና ልጅህን አምጣ ቢሉት ልጁን ወደ ሌላ ቦታ እናቱ ይዛው ሔዳለች ቢላቸው በዚህ ምክንያት ገደሉት። እንዲህም የሚል ሌላ ታሪክ አለ። ዘካርያስ ልጁ ዮሐንስን ወደ ቤተ መቅደስ ወስዶ በመሠዊያው ጠርዝ /ጫፍ/ ላይ አኑሮ ጸለየበት። ሀብተ በረከት ለማሳደር። ያን ጊዜም የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ሕፃኑን ከእናቱ ጋራ ዚፋታ ወደሚባል በረሀ ኑየቆ ወሰደው። ሕፃኑን ባላገኙት ጊዜ አባቱ ዘካርያስን ገደሉት። የዘካርያስንም ደም የሚያቀል እስኪመጣ ድረስ ለሰ ዓመት ያህል ደሙ ስትፈሀ ኖረች። በዚ ዓ.ም ካህኑ ዘካርያስ በሰማዕትነት ተገደለ። ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከተገደለ በኋላ ማቴ ፳፫፡፴፭-፴፮። ክብር ይግባውና እግዚአብሔር ሥጋውን ሠወረ። ደሙ ግን እንደ ደንቢያ ሆነች። ካህናቱና ሕዝቡ እንደልማዳቸው ለጸሎት በመጡ ጊዜ አካህናት አንዱ ወደ ቤተመቅደስ ውስጥ ገባ። የረጋ ደምን እገኘ ስመሠዊያውም ውስጥ እንዲህ የሚል ቃልን ሰማ። እነሆ የበራክዩ ልጅ ካህኑ ዘካርያስ ተገደለ። ከተገደለ በኋላም የካህኑ

www.zeyeneta.com

ዘካርያስ ደም ሮ ዘመን ሲፈላ ኖሯል። የሚበቀል እስኪመጣ ድረስ ደሙ ስትጮህ ትኖራለች የሚለውን ለመግለጽ የሚከተለውን ታሪክ እንመለከታለን።

ታሪክ

ከክርስቶስ ስቅለት አስቀድሞ አይሁድ ፈጽመው ስሮም መንግሥት ተገዝተው ነበር። ነገር ግን ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ በ፸ ዓ.ም በሮም ግዛት ላይ ሽፈቱ ወይም ስሮም መንግሥት አንገዛም አሉ። በዚህ ምክንያት የሮም አገረ ገዢ ጥቦስ አየሩሳሌምን ሰመክበብ ገሠገሠና ታላቅ የሚያስፈራ ጦርነት ሆነ። ዘዲያው ሌሊቱን ከተማዋ /አየሩሳሌም/ ተያዘችና ተቃጠለች። ቤተ መቅደሱም በእሳት ነበልባል ተያያዘ። ዘጠና ስባት ሺሕ አይሁድ ተማረኩ። ሌሎችም ምግብ እንዲሆኑ ለአራዊት ተወረወሩ። በሕይወት የተረፉትም ወደ ዓለም ሁሉ ተበተኑ። ይህ ሁሉ እንዲሆንና እንዲፈጸም ገና አስቀድሞ በነቢያት ትንቢት ተነግሮ ነበር። ከነቢያትም አንዱ ዳንኤል ነው። የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ፡ ፍጻሜውም በጎርፍ ይሆናል። እስከመጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል ጥፋትም ይቆጠራል። ዳን ፱፡፳፮-፳፯። ስለዚህ የሚበቀል እስኪመጣ ድረስ የሚሰው ከላይ የታሪኩን ምንጭ እንደዘረዘርነው ሮማዊው ጦቦስም በ፹ ዓ.ም። የአየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ባፈራረስ ጊዜ ደሙ ሲፈላ አግኝቶ ይህ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀ። ደግ ሰው ነበር በግፍ /ያለ በደል/ የተገደለ ካህን ነው አሉት። ጥቦስም ከገዳዮቹ ወገን ፯ ሰዎችን አስመጥቶ ቢያስገድል ደሙ መፍላቱን ትቷል። የሚበቀል እስኪመጣ ያሰኘው ቃል ይህ ነው።

አንቀጽ ፲፱ ተፈጸመ።

አንቀጽ ፲፩
ስለ ነቢዩ /ካህኑ/ ስምዖን ትንቢትና ዕረፍት

ስምዖን፡- ማለት እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰማ ማለት ነው። ካህኑ ስምዖን ዘአምስት ሺህ ዓመተ ዓለም ተወለደ።

ታሪክ

አዳም ሁተፈጠረ በአምስት ሺሕ ሁለት መቶ አርባ አምስት ዓመተ ዓለም ሁነሲሞስ ነገሠ። አባቱ አግለዋ ይባላል፡ እናቱ ዘራኒኑት ትባላለች። በአገር አዞዘዘ በጣም የተመሰገነ ንጉሥ ነበር። ከአሰራኤል ሁሰየ ሲቃውንትን መርጦ መጻሕፍተ አሪትንና መጻሕፍተ ነቢያትን ከሱበራይስየ ወደ ጽርዕ ዘሚያስተረጉምበት ጊዘአጻፈሥቱና ከተርጓሚም አንዱ ስምዖን ነው።

ጌታ ከተወለደ ዘ፹ ተኑ ሕጻኑን ዘቤተ መቅደስ ታቅፎ ዘዲያው ትንቢት ተነልጾለት ይህ ልጅሽ በአሰራኤል ውስጥ ሰብዙዎች ስመሠይዎቻቸውና ሰመነሣታቸው ነው አለ። አያይዞ በዕለተ ስቅለት ጊዘ በአመፀኞችን ድንግል ማርያም በልባ የሚደርስባትን ነበን አሰሪዳት እንዲህም አላት። ከልብሽ የሚዘፋፍል ጎሳጻ ይገባል ብሎ በዕለተ ስቅለት የሚደርስባትን መራራ ነበን አመለከተ ትንቢቱም ተፈጸመ።

ከዘህ በኋላ እግዚአብሔርን አመስገነ እንዲህ ሰል። ወይቤ ሠባዕር ስንብርክ፡ ባሪያህን በሰላም አሰናብተው ብሎ በሰላም አረፈ። ሰ፦ ፱፡፳፱-፴፪ አንቀጽ ፲፫ ተፈጸመ።

የ፲፫ቱ ነቢያት ምስባኤ ሐተታ በዘህ ተፈጸመ።

አንሣሥቶ ሳስጀመረን አስጀምሮ ሳስፈጸመን ሰልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

www.zeyeneta.com

ስነፍጥነቢያት ምቅናይ ሐተታ

ምንጭ የሆኑ መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /አስቃ/ 1948 ዓ.ም
2. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 50 እና 51 ዓ.ም
3. መጽሐፍ ቅዱስ 81 ብርሃንና ሰላም 1980
4. ሃይማኖተ አበው ትንሣኤ ዘተባሉ 1986 ዓ.ም
5. መጽሐፈ ስንክሣር 1993/94 ዓ.ም
6. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 1996 ዓ.ም ንግድ ማተሚያ ቤት
7. የኢንተርኔት መረጃ